ከኢስላም መርሆዎች

መግቢያ 5
ምእራፍ አንድ 8
ሰላሳኛው ጁዝእ 9
የሰላሳኛው ምእራፍ አጠቃላይ ዓላማዎች 9
ዓምመ ምእራፍ 11
አልናዚዓህ 27
ዓበሰ ምእራፍ 45
አልተክዊር ምእራፍ 61
አል ኢንፊጣር 73
አል-ሙጦፊፊን 80
አል ኢንሺቃቅ 98
አል ቡሩጅ 109
አል ጣሪቅ 120
ምእራፍ ሁለት 126
የመጀመሪያው ሐዲስ 127
ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው 127
ሁለተኛ ሐዲስ 132
ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን 132
ሦስተኛ ሐዲስ 138
የእስልምና መሠረቶችና ታላላቅ ምሰሶዎች 138
አራተኛ ሐዲስ 142
የሰው ልጅ አፈጣጠር እርከኖችና ፍጻሜው 142
አምስተኛ ሐዲስ 148
እኩይ ነገሮችንና አዳዲስ ፈጠራዎችን ማውገዝ 148
ምእራፍ ሦስት 151
የኢማን ትርጉምና አስፈላጊነት 152
የኢማን መሠረቶች 158
የተውሂድ አይነቶች 159
ምእራፍ አራት 175
ምእራፍ 5 192
አቡበክር ሲዲቅ 193
ጦልሐ ቢን ኡበይዱላህ 213

ዙበይር ቢን ዓዋም 220
ምእራፍ 6.....226
ሀ) የሰው ልጅ የተፈጠረበት ዓላማ፡- ፡.....227
የሁሉም ነብያት ጥሪ.....230
ለ) በሰው ልጅና በዙሪያው ባለው ዓለም መካከለ ያለው ግንኙነት 233
የኢባዳ ትክክለኛና ሁለንተናዊ ትርጉም.....235
ኢባዳ ሕይወትን ሁሉ ያጠቃልላል.....237
በላጩ ኢባዳ.....242
የኢባዳ ተቀባይነት መሰፈርቶች.....245
የኢባዳ ክብደትና ፋይዳ.....247
ሀ) የኢባዳ ግለሰባዊ ፋይዳ.....248
ለ) የኢባዳ ቤተሰባዊ ጠቀሜታ፡-.....258
የኢባዳ ማሕበረሰባዊ ፋይዳ.....260
ሁለንተናዊ የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብን እውን ማድረግ.....265
ጠቃሚ ማሕበራዊ ተግባራት ዒባዳዎች ናቸው.....266
እንጀራ መፈለግም ኢባዳ ነው.....267
ጸታዊ ግንኙነት ኢባዳ ነው.....268
ሕይወትህ ኢባዳ ይሆንልህ ዘንድ አቅጣጫህን አስተካክል..269
ለ) ሁለንተናዊውን የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ በገቢር ማዋል.....270
ምእራፍ ሰባት.....275
የመልካም ስነ ምግባር ጽንሰ ሐሳብ.....276
የኢማንና የስነ ምግባር ትስስር.....279
ከአላህ መልእክተኛ ትምህርት በጥቂቱ.....280
መልካም ስነ ምግባር የኢማን ፍሬ ነው.....281
መጥፎ ስነ ምግባር የኢማንን መድከም አመልካች ነው.....285
የተላቀ ስነ-ምግባር ባለቤት.....289
የመልካም ስነ ምግባር ከፊል ገጽታዎች፣ መገለጫዎቻቸውና እነርሱን ለመጎናጸፍ የሚያስችሉ ስልቶች.....292
አንደኛ፡- ሐያእ.....292
ቁጥብነት (ተዓፉፍ).....310
መቻልና ቁጣን መቆጣጠር.....323

መግቢያ

የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ምስጋና ይድረሰው። የአላህ እዝነትና ሰላም በነብያትና በመልእክተኞች መቋጫ ላይ ይስፈን።

ኢስላማዊው እነጻ (ተርቢያ) ለሰው ልጆች ከተገለጹ ሕዝቦች ሁሉ በላጭና ምርጥ ኡምማ የተፈጠረበት ድንቅ የኩትኩታ ስልት ነው። ይሁንና ይህ ስልት በመጨረሻዎቹ ክፍለ ዘመናት ከአረብና ከሙስሊም ሐገሮች የትምህርትና የእነጻ መስክ እንዲወገድ ተደርጓል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከነርሱ ውስጥ የእስልምና ጠላቶች ሴራና ሙስሊሞች ሐይማኖታቸውን አለማወቃቸው፣ እንዲሁም በምእራቡ ዓለም የትምህርት እና የእነጻ አስተሳሰቦች መደመማቸው ይጠቀሳሉ። የአላህ ችሮታ ሆነና በአረቡና በሙስሊሙ ዓለም ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሊቃውንት የሴራውን ግዝፈት በመረዳት የእነጻን ትክክለኛ አስተሳሰብ ለማስረጽና ከወራሪው የምእራቡ ዓለም አስተሳሰብ ባርነት ለመላቀቅ የሚረዱ ጉባኤዎች እንዲጠሩ፣ መጽሐፍትም እንዲዘጋጁ ጥሪ አደረጉ።

ከኢስላማዊው መርሆዎች ጋር የሚጣጣምና ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ ማንኛውም መጽሐፍ ከዘመናዊው ኢስላማዊ የእነጻ ግንብ ላይ የሚተከል ተጨማሪ ጡብ በመሆን ያገለግላል።

ይህ መጽሐፍ ስለ ኢስላማዊ የእነጻ ስልት ትርጉምና ይዘት፣ ስለ ባህሪውና ከቁርአንና ከሱንና ስለመነጨ አበይት የእነጻ ስልቶች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታልሞ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ቁርአንን፣ ሐዲስን፣ የነብዩን ሙሐመድን ታሪክ (ሲራ)፣ ዓቂዳንና ፊቅህን በማስተማሩ ሂደት መከተል ተገቢ የሆኑ ስልቶችን ያስተዋውቃል። በዚህም ብቻ ሳይወሰን ወደ እስላማዊው የትምህርትና የእነጻ ስልት የሚያደርሰውን ትክክለኛ አቅጣጫ በማበልጸግ ይህ የእነጻ ስልት ከአፈር በቀል ስልቶችና ስርዓቶች ሁሉ ብልጫ እንዳለው ሰዎች ተገንዝበው በርሱ ላይ ያላቸው እምነት ይበልጥ ይጸና ዘንድ የመርዳት አላማም አለው። ከዚህ በተጨማሪም አንባብያን የአንድን የተለየ ትምህርት ዓላማዎች የመዘርዘርና

የመተንተን፣ ጥያቄዎችን የማውጣት እና መልሶችን የማዘጋጀት፣ እንዲሁም በየትኛው የሽሪዓ ትምህርት ዘርፍ ለአንድ የተለየ ትምህርት መርሃ ግብር የማዘጋጀትና ሌሎችንም ክሕሎቶች ያዳብሩ ዘንድ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የትምህርትና የእነጻ መርሆዎችን ከምንጫቸው፣ በዋነኛነት ከቁርአንና ከሱንና ለማመነጨት ብርቱ ጥረት አድርጊያለሁ። ለእያንዳንዱ የሽሪዓ እውቀት ዘርፍም ከአጠቃላዩ የእነጻ ዓላማ የተመዘዙ መለስተኛ ዓላማዎችን በመዘርዘር ሌሎች ዓላማዎችን ማመንጨት ለሚሹ ሁሉ በናሙናነት ያገለግሉ ዘንድ አድርጊያለሁ።

የአንባብያንን ግንዛቤ ለማስፋት የሚያስችሉ የመመዘኛ ጥያቄዎችን በየምእራፉ መቋጫ ላይ አስፍሪያለሁ። የመረጃ ምንጮችን በግርጌ ማስታወሻዎች ላይ ከትቢያለሁ። በየምእራፉ ማጠናቀቂያ ላይ ደግሞ ዋቢ መጽሐፍትን በደራሲዎች ስም የአረብኛ ሆህያት ቅደም ተከተል መሠረት አስቀምጫለሁ።

መጽሐፉ ሰባት ምእራፎችን የያዘ ነው። እነርሱም፡-

ምእራፍ አንድ፡- አልቁርአኑል ከሪም (ከአልነበእ እስከ አልጧሪቅ ምእራፎች ያሉ አናቅጽ ትርጉም)

ምእራፍ ሁለት፡- የተከበረው ሐዲስ (ከአልነወዊ አርባ ሐዲሶች መካከል ከ1-5 ያሉትን ሐዲሶች ማብራራት)

ምእራፍ ሦስት፡- ዓቂዳ፡- የእምነት መሠረቶች (በአላህ ማመን)

ምእራፍ አራት፡- ሲራ የነቢዩ ሙሐመድ ታሪክ ጉልህ ክስተቶች

ምእራፍ አምስት፡- የነቢዩ ሶሐቦች ታሪክ

ምእራፍ ስድስት፡- አጠቃላይ ዓላማ፣ አላህ እኛን የፈጠረበትን ዓላማ አንባቢ እንዲገነዘብ እና ለርሱም እንዲሰራ ለማነሳሳት ያለመ ምእራፍ፣

ምእራፍ ሰባት፡- አጠቃላይ ዓላማ፣ የእምነት ጽንሰ ሐሳቦችን ግንዛቤ ከመልካም ስነ ምግባር ጋር ለማቆራኘት ያለመ ምእራፍ ።

ልዑልና የላቀ የሆነው አላህ ለሚወደው ተግባር ይገጥመን ዘንድ እማጸነዋለሁ፡፡ ይህ መጽሐፍ በትምህርትና እነጻ ኮሌጆች ውስጥ ለሚገኙ ሙስሊም መምህራንና ተማሪዎች ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በመጨረሻም የዓለማት ጌታ የሆነው አላህን አመሰግናለሁ፡፡ በአለቃችን በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን፡፡

* * *

ምእራፍ አንድ

ከተላቀው ቁርአን ጋር

ሰላሳኛው ጁዝእ

የሰላሳኛው ምእራፍ አጠቃላይ ዓላማዎች

⇒ ተማሪው የጁዝኡን አጠቃላይ ባህሪ እንዲያብራራ፡፡

⇒ በዚህ ጁዝእ ውስጥ የተካተቱ ሱራዎች (ምእራፍ) ያላቸውን ልቅና የሚዘክር ነገር ከተገኘ እንዲያወሳ

⇒ እያንዳንዱ ምእራፍ የዳሰሳቸውን የእምነት ጽንሰ ሐሳቦች እንዲገልጽ

⇒ ከእያንዳንዱ ምእራፍ የሚቀሰሙ ትምህርቶችን እንዲተነትኑ ማስቻል፡፡

የዚህ ጁዝእ ምእራፎች -ከአልበይናህ እና ከአልነስር ምእራፍ ውጭ- ሁሉም መካዊ ሲሆኑ፣ መጠናቸው ቢለያይም ከአጫጭር ሱራዎች የሚፈረጁ ናቸው፡፡ በይዘት፣ በትኩረት፣ በአቀጣጫ፣ በመልእክት አወቃቀር፣ በሚፈጥሩት ገጽታና ድባብ እንዲሁም በአጠቃላይ የአቀራረብ ስልት በእጅጉ ይመሳሰላሉ፡፡ በሰው ልጅ ሕሊና ላይ በተከታታይ የሚያቃጭሉ ደወሎች፣ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ያሉ ሰዎችን የሚጠሩ ጩኸቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ጁዝእ ሱራዎች የሚመነጩ ደውሎችና ጩኸቶች በተመሳሳይ ድምጸት እና ማስጠንቀቂያ በሕሊናቸው ላይ አከታትለው ይደውላሉ፡፡ ‹ንቁ› ይሏቸዋል፡፡ ‹ተመልከቱ› አስተውሉ፣ አስተንትኑ፣ እነሆ አምላክ አለ፡፡ (እጡራንን የሚመራ) ስርዓት፣ ፍቃድና ውሳኔ አለ፡፡ ፈተና አለ፡፡ ሐላፊነት አለ፡፡ ምርመራ አለ፡፡ የስራ ውጤት የሚሰጥበት አለም አለ፡፡ እነሆ፣ ብርቱ ቅጣት ወይም ታላቅ ድሎት አለ፡

⇒ ጁዝኡ ባጠቃላይ በዚህች ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሕያውያንን ማለትም የሰውን ልጅ፣ የእንስሳትንና የእጽዋትን መነሻ በማስታወስ፣ በተከፈተው የዩኒቨርሱ መጽሐፍ ውስጥ የተረጨ የአላህ ተአምራትን በማሳየት እጅግ ብርቱ እና አስደንጋጭ፣ ጩኸታማ፣ ቆርቋሪና ሸፋኝ የሆነውን የመጭውን ዓለም፣ ምርመራውን፣ እንዲሁም ድሎቱንና ቅጣቱን፣ ይህች አለም ስትፈራርስ፣ ዩኒቨርሱ ሲንኮታኮት

የሚፈጠረውን ግዙፍ ሁነት፣ የድንጋጤ ስሜትን በሚያሰርጽ፣ እጅግ በሚያሸብር፣ ልቦናን በፍርሃት በሚያርድ፣ ቀልብን በስጋት በሚያርገፈግፍ አኳኋን ያስታውሳል።

ይህን ሁሉ ለፈጣሪ ሕልውና፡ ዩኒቨርሱን የሚመራ ስርዓትና ፈቃድ እንዲሁም ከሞት መቀስቀስና ወሳኝ የምርመራና የፍርድ ሂደት ለመኖሩ በመረጃነት ያቀርበዋል። የመጭውን ዓለም አስደንጋጭነት ይገልጻል። ከርሱም ያስጠነቅቃል። አልፎ አልፎም የጥንት ካህድያንና አስተባባዮችን አስከፊ ፍጻሜ በተንዳኝ ይዘክራል።

* * *

ዓምመ ምእራፍ

አንቀጽ 1-16

﴿ عَمَّ يَتَسَآءَلُونَ ١ عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ٢ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ٣ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٤ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٥ أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ٦ وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ٧ وَخَلَقۡنَٰكُمۡ أَزۡوَٰجٗا ٨ وَجَعَلۡنَا نَوۡمَكُمۡ سُبَاتٗا ٩ وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِبَاسٗا ١٠ وَجَعَلۡنَا ٱلنَّهَارَ مَعَاشٗا ١١ وَبَنَيۡنَا فَوۡقَكُمۡ سَبۡعٗا شِدَادٗا ١٢ وَجَعَلۡنَا سِرَاجٗا وَهَّاجٗا ١٣ وَأَنزَلۡنَا مِنَ ٱلۡمُعۡصِرَٰتِ مَآءٗ ثَجَّاجٗا ١٤ لِّنُخۡرِجَ بِهِۦ حَبّٗا وَنَبَاتٗا ١٥ وَجَنَّٰتٍ أَلۡفَافًا ١٦ ﴾ النبأ: ١ - ١٦

‹‹ስለ ምንድነው የሚጠያየቁት? ስለ ታላቁ ዜና ነው፤ (ስለ ዕለተ ቂያማ)። ስለዚያ ስለተወዛገቡበት (ታላቅ ዜና)። ይታቀቡ! ወደፊት (የቂያማን ምንነት) በሚገባ ያውቃሉ። ይታቀቡ! ወደፊት በሚገባ ያውቃሉ። ምድርን ምንጣፍ አላደረግናትምን? ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን? (ተቃራኒ ያላቸው) ጥንዶች አድርገን ፈጠርናችሁ። እንቅልፋችሁን ዕረፍት አደረግን። ሌሊትን ልባስ አደረግን። ቀኑን ደግሞ የኑሮን ስንክሳር መከወኛ አደረግን። ከበላያችሁ ሰባት ጠንካራ (ሰማያትን) ገነባን። አንፀባራቂ ብርሃንንም አደረግን። ከአረገዙ ደመናዎችም የሚንቧቧ ውሃን አወረድን፤ በርሱ (በዚህ ውሃ) እህልንና ቅጠላ ቅጠሎችን ልናበቅል፤ በርካታ ዕፅዋት የበቀሉባቸውን የአትክልት ቦታዎችም (ልናዘጋጅ)።›› (አል ነበእ አንቀጽ 1-16)

የትምህርቱ ዓላማዎች

- ተማሪው የአንቀጾቹን አጠቃላይ ባህሪ እንዲገልጽ፣
- ምእራፉ በጥያቄ የተወጠነበትን ዓላማ እንዲያብራራ፣
- አላህ ለሰው ልጅ የለገሳቸውን በነዚህ አናቅጽ የተወሱ ልዩ ልዩ ጸጋዎች እንዲዘረዝር፣
- አላህ በነዚህ አናቅጽ ውስጥ እነዚህን ጸጋዎች የማውሳቱን ዓላማ እንዲያብራራ።

﴿ عَمَّ يَتَسَآءَلُونَ ١ عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ٢ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ٣ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٤ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٥ ﴾ النبأ: ١ ـ ٥

‹‹ስለ ምንድነው የሚጠያየቁት? ስለ ታላቁ ዜና ነው፤ (ስለ ዕለተ ቂያማ)። ስለዚያ ስለተወዛገቡበት (ታላቅ ዜና)። ይታቀቡ! ወደፊት (የቂያማን ምንነት) በሚገባ ያውቃሉ። ይታቀቡ! ወደፊት በሚገባ ያውቃሉ።›› (አል ነበእ 1-5)

የመጭው ዓለመ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ መግባቱን በሚያወግዝና የመገረም ድምጸት ባዘለ ጥያቄ ምእራፉ ይወጠናል። ‹‹ስለምንድን ነው የሚጠያየቁት›› ከዚያም መልሱን ራሱ ይሰጣል። ወትሮውንም ጥያቄውን ያቀረበው ከነርሱ ምላሽ ከጅሎ አይደለም። ሁኔታቸው አስገርሞት፣ ድርጊታቸው አስደንቆት፣ የጥያቄያቸውን ትንግርትነት ለማሳየት ሽቶ እንጅ።

عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ٢ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ٣

ስለ ታላቁ ዜና ነው፤ (ስለ ዕለተ ቂያማ)። ስለዚያ ስለተወዛገቡበት (ታላቅ ዜና)።

የተጠያየቁበትን ነገር ቃል በቃል ሳያወሳ ‹ስለታላቁ ዜና› በማለት ባህሪውን ገለጸ። ቀጥሎም ዛቻ አዘል መልእክት ሰነዘረ። ለጥያቄያቸው ቀጥተኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ይህ ገለጻ የሚፈለገውን መልእክት ያስተላልፋል። ከቀጥተኛ ማስፈራሪያ ይበልጥም ጥልቅ የፍርሃት ስሜት ያሰርጻል።

كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٤ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٥

ይታቀቡ! ወደፊት (የቂያማን ምንነት) በሚገባ ያውቃሉ። ይታቀቡ! ወደፊት በሚገባ ያውቃሉ።

‹ከላ› (ይከልከሉ) የሚለው የአረብኛ ቃል ለውግዘት አገልግሎት የሚውል ነው። ይህ ቃል እና ሐረጉ መደጋገሙ ዛቻ እና ማስጠንቀቂያውን ይበልጥ ያጸናዋል።

በመቀጠል እነርሱ የተወዛገቡበትን ታላቅ ዜና ጉዳይ በመተው በዩኒቨርሱ ውስጥ መጠነኛ ቅኝት ያደርጋል። በውስጡ የተቋቱና ላስተነተናቸው ልቦናን የሚያርገፈግፉ ክስተቶችን፣ እውነታዎችንና ትእይንቶችን ይዳሰሳል።

በሰፊው የዩኒቨርሱ መስክ የሚደረገው ይህ ቅኝት በውስን ቃላት እና ገለጻዎች አማካይነት በሕሊና ላይ ከባድ እና ብርቱ ተጽእኖ ያሳርፋል። ያለማቋረጥ የሚሰነዘር በትር ማለት ነው። አጀንዳዎቹ አዎንታዊ ምላሽ ባዘሉ ጥያቄዎች መልክ መቅረባቸው ሆነ ተብሎ የተመረጠ ስልት ነው። ዝንጉዎችን እየነቀነቀ ከበስተጀርባቸው ፈጣሪና አስተናባሪ፣ እቅድና ፈቃድ መኖሩን ወደሚያመላክቱ የዩኒቨርሱ ክስተቶችና ትእይንቶች ፊታቸውን እንደሚያዞር ጠንካራ ክንድ ማለት ናቸው።

በዚህ ቅኝት የመጀመሪያው ዳሰሳ ምድርንና ጋራዎችን የተመለከተ ነው፦

﴿أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ٦ وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ٧﴾ النبأ: ٦ - ٧

‹‹ምድርን ምንጣፍ አላደረግናትምን? ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን?›› (ሱል ነበእ 6-7)

1) ‹‹ሚሐድ›› የሚለው ቃል ለኑሮ የተገራ፣ ልክ እንደ አንቀልባ (መህድ) ልስልስና ምቹ ማለት ነው። ሁለቱም ትርጉሞች ተቀራራቢ መልእክት አላቸው። የሰው ልጅ በቅርበት የሚያውቀውና የሚኖረው እውነታ በመሆኑ ለመገንዘብ ሰፊ እውቀት አያስፈልግም። ተራሮች ችካል መሆናቸውንም ማንም ሰው በቀላሉ የሚያየው እውነታ ሲሆን፣ የሰው ልጅ እውቀቱ በጨመረ ቁጥር የዚህ እውነታ ግዝፈት በልቦናው ውስጥ የበለጠ እየጨመረና እየገዘፈ ይሄዳል።

ከበስተጀርባው ያለውን የታላቁን አምላክ ስሌትና ረቂቅ ጥበብም ይበልጥ ይገነዘባል።

ሁለተኛው ዳሰሳ የሕያውያንን የተለያዩ እውነታዎችና ገጽታዎች የቃኘ ነው።

﴿ وَخَلَقۡنَٰكُمۡ أَزۡوَٰجٗا ٨ ﴾ النبأ: ٨

‹‹(ተቃራኒ ያላቸው) ጥንዶች አድርገን ፈጠርናችሁ።›› (አል ነበእ 8)

ይህም እውነታ እንደዚሁ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ይረዳዋል። አላህ የሰውን ልጅ ሁለት ጾታዎች አድርጎ ፈጥሯል። የሕልውናውንም ቀጣይነት ከሁለቱ ጾታዎች ግንኙነት ጋር አስተሳስሯል። እናም ቁርአን በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሚገኝን ሰው ወደዚህ ቀላል እውነታ ያመለክታል። ይህን እውነታ ያስተነተነ ልቦናው መነካቱ አይቀሬ ነው። ከበስተጀርባው ዓላማና ጥበብ መኖሩን ይረዳል። እቅድና ፈቃድ እንዳለ ይገነዘባል።

﴿ وَجَعَلۡنَا نَوۡمَكُمۡ سُبَاتٗا ٩ وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِبَاسٗا ١٠ وَجَعَلۡنَا ٱلنَّهَارَ مَعَاشٗا ١١ ﴾ النبأ: ٩ - ١١

‹‹እንቅልፋችሁን ዕረፍት አደረግን። ሌሊትን ልባስ አደረግን። ቀኑን ደግሞ የኑሮን ስንክሳር መከወኛ አደረግን።›› (አንቀጽ 9-11)

አላህ እንቅልፍን ረፍት ማድረጉ የሰውን ልጅ ሕይወት የማሰናዳት አካል ነው። ሰዎች በእንቅልፍ ለአት ራሳቸውን ስተው፣ ከእንቅስቃሴ ታቅበው፣ በሞትና በሕይወት መሐል ይሆናሉ። በሕይወት ጉዳዮች፣ በኑሮ ጣጣዎች ሲሮጥ ውሎ የዛለን አካልና መንፈስ ያሳርፋል። እንቅልፍ አላህ በሕያውያን ስሪት ውስጥ ያስቀመጠው ሚስጥር ሲሆን፣ ሕያውያንን ከፈጠረው፣ ይህን ሚስጥር ካኖረባቸው እና ሕይወታቸውን ከርሱ ጋር ካስተሳሰረው አምላክ ውጭ ምንነቱን የሚያውቅ የለም። ያለ እንቅልፍ ከተወሰነ ጊዜ በላይ መኖር የሚችል ሕይወት ያለው ነገር

የለም። በውጫዊ ግፊትና ተጽእኖ ያለ እንቅልፍ እንዲቆይ የተገደደ ለሞት እንደሚበቃ እመኑን ነው።

አላህ ለሰው ልጅ በስራና በድካም የዛለ አካሉን የሚያሳርፍበት እንቅልፍ እንደሰጠው ሁሉ ለሌሎቹም ፍጡራን የሚያርፉበትን እና የሚከወኑበትን ሌሊት፣ እንዲሁም እንቅስቃሴ እና ስራ የሚስተናገድበትን ቀን ለግሷቸዋል። በዚህ መልክ የአላህ ፍጥረት ተጣጥሞና ተናቦ ይኖራል። ይህም ዓለም ለሕያውያን ተስማሚ ቦታ ሊሆን ችሏል። ሦስተኛው ዳሰሳ ሰማያት ከምድር እና ከሕያውያን ጋር በተጣጣመ አኳኋን መፈጠራቸውን የሚመለከት ነው።

﴿ وَبَنَيۡنَا فَوۡقَكُمۡ سَبۡعٗا شِدَادٗا ١٢ ﴾ النبأ: ١٢

‹‹ከበላያችሁ ሰባት ጠንካራ (ሰማያትን) ገንባን።›› (አንቀጽ 12)

‹‹ሰባት ብርቱዎች›› የተሰኙት ሰባቱ ሰማያት ናቸው። በሌላ ቦታ ‹‹ሰባት መንገዶች›› ተብለዋል። ከዚህ ውጭ አላህ ብቻ የሚያውቃቸው የዩኒቨርሱ ስፋት አካሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። የሰው ልጅ ስለ ፍጥረተ ዓለሙ የሚያውቀው እጅግ ኢምንት የሆነን ነገር ብቻ ነው። ይህ አንቀጽ የሚያመለክተው እነዚህ ሰባት አካላት ከመበታተን እና ከመለያየት በሚታደጋቸው ብርቱ አኳኋን መታነጻቸውን ነው።

وَجَعَلۡنَا سِرَاجٗا وَهَّاجٗا ١٣

‹‹አንፀባራቂ ብርሃንንም አደረግን።›› (አንቀጽ 13)

የብርሃንና የሙቀት ምንጭ የሆነችውን ጸሐይን የሚመለከት ነው። ጸሐይ ለመሬትና ከውስጧ ላሉ ሕያውያን ሕልውና እጅግ አስፈላጊ ናት፡ ፡ በተጨማሪም በምድር ላይ ያሉ ሰፋፊ የውሃ አካሎች እንዲተኑ በማድረግ እና ትነቱን ወደ ሕዋው በማንሳት ዳመና እንዲፈጠር አብይ ሚና ትጫወታለች።

﴿ وَأَنزَلۡنَا مِنَ ٱلۡمُعۡصِرَٰتِ مَآءٗ ثَجَّاجٗا ١٤ ﴾ النبأ: ١٤

‹‹ከአረገዙ ደመናዎችም የሚንቧቧ ውሃን አወረድን፤›› (አንቀጽ 14)

ከዳመና ውሃ ይጨመቃል። ዝናብ ሆኖም ይወርዳል። በርሱ አማካይነትም ለምግብነት የሚውሉ እጽዋት ይበቅላሉ። ባለብዙ ዛፍ የእጽዋት ስፍራዎች ይፈጠራሉ። ይህ ሁሉ ዓለማዊ ኑሮን ለማመቻቸት የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህች ዓለም በኋላ ምርመራና ምንዳ ወቅም ቅጣት አለ። የመለያያው ቀን ይመጣል። የፍርዱ እለት ይከሰታል።

﴿ إِنَّ يَوۡمَ ٱلۡفَصۡلِ كَانَ مِيقَٰتٗا ١٧ يَوۡمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ فَتَأۡتُونَ أَفۡوَاجٗا ١٨ وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتۡ أَبۡوَٰبٗا ١٩ وَسُيِّرَتِ ٱلۡجِبَالُ فَكَانَتۡ سَرَابًا ٢٠ ﴾ النبأ: ١٧ - ٢٠

‹‹የመወሰኛው ቀን የተወሰነ ነው። ቀንዱ የሚነፋበትና እናንተም በመንጋዎች ሆናችሁ የምትመጡበት ቀን ነው። ሰማይ በራፎች የሆነች ያህል (በሁ ሉም አቅጣጫዎች) የምትከፈትበት (ቀን ነው።) ጋራዎች ሲረበደም የሆኑ ያህል ከቦታቸው የሚወገዱበት (ተንኮታኩ ተውና ደቀው ወደ ብናኝነት የሚለ ወጡበት) ቀን ነው።›› (አንቀጽ 17-20)

ሰዎች ያለ አላማ አልተፈጠሩም። እንዲሁም አይተውም። ሕይወታቸውን በዚህ ድንቅ ስሌት ያዋቀረና ያቀናበረው፣ ከሚኖሩበት ዓለም ጋር በዚህ አኳኋን ያጣጣመ አምላክ ያለ አላማ እና ስርዓት እንዲሁ ኖረው እንዲሁ እንዲሞቱ አይተዋቸውም። እነሆ፣ የፍርዱ ቀን አለ። በዚህች ዓለም የተከሰቱ ነገሮች ሁሉ ምንነታቸው የሚለይበት እለት አለ። ይህ ቀን በአላህ የታወቀና የተወሰነ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

⇒ ከአንቀጽ 1-5 ያሉ አናቅጽን አጠቃላይ ባህሪ ግለጽ።

⇒ በምእራፉ መጀመሪያ ላይ የቀረበውን ጥያቄ ዓላማ አብራራ

⇒ በአንቀጽ 4-5 የተጠቀሰውን ድግግሞሽ መልእክት አውሳ።

⇒ አላህ በነዚህ አናቅጽ ውስጥ የተወሱትን ጸጋዎች የማስታወሱ ዓላማ ምንድን ነው?

⇒ የአላህን የተለየ ጸጋ ያስታወስክበትን አጋጣሚ አስታውስ። በዚህ አጋጣሚ ምን አደረግክ?

አንቀጽ 17-30

﴿إِنَّ يَوۡمَ ٱلۡفَصۡلِ كَانَ مِيقَٰتًا ١٧ يَوۡمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ فَتَأۡتُونَ أَفۡوَاجٗا ١٨ وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ
فَكَانَتۡ أَبۡوَٰبٗا ١٩ وَسُيِّرَتِ ٱلۡجِبَالُ فَكَانَتۡ سَرَابًا ٢٠ إِنَّ جَهَنَّمَ كَانَتۡ مِرۡصَادٗا ٢١ لِّلطَّٰغِينَ
مَـَٔابٗا ٢٢ لَّٰبِثِينَ فِيهَآ أَحۡقَابٗا ٢٣ لَّا يَذُوقُونَ فِيهَا بَرۡدٗا وَلَا شَرَابًا ٢٤ إِلَّا حَمِيمٗا وَغَسَّاقٗا ٢٥
جَزَآءٗ وِفَاقًا ٢٦ إِنَّهُمۡ كَانُواْ لَا يَرۡجُونَ حِسَابٗا ٢٧ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا كِذَّابٗا ٢٨ وَكُلَّ
شَيۡءٍ أَحۡصَيۡنَٰهُ كِتَٰبَۢا ٢٩ فَذُوقُواْ فَلَن نَّزِيدَكُمۡ إِلَّا عَذَابًا ٣٠﴾ النبأ: ١٧ - ٣٠

‹‹የመወሰኛው ቀን የተወሰነ ነው። ቀንዱ የሚነፋበትና እናንተም በመንጋዎች ሆናችሁ የምትመጡበት ቀን ነው። ሰማይ በራፎች የሆነች ያህል (በሁሉም አቅጣጫዎች) የምትከፈትበት (ቀን ነው።) ጋራዎች ሲረበደም የሆኑ ያህል ከቦታቸው የሚወገዱበት (ተንኮታኩተውና ደቀው ወደ ብናኝነት የሚለወጡበት) ቀን ነው። ገሃነም (ከሓዲ እንግዶቿን ለማደን) ታደፍጣለች። ለአመፀኞችም ማረፊያ ናት። በውስጧ ዘወትር ይኖራሉ። (ነዋሪዎቿ) ከርሷ ውስጥ (የገሃነምን ቃጠሎ የሚያበርድላቸው) ቅዝቃዜ፥ (ጥማቸውን የምቆርጥላቸው) መጠጥም አይቀምሱም። እጅግ የፈላ ውሃና እዥ ብቻ እንጂ (ሌላ መጠጥ አያገኙም)። (ይህ ቅጣት በዚህች ዓለም ውስጥ የፈፀሙትን ጥፋት) የሚመጥን ቅጣት ነው። (ለሚፈጽሟት እያንዳንዷ ድርጊት) ተጠያቂ እንደሚሆኑ ቅንጣት አይጠብቁም ነበር። አንቀጾቻችንን አስተባብለዋልና። ሁሉንም ነገር (ይፈጽሙት የነበረውን እያንዳንዱን የኃጢአት ድርጊት) መዝገብ ውስጥ አስፍረናል። (ከሓዲያን ሆይ! የድርጊታችሁን ፍሬ) ቅመሱ፤ ከቅጣት ውጭ ምንም የምናክልላችሁ ነገር የለም፥ (እንላቸዋለን)።›› (አንቀጽ 17-30)

የትምህርቱ ዓላማዎች

⇒ ተማሪው በምእራፉ መጀመሪያ ላይ ለቀረበው ጥያቄ በነዚህ አናቅጽ የተሰጠውን ምላሽ እንዲያስታውስ።

⇒ የመለያያውን ቀን ክስተቶች እንዲገልጽ፣

⇒ የጀሃነምን ቅጣት ትእይንት አንቀጾቹ ባብራሩት መልኩ እንዲስል፣

⇒ ይህ ቅጣት ‹ተስማሚና ተገቢ ዋጋ› የተሰኘበትን ምክንያት እንዲያብራራ።

إِنَّ يَوۡمَ ٱلۡفَصۡلِ كَانَ مِيقَٰتًا ١٧

‹‹የመወሰኛው ቀን የተወሰነ ነው።›› አንቀጽ 17

የዚህ ዩኒቨርስ ስርዓት የሚፋለስበት፣ መቋጠሪያ ውሉ የሚፈታበት ቀን ነው።

يَوۡمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ فَتَأۡتُونَ أَفۡوَاجٗا ١٨

ቀንዱ የሚነፋበትና እናንተም በመንጋዎች ሆናችሁ የምትመጡበት ቀን ነው። አንቀጽ 18፡

- ስለዚህ ጡሩንባ ከስም ባሻገር የምናውቀው ነገር የለም። በርሱ መነፋቱን እንጅ ተጨማሪ መረጃ የለንም። ስለዚህም ምንነቱን ለመዘርዘር መባከን ተገቢ አይደለም። በቀንዱ ሲነፋ የሚከተለውን ትእይንት ብቻ በዓይነ ልቦናችን እንስላለን። ሙታን ከቀብራቸው ተነስተው በቡድን በቡድን እየሆኑ ይወጣሉ። ፍጡራን ባጠቃላይ ከየአቅጣጫው ወደ መሰብሰቢያው ቦታ ይጎርፋሉ። ይህ የመሰብሰቢያ ቦታ የት ነው? አናውቅም።

በምናውቀው ዩኒቨርስ ውስጥ እጅግ ግዙፍና አስደንጋጭ ሁነቶች እውን ይሆናሉ፡-

﴿ وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتۡ أَبۡوَٰبٗا ١٩ وَسُيِّرَتِ ٱلۡجِبَالُ فَكَانَتۡ سَرَابًا ٢٠ ﴾ النبأ: ١٩ - ٢٠

‹‹ሰማይ በራፎች የሆነች ያህል (በሁ ሉም አቅጣጫዎች) የምትከፈትበት (ቀን ነው።) ጋራዎች ሲረብደም የሆኑ ያህል ከቦታቸው የሚወገዱበት

(ተንኮታኩ ተውና ደቀው ወደ ብናኝነት የሚለ ወጠብት) ቀን ነው።›› *(አንቀጽ 19-20)*

በጥንካሬ የታነጸችው ሰማይ እኛ ባልለመድነው መልኩ በየቦታው ተሸንቁራ ቀዳዳ ብቻ ትሆናለች። ግዙፍ የተራራ ችካሎች ፈራርሰውና አመድ ሆነው በሕዋው ውስጥ ይበታተናሉ። ሕልውናቸውም አክትሞ እንደሲርቢዶም ይሆናሉ። ወይም ደግሞ እንደ ብናን ደቀው ብርሃን ሲያርፍባቸው እንደ ሲርቢዶም ያንጸባርቃሉ።

አንቀጾቹ ከመቀስቀስና ከመሰብሰብ ባሻገር አንድ እርምጃ ተራምደው የወንጀለኞችን ፍጻሜ ይስሉልናል። ቅኝታቸውን የጀመሩት ስለ ታላቁ ዜና ይጠይቁና ይወዛገቡ በነበሩበት አስተባባዮች ነው።

﴿ إِنَّ جَهَنَّمَ كَانَتۡ مِرۡصَادٗا ٢١ لِّلطَّٰغِينَ مَـَٔابٗا ٢٢ لَّٰبِثِينَ فِيهَآ أَحۡقَابٗا ٢٣ ﴾ النبأ: ٢١ - ٢٣

‹‹ገሃነም (ክሓዲ እንግዶቿን ለማደን) ታደፍጣለች። ለአመፀኞችም ማረፊያ ናት። በውስጧ ዘወትር ይኖራሉ።›› *(አንቀጽ 21-23)*

ጀሃነም ተፈጥራለች። አሁንም ሕልውና አላት። ካህድያንን በመጠባበቅ ላይ ናት። ለነርሱ ተዘጋጅታለች። ልትቀበላቸው ተሰናድታለች። የጉዟቸው ፍጻሜም ትሆናለች። በምድረ ዓለም በጉዞ ላይ ነበሩ። በመጨረሻም ወደዋናው ማረፊያቸው ደረሱ። ዝንተ ዓለም ሊኖሩበት። ሁሌም ሊቀመጡበት።

لَّا يَذُوقُونَ فِيهَا بَرۡدٗا وَلَا شَرَابًا ٢٤

ከርሷ ውስጥ (የገሃነምን ቃጠሎ የሚያበርድላቸው) ቅዝቃዜ፥ (ጥማቸውን የምቆርጥላቸው) መጠጥም አይቀምሱም። *(አንቀጽ 24)*

ምንም ነገር እንዲቀምሱ አይፈቀድላቸውም። አንድ ነገር ሲቀር። እርሱም በረሃብና በጥማት ከመቃጠል ይበልጥ ያሰቃያል፦

﴿ إِلَّا حَمِيمٗا وَغَسَّاقٗا ٢٥ ﴾ النبأ: ٢٥

‹‹እጅግ የፈላ ውሃና እዥ ብቻ እንጂ (ሌላ መጠጥ አያገኙም)።›› (አንቀጽ 25)

ጉሮሮንና ሆድን የሚያቃጥል ፍል ውሃ፣ በእሳት ከሚቃጠሉ ሰዎች አካል እየተጨመቀና እየተንፈቀፈቀ የሚወጣ እዥ። የሚያገኙት ***‹‹ቅዝቃዜ››*** የሚፈቀድላቸው ***‹‹መጠጥ»*** ይህ ብቻ ነው።

በምድረ ዓለም ከፈጸሙት ተግባር ጋር የሚስማማ ምንዳ ይመነዳሉ።

﴿ إِنَّهُمۡ كَانُواْ لَا يَرۡجُونَ حِسَابٗا ٢٧ ﴾ النبأ: ٢٧

‹‹ለሚፈጽሟት እያንዳንዷ ድርጊት) ተጠያቂ እንደሚሆኑ ቅንጣት አይጠብቁም ነበር።›› (አንቀጽ 27)

ወደ አላህ እንደሚመለሱ፣ ከሞት እንደሚቀሰቀሱ አይገምቱም ነበር።

﴿ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا كِذَّابٗا ٢٨ ﴾ النبأ: ٢٨

‹‹አንቀጾቻችንን አስተባብለዋልና።›› (አንቀጽ 28)

የዓረብኛው ገለጻ ድምጸት የማስተባበላቸውን ብርታትና ጽናት ያሰርጻል። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ እነርሱ በማስተባበል ሲጸኑ አላህ ሁሉንም ድርጊታቸውን ኢምንት ሳታመልጠው ይቆጥርና ይመዘግብ ነበር።

﴿ وَكُلَّ شَيۡءٍ أَحۡصَيۡنَٰهُ كِتَٰبَۢا ٢٩ ﴾ النبأ: ٢٩

‹‹ሁሉንም ነገር (ይፈጽሙት የነበረውን እያንዳንዱን የኃጢአት ድርጊት) መዝገብ ውስጥ አስፍረናል።›› (አንቀጽ 29)

በመጨረሻም ያሉበት ሁኔታ እንደማይቀር፣ ቅጣቱም እንደማይቃለል እቅጩን የሚነግርና የሚያረዳ ተስፋ አስቆራጭ ወቀሳ ይከተላል፡-

﴿ فَذُوقُواْ فَلَن نَّزِيدَكُمۡ إِلَّا عَذَابٗا ٣٠ ﴾ النبأ: ٣٠ - ٣١

‹‹(ክሓዲያን ሆይ! የድርጊታችሁን ፍሬ) ቅመሱ፤ ከቅጣት ውጭ ምንም የምናክልላችሁ ነገር የለም፥ (እንላቸዋለን)።›› (አንቀጽ 30)

ቀጥሎም በካህድያን ላይ በገሃነም የሚፈጸመውን አሰቃቂ ቅጣት የሚቃረን ሌላ ትእይንት ያስቃኝናል። የአማኞች የገነት ሕይወት።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

⇒ ለምእራፏ የመጀመሪያ ጥያቄ ባለፉት አናቅጽ የተሰጠውን ምላሽ አብራራ፣

⇒ የመለያያውን ቀን ክስተቶችና ትእይንቶች ግለጽ፣

⇒ የገሐነምን ቅጣት አንቀጾቹ በሳሉት መልኩ ግለጽ፣

⇒ ቅጣቱ ‹ተስማሚ ምንዳ› የተባለው ለምን እንደሆነ አብራራ፣

⇒ የምርመራው ቀን መከሰቱ አይቀሬ ነው። ይህን ነጥብ አብራራ። ለዚያ ቀን ምን እያዘጋጀህ እንደሆነም አያይዘህ ግለጽ።

⇒ የቂያማን አስደንጋጭ ትእይንት ስታነብ የተሰማህን ስሜት ለጓደኛችህ አካፍል።

አንቀጽ 31-40

﴿إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا ﴿٣١﴾ حَدَآئِقَ وَأَعْنَٰبًا ﴿٣٢﴾ وَكَوَاعِبَ أَتْرَابًا ﴿٣٣﴾ وَكَأْسًا دِهَاقًا ﴿٣٤﴾ لَّا يَسْمَعُونَ فِيهَا لَغْوًا وَلَا كِذَّٰبًا ﴿٣٥﴾ جَزَآءً مِّن رَّبِّكَ عَطَآءً حِسَابًا ﴿٣٦﴾ رَّبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ٱلرَّحْمَٰنِ لَا يَمْلِكُونَ مِنْهُ خِطَابًا ﴿٣٧﴾ يَوْمَ يَقُومُ ٱلرُّوحُ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ صَفًّا لَّا يَتَكَلَّمُونَ إِلَّا مَنْ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحْمَٰنُ وَقَالَ صَوَابًا ﴿٣٨﴾ ذَٰلِكَ ٱلْيَوْمُ ٱلْحَقُّ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ مَـَٔابًا ﴿٣٩﴾ إِنَّآ أَنذَرْنَٰكُمْ عَذَابًا قَرِيبًا يَوْمَ يَنظُرُ ٱلْمَرْءُ مَا قَدَّمَتْ يَدَاهُ وَيَقُولُ ٱلْكَافِرُ يَٰلَيْتَنِى كُنتُ تُرَٰبًۢا ﴿٤٠﴾﴾ النبأ: ٣١ - ٤٠

‹‹አላህን ለሚፈሩ ጥንቁቆች (የሚፈልጉትን ሁሉ የሚያገኙበት) የስኬት ማዕከል ተዘጋጅቶላቸዋል። (ለዓይን የሚስቡ) የአትክልት ቦታዎችና ወይኖች፣ ጡቶቻቸው ጉች ጉች ያሉና በተመሣሣይ ዕድሜ ላይ የሚገኙ እጅግ ማራኪ እንስት ጓደኞችም፣ (በወይን ጠጅ) የተሞሉ ብርጭቆዎችም (ይጠብቋቸዋል)። ከርሷ ውስጥ አላስፈላጊ ቃላትንም ሆነ ሐሰትን ፈፅሞ አይሰሙም። (ይህ ሁሉ) ከጌታህ የተሰጣቸው ምንዳ ነው። በቂ የሆነ ስጦታ! የሰማያትና የምድር፥ እንዲሁም በመካከላቸው ያሉት (ፍጡራን) ሁሉ ጌታ የሆነው አዛኝ (አምላክ ስጦታ ነው)። (ከአስፈሪ ግርማ ሞገሱ የተነሳ ሰዎች) ሊያናግሩት አይደፍሩም። መንፈሱ (ጂብሪል) እና መላእክት በሰልፍ በሚቆሙበት (በዚያ አስፈሪ) ቀን፥ አር-ረሕማን የፈቀደለትና ትክክለኛውን የሚናገር ካልሆነ በቀር ከመካከላቸው አንድ የሚናገር የለም። ያ የተረጋገጠ (መከሠቱ ቅንጣት የማያጠራጥር) ቀን ነው። (ጽድቅ ተግባራትን በማክናወን ስኬትን) የሚከጅል ሰው (ይህንኑ በመፈፀም) ወደ ጌታው የሚያደርሰውን ጉዳና ይከተል። የሰው ልጅ እጆቹ ያስቀደሙትን (መልካም ይሁን ክፉ ተግባር በግልጽ) በሚመለከትበትና ከሓዲም፦ “ወይኔ፥ ምነው አፈር በሆንኩ” በሚልበት ቀን የሚከሠትን እጅግ ቅርብ የሆነ ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ።›› (አንቀጽ 31-40)

አጠቃላይ ዓላማ

⇒ ተማሪው የገነትን ጸጋ በአንቀጾቹ ውስጥ በተብራራው መልኩ እንዲገልጽ፣

⇒ የቂያማን ትእይንት በአንቀጾቹ በተዘረዘረው መልክ እንዲረዳ፣

⇒ የመለያያውን ቀን ሕልውና ለሚጠራጠሩ ወገኖች አላህ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ እንዲያብራራ፣

⇒ ምእራፏ የምትሸከረከርበትን አብይ አጀንዳ እንዲገልጽ፣

﴿إِنَّ لِلْمُتَّقِينَ مَفَازًا ﴿٣١﴾﴾ النبأ: ٣١

‹‹አላህን ለሚፈሩ ጥንቁቆች (የሚፈልጉትን ሁሉ የሚያገኙበት) የስኬት ማዕከል ተዘጋጅቶላቸዋል።›› (አንቀጽ 31)

ገሐነም አስተባባዮችን የምትጠባበቅ መሆኗ ተገልጿል። ከርሳ እንደማያመልጡ ተብራርቷል። በአንጻሩ አላህን የማፈሩ ሰዎች ፍጻሜያቸው ***መዳኛ ሰፍራ፣ የስክነት ማእከል*** የሆነችው ገነት ናት። ከድሎቷ መገለጫዎች ውስጥ ***አትክልቶችና ወይኖች፣ ተመሳሳይ እድሜና ውበት ያላቸው ማራኪ ልጃገረዶች፣ በመጠጥ የተሞሉ ብርጭቆዎች*** ይገኙበታል። ሕይወታቸው ከከንቱ ወሬ እና ከሐሰት የራቀ፣ ሰላሙ የተጠበቀ ነው። ከንቱ ወሬንና ሐሰትን አይሰሙም። እውነታው ግልጽ በመሆኑ ለክርክርም፣ ለማስተባበልም እድል አይኖርም። በጎ ነገር የሌለበት ከንቱ ወሬም ቦታ አይኖረውም። ለዘልዓለማዊው ገነት ተስማሚ የሆነ ንጹህ እና ምጡቅ የደስታ ሕይወት ይኖራሉ።

جَزَآءً مِّن رَّبِّكَ عَطَآءً حِسَابًا ﴿٣٦﴾

ከጌታህ የሆነ ምንዳ፣ በቂ የሆነ ስጦታ።

* * *

የምእራፏ መቋጫ ጠያቂዎች የሚጠይቁትን፣ አስተባባዮች የሚያስተባብሉትንና ይህ ሁሉ ክስተት የሚፈጸምበትን የመጭውን ዓለም ትእይንት ማሚያ ሁነት ይከስታል። ይህውም ጅብሪል እና

መላእክት ሞገሳማና አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ይቆማሉ። ትእይንቱ የእለቱን አስፈሪ ድባብ የበለጠ ያከብደዋል።

ይህ ምንዳ ከጌታህ የተገኘ ነው።

رَّبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا ٱلرَّحۡمَٰنِۖ

‹የሰማያትና የምድር፣ እንዲሁም በመካከላቸው ያሉ ፍጡራን ጌታ ከሆነው አዛኝ አምላክ።›››

ይህን ታላቅ እውነታ፣ ማለትም ሰማያትንና ምድርን ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጅም ያጠቃለለውን የአምላክ ተንከባካቢነት፣ ለማወጅ ምቹ ሁኔታ ነው። ይህ አምላክ ‹እጅግ በጣም ሩህሩህ› መሰኘቱንም ልብ ይሏል። ለካህድያንም ሆነ ለአማኞች ከላይ የተገለጸውን ምንዳ መስጠቱ የእዝነቱ መገለጫ፣ የሩህሩህነቱ እንጽብራቂ ነው። መላእክትና ጅብሪል ረድፍ ሰርተው፣ ቃላት ሳይተነፍሱ በሚቆሙበት በዚያ አስፈሪ ቀን ያለ ‹‹አልረህማን›› ፈቃድ አንዲት ቃል አይናገሩም። የሚናገሩትም ትክክለኛውን ብቻ ነው። አምላክ እንዲናገሩ የሚፈቅደውም የሚናገሩት ነገር ትክክለኛ መሆኑን ሲያውቅ ብቻ ነው።

يَوۡمَ يَقُومُ ٱلرُّوحُ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ صَفّٗاۖ لَّا يَتَكَلَّمُونَ إِلَّا مَنۡ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَقَالَ صَوَابٗا

በዚህ ትእይንት አስፈሪ ድባብ መካከል ተከታዩ የማስጠንቀቂያ መልእክት ይተላለፋል።

﴿ ذَٰلِكَ ٱلۡيَوۡمُ ٱلۡحَقُّۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ مَـَٔابًا ٣٩ إِنَّآ أَنذَرۡنَٰكُمۡ عَذَابٗا قَرِيبٗا يَوۡمَ يَنظُرُ ٱلۡمَرۡءُ مَا قَدَّمَتۡ يَدَاهُ وَيَقُولُ ٱلۡكَافِرُ يَٰلَيۡتَنِي كُنتُ تُرَٰبَۢا ٤٠ ﴾ النبأ: ٣٩ - ٤٠

‹‹ያ የተረጋገጠ (መከሠቱ ቅንጣት የማያጠራጥር) ቀን ነው። (ጽድቅ ተግባራትን በማክናወን ስኬትን) የሚከጅል ሰው (ይህንኑ በመፈፀም) ወደ ጌታው የሚያደርሰውን ጐዳና ይከተል። የሰው ልጅ እጆቹ ያስቀደሙትን (መልካም ይሁን ክፉ ተግባር በግልጽ) በሚመለከትበትና

ከሓዲም፦ "ወይኔ፥ ምነው አፈር በሆንኩ" በሚልበት ቀን የሚከሠትን እጅግ ቅርብ የሆነ ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ።›› (አንቀጽ 39-40)

‹የተረጋገጠ ቀን›› የሚጠራጠሩ ወገኖችን የሚነዝርና የሚያርገፈግፍ ማስጠንቀቂያ። ቀኑ መምጣቱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ለጥያቄና ለውዝግብ መስክ የለም። ይህም ሆኖ አሁንም የእድል በር አልተዘጋም። ‹የፈለገ ሰው› ካህድያንን የምትጠባበቀው ጀሃነም ማረፊያው ከመሆኗ በፊት ወደ አምላክ ይመለስ።

إِنَّآ أَنذَرۡنَٰكُمۡ عَذَابٗا قَرِيبٗا

‹‹ቅርቢቱን ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ።››

ሌላ ማስጠንቀቂያ። ቅጣቱ ሩቅ አይደለም። አስፈሪነቱ ከላይ የተገለጸላችሁ ገሃነም እየተጠባበቃችሁ ነው። ካህድያን ከመኖር አለመኖርን እንዲመርጡ የሚያስገድዳቸው አስፈሪ ቅጣት ሳይውል ሳያድር መከሰቱ እሙን ነው።

يَوۡمَ يَنظُرُ ٱلۡمَرۡءُ مَا قَدَّمَتۡ يَدَاهُ وَيَقُولُ ٱلۡكَافِرُ يَٰلَيۡتَنِي كُنتُ تُرَٰبَۢا ٤٠

የሰው ልጅ እጆቹ ያስቀደሙትን (መልካም ይሁን ክፉ ተግባር በግልጽ) በሚመለከትበትና ከሓዲም፦ "ወይኔ፥ ምነው አፈር በሆንኩ" በሚልበት ቀን

ስቃይ ጠንቶበት፣ በመከራ ተከብቦ ይህን ጩኸቱን ያሰማል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

⇒ የጀነትን ድሎት በአንቀጾቹ በተብራራዉ መልኩ አብራራ፣

⇒ የቂያማን ትእይንት አንቀጾቹ በሳሉት መልክ ግለጽ፣

⇒ የመለያያውን ቀን ለተጠራጠሩ ወገኖች አላህ የሰነዘራቸውን ማስጠንቀቂያዎች ዘርዝር፣

⇒ **የምእራፉን አብይ አጀንዳና ፍሬ ነገር ግለጽ፣**

⇒ **ስለቂያማ ቀን አስፈሪ ትእይንት ያደረብህን ስሜት አካፍል።**

⇒ **አላህ ይህን ዩኒቨርስ የመፍጠሩን እውነታና የውለታውን ግዝፈት ግለጽ፣**

* * *

አልናዚዓህ

አንቀጽ 1-14

﴿ وَٱلنَّٰزِعَٰتِ غَرۡقٗا ١ وَٱلنَّٰشِطَٰتِ نَشۡطٗا ٢ وَٱلسَّٰبِحَٰتِ سَبۡحٗا ٣ فَٱلسَّٰبِقَٰتِ سَبۡقٗا ٤
فَٱلۡمُدَبِّرَٰتِ أَمۡرٗا ٥ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلرَّاجِفَةُ ٦ تَتۡبَعُهَا ٱلرَّادِفَةُ ٧ قُلُوبٞ يَوۡمَئِذٖ وَاجِفَةٌ ٨
أَبۡصَٰرُهَا خَٰشِعَةٞ ٩ يَقُولُونَ أَءِنَّا لَمَرۡدُودُونَ فِي ٱلۡحَافِرَةِ ١٠ أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمٗا نَّخِرَةٗ ١١
قَالُواْ تِلۡكَ إِذٗا كَرَّةٌ خَاسِرَةٞ ١٢ فَإِنَّمَا هِيَ زَجۡرَةٞ وَٰحِدَةٞ ١٣ فَإِذَا هُم بِٱلسَّاهِرَةِ ١٤ ﴾

النازعات: ١ - ١٤

‹‹(የከሓዲያንን ነፍስ) በኃይል መንጭቀው በሚያወጡ፤ (የምእምናንን ነፍስ) በእዝነትና በእርጋታ በሚመዙ፤ (አየር ውስጥ) በፍጥነት በሚዋኙ፤ (ወደ እምነት) ቀዳሚዎች በሆኑ፤ (በአላህ ትእዛዝ) ጉዳዮችን በሚፈጽሙ (መላእክት) እምላለሁ! (ከሞት በኋላ ዳግም የመቀስቀሳችሁ ነገር እርግጥ ነው።) ተርገፍጋፊይቱ በምትርገፈገፍበት ቀን፤ ለጣቂይቱም እርሷን በምትከተልበት (ቀን)። በዚያን ቀን (የከሓዲያን) ልቦች በፍርሃት ይርዳሉ። ዓይኖቻቸው (በውርደት) ይሰበራሉ። (በዚህች ዓለም ውስጥ የትንሣኤን እምነት ባለመቀበል) እንዲህ ይላሉ፦ “ወደ ድሮው እኛነታችን እንመለሳለን? ወደ በሰበሱ አጥንቶች ከተለወጥን በኋላ?” ይላሉም፦ “ይህች በኪሣራ የተሞላች መመለስ ናት፥ (ከሞት በኋላ ዳግም የመቀስቀስ ነገር እውነት ከሆነ የሚገጥመን ኪሣራ እጅግ አስከፊ ነው)።” (ሙታንን ከመቃብር የምትቀሰቅሰው) አንዲት (አስደንጋጭ) ጩኸት ብቻ ናት። (ሙታን ድምጿን ሲሰሙ የተጫናቸውን አፈር አራግፈው) ከምድር በላይ ይሆናሉ።›› *(አንቀጽ 1-14)*

አጠቃላይ ዓላማዎች

⇒ ተማሪው ለነዚህ አናቅጽ የተሰጡ የተለያዩ ትርጉሞችን እንዲያስታውስ፣

⇒ እነዚህን አናቅጽ ሲያነብ የሚያሰርጽበትን ስሜት እንዲያብራራ፣

⇒ በአንቀጾቹ የተገለጹትን የቂያማ ትእይንቶች እንዲያብራራ፣

⇒ በአንቀጹ የተገለጸውንና መንገድ የሳቱ ወገኖች በእለተ ቂያማ በመካከላቸው የሚያደርጉትን ውይይት ማስታወስ፣

⇒ በእለተ ቂያማ የሚከሰቱትንና ለአስተባባዮች ፈጣን ምላሽ ይሆኑ ዘንድ የሚያስችሉትን ክስተቶችና እውነታዎች ማስታወስ፣

* * *

የመጭው አለም አስፈሪ፣ ግዙፍ እና የምር የሆነ እውነታ የሰው ልጅ ልቦና እንዲሰማው ለማድረግ ለወረደው ለዚህ ጁዝእ ይህ ምእራፍ ጥሩ ናሙና ነው። የአኼራን እጅግ ግዙፍ፣ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ክስተት በሰው ልጅ ልቦና ውስጥ ለማስረጽ በሚያደርገው በዚህ ጥረት ቅኝቱን በመለዋወጥ ቀልብን ያነቃል።

﴿ وَٱلنَّٰزِعَٰتِ غَرۡقٗا ١ وَٱلنَّٰشِطَٰتِ نَشۡطٗا ٢ وَٱلسَّٰبِحَٰتِ سَبۡحٗا ٣ فَٱلسَّٰبِقَٰتِ سَبۡقٗا ٤ فَٱلۡمُدَبِّرَٰتِ أَمۡرٗا ٥ ﴾ النازعات: ١ - ٥

‹‹(የከሓዲያንን ነፍስ) በኃይል መንጭቀው በሚያወጡ፤ (የምእምናንን ነፍስ) በእዝነትና በእርጋታ በሚመዙ፤ (አየር ውስጥ) በፍጥነት በሚዋኙ፤ (ወደ እምነት) ቀዳሚዎች በሆኑ፤ (በአላህ ትእዛዝ) ጉዳዮችን በሚፈጽሙ (መላእክት) እምላለሁ! (ከሞት በኋላ ዳግም የመቀስቀሳችሁ ነገር እርግጥ ነው።)›› (አንቀጽ 1-5)

የእነዚህን ቃላት ትርጉም በተመለከተ፡- ነፍስን ከአካል በሐይል መንጭቀው የሚያወጡ፣ በብርቱው የሚንቀሳቀሱ፣ በላይኛው ዓለም ውስጥ የሚዋኙ፣ የአምላካቸውን ትእዛዝ ለመፈጸም ቀዳሚዎች የሆኑ፣ የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ የሚያከናውኑ መላእክት ናቸው ተብሏል፡ ፡ ከምሕዋራቸው ተመንጭቀው በመውጣት እየተሽቀዳደሙ ከአንድ ማረፊያ ወደሌላው በትጋት የሚንቀሳቀሱ፣ በሕዋቸው ውስጥ የሚዋኙ፣ አላህ የጣለባቸውን ሐላፊነት በመወጣት በምድር ሕይወት ላይ ተጽእኖ

የሚያሳድሩ ተግባራትን የሚያከናውኑ ከዋክብትና ኘላኔቶች ናቸውም ተብሏል።

‹በሐይል አውጭ፣ በእዝነትና በእርጋታ በሚመዙ ፣ ዋኝዎችና ቀዳሚዎች› የተባሉት ከዋክብት ሲሆኑ፣ የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ የሚያከናውኑት › መላእክት ናቸው ተብሏል።

ትርጉማቸው ምንም ይሁን ምን በቁርአን ድባብ ውስጥ ካሳለፍነው ሕይወት አኳያ እንደሚሰማን እነዚህ እውነታዎች በዚህ ቦታ ላይ መጠቀሳቸው ከሁሉም ነገር በፊት ቀልብን ያርገፈግፋል። ሕሊናን ያነቃል። አንዳች አስፈሪ ነገር የመጠበቅን ስሜት ያሳድራል። ይህን ስሜት ሳንነካከ እንደወደረደ በመጠበቅ በቁርአን ጥላ ስር ተፈጥሯዊ ድባቡን ለማስተናገድ መልእክታቸውን ስናብራራ፣ ሳንጨምር እና ሳንቀንስ እንዳለ መተውን መርጠናል። ቀልብን መቀስቀስና ማንቃት፣ ማርገፍገፍና ማስፈራት ቁርአን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እውን ማድረግ የሚሻው ራሱን የቻለ ዓላማ ነው።

ይህ የምእራፏ መወጠኛ በቀጣዮቹ አናቅጽ የተገለጸውን እውነታ ለማጽናት በመሐላ መልክ የቀረበ ነው።

﴿ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلرَّاجِفَةُ ٦ تَتۡبَعُهَا ٱلرَّادِفَةُ ٧ ﴾ النازعات: ٦ - ٧

‹‹ተርገፍጋፊይቱ በምትርገፈገፍበት ቀን፤ ለጣቂይቱም እርሷን በምትከተልበት (ቀን)።›› (አንቀጽ 6-7)

ተርገፍጋፊይቱ ምድር መሆኗ ተነግሯል።

﴿ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلۡأَرۡضُ وَٱلۡجِبَالُ وَكَانَتِ ٱلۡجِبَالُ كَثِيبًا مَّهِيلًا ١٤ ﴾ المزمل: ١٤

‹‹ምድርም ጋራዎችም በሚርገፈገፉበት፥ ጋራዎች ፈሳሽ የአሸዋ ክምር በሚሆኑበት (እጅግ) አስደንጋጭና አስፈሪ) ቀን።›› (ሱል መዘሚል 14)

ለጣቂይቱ ደግሞ ሰማይ መሆኗ ተነግሯል። በመፈራረስ ምድርን ትከተላለች ማለት ነው። ትሰነጠቃለች፣ ከዋክብቶቿም ይረግፋሉ። *ተርገፍጋፊይቱ* በቀንድ መነፋት ጊዜ የምትሰማው የመጀመሪያዋ ጩኸት እንደሆነችም ተነግሯል። እርሷ ስትሰማ ምድር፣ ጋራዎች እና ሕያውያን በሙሉ ይርገፈገፋሉ። አላህ ከሻው ውጭ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉ ሁሉ ይሞታሉ። ለጣቂይቱም ሰዎች ከሞት የሚቀሰቀሱባትና የሚሰበሰቡባት ሁለተኛዋ መነፋት ናት ተብሏል።

ይህም ሆነ ያ የሰው ልጅ ቀልብ ይህን መልእክት ሲሰማ ድንጋጤ ይነዝረዋል። ፍርሃት ያርደዋል። ስጋት ያርገፈግፈዋል። በሁከት ይናጣል። በጭንቀት ይንቀጠቀጣል። በዚያን ቀን ሕሊና የሚያገኘው ከባድ ድንጋጤ፣ ጽናትና መረጋጋት አልባ ፍርሃት እንዲሰማ፣ ተከታዩን የአላህ ቃል መልእክት እንዲሰርጸው ያደርጋል፦

﴿ قُلُوبٌ يَوۡمَئِذٖ وَاجِفَةٌ ۝٨ أَبۡصَٰرُهَا خَٰشِعَةٞ ۝٩ ﴾ النازعات: ٨ - ٩

‹‹በዚያን ቀን (የከሓዲያን) ልቦች በፍርሃት ይርዳሉ። ዓይኖቻቸው (በውርደት) ይሰበራሉ።›› (አንቀጽ 8-9)

ቀልቦች የዚያን ቀን በብርቱው ይታወካሉ። በውርደት ይሰበራሉ። ፍርሃት ይውጣቸዋል። ቅስማቸው ይሰበራል። ድንጋጤ ያንዘፈዝፋቸዋል። ስጋት ያፈራርሳቸዋል።

ቀጣዩ ቅኝት ከመቃብሮቻቸው ሲነሱ በግርምት መደመማቸውን፣ እጅጉን መደነቃቸውን የሚገልጽ ነው፦

﴿ يَقُولُونَ أَءِنَّا لَمَرۡدُودُونَ فِي ٱلۡحَافِرَةِ ۝١٠ أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمٗا نَّخِرَةٗ ۝١١ ﴾ النازعات: ١٠ - ١١

‹‹በዚህች ዓለም ውስጥ የትንሣኤን እምነት ባለመቀበል) እንዲህ ይላሉ፦ “ወደ ድሮው እኛነታችን እንመለሳለን? ወደ በሰበሱ አጥንቶች ከተለወጥን በኋላ?” (አንቀጽ 10-11)

“ወደ መጀመሪያይቱ ሁኔታ፣ ወደ ሕይወት እንመለሳለን?” ሲሉም ይጠይቃሉ- በመደነቅ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ስጋችን ከፈራረሰ፣ አጥንታችን ከበሰበሰ በኋላ እንዴት ሊሆን ይችላል?›

ወዲያውኑ ከቅኸርታቸው ይነቃሉ። በእርግጥም ወደ ሕይወት መመለሳቸውን ይገነዘባሉ። ግና ሌላ ሕይወት ነው። ኪሣራቸው ይገለጽላቸዋል። እንዲህ ሲሉ በቁጭት ይንገበገባሉ፡-

﴿ قَالُوا۟ تِلْكَ إِذًا كَرَّةٌ خَاسِرَةٌ ﴿١٢﴾ ﴾ النازعات: ١٢

ይላሉም፡- “ይህች በኪሣራ የተሞላች መመለስ ናት፥ (ከሞት በኋላ ዳግም የመቀስቀስ ነገር እውነት ከሆነ የሚገጥመን ኪሣራ እጅግ አስከፊ ነው)።” (አንቀጽ 12)

ተገቢ ትኩረት ያልሰጧት፣ በቂ ዝግጅት ያላደረጉባት፣ ኪሣራ እንጅ የማይጠብቁባት መመለስ።

በዚህ ትእይንት መሐል ቁርአናዊው ቅኝት አንድን አይቀሬ እውነታ በመግለጽ ይቋጫል፡-

﴿ فَإِنَّمَا هِىَ زَجْرَةٌ وَٰحِدَةٌ ﴿١٣﴾ فَإِذَا هُم بِٱلسَّاهِرَةِ ﴿١٤﴾ ﴾ النازعات: ١٣ - ١٤

‹‹(ሙታንን ከመቃብር የምትቀሰቅሰው) አንዲት (አስደንጋጭ) ጩኸት ብቻ ናት። (ሙታን ድምጿን ሲሰሙ የተጫናቸውን አፈር አራግፈው) ከምድር በላይ ይሆናሉ።›› (አንቀጽ 13-14)

‹‹እንቅልፍ የሌለባት›› ምድር የተባለችው ሰዎች ለፍርድ የሚሰበሰቡባት ሜዳ ናት። የት እንደምትገኝ አናውቅም። ጨኸቷ ሰዎች ከሞት ከማቀሰቀሱባት ሁለተኛዋ መነፋት እንደሆነች ሚዛን የሚደፋው እይታ ያመለክታል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

⇒ ለአንቀጾቹ የተሰጡ የተለያዩ ትርጉሞችን ጥቀስ፣

⇒ አንድ ሰው እነዚህን አናቅጽ ሲያነብ የሚሰማውን ስሜት አብራራ፣

⇒ በአንቀጾቹ የተጠቀሰውን የእለተ ቂያማ ክስተት ግለጽ፣

⇒ መንገድ የሳቱ ወገኖች በመካከላቸው የሚያደርጉትን ውይይት አውሳ፣

⇒ በዚህ የእለተ ቂያማ ትእይንት መሐል የሚከሰቱና ለአስተባባዮች ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ የሚሰጡ ሁነቶችን አውሳ፣

* * *

አንቀጽ 15-26

﴿ هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ مُوسَىٰٓ ١٥ إِذۡ نَادَىٰهُ رَبُّهُۥ بِٱلۡوَادِ ٱلۡمُقَدَّسِ طُوٗى ١٦ ٱذۡهَبۡ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ١٧ فَقُلۡ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ١٨ وَأَهۡدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخۡشَىٰ ١٩ فَأَرَىٰهُ ٱلۡأٓيَةَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ٢٠ فَكَذَّبَ وَعَصَىٰ ٢١ ثُمَّ أَدۡبَرَ يَسۡعَىٰ ٢٢ فَحَشَرَ فَنَادَىٰ ٢٣ فَقَالَ أَنَا۠ رَبُّكُمُ ٱلۡأَعۡلَىٰ ٢٤ فَأَخَذَهُ ٱللَّهُ نَكَالَ ٱلۡأٓخِرَةِ وَٱلۡأُولَىٰٓ ٢٥ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَعِبۡرَةٗ لِّمَن يَخۡشَىٰٓ ٢٦ ﴾ النازعات: ١٥ - ٢٦

የሙሳ ታሪክ ደርሶሃልን?ጌታው በተቀደሰው የ"ጡዋ" ሸለቆ ውስጥ ጥሪ ባደረገለት ጊዜ፤(አለውም)፦ "ወደ ፈርዖን ሂድ፤ ወሰኖችን ሁሉ አልፏልና።"በለውም፦ "(ከወንጀል ርክሰት) ለመጽዳት ዝንባሌው አለህን?ትፈራው ዘንድ ወደ ጌታህ እንድመራህ (ፍላጐቱ9 አለህን?)"

(ሙሳ ለፈርዖን) ታላቅ ተዓምር አሳየው።(ፈርዖን ሙሳን) አስተባበለው፤ (በአላህ ትእዛዝ ላይ) አመፀም። ከዚያም (ለጥፋት ተልዕኮ) በትጋት ለመንቀሳቀስ (ወሰኖ) 5ረ።(ደጋፊዎቹ9ን) ሰበሰበ፤ ተጣራም፤ "እኔ ልዑል ጌታችሁ (የበላይ ገዦችሁ) ነኝ" አለም። አላህም የመጭውንም የዚህችንም ዓለም ሕይወት ቅጣት ቀጣው።ይህ (የተጠቀሰው የፈርዖን ታሪክና ፍፃሜው) አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ትምህርት አዘል ማስጠንቀቂያ ነው። *(ሰንቀጽ 15-26)*

አጠቃላይ ዓላማዎች

⇒ **በአንቀጾቹ ውስጥ የተወሱትን የሙሳና የፊርአውን ታሪክ ክስተቶች ተማሪው እንዲያስታውስ፣**

⇒ **በዚህ ታሪክና በምእራፏ ፍሬ ነገር መካከል ያለውን ትስስር እንዲረዳ፣**

* * *

ቁርአናዊው ቅኝት ጥቂት ረገብ ባለ ድምጸት የሙሳንና የፊርአውንን ታሪክ፣ አምባገነኑ ፊርአውን ያጋጠመውን ፍጻሜ ይተርካል።

የሙሳ ታሪክ በቁርአን ውስጥ ከየትኛውም ታሪክ በበለጠ ሁኔታ ለበርካታ ጊዜና በዝርዝር ቀርቧል። በዚህ ቦታ ላይም ይህው ታሪክ

ባጭሩ እና በፈጣን የትረካ ስልት ተመልክቷል። ሙሳ በተቀደሰው ሸለቆ ውስጥ በተደረገላቸው ጥሪ ተወጥኖ፣ በፊርዓውን ላይ የተላለፉ የሁለቱን ዓለማት ቅጣቶች ቃኝቶ ይጠናቀቃል። ነቢዩ ሙሐመድን ‹የሙሳ ወሬ መጥቶሃልን?› ሲል በመጠየቅ ይጀመራል። ልቦና ቀሪውን የታሪኩን ክፍል በጉጉት እንዲጠባበቅና ለማድመጥ እንዲዘጋጅ ለማድረግ የቀረበ ጥያቄ ነው።።

በመጀመሪያ ለሙሳ የተደረገላቸውን ጥሪ ይጠቅሳል፡-

﴿إِذۡ نَادَىٰهُ رَبُّهُۥ بِٱلۡوَادِ ٱلۡمُقَدَّسِ طُوٗى ١٦﴾ النازعات: ١٦

‹‹ጌታው በተቀደሰው የ“ጡዋ” ሸለቆ ውስጥ ጥሪ ባደረገለት ጊዜ፤›› (አንቀጽ 16)

‹‹ጡዋ›› የሸለቆው ስም እንደሆነ ሚዛን የሚደፋው እይታ ያመለክታል። ከሂጃዝ በስተሰሜኔ በኩል ከምትገኘው የመድየን ኩተማ ለሚመጣ ሰው ይህ ሸለቆ ከጡር ጋራ በስተቀኝ በኩል ይገኛል። የጥሪው ቅጽበት እጅግ አስፈሪ ብቻ ሳይሆን አስገራሚም ነው። አላህ ለአንድ ባሪያው የሚያደርገው ይህ ጥሪ በእርግጥም ግዙፍ ክስተት ነው። ምንነቱን ለመግለጽ ቃላት ጉልበት የላቸውም።

﴿ٱذۡهَبۡ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ١٧﴾ النازعات: ١٧

(አለውም)፦ “ወደ ፈርዖን ሂድ፤ ወሰኖችን ሁሉ አልፏልና።” (አንቀጽ 17)

ወሰን አላፊነት ሊከሰትም፣ ሕልውና ሊኖረውም የማይገባ ባህሪ ነው። እጅግ የሚያስጠላ፣ ምድርን የሚበክል፣ አላህ የሚወደውን ድርጊት የሚቃረን፣ ወደሚጠላው የሚያደርስ እኩይ ምግባር ነው። ስለዚህም ይህን ምግባር ለመከልከል አላህ ከምርጥ ባሪያዎቹ መካከል አንዱን በልዑክነት ይልከዋል። ይህን ክፉ ነገር፣ ወሰን አላፊነት ለማስቆም መከራ እንዲያደርግም ያዘዋል። ከዚያም ወሰን አላፊው አምባገነን

የአላህን ቅጣትና ቁጣ ፈርቶ ከድርጊቱ ይታቀብ ዘንድ የሚያናግርበትን ውብና ልቦናን የሚስብ የአነጋገር ስልት አስተማረው፡-

﴿ فَقُلۡ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ١٨ ﴾ النازعات: ١٨

‹‹በለውም፡- “(ከወንጀል ርክሰት) ለመጽዳት ዝንባሌው አለህን?›› (ሱንቀጽ 18)

ከወሰን አላፊነት ቆሻሻ፣ ከሐጢአት ርክሰት ትጸዳ ዘንድ ትሻለህን? ወደ በረከታማ መንገድ ልምራህን?

﴿ وَأَهۡدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخۡشَىٰ ١٩ ﴾ النازعات: ١٩

‹‹ትፈራው ዘንድ ወደ ጌታህ እንድመራህ (ፍላጐቱ አለህን?)” (ሱንቀጽ 19)

የአምላክህን መንገድ ላሳውቅህን? እርሱን ስታውቅ የአምላክ ፍርሃት ከልቦህና ላይ ያድራል። አንድ ሰው ወሰን ሊያልፍ የሚችለው ከጌታው ሲርቅ ብቻ ነው። ያኔ አምባገነንነት እና አመጽ ይጠናወተዋል።

﴿ فَأَرَىٰهُ ٱلۡأٓيَةَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ٢٠ فَكَذَّبَ وَعَصَىٰ ٢١ ﴾ النازعات: ٢٠ - ٢١

‹‹(ሙሳ ለፈርዖን) ታላቅ ተዓምር አሳየው። (ፈርዖን ሙሳን) አስተባበለው፣ (በአላህ ትእዛዝ ላይ) አመፀም።›› (ሱንቀጽ 20-21)

ሙሳ አምላካቸው ባስተማራቸው ጥበብና ስልት መልእክታቸውን አደረሱ። ይህ ተወዳጅ የዳእዋ ስልት አምላክን ከማወቅ የነጠፈውን የዚህን አምባገነን ልቦና ሊያለዝብ አልቻለም። እናም ትልቁን ተአምር፣ ማለትም ዘንጋቸውን ወደ እባብነት ለውጠው፣ እጃቸውንም አብርተው አሳዩት። እርሱ ግን አልተቀበላቸውም። አስተባበለ። አመጸም። የሁለቱ ወገኖች ግንኙነትእዚህ ላይ አከተመ።

* * *

ቀጣዩ ቅኝት ፊርዓውን እውነትን መቀበል፣ መቀናትን መምረጥ ተስኖት፣ ከሙሳ ዞሮና ሸሽቶ፣ ድግምትን ከሐቅ ሊያፋልም ደጋሚዎችን ለመሰብሰብ ሲሮጥና ሲተጋ የሳያል።

﴿ ثُمَّ أَدۡبَرَ يَسۡعَىٰ ٢٢ فَحَشَرَ فَنَادَىٰ ٢٣ ﴾ النازعات: ٢٢ - ٢٣

‹‹ከዚያም (ለጥፋት ተልዕኮ) በትጋት ለመንቀሳቀስ (ወሰኖ) ዞረ። (ደጋፊዎቹን) ሰበሰበ፤ ተጣራም፤›› (አንቀጽ 22-23)

ለጥፋት ዞረ። ለማሴር ተጋ። ሕዝቡንም ደጋሚዎችንም ሰበሰበ። በትእቢትና በመሐይምነት የተሞላ እጅግ አስቀያሚና ስርዓት አልባ ቃልም እንዲህ ሲል ተናገረ፦

﴿ فَقَالَ أَنَا۠ رَبُّكُمُ ٱلۡأَعۡلَىٰ ٢٤ ﴾ النازعات: ٢٤

“እኔ ልዑል ጌታችሁ (የበላይ ገዣችሁ) ነኝ” አለም። (አንቀጽ 24)

በሚገዛው ሕዝብ ቂልነትና እርሱን አሜን ብሎ በመገዛቱ ተሞኝቶ ይህን ቃል ከአንደበቱ አወጣ። አምባገነኖችን እንደሚገዙት ሕዝብ ዝንጋታ፣ ወራዳነትና አሜን ብሎ ታዛዥነት የሚያቂላቸው ነገር የለም። አምባገነን፣ ሐይልም ስልጣንም የሌው ግለሰብ እንጅ ሌላ አይደለም። ግና ማሕበረሰቡ ትክሻውን ሲያመቻችለት ይጋልበዋል። አንገቱን ሲሰጠው እንዳሻው ይጎትተዋል። ራሱን ሲያቀረቅርለት ይኮፈሳል። ክብሩንና መብቱን እንዲዳፈር ሲፈቅድለት ወሰን ያልፋል። ፊርዓውንም ከሚያስተዳድረው ሕዝብ ይህን ቂልነት፣ ውርደትና እምነት አልባነት በማግኘቱ በክህደት የተሞላ እኩይ ቃሉን ተናገረ። ‹‹እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ።›› ለማለት ደፈረ። ሕዝቡ ንቁና ለክብሩ ቀናኢ፣ እንዲሁም ፊርዓውን ምንም ማድረግ የማይችል ደካማ ግለሰብ መሆኑን የተረዳ አማኝ ሕዝብ ቢሆን ኖሮ ንጉሱ ይህን ቃል ለመናገር አይደፍርም ነበር።

ከከፋ ወሰን አላፊነት በተጓዳኝ ይህ አስቀያሚ ትእቢት ቢታከል ታላቁ ሐይል ተንቀሳቀሰ። አስከፊ ቅጣትም ቀጣው፦

﴿ فَأَخَذَهُ ٱللَّهُ نَكَالَ ٱلۡأٓخِرَةِ وَٱلۡأُولَىٰ ٢٥ ﴾ النازعات: ٢٥

‹‹አላህም የመጭውንም የዚህችንም ዓለም ሕይወት ቅጣት ቀጣው።›› *(አንቀጽ 25)*

የመጭው ዓለም ቅጣት ከዚህኛው ይበልጥ የበረታ እና ዘልዓለማዊ በመሆኑ እርሱን አስቀድሞ ጠቀሰ። በእርግጥም ወሰን አላፊነትን በብርታትና ዘወትር የሚያሰቃይ እውነተኛ ቅጣት እርሱ ነው።

የመጀመሪያው (የዚህች ዓለም) ቅጣቱም እጅግ አስቃቂና አስከፊ ነበር። ከርሱ የሚበረታው የመጭው ዓለም ቅጣት እንዴት ይሆን?

ከአያት ቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሐይልና ስልጣን የነበረው ፊርዓውን ይህን ያህል ከተንኮታኮተ ሌሎች አስተባባዮችና ወሰን አላፊዎች፣ ነቢዩ ሙሐመድን የተቀናቀኑ አጋሪዎችማ ይበልጥ ይፈራርሳሉ።

﴿ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَعِبۡرَةٗ لِّمَن يَخۡشَىٰٓ ٢٦ ﴾ النازعات: ٢٦

‹‹ይህ (የተጠቀሰው የፈርዖን ታሪክና ፍፃሜው) አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ትምህርት አዘል ማስጠንቀቂያ ነው።›› *(አንቀጽ 26)*

የፊርዓውን ታሪክ ለሌሎች ሰዎች ትምህርት ሰጭ መሆኑን የሚነገዘበው አምላክን የሚያውቅና የሚፈራርሰው ነው። ልቦናው የአምላክን ፍርሃት የማያውቀውማ በርሱና በተግሳጽ መካከል ግርዶ አለ። እንዲህ አይነቱ ሰው ከጥንት መሰሎቹ ትምህርት ሳይቀስም ከክፉ ፍጻሜው ጋር ይላተማል። አላህ የሁለቱን አለማት ብርቱ ቅጣት ያቀምሰዋል። ሁሉም ሰው ለመረጠው ጎዳናና ለሚያደርሰው ፍጻሜ የተገራ ነው። በእርግጥም ከሌሎች የሚማረው አላህን የሚፈራ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ✓ በአንቀጾቹ የተጠቀሱትን የሙሳና የፊርዓውን ታሪክ አውሳ
- ✓ በዚህ ታሪክ እና በምእራፏ አብይ ፍሬ ነገር መካከል ያለውን ትስስር አብራራ።

አንቀጽ 27-46

﴿ ءَأَنتُمۡ أَشَدُّ خَلۡقًا أَمِ ٱلسَّمَآءُۚ بَنَىٰهَا ﴿٢٧﴾ رَفَعَ سَمۡكَهَا فَسَوَّىٰهَا ﴿٢٨﴾ وَأَغۡطَشَ لَيۡلَهَا وَأَخۡرَجَ ضُحَىٰهَا ﴿٢٩﴾
وَٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ ذَٰلِكَ دَحَىٰهَآ ﴿٣٠﴾ أَخۡرَجَ مِنۡهَا مَآءَهَا وَمَرۡعَىٰهَا ﴿٣١﴾ وَٱلۡجِبَالَ أَرۡسَىٰهَا ﴿٣٢﴾ مَتَٰعًا لَّكُمۡ
وَلِأَنۡعَٰمِكُمۡ ﴿٣٣﴾ فَإِذَا جَآءَتِ ٱلطَّآمَّةُ ٱلۡكُبۡرَىٰ ﴿٣٤﴾ يَوۡمَ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ مَا سَعَىٰ ﴿٣٥﴾ وَبُرِّزَتِ
ٱلۡجَحِيمُ لِمَن يَرَىٰ ﴿٣٦﴾ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٣٩﴾
وَأَمَّا مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَنَّةَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٤١﴾ يَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ
ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرۡسَىٰهَا ﴿٤٢﴾ فِيمَ أَنتَ مِن ذِكۡرَىٰهَآ ﴿٤٣﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ مُنتَهَىٰهَآ ﴿٤٤﴾ إِنَّمَآ أَنتَ مُنذِرُ مَن
يَخۡشَىٰهَا ﴿٤٥﴾ كَأَنَّهُمۡ يَوۡمَ يَرَوۡنَهَا لَمۡ يَلۡبَثُوٓاْ إِلَّا عَشِيَّةً أَوۡ ضُحَىٰهَا ﴿٤٦﴾ ﴾ النازعات: ٢٧ - ٤٦

‹‹(እናንተ አጋሪዎች ሆይ!) ለመፍጠር ይበልጥ አስቸጋሪ የትኛው ነው? እናንተ ወይስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፤ ጣሪያዋን አንሄ፤ አስተካከላትም። ሌሊቱን ጨለማ፥ ቀኑን ግልጽ አደረገ። ከዚያ በኋላ ምድርን ዘረጋ። ከውስጧም ውሃን አፈለቀ፥ (የእንስሳ ትንና የሰዎችን) ምግቦች አበቀለም። ጋራዎችን (ምድር ላይ) ቸከለ። (ይህን ሁሉ ያደረገው) ለናንተና ለእንሰሳዎቻችሁ መጠቀሚያ ነው። ታላቂ መዓት (ዕለተ ምጽዓት) በተከሠተች ጊዜ፤ የሰው ልጅ (በዚህች ዓለም) የፈፀማቸውን ድርጊቶች በሚያስታውስበት (በዚያ) ዕለት፤ ገሃነም ለተመልካች ግልጽ በምትደረግበት (በዚያ) ዕለት፤ በክህደትና ጥመት) ወሰንን ያለፈ፣ (ከመጭው ዓለም ሕይወት ይልቅ) የዚህችን ዓለም ሕይወት የመረጠ፣ መኖሪያው ገሃነም ናት።ከጌታው ፊት መቆምን የፈራና ነፍሱን ከመጥፎ ስሜት ያቀበ፥መኖሪያው ገነት ናት። (ሙሐመድ ሆይ!)፦ “ሰዓቲ (ቂያማ) የምትከሠተው መቼ ነው?” በማለት አጋሪዎች ይጠይቁሃል።አንተ ስለርሷ ለመናገር ዕውቀተ9 መች አለህና? የእርሷን (የትንሣኤን መከሠቻ ወቅት በሚመለከት) ትክክለኛ ዕውቀት ያለው አላህ ብቻ ነው።የአንተ ተልዕኮ (የምትከሠትበትን ወቅት መግለጽ ሳይሆን) የሚፈራትን ሰው ማስፈራራት ብቻ ነው። እነርሱ (ከሓዲያን) (ትንሣኤን) በሚመ ለከቷት ቀን (ከዚህች ዓለም ውስጥ) አንድ ምሽት ወይም አንድ ረፋድ ብቻ የቆዩ ያህል ይሰማቸዋል።›› (አንቀጽ 27-46)

አጠቃላይ ዓላማ

- ✓ በዚህ ግልጽ ዩኒቨርስ ውስጥ የተረጨና በአንቀጾቹ የተዘረዘሩ የአላህ ተአምራትን ማብራራት፣
- ✓ በዚህ ክፍል ውስጥ በተወሱ አናቅጽና በምእራፏ አብይ ፍሬ ነገር መካከል ያለውን ትስስር መገንዘብ፣
- ✓ በዚህ ክፍል አናቅጽ የተወሱ የታላቂቱን መዓት፣ የግዙፏን መከራ ትይእንቶች ማብራራት፣
- ✓ እያንዳንዱ ሰው ከስራው ውጤት አኳያ የሚጓዝበትን ፍጻሜ ማመላከት፣
- ✓ ጣኦታዊያን ለአላህ መልእክተኛ ቂያማን አስመልክቶ ላቀረቡላቸው ጥያቄዎች አላህ የሰጣቸውን ምላሾች መግለጽ።

በሐይላቸው ተማምነው ወሰን ያለፉ አምባገነኖችን መጥፋት ከቃኘ በኋላ በሐይላቸው ወደሚመኩት ጣኦታውያን ፊቱን በማዞር ወደዚህ ግዙፍ ዩኒቨርስ ትኩረታቸውን ይመልሳል። የነርሱ ብርታት ከዩኒቨርሱ አንጻር ሲታይ ኢምንት ነው።

﴿ءَأَنتُمۡ أَشَدُّ خَلۡقًا أَمِ ٱلسَّمَآءُۚ بَنَىٰهَا ﴿٢٧﴾﴾ النازعات: ٢٧

‹‹(እናንተ አጋሪዎች ሆይ!) ለመፍጠር ይበልጥ አስቸጋሪ የትኛው ነው? እናንተ ወይስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፤›› (አንቀጽ 27)

አንድ ብቻ እንጅ ሌላ ተጨማሪ መልስ የሌለው ጥያቄ፣ መቀበል እንጅ ክርክር የማያሻው እውነት። በእርግጥ የሰማይ አፈጣጠር ይበረታል። ሰማይ ከናንተ የበረታች፣ ፈጣሪዋም ከርሷ የበረታ ሆኖ እያለ በሐይላችሁ መኮፈሳችሁ ለምን? ‹‹ሰማይን ገንብቷል።›› ግንብ ጥንካሬን እና እርስ በርስ መተሳሰርን ያመለክታል። ሰማይም እንደዚሁ እርስ በርስ የተያያዘች ናት። አትፈራርስም። ከዋክብቱና ኘላኔቶቹም

አይበታተኑም። ምህዋሯን አትስትም። አትንኮታኮትም። የተለያዩ ክፍሎቿ በጥብቅ የተሳሰሩ፣ ጠንካራና ጽኑ ግንብ ናት።

رَفَعَ سَمۡكَهَا فَسَوَّىٰهَا

‹‹ከፍታዋን አጎነ። አስተካከላትም።››

ሰማይ የተለያዩ ክፍሎቿ በረቂቅ ጥበብ የተዋደዱባት፣ ተጣጥመው የተዛመዱባት ጣሪያ ናት። ‹‹አስተካከላትም›› የሚለው ቃል ትርጉም ይህ ነው። ሰማይን በዓይን በማየት ብቻ ይህን ፍጹም ድንቅ ትስስር፣ መጣጣምና ጥበብ መገንዘብ ይቻላል።

ግዙፍ የሰማይ አካላትን (ከዋክብትንና ኅላኔቶችን) ያስተካከለውንና እንቅስቃሴያቸውን የሚገዛውን የተፈጥሮ ሕግ ማወቅ ደግሞ የዚህን ገለጻ መልእክት የበለጠ ጥልቀት ያጎናጽፈዋል። መስኩንም የበለጠ ያሰፋዋል።

وَأَغۡطَشَ لَيۡلَهَا وَأَخۡرَجَ ضُحَىٰهَا

‹‹ሌሊቱንም አጨለመ። ቀኑንም ገለጸ።››

-የቀንና የሌሊት፣ የጨለማና የብርሃን መተካካት እያንዳንዱ ሰው ዘወትር የሚያየው እና ልቦናውንም የሚነካ እውነታ ነው። ግና ከመደጋገሙ የተነሳ (ተአምርነቱን) ስለሚዘነጋው ቁርአን ስሜቱን ወደርሱ በመሳብ እንደ አዲስ ያስተዋውቀዋል። ከቀንና ከሌሊት መፈራረቅ ጀርባ ያለው የተፈጥሮ ሕግ ደግሞ እጅግ ረቂቅና ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ተማራማሪዎችን በግርምት ያስደምማል።

وَٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ ذَٰلِكَ دَحَىٰهَآ ﴿٣٠﴾ أَخۡرَجَ مِنۡهَا مَآءَهَا وَمَرۡعَىٰهَا ﴿٣١﴾

‹‹ከዚያ በኋላ ምድርንም ዘረጋት።ውሃዋንና ግጦሽዋንም ከርሷ አወጣ።››

‹ዳሐ› የሚለው ቃል ምድር ለሰው ልጅ ሕይወት ምቹ ትሆን ዘንድ መዘርጋቷን ያመለክታል። ከሰማይ በዝናብ መልክ የሚወርደው ውሃ ከራሷ ከምድር በትነት አማካይነት የወጣ በመሆኑ ‹‹ዝናቧ› ተሰኝቷል። ለሰው ልጅም ሆነ ለእንስሳት ቀለብ፣ የሕይወትም መሠረት የሆኑትን እጽዋት (ግጦሿን) ከምድር እንዲበቅሉ አድርጓል። ይህ ሁሉ የሆነው ሰማይ ከታነጸች በኋላ ነው።

فَإِذَا جَآءَتِ ٱلطَّآمَّةُ ٱلۡكُبۡرَىٰ ﴿٣٤﴾ يَوۡمَ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ مَا سَعَىٰ ﴿٣٥﴾

‹‹ታላቁ መዓት (ዕለተ ምጽዓት) በተከሠተች ጊዜ፣ የሰው ልጅ (በዚህች ዓለም) የፈፀማቸውን ድርጊቶች በሚያስታውስበት (በዚያ) ዕለት

የዚህች ዓለም ሕይወት በረቀቀ ጥበብ የተዋቀረ ነው። ግና ኢምንት ነው፡ ፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ያከትማል። ታላቋ ማዓት ስትመጣ ሁሉንም ነገር ትሸፍናለች፡ በጥበብ ከታነጸው ሰማይ፣ ከተዘረጋችው ምድር፣ ከተተከሉ ግዙፍ ተራሮች፣ ከሕያውያንና ከሕይወት፣ ከዚህ ሁሉ ትበልጣለች። ይህን ሁሉ ታፈራርሳለች።

ያኔ የሰው ልጅ በዓለማዊ ሕይወት ተጠምዶ የረሳውን ስራውን ያስታውሳል። ግና ማስታወስ ከቁጭት በቀር በማይፈይድበት፣ መጭውን ቅጣትና መከራ ከማየት ባሻገር በማይጠቅምበት ሰአት።ያኔ ገሐነም ለሁሉም ሰው በምትታይበት ሁኔታ ትገለጣለች።

وَبُرِّزَتِ ٱلۡجَحِيمُ لِمَن يَرَىٰ ﴿٣٦﴾

የሰዎች ፍጻሜ ይለያያል። የሕይወት ዓላማም ይከሰታል።

فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٣٩﴾

‹‹የካደና የቅርቢቱን ሕይወት የመረጠ፣ ገሐነም በእርግጥ መኖሪያው ትሆናለች።››

የወሰን ማለፍ (ጡግያን) ትርጉሙ ሁሉንም የሐቅና የመቀናት ወሰኖችን ሁሉ መተላለፍን ያጠቃልላል። በዚያ ላይ ይህችን ዓለም በመምረጥ መጭውን ዓለም ከስሌቱ ውስጥ ሳያስገባ ለርሷ ብቻ ሲለፋና ሲደክም የኖረ፣ ‹ታላቁ መዓት› በሚከሰትበት ቀን ‹መኖሪያው› ‹ጀሃነም› እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም።

በአንጻሩ፡- ‹‹በጌታው ፊት መቆምን የፈራ›› ወንጀልን አይዳፈርም። ሰዋዊ ድክመት አጥቅቶት ከሐጢአት ላይ ቢወድቅ እንኳ ፍርሃቱ ወደ ጸጸት፣ ወደ ኢስቲግፋርና ወደ ተውባ ይመልሰዋል። እናም ለአላህ ታዛዥና ተገዥ በመሆን ጥላ ስር ዘወትር ይኖራል።

ነፍስን ከከንቱ ዝንባሌ መከልከል ለአላህ የመታዘዝ መሠረት ነው። የወሰን ማለፍ፣ የወንጀሎችና የሐጢአቶች ሁሉ መነሻ ከንቱ ስሜት የሚያሳድረው ግፊት ነው። የሰው ልጅ በአብዛኛው ከወንጀል ላይ የሚወድቀው በከንቱ ስሜቱ በኩል ነው። አለማወቅን ማከም ቀላል ነው፡ ካወቁ በኋላ ከንቱ ስሜት የሚያሳድረውን ግፊት ለማከም ግን የረዥም ትግል ያሻል። ብርቱ ጥረት ያስፈልጋል።

ጠንካራውን የከንቱ ዝንባሌ ግፊት ለመቋቋም ጽኑው መሣሪያም አላህን መፍራት ነው። ይህም ስለሆነ ቁርአናዊው ገለጻ ሁለቱንም በአንድ አንቀጽ አካትቶ አቅርቧቸዋል። ይህን እየተናገረ ያለው የሰውን ልጅ ነፍስ የፈጠረ፣ በሽታዋንና መድሃኒቷን የሚያውቀው አምላክ መሆኑን ማስታወስ ያሻል።

ልጅ ከንቱ ዝንባሌ ከልቦናው ውስጥ እንዳይበቅል አላህ የሰውን አላዘዘውም። የሰው ልጅ ሐላፊነት የተጣለበት ልጓሙን ይዞ እንዲቆጣጠረው ብቻ ነው። ለዚህ ጥረቱም ከታላቁ ጌታው ፊት በመቆም ፍርሃት እንዲታገዝ አመላክቶታል። በዚህ ረገድ ለሚያደርገው ረዥምና ብርቱ ትግልም፣ ለጥረቱ ዋጋም ጀነትን ሊመነዳው፣ እርሷን መኖሪያው ሊያደርግለት ቃል ገብቶለታል፡-

وَأَمَّا مَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفْسَ عَنِ ٱلْهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ فَإِنَّ ٱلْجَنَّةَ هِىَ ٱلْمَأْوَىٰ

‹‹በእርግጥም መኖሪያው ገነት ናት።››

* * *

በመጨረሻም የምእራፏ ግዙፍና ጥልቅ መልእክት ይከተላል፡-

﴿ يَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرۡسَىٰهَا ﴿٤٢﴾ فِيمَ أَنتَ مِن ذِكۡرَىٰهَآ ﴿٤٣﴾ ﴾ النازعات: ٤٢ - ٤٣

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!)፡- "ሰዓቲ (ቂያማ) የምትከሠተው መቼ ነው?" በማለት አጋሪዎች ይጠይቁሃል። አንተ ስለርሷ ለመናገር ዕውቀቱ መች አለህና?›› (አንቀጽ 42-43)

መንቻካ ጣአታውያን ስለ ትንሳኤ አስደንጋጭ ክስተቶች፣ ስለምርመራው እና ስለምንዳ በሰሙ ቁጥር፡- ‹‹መከሰቻው መቼ ነው?›› በማለት መልእክተኛውን አጥብቀው ይጠይቃሉ።

فِيمَ أَنتَ مِن ذِكۡرَىٰهَآ

‹‹አንተ ስለርሷ ለመናገር ዕውቀቱ መች አለህና?›› (አንቀጽ 43)

ታላቅነቱንና ግዙፍነቱን የሚጠቁም መልስ ነው። ታላቁ ነብይ፡- ‹‹አንተ ማስታወስ አትችልም›› ተብለዋል። ‹‹መከሰቻዋን ከመጠየቅህም ሆነ ከመጥጠየቅህ የገዘፈች ናት። ስለርሷ የሚያውቀው አምላክህ ብቻ ነው። የርሱ እንጅ ያንተ ጉዳይ አይደለችም። ‹‹የእውቀቷ መጨረሻ ወደጌታህ ብቻ ነው።›› መቼ እንደምትከሰት ያውቃል። እውስጧ እውን የሚሆኑ ነገሮችንም በበላይነት ያከናውናል። ያንተ ተግባር የሚፈሯትን እና ለርሷ ተግቶ ለመስራት የፈቀደን ሰው ማስጠንቀቅ ብቻ ነው። የተግባርህ ወሰን እዚህ ላይ ያበቃል። ተልእኮህ እዚህ ላይ ይጠናቀቃል።

በመቀጠልም አስፈሪነቷንና ግዝፈቷን፣ በሰው ልጅ እይታና ልቦና ላይ የምትፈጥረውን ድንጋጤ፣ በሕይወትም በሰው ላይ የምታስከትለውን ለውጥ ይገልጻል፡-

﴿كَأَنَّهُمۡ يَوۡمَ يَرَوۡنَهَا لَمۡ يَلۡبَثُوٓاْ إِلَّا عَشِيَّةً أَوۡ ضُحَىٰهَا ٤٦﴾ النازعات: ٤٦

‹‹እነርሱ (ከሓዲያን) (ትንሣኤን) በሚመለከቷት ቀን (ከዚህች ዓለም ውስጥ) አንድ ምሽት ወይም አንድ ረፋድ ብቻ የቆዩ ያህል ይሰማቸዋል።›› (አንቀጽ 46)

እጅግ ግዙፍና አስደንጋጭ ከመሆኗ የተነሳ የዚህች ዓለም ሕይወት፣ ዓመታቶቹ፣ ክስተቶቿ፣ ሐሴትና ነገሮቿ ሁሉ ይሟሸሻሉ። በሰው ልጅ ሕሊና ውስጥ ጊዜዋ አጥሮ አንድ ምሽት ወይም ረፋድ የሆነች ያህል ይሰማዋል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- በአንቀጹ የተዘረዘሩትን የዩኒቨርሱ አምላካዊ ተአምራት ዘርዝር፣
- በዚህ የምራፏ ክፍል አናቅጽ እና በምእራፏ አብይ ፍሬ ነገር መካከል ያለውን ትስስር አስረዳ።
- ታላቁን መዓት በአንቀጾቹ በተብራራው መልኩ ግለጽ።
- እያንዳንዱ ሰው ከስራው አኳያ የሚያጋጥመውን ፍጻሜ አንቀጾቹ በዳሰሱት አኳኋን አብራራ።
- ጣኦታውያን ስለ ቂያማ ቀን ለአላህ መልእክተኛ ላቀረቧቸው ጥያቄዎች የክብርና የልቅና ባለቤት የሆነው አምላክ የሰጠውን መልስ ግለጽ።

* * *

ዓበሰ ምእራፍ

አንቀጽ 1-16

﴿ عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ١ أَن جَآءَهُ ٱلۡأَعۡمَىٰ ٢ وَمَا يُدۡرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ٣ أَوۡ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكۡرَىٰٓ ٤
أَمَّا مَنِ ٱسۡتَغۡنَىٰ ٥ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ٦ وَمَا عَلَيۡكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ٧ وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسۡعَىٰ ٨ وَهُوَ
يَخۡشَىٰ ٩ فَأَنتَ عَنۡهُ تَلَهَّىٰ ١٠ كَلَّآ إِنَّهَا تَذۡكِرَةٞ ١١ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ١٢ فِي صُحُفٖ مُّكَرَّمَةٖ ١٣
مَّرۡفُوعَةٖ مُّطَهَّرَةِۭ ١٤ بِأَيۡدِي سَفَرَةٖ ١٥ كِرَامِۭ بَرَرَةٖ ١٦ ﴾ عبس: ١ - ١٦

‹‹(የአላህ መልዕክተኛ) ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም፤ ዓይነ-ሥውሩ ከርሱ ዘንድ በመምጣቱ። (ሙሐመድ ሆይ!) ምናልባትም (ይህ ፊትህን ያጨፈገግክበት ዓይነ-ሥውር በምትለግሰው እውቀትና ምክር ተጠቅሞ ከወንጀል) ይፀዳ ይሆናል፤ ምን የምታውቀው ነገር አለ? ወይም ሊገሰጥና ምክርህም ሊጠቅመው ይችል ይሆናል። (በሃብትና ንብረቱ ተኩራርቶ ከአላህ) የተብቃቃውን፥ (ከእምነት የሸሸውን) ሰው፥ (ለእምነቱ በመጓጓት) ሙሉ ትኩረት ትሰጠዋለህ፤ (ከወንጀልና ክህደት ርክሰት) ባይፀዳ ባንተ ላይ የሚደርስ ጉዳት ባይኖርም። (ምክርና ተግሳጽህን ፍለጋ) ወደ አንተ በጉጉት የመጣውን፤ በአላህ ፍርሃት ስሜት ተውጦ (ከአንተ ዘንድ የቀረበውን)፤ ችላ ትለዋለህ። (ወደፊት እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከመፈፀም) ታቀብ! ይህች (መልዕክት) ተግሳጽ ናት። ፍላጐቱ ያለው ይገሰጽበታል፥ (ቁርአን ከሚሰጠው መመሪያ ይጠቀማል)። እርሱ (ቁርአን) (ከአላህ ዘንድ) ከተላቀች መዝገብ ውስጥ (የሠፈረ) ነው። ከፍተኛ የክብር ሥፍራ የተሰጠውና (ከጉድለት) የፀዳ (ከሆነ መዝገብ ውስጥ የሰፈረ ነው)። በፀሐፊዎች (መላእክት) እጆች (በክብር ከተያዘ መዝገብ ውስጥ የሠፈረ ነው)። እጅግ የተከበሩና (አላህንም) ታዛገሮች በሆኑ (መላእክት እጆች በክብር ከተያዘ መዝገብ ውስጥ)።›› *(አንቀጽ 1-16)*

አጠቃላይ ዓላማዎች

- ምእራፉ የወረደችበትን ምክንያት ማስታወስ

- የሰው ልጆች የሚመዘኑበትን አምላካዊ መስፈርት ማስታወስ
- አላህ በዚህች ምእራፍ ውስጥ ለተወዳጁ ነብይ የሰነዘረውን ነቀፌታ ማብራራት
- የአላህ መልእክተኛ ይህን አምላካዊ የሰው ልጅ መመዘኛ መስፈርት በተጨባጭ ሕይወት ውስጥ በማጽናቱ ረገድ ያስመዘገቡትን ስኬት ማብራራት፡፡

* * *

﴿ عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١﴾ أَن جَآءَهُ ٱلۡأَعۡمَىٰ ﴿٢﴾ وَمَا يُدۡرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ﴿٣﴾ أَوۡ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكۡرَىٰٓ ﴿٤﴾ ﴾

﴿ عبس: ١ - ٤

‹‹(የአላህ መልዕክተኛ) ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም፤ ዓይነ-ሥውሩ ከርሱ ዘንድ በመምጣቱ። (ሙሐመድ ሆይ!) ምናልባትም (ይህ ፊትህን ያጨፈገግክበት ዓይነ-ሥውር በምትለግሰው እውቀትና ምክር ተጠቅሞ ከወንጀል) ይፀዳ ይሆናል፤ ምን የምታውቀው ነገር አለ? ወይም ሊገሰጥና ምክርህም ሊጠቅመው ይችል ይሆናል።›› (አንቀጽ 1-4)

ክስተቱን ተከትሎ የወረው ይህ መመሪያ እኛ ከምንገምተው በላይ እጅግ የላቀ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ኢስላም በምድር ላይ ሊያጸናው የፈለገው እውነተኛ ተአምር ነው፡፡ ይህ መልክት በምድር ላይ ያሳደረው ተጽእኖም ጥልቅ እና ተአምራዊ ነው፡፡

ይህ መመሪያ ማጽናት የከጀለው ትልቅ እውነት ይህ ነው፡- የሰው ልጆች ምድራዊ ግፊቶችና ተጨባጭ ሕይወታቸው ከሚያሳድሩባቸው ተጽእኖዎች ሁሉ ተላቀው፣ ከእነዚህ ግፊቶችና ተጨባጮች ከመነጩ ርእዮቶቻቸው ሁሉ ጸድተው፣ እሴቶቻቸውና መስፈርቶቻቸው ከሰማይ የወረዱ፣ ከአምላክ የተላለፉ ብቻ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ይህ በእርግጥ እጅግ ታላቅ ብቻ ሳይሆን በጣም አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ ሰዎች በምድር ላይ እየኖሩ ከምድራዊ ተጽእኖዎች ሁሉ ነጻ በመውጣት

ከሰማይ በወረደ እሴትና መስፈርት ሕይወታቸውን መምራታቸው በእርግጥም በጣም ከባድ ነገር ነው።

ይህ አምላካዊ መመሪያ ከአብደላህ ቢን ኡም መክቱም ጋር የተያያዘውን ክስተትና አጋጣሚ ተጠቅሞ በምድር ላይ ሊያጸናው የከጀለው ታላቅ እውነታ ይህ ነው። ይህ በእርግጥም ታላቅ ቁም ነገር መሆኑ ጥርጥር የለውም። አላህ ለሰው ልጆች እሴቶችን ሁሉ ይመዝኑበት ዘንድ በመልእክተኛው በኩል ያወረደው ሚዛን፦ ‹‹ከናንተ ውስጥ በላጩ አላህን ፈሪያችሁ ነው።››[1] በሚለው መልእክት ውስጥ ተካትቷል። ሰዎች የሚመዘኑበት ብቸኛው መስፈርት ይህ ሲሆን፣ ከምድራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ምንም ዓይነት ትስስር የሌለው ፍጹም አምላካዊ ሚዛን ነው።

ይህን አጋጣሚ በመጠቀምም መስፈርቱን ይበልጥ ለማጽናት ይህ መመሪያ ተላለፈ። መሠረታዊውን መርህም አጸደቀ። ይህውም፦ ‹‹ሰዎች የሚመዘኑበት መስፈርት፣ እሴቶቻቸውም አምላካዊ መሆን አለባቸው።›› የሚል ነው።

‹‹መስሊመ ኡምማ በሰዎች ዘንድ የታወቁና የተለመዱ፣ ከምድራዊ ግንኙነት የመነጩ ርእዮቶችን፣ እሴቶችንና መስፈርቶችን እርግፍ አድርገው በመተው ከሰማይ የወረደውን እሴት ይጠቀሙ። ሕይወታቸውን በርሱ ብቻ ይመዝኑ›› የሚል ነው።

አንድ ድሃ አይነ ስውር ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ መጣ። ኢብን ኡም መክቱም ይባላል። መልእክተኛው የቁረይሽ ባላባቶችን ወደ ኢስላም በመጥራት ተግባር ተጠምደዋል። የነርሱ መስለም በመካ ከተማ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለነበረው ኢስላም በጎ እርምጃ ነበር። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለራሳቸው ሳይሆን ለእስልምና እድገት እየደከሙ ባሉበት በዚህ ሁኔታ ውስጥ ይህ ድሃ ዓይነ ስውር ይመጣና፦ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ አላህ ካስተማረህ አስተምረኝ››

[1] አል ሁጁራት 13

ይላቸዋል፡፡ በዳእዋ መጠመዳቸውን ባለማጤን ደጋግሞ ይጠይቃቸዋል፡፡ መልእክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ንግግራቸውን ስላቋረጣቸው፣ ከያዙት የዳእዋ ተግባር ስላወሳቸው የመከፋት ስሜት አሳዩ፡፡ ገጽታቸውን አጨፈገጉ፡፡ ለሐይማኖታቸውና ለዳእዋቸው ብዙ መልካም ነገርን ተስፋ በማድረግ እጅግ ከባድ ከሆነ ቁም ነገር ካስተጓጎላቸው ከዚህ ድሃ ዓይነ ስውር ሸሹ፡፡

በዚህ ጊዜ አላህ ጣልቃ በመግባት ወሳኝና ጠንካራ መልእክት አስተላለፈ። እሴቶች የሚመዘኑበትን መስፈርትም አጸደቀ፡፡ ይህን ሁሉ ሲያደርግ የትኛውንም ምድራዊ ተጨባጭ፣ ሌላው ቀርቶ በሰዎች እይታ የዳእዋ ጥቅም ተብሎ የሚታሰበው ነገር፣ ከዚህም በላይ የሰው ልጆች ፈርጥ ለኢስላም እንደሚበጅ ያሰቡትን ነገር ክብደት እና ግምት ባለመስጠት ነው፡፡

የላቀ ስነ ምግባር ባለቤት የሆኑት ታላቁ ነብይ ልዑል ከሆነው አላህ ጠንካራ ነቀፍታ ተሰነዘረባቸው፡፡ በቁርአን ውስጥ ተወዳጁ የአላህ መልእክተኛ ‹‹ከልላ›› በሚል ብርቱ የሂስ ቃል የተተቹት ከዚህ ቦታ ላይ ብቻ ነው፡፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ይህ ሐይማኖት የቆመበት መሠረት ጉዳይ ነውና፡፡

ቁርአን ይህን መለኮታዊ ነቀፌታ ያስተላለፈበት ስልትም ፍጹም የተለየ ነው፡-

﴿ عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ۝١ أَن جَآءَهُ ٱلۡأَعۡمَىٰ ۝٢ ﴾ عبس: ١ - ٢

‹‹(የአላህ መልዕክተኛ) ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም፤ ዓይኑ-ሥውሩ ከርሱ ዘንድ በመምጣቱ።›› (አንቀጽ 1-2)

መልእክተኛውን ሳይሆን ሩቅ ያለን ሌላ ሦስተኛ ወገን የሚያናግር ይመስላል፡፡ ይህ የአገላለጽ ስልት ጉዳዩን አላህ በእጅጉ እንደጠላውና ነብዩንና ወዳጁን በቀጥታ ሊያናግርበት አለመፈለጉን ይጠቁማል፡፡

ለርሳቸው ስለደሚያዝንና ስለሚያልቃቸው በዚህ አስቀያሚ አጀንዳ በቀጥታ ሊያናግራቸው አልፈቀደም።

ከዚያም የመልእክት አቅጣጫውን ወደርሳቸው በማዞር በቀጥታ ያናግራቸዋል። ይተቻቸዋልም። እዚህ ላይ ድምጹን ትንሽ ረገብ ያደርጋል፡-

﴿ وَمَا يُدۡرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ٣ أَوۡ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكۡرَىٰٓ ٤ ﴾ عبس: ٣ - ٤

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ምናልባትም (ይህ ፊትህን ያጨፈገግክበት ዓይነ-ሥውር በምትለግሰው እውቀትና ምክር ተጠቅሞ ከወንጀል) ይፀዳ ይሆናል፤ ምን የምታውቀው ነገር አለ? ወይም ሊገሰጥና ምክርህም ሊጠቅመው ይችል ይሆናል።›› (አንቀጽ 3-4)

ይህ ታላቅ በጎ ነገር ሊረጋገጥ ይችላል። ይህ ድሃ አይነ ስውር ሊጸዳ፣ ሕሊናው ነቅቶ ሊገሰጽ ይችላል።

ቀጥሎ የነቀፌታው ድምጸት ይበረታል። በተፈጠረው ክስተት ወደ መገረም ይሸጋገራል፡-

﴿ أَمَّا مَنِ ٱسۡتَغۡنَىٰ ٥ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ٦ وَمَا عَلَيۡكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ٧ وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسۡعَىٰ ٨ وَهُوَ يَخۡشَىٰ ٩ فَأَنتَ عَنۡهُ تَلَهَّىٰ ١٠ ﴾ عبس: ٥ - ١٠

‹‹(በሃብትና ንብረቱ ተኩራርቶ ከአላህ) የተብቃቃውን፥ (ከእምነት የሸሸውን) ሰው፥ (ለእምነቱ በመጓጓት) ሙሉ ትኩረት ትሰጠዋለህ፤ (ከወንጀልና ክህደት ርኩሰት) ባይፀዳ ባንተ ላይ የሚደርስ ጉዳት ባይኖርም። (ምክርና ተግሳጽህን ፍለጋ) ወደ አንተ በጉጉት የመጣውን፤ በአላህ ፍርሃት ስሜት ተውጦ (ከአንተ ዘንድ የቀረበውን)፤ ችላ ትለዋለህ።›› (አንቀጽ 5-10)

ካንተና ከሐይማኖትህ፣ እንዲሁም ከያዝከው በጎ ነገር፣ መቀናት እና ብርሃን የሸሸውን ትኩረት ችረህ ልታቃናው ትተጋለህ። ልትመራው ትለፋለህ። እርሱ ግን ይሸሽሐል። ‹‹ባይጸዳ፣ ባይቀና፣ ባይመጣ›› ምን

ይቀርብሐል? አንተ በርሱ ወንጀል ተጠያቂ አይደለህም። በአንጻሩ ወዶህና ፈቅዶህ፣ አላህንም ፈርቶ፣ እየገሰገሰ ወዳንተ የመጣውን ችላ ትላለህ። ከርሱም ትዘናጋለህ።

ይህን በጎ ፈላጊ ሰው ትቶ በሌሎች መጠመድ ‹‹መዘናጋት›› ተሰኝቷል። ብርቱ አገላለጽ ነው። ነቀፌታው ይበልጥ በርትቶም ‹‹ከላ (ተከልከል) ይህ መቼም ቢሆን መደገም የሌለበት ነገር ነው›› ሲል የጥንካሬ ጣሪያን ይነካል።

በመቀጠልም የዚህን ዳእዋ (ኢስላምን) ምንነት ያስረዳል። ልቅናውንና ክብሩን ይገልጻል። ከየትኛውም ሰው የተብቃቃ ነው ይላል። አቃፊ ደጋፊ አያስፈልገውም። ማንም ይሁን ማን፣ በዚህች ዓለም ሚዛን የቱን ያህል የላቀ ደረጃ ቢኖረውም። ምክንያቱም፡-

﴿ كَلَّآ إِنَّهَا تَذۡكِرَةٞ ١١ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ١٢ فِي صُحُفٖ مُّكَرَّمَةٖ ١٣ مَّرۡفُوعَةٖ مُّطَهَّرَةِۭ ١٤ بِأَيۡدِي سَفَرَةٖ ١٥ كِرَامِۭ بَرَرَةٖ ١٦ ﴾ عبس: ١١ - ١٦

‹‹(ወደፊት እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከመፈፀም) ታቀብ! ይህች (መልዕክት) ተግሳጽ ናት። ፍላጐቱ ያለው ይገሰጽበታል፥ (ቁርአን ከሚሰጠው መመሪያ ይጠቀማል)። እርሱ (ቁርአን) (ከአላህ ዘንድ) ከተላቀች መዝገብ ውስጥ (የሠፈረ) ነው። ከፍተኛ የክብር ሥፍራ የተሰጠውና (ከጉድለት) የፀዳ (ከሆነ መዝገብ ውስጥ የሰፈረ ነው)። በፀሐፊዎች (መላእክት) እጆች (በክብር ከተያዘ መዝገብ ውስጥ የሠፈረ ነው)። እጅግ የተከበሩና (አላህንም) ታዛገሮች በሆኑ (መላእክት እጆች በክብር ከተያዘ መዝገብ ውስጥ)።›› (አንቀጽ 11-16)

ኢስላም በሁሉም መመዘኛዎች የላቀና የከበረ ነው። ገጾች የተከበሩ፣ ንጹህና ከፍ የተደረጉ፣ የላቁና ታዛገሮች በሆኑ መላእክት እጅ የሚገኙ፣ ከሰዎች መሐል በጣም ለተላቁትም የሚተላለፉ። ይህ መልእክት በሁሉም አቅጣጫ የላቀ ነው። ከርሱ ጋር በቅርብም ይሁን በሩቅ ንክኪ ያለው ነገር ሁሉ የተከበረ ነው። እናም ለሚሸሹትና ለሚርቁት በስጦታ

የሚበረክት ርካሽ ነገር አይደለም። ልቅናውን ለሚያውቅ እና በርሱ አማካይነት ከርክሰት መጽዳት ለሚሹት የሚቸር ውድ መልእክት እንጅ።

እሴቶች የሚለኩበት፣ ሰዎችና ተጨባጩ የሚመዘንበት የአላህ ሚዛን ይህ ነው። የእይታዎች፣ የቃሎች እና የውሳኔዎች ሁሉ የበላይ የሆነው የአላህ ቃል እና ውሳኔ ይህ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ልቦና በዚህ መመሪያና ሂስ በጣም ተነካ። በመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ ክስተቱን ተከትሎ ከአላህ የተሰነዘረባቸውን ሂስ ማወጅ ነበር። ይህ እርምጃ እጅግ ሲበዛ ትልቅ ነው። ከአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ውጭ ሌላ ማንም ሰው ሊያደርገው አይችልም። ከነብያት ውጭ ያለ ሌላ ታላቅ ስብእና የቱን ያህል ታላቅ ቢሆንም ቢበዛ ሂሱን በጸጋ ተቀብሎ ወደፊት ላለመድገም ከመጠንቀቅ ያለፈ ተግባር አያከናውንም። ግና ነብይነት የአስገራሚ እርምጃዎች ባለቤት ያደረጋል።

የአላህ መልእክተኛ ከዚህ ክስተት በኋላ ኢብን ኡም መክቱምን በጣም ይንከባከቡት ነበር። ባገኙት ቁጥርም ‹ከአምላኬ ሂስ ያስተናገድኩብህ ሰው እንዴት ነህ›› ይሉት ነበር። ወደ መዲና ከተሰደዱ በኋላ ሁለት ጊዜ እርሳቸውን ተክቶ ከተማዋን እንዲያስተዳድር ሹመውታል።

በምድር ላይ እየኖረ ከምድር ተጽእኖዎች ተላቅቆ እሴቱንና መስፈርቱን ከሰማይ የሚቀበል ድንቅ ትውልድ ተፈጠረ። የኢስላም ትልቁ ተአምር ይህ ነው። ይህ እውነታ በሙስሉሙ ሕብረተሰብ ውስጥ ሰረጸ። በጉላ ላይ ከእስልምና መንፈስ የመራቅ ብዙ አጋጣሚዎች ቢከሰቱም ይህ እሴት ግን እንደጸና ቀጠለ። አላህን የሚፈሩ ሰዎች ክብር በራሳቸውም ሆነ በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች እይታ ከምድራዊ ክብር የራቁ ቢሆኑም እንኳ አምላካዊው ሚዛን ልቅናን አጎናጸፋቸው። ይህ ሚዛን ከምድር የተነሳው በቅርቡ፣ ማለትም መሐይምነት (ጃሂልያ) ምድርን ባጠቃላይ ሲያጥለቀልቅ ነው። የሰውን ልጅ ከዚህ አጠቃላይ መሐይምነት ለማውጣት ተስፋ የሚጣለው በኢስላማዊ የዳእዋ እንቅስቃሴዎች ብቻ ነው። በነርሱ አማካይነት የሰው ልጅ ዳግም ውልደትን ይጎናጸፋል።

በዚህ ምእራፍ መወጠኛ ላይ በሰፈሩ፣ ታላቅ እና ወሳኝ መልእክት በያዙ ጥቂት አናቅጽ አማካይነት የታየው ዓይነት አዲስ ልደት እውን ይሆናል፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ይህች ምእራፍ የወረደችበትን ሰበብ አውሳ፡፡
- የሰው ልጅ የሚመዘንበትን እና በዚህች ምእራፍ ውስጥ የተጠቀሰውን አምላካዊ መስፈርት ግለጽ፡፡
- አላህ ለተወዳጁ መልእክተኛ የሰነዘረውን በዚህ ምእራፍ ውስጥ የሰፈረ ነቀፌታ አውሳ፡፡
- ከነቢያዊው ታሪክ ውስጥ የአላህ መልእክተኛ ይህን አምላካዊ መስፈርት በተጨባጭ ሕይወት ውስጥ በማጽናት ሂደት ያስመዘገቡትን ስኬት አብራራ፡፡
- ከሰዎች ጋር በነበራቸው ግንኙነት ይህን መስፈርት እንዴት እንዳረጋገጡት አብራራ
- ይህ መስፈርት በአሁኑ ሰአት በተጨባጭ ምን ያህል እየተሰራበት እንደሆነ አብራራ
- ይህን ሚዛን ወደ ኡማው ተጨባጭ ሕይወት ለመመለስ ምን መደረግ እንዳለበት ሐሳብ ስጥ፡፡

* * *

አንቀጽ 17-32

﴿ قُتِلَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَآ أَكۡفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنۡ أَيِّ شَيۡءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطۡفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾ ثُمَّ ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقۡبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾ كَلَّا لَمَّا يَقۡضِ مَآ أَمَرَهُۥ ﴿٢٣﴾ فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ إِلَىٰ طَعَامِهِۦٓ ﴿٢٤﴾ أَنَّا صَبَبۡنَا ٱلۡمَآءَ صَبّٗا ﴿٢٥﴾ ثُمَّ شَقَقۡنَا ٱلۡأَرۡضَ شَقّٗا ﴿٢٦﴾ فَأَنۢبَتۡنَا فِيهَا حَبّٗا ﴿٢٧﴾ وَعِنَبٗا وَقَضۡبٗا ﴿٢٨﴾ وَزَيۡتُونٗا وَنَخۡلٗا ﴿٢٩﴾ وَحَدَآئِقَ غُلۡبٗا ﴿٣٠﴾ وَفَٰكِهَةٗ وَأَبّٗا ﴿٣١﴾ مَّتَٰعٗا لَّكُمۡ وَلِأَنۡعَٰمِكُمۡ ﴿٣٢﴾ ﴾

‹‹የሰው ልጅ ተረገመ፤ ለክህደት መዳረጉ እጅግ የሚደንቅ ነው! (አላህ) ከምንድን ነው የፈጠረው? ከፈትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም። ከዚያም (ጉዳናውን) ገርና ቀላል አደረገለት። ከዚያም ለሞት አበቃው፣ እንዲቀበር አደረገውም። በሚፈልግ ጊዜም (ከሞት) ይቀሰቅሰዋል። (የሰው ልጅ ከክህደቱ) ይታቀብ! (ጌታው) ያዘዘውን አልፈፀመም። የሰው ልጅ የሚመገበውን ምግብ ያስተውል! (ከሰማይ) ውሃን አወረድን፡ ከዚያም መሬቱን (ለቡቃያው መውጫ) ሰነጠቅን፤ እህልንም አበቀልን፤ ወይንንም፥ እርጥብ ሣርንም፤ ዘይቱንንም፥ ዘንባባንም፤ በዕፅዋት የተጨናነቁ የአትክልት ቦታዎችንም፤ ፍራፍሬንም፥ ገለባንም። (የሰው ልጆች ሆይ! ይህ ሁሉ ዐጋ) ለናንተና ለእንሰሳቶቻችሁ መጠቀሚያ ነው።›› (አንቀጽ 17-32)

አጠቃላይ ዓላማዎች

- የሰው ልጅ ለአምላኩ እርግማን ለምን ተገቢ እንደሚሆን ማብራራት፣
- አላህ ለሰው ልጆች በሕይወታቸው፣ በምግብና መጠጣቸው የዋለውን ውለታና የለገሳቸውን ጸጋዎች መዘርዘር፣
- አላህ ለሰው ልጅ ምግብ እና መጠጥ እንዴት እንደለገሰው ማብራራት።

* * *

ከላይ የተወሱ ታላላቅ እውነታዎችን ከገለጸ በኋላ ከመቀናት በሚርቀው፣ ከእምነት በሚብቃቃው፣ በአምላኩ ጥሪ ላይ በሚኩራራው የሰው ልጅ ድርጊት ይገረማል። ክህደቱ፣ የሕልውናውን ምንጭና መነሻ መሠረቱን አለማስታወሱ፣ በዚህችም ሆነ በመጭው ዓለም የሕይወት እርከኖች የአምላክ ጥበቃ፣ እንክብካቤና ክትትል መኖሩን አለማስተዋሉ፣ የሚንከባከበው፣ የሚቆጣጠረው እና የሚመረምረው አምላክ የጣለበትን ግዴታ አለመወጣቱ ያስገርመዋል።

قُتِلَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَآ أَكۡفَرَهُۥ

‹‹የሰው ልጅ የተረገመ ነው።›››

በእርግጥ ስለ አስገራሚ ድርጊቱ እርግማን ይገባዋል።

مَآ أَكۡفَرَهُۥ

‹‹ምን ካሐዲ አደረገው?››

ክህደቱ፣ አስተባባይነቱ፣ ሕልውናው ግድ የሚያደርግበትን ሐላፊነት አለመወጣቱ አስከፊ ድርጊት፣ ብርቱ ክህደት ነው።

ይህ ካልሆነ በምን ሰበብ ከመቀናት ይርቃል? ከእምነት ይብቃቃል? መነሻው ምን እንደሆነ ዘነጋውን? ጌታው ከምን እንደፈጠረው አያስብምን?›› መነሻው ተራ ነገር ነው። ክብሩን ያገኘው በጌታው ችሮታና ጸጋ፣ በርሱ ጥበብና ፈቃድ እንጅ በሌላ አይደለም።

مِن نُّطۡفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ

‹‹ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው። መጠነውም››

አንዳች ፋይዳ ከሌለው ከዚህ ነገር፣ ጥንካሬ አልባ ከሆነ መሠረት ተገኘ። ግና አምላክ በጥበቡ አከበረው። በችሮታው የተስተካከለና የላቀ፣ እንዲሁም ዋጋ ያለው ፍጡር አደረገው።

ከዚያም መውጫ መንገዱን አገራለት። የሕይወትን ጎዳና ወይም የመቀናትን መንገድ አቀለለለት። ለዚህ የሚረዳውን አቅምና ባህሪያትም አላበሰው።

የሕይወትን ጉዞ ሲያጠናቅቅ ሕያውያን ወደሚገዙበት ፍጻሜ ይደርሳል። በዚህ ረገድ ምርጫም ማምለጫም የለውም።

ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقۡبَرَهُۥ

‹‹ከዚያም ገደለው። እንዲቀበርም አደረገው።›››

ፍጻሜው እንደ ጅምሩ በአምላኩ እጅ ነው። በፈቃዱ ወደ ሕይወት መድረክ አመጣው። ሲሻም ሕይወቱን ፍጻሜ አደረገለት። መኖሪያውን በመሬት ሆድ ውስጥ በማበጀትም አከበረው። ሙታንን መቅበርን የተፈጥሯዊ ስሌቱ አካል አደረገለት።

እርሱ የወሰነው ጊዜ ሲደርስም እርሱ ለሻው ጉዳይ ወደ ሕይወት ይመልሰዋል።

ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ

‹‹ከዚያም በሻ ጊዜ ያስነሳዋል።››

ስለዚህ ያለምርመራ እንዲሁ የሚተው፣ የስራውን ዋጋ ሳያገኝ የሚቀር አይደለም። የሰው ልጅ ለዚህ ሁሉ ተገቢውን ዝግጅት አድርጓልን?

كَلَّا لَمَّا يَقۡضِ مَآ أَمَرَهُۥ

‹‹በእውነቱ ያንን ጌታው ያዘዘውን ነገር ገና አልፈጸመም።››

የሰው ልጅ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ትውልድ እስከ መጨረሻው የሕይወት እስትንፋሱ የጌታውን ትእዛዝ ሲፈጽም፣ ሐላፊነቱን ሲወጣ፣ የሚጠበቅበትን ሲያደርግ አይስተዋልም። ቅኑን መንገድ ለመራውና

ለተንከባከበው አምላኩ ተገቢውን ምስጋና አላደረሰም። ምድራዊ ሕይወቱን ለመጭው ዓለም በመዘጋጀት ሲያሳልፍ አይስተዋልም።

ወደ ሌላ ቅኝት ያመራል።

የሰው ልጅ አነሳስ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል። በሕይወት ጉዞው ውስጥ እርሱም ሆነ እንስሳቱ የሚመገቡትን ምግብ አስተውሏልን? አምላክ ከገራለት በርካታ ነገሮች መካከል አንዱ ነው።

فَلْيَنظُرِ ٱلْإِنسَٰنُ إِلَىٰ طَعَامِهِۦٓ

‹‹የሰው ልጅ ወደ ምግቡ ይመልከት።።››

ከቅርቡ የሚያገኘው፣ ዘወትር የማይለየውን ነገር፣ አስገራሚና ቀላል ታሪኩን ያስተውል። ቀላልነቱ አስደናቂነቱን ያስረሳዋል። ግና ልክ እንደርሱው አፈጣጠር ተአምር ነው።

أَنَّا صَبَبْنَا ٱلْمَآءَ صَبًّا

‹‹ውሃን አንቧቧን››

ውሃ በዝናብ መልክ መንቧቧቱ በየትኛውም ቦታና ዘመን፣ በየትኛውም የእውቀትና የተሞክሮ ደረጃ ያለ ሰው በቀላሉ የሚገነዘበው እውነታ ነው። ሁሉንም ሰዎች በዚህ እውነታ ያናግራል። በትኛውም የታሪክ ወቅት የሚገኝ የሰው ልጅ ይህን ውሃ በየትኛውም መልክ ፈጥሪያለሁ ወይም አዘንበዋለሁ ሊል አይችልም።

የምግብ አፈጣጠር ታሪክ ይቀጥላል።

ثُمَّ شَقَقْنَا ٱلْأَرْضَ شَقًّا

‹‹ከዚያም ምድርን ሰነጠቅን።።››

ይህኛው ከዝናብ ቀጥሎ የሚመጣ እርከን ሲሆን እጽዋት አፈሩን ሰንጥቀው የሚወጡበትን ሁኔታ ያስተነተነ ሁሉ ይገነዘበዋል። ደካማ ከሆነችው እጽዋት ውስጥ የተደበቀ አንዳች እምቅ ሐይል መኖሩ ይሰማዋል።

فَأَنۢبَتۡنَا فِيهَا حَبّٗا

‹‹በውሰጧም እህልን አበቀልን።››

የሰው ልጅ በየትኛውም መልክ የሚመገበውን፣ እንስሳት በየትኛውም ሁኔታ ለመኖነት የሚያውሉትን የትኛውም እህል ያጠቃልላል።

﴿ وَزَيۡتُونٗا وَنَخۡلٗا ٢٩ وَحَدَآئِقَ غُلۡبٗا ٣٠ وَفَٰكِهَةٗ وَأَبّٗا ٣١ ﴾ عبس: ٢٩ - ٣١

‹‹ዘይቱንንም፥ ዘንባባንም፤ በዕፅዋት የተጨናነቁ የአትክልት ቦታዎችንም፤ ፍራፍሬንም፥ ገለባንም።›› (አንቀጽ 29-31)

የምግባችን **‹የሕይወት ታሪክ›** ይህን ይመስላል። ሁሉም እርከኖች የአምላክን ድንቅ ጥበብ ያሳያሉ። አምላካዊው ሐይል *ለሰዎችም ለእንስሳዎችም መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ* ያበቀለው እህል ታሪክ ይህን ይመስላል።

የሰው ልጅ በዚህ ጸጋ እስከተወሰነ ጊዜ ይጠቀማል። ከመከሰቱ በፊት የሰው ልጅ ሊያስብበት የሚገባ ሌላ ነገር ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ✓ የሰው ልጅ በአምላክ ለመረገም ተገቢ የሚያደርገውን ነገር አብራራ፣
- ✓ አላህ ለሰው ልጅ በራሱ፣ በምግቡና በመጠጡ የለገሰውን ጸጋ ዘርዝር፣
- ✓ አላህ ለሰው ልጅ ምግብንና መጠጥን እንዴት እንደለገሰው አብራራ።

* * *

አንቀጽ 33-42

﴿ فَإِذَا جَآءَتِ ٱلصَّآخَّةُ ﴿٣٣﴾ يَوۡمَ يَفِرُّ ٱلۡمَرۡءُ مِنۡ أَخِيهِ ﴿٣٤﴾ وَأُمِّهِۦ وَأَبِيهِ ﴿٣٥﴾ وَصَٰحِبَتِهِۦ وَبَنِيهِ ﴿٣٦﴾
لِكُلِّ ٱمۡرِيٕ مِّنۡهُمۡ يَوۡمَئِذٖ شَأۡنٞ يُغۡنِيهِ ﴿٣٧﴾ وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٖ مُّسۡفِرَةٞ ﴿٣٨﴾ ضَاحِكَةٞ مُّسۡتَبۡشِرَةٞ ﴿٣٩﴾ وَوُجُوهٞ
يَوۡمَئِذٍ عَلَيۡهَا غَبَرَةٞ ﴿٤٠﴾ تَرۡهَقُهَا قَتَرَةٌ ﴿٤١﴾ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡكَفَرَةُ ٱلۡفَجَرَةُ ﴿٤٢﴾ ﴾ عبس: ٣٤ - ٤٢

‹‹(የቂያማ) አደንቋሪ ጩኸት በመጣች ጊዜ፤በዚያ ቀን እያንዳንዱ ሰው ከወንድሙ ይሸሻል። ከእናቱም፣ ከአባቱም፣ ከሚስቱም፣ ከልጆቹም። በዚያን ቀን ከመካከላቸው እያንዳንዱ ሰው (የሚያስጨንቀውና የሚያሳስበው) የየግል ጉዳይ ይኖረዋል። በዚያን ቀን (የከፈሎቹ የአማኞች) ፊቶች ያበራሉ፤ በፈገግታ ይሞላሉ፤ በደስታ ይዋጣሉ። (ከፈሎ) ፊቶችቹ ደግሞ -በዚያን ቀን- ትቢያ ይለብሳሉ፤ በጥቁረት ይሸፈናሉ። እነዚያ (አቧራ የለበሱ፥ በጽልመት የተዋጡ ፊቶች የሚኖራቸው) ከሓዲያንና አመፀኞች ናቸው።›› (አንቀጽ 33-42)

አጠቃላይ ዓላማዎች

አስደንጋጭ ጩኸት የሚሰማበትን የመከራ ቀን በአንቀጾቹ በተጠቀሰው መልኩ ማብራራት፣

- ስለዚህ ቀን ያለህን ስሜት መግለጽ
- ይህን አንቀጽ ካነበብክ በኋላ ልታደርገው የወሰንከውን ነገር መዘርዘር።

﴿ فَإِذَا جَآءَتِ ٱلصَّآخَّةُ ﴿٣٣﴾ ﴾ عبس: ٣٣

‹‹(የቂያማ) አደንቋሪ ጩኸት በመጣች ጊዜ፤›› (አንቀጽ 33)

የዓለማዊ ሕይወት መቋጫ፣ በሰው ልጅ ሕይወት እያንዳንዱ እርከን አምላክ ከዘረጋው ረኸርምና ሁለንተናዊ ‹‹ተድቢር›› (ቅንጅት) ጋር የሚጣጣመው ፍጻሜ ይህ ነው።

‹‹ሷኸህ›› የሚለው ቃል ድምጸቱ ጠንካራና ሰርሳሪ ሲሆን፣ ቀጣዩን መልእክት ለመግለጽ የሚያመች አስፈሪ ድባብ ይፈጥራል። ይህም

ትእይንት የሰው ልጅ እጅግ ከሚወዳቸውና ከማንም በላይ ከሚቀርቡት ወገኖቹ የሚሸሽበት ቀን ነው።

﴿ يَوۡمَ يَفِرُّ ٱلۡمَرۡءُ مِنۡ أَخِيهِ ٣٤ وَأُمِّهِۦ وَأَبِيهِ ٣٥ وَصَٰحِبَتِهِۦ وَبَنِيهِ ٣٦ ﴾ عبس: ٣٤ - ٣٦

‹‹በዚያ ቀን እያንዳንዱ ሰው ከወንድሙ ይሸሻል። ከእናቱም፣ ከአባቱም፣ ከሚስቱም፣ ከልጆቹም።›› (አንቀጽ 34-36)

እነዚህ ጠንካራ የዝምድና ትስስር ያላቸው ናቸው። ግና አስደነጋጩ ጩኸት ትስስራቸውን ይበጥሰዋል። እያንዳንዱ ሰው ወገኖቹን ፍጹም ረስቶ ወደራሱ ጉዳይ ይዞራል። በርሱ ብቻ ይጠመዳል። ሌሎችን የሚያስብበትና ስለነርሱ የሚተጋበት እድል ያጣል።

﴿ لِكُلِّ ٱمۡرِيٕ مِّنۡهُمۡ يَوۡمَئِذٖ شَأۡنٞ يُغۡنِيهِ ٣٧ ﴾ عبس: ٣٧

‹‹በዚያን ቀን ከመካከላቸው እያንዳንዱ ሰው (የሚያስጨንቀውና የሚያሳስበው) የየግል ጉዳይ ይኖረዋል።›› (አንቀጽ 37)

በመቀጠልም ካህድያንና አማኞች በአምላክ ሚዛን ከተመዘኑ በኋላ የሚገጥማቸውን ሁኔታ ይስላል፦

﴿ وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٖ مُّسۡفِرَةٞ ٣٨ ضَاحِكَةٞ مُّسۡتَبۡشِرَةٞ ٣٩ ﴾ عبس: ٣٨ - ٣٩

‹‹በዚያን ቀን (የከፊሎቹ የአማኞች) ፊቶች ያበራሉ፤ በፈገግታ ይሞላሉ፤ በደስታ ይዋጣሉ።›› (አንቀጽ 38-39)

የሚያበሩ እና የሚያንጸባርቁ፣ በፈገግታ የተሞሉ ፊቶች፣ አምላካቸውን ተስፋ ያደረጉ፣ ስራቸውን እንደወደደላቸው ተሰምቷቸው የተረጋጉ ወይም ፍጻሜያቸውን ያወቁ፣ ማረፊያቸው የተገለጸላቸው ፊቶች ናቸው፡ ፡ ይህ በመሆኑ ከአስደንጋጩ ጩኸት በኋላ እንዲረጋጉና እንዲደሰቱ አደረጋቸው።

በሌላ በኩል የካህድያን ፊቶች በሐዘን ይጠቁራሉ። በቁጭት ይጠለሻሉ። ውርደትና ሰቀቀን ያከስላቸዋል። የስራቸውን ክፉነት አውቀዋል። የሚጠብቃቸውን ቅጣትም አረጋግጠዋል።

﴿ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡكَفَرَةُ ٱلۡفَجَرَةُ ﴿٤٢﴾ ﴾ عبس: ٤٢

‹‹እነዚያ (አቧራ የለበሱ፥ በጽልመት የተዋጡ ፊቶች የሚኖራቸው) ከሓዲያንና አመፀኞች ናቸው።›› (አንቀጽ 42)

እነርሱም በአላህና በመልእክተኛው የማያምኑ፣ ወሰኑን የተላለፉ፣ ክልክሉን የተዳፈሩ ‹‹ከሐዲዎችና አመጸኞች››ናቸው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- የአስደነጋጩን ጩኸት ቀን በአንቀጾቹ በተገለጸው መልኩ አብራራ፣
- ስለዚህ ቀን ያለህን ስሜት ግለጽ፣
- እነዚህን አናቅጽ ከሰማህ በኋላ ምን ለማድረግ እንደወሰንክ ተናገር፣

* * *

አልተክዊር ምእራፍ

ይህ ምእራፍ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ ሁለቱም ክፍሎቹ ታላላቅ የእምነት ጽንሰ ሐሳቦችን ይዳስሳሉ፡፡

አንደኛ፡- የቂያማ ጽንሰ ሐሳብ፣ በዓለም ፍጻሜ ወቅት በዩኒቨርሱ ላይ የሚደርሰው ጸሐይን፣ ከዋክብትን፣ ተራራዎችንና ባህሮችን፣ ሰማይንና ምድርን፣ እንስሳትና አውሬዎችን፣ እንዲሁም የሰውን ልጅ ራሱን ያጠቃለለ ግዙፍ መንኮታኮትና መናጋት፡፡

ሁለተኛ፡- የወህይ ምንነት፣ የወህይ አድራሽ መላኢካ ባህሪና የተቀባዩ ነብይ ስብእና፡፡ ይህ ወህይ የሚመለከታቸው ሕዝቦች ከርሱ እንዲሁም እነርሱን ከፈጠረውና ወህይ ካወረደላቸው አምላክ ጋር ያላቸው ግንኙነት፡፡

የምእራፉ አጠቃላይ ቅኝት ከእስሩ በተለቀቀ ፈጣንና አውዳሚ እንቅስቃሴ የሚገለጽ ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ሁሉንም ነገር ያወድማል፣ ይበትናል፡፡ የሰከነ ያስበረግጋል፡፡ ጸጥታን ያደፈርሳል። ሰላምን ይነሳል፡፡ ያውካል፡፡ ያሸብራል፡፡ የሰውን ልጅ ነፍስ ረኸርም እና ብርቱ በሆነ አኳኋን በማርገፍገፍ ከለመደችውና አጥብቃ ከያዘችው ነገር ሁሉ ያላቅቃታል፡፡ ሐያል ከሆነው አላህ ውጭ መመለሻ እና መርጊያ የላትም፡፡ ዘልዓለማዊነት የርሱ ብቻ ነው፡፡ መረጋጋትና ሰላም የሚገኘውም ከርሱ ዘንድ ብቻ ነው፡፡

* * *

አንቀጽ 1-14

﴿إِذَا ٱلشَّمۡسُ كُوِّرَتۡ ١ وَإِذَا ٱلنُّجُومُ ٱنكَدَرَتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ سُيِّرَتۡ ٣ وَإِذَا ٱلۡعِشَارُ عُطِّلَتۡ ٤ وَإِذَا ٱلۡوُحُوشُ حُشِرَتۡ ٥ وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ سُجِّرَتۡ ٦ وَإِذَا ٱلنُّفُوسُ زُوِّجَتۡ ٧ وَإِذَا ٱلۡمَوۡءُۥدَةُ سُئِلَتۡ ٨ بِأَيِّ ذَنۢبٖ قُتِلَتۡ ٩ وَإِذَا ٱلصُّحُفُ نُشِرَتۡ ١٠ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ كُشِطَتۡ ١١ وَإِذَا ٱلۡجَحِيمُ سُعِّرَتۡ ١٢ وَإِذَا ٱلۡجَنَّةُ أُزۡلِفَتۡ ١٣ عَلِمَتۡ نَفۡسٞ مَّآ أَحۡضَرَتۡ ١٤﴾

التكوير: ١ - ١٤

‹‹ወሐይ በተጠቀለለች (ብርሃኗን ባጣች) ጊዜ፤ ከዋክብት በረገፉ ጊዜ፤ ጋራዎች በተንኮታኮቱ ጊዜ፤ የአሥር ወር እርጉዝ ግመሎች ያለ ጠባቂ በተተዉ ጊዜ፤ የዱር እንስሳት በተሰባሰቡ ጊዜ፤ ባሕሮች በተቃጠሉ ጊዜ፤ ነፍሶችም (ከየአካሎቻቸው ጋር) በተቆራኙ ጊዜ፤ ከነሕይወቷ የተቀበረች ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ፤ በምን ወንጀሏ እንደተገደለች፤ (የሥራ) መዛግብት በተገለው ጊዜ፤ ሰማይ በተገሸለጠች ጊዜ፤ ገሀነም (ለከሓዲያን) በተቀጣጠለች ጊዜ፤ ገነት (ለአማኞች) እንድትቀርብ በተደረገች ጊዜ፤ (ይህ ሁሉ በሚከሠትበት ወቅት ለዕለተ ትንሣኤ) እያንዳንዷ ነፍስ ያቀረበችውን (መልካም ወይም ክፉ ሥራ) ታውቃለች።›› (አንቀጽ 1-14)

አጠቃላይ ዓላማ

- በአንቀጹ የተብራራውን ሁለንተናዊና ግዙፍ የዩኒቨርሱ ስርዓት መናጋት መግለጽ፣
- ለዚህ የቂያማ ቀን ባህሪ ቁርአናዊ መረጃዎችን ማቅረብ፣

* * *

ትእይንቱ የተለመዱ ነገሮች ሁሉ የሚናጉበት፣ ስርዓታቸው የሚፋለስበት ነው። የሰማይ ኘላኔቶችን፣ ምድርን፣ የዱር አውሬዎችን፣ ለማዳ እንስሳዎችንና የሰውን ልጅ ነፍስ ሁሉ ያጠቃልላል። በትርምሱ መሐል የሰው ልጅ ከስራው ጋር ይፋጠጣል።

አካሎቹ ተገጣጥመውና እንቅስቃሴው ሚዛናዊ ሆኖ የምናየውና የለመድነው ይህ ዩኒቨርስ ስርዓቱ እንደሚፋለስ፣ አካሎቹ እንደሚበታተኑ፣ የታነጸበት ባህሪው እንደሚወገድ፣ በተወሰነለት ጊዜም ፍጻሜ እንደሚኖረው፣ ይህም ጊዜ ፍጡራን የለመድነው ገጽታቸው ተቀይሮ ሌላ ገጽታ በሚላበሱበት ጊዜ እንደሚሆን እነዚህ የዩኒቨርሱ ግዙፍ ክስተቶች ያመለክታሉ።

ምእራፏ በሕሊናና በልቦና ላይ ይህን ስሜት በማስረጽ ከዚህ ቋሚ ከሚመስል፣ ግና ተወጋጅ ከሆነ ስርዓት ተነጥለን ዘልዓለማዊ ከሆነው እውነታ፣ ማለትም ሁሉም ነገር ሲለወጥ እና ሲወገድ እርሱ ከማይለጠው እና ከማይወገደው አላህ ጋር እንድንገናኝ ከፍተኛ ግፊት ታደርጋለች።

إِذَا ٱلشَّمۡسُ كُوِّرَتۡ

ፀሐይ በተጠቀለለች (ብርሃኗን ባጣች) ጊዜ፤

የጸሐይ መጠቅለል ብርሃኗን እና ሙቀቷን እንደምታጣ፣ ነበልባሏ እንደሚከስም ለመግለጽ ታስቦ ይሆናል። ወይም ሌላ መልእክት ይኖረዋል። ይህ እንዴት እንደሚከሰትና ምክንያቶቹን የሚያውቀው አላህ ነው።

وَإِذَا ٱلنُّجُومُ ٱنكَدَرَتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ سُيِّرَتۡ

ከዋክብት በረገፉ ጊዜ፤ ጋራዎች በተንኮታኮቱ ጊዜ፤

የከዋክብት መርገፍ በአንድ አቆራኝቶ ከሚይዛቸው ስርዓት ማፈትለካቸውን፣ ነበልባላቸውና ብርሃናቸው መክሰሙን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። የተራራዎች መነዳት ተፈረካክሰው እና ወደ አመድነት ተቀይረው በሕዋው ውስጥ መበተናቸው ሊሆን ይችላል።

وَإِذَا ٱلۡعِشَارُ عُطِّلَتۡ

የአሥር ወር እርጉዝ ግመሎች ያለ ጠባቂ በተተዉ ጊዜ፤

ከአረቦች ዘንድ እጅግ ውድ ዋጋ ያላቸው እርጉዝ ግመሎች ፋይዳ ያጣሉ። ስለነርሱ ማንም አያስብም።[1]

وَإِذَا ٱلۡوُحُوشُ حُشِرَتۡ

የዱር እንስሳት በተሰባሰቡ ጊዜ፤

የዚያን ቀን በየጫካውና ሸለቆው የተበተኑ፣ ሰዎችን የማይቀርቡ፣ የሚፈሩና የሚበረግጉ እንስሳት የዚያን ቀን ባህሪያቸው ይለወጣል። ከድንጋጤ የተነሳ ፍርሃታቸው ተወግዶ፣ እርስ በርስ መፈራራታቸውን አቁመው፣ ታዳኞቻቸውን ረስተው በአንድ ይሰባሰባሉ።

وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ سُجِّرَتۡ ٦ وَإِذَا ٱلنُّفُوسُ زُوِّجَتۡ

ባሕሮች በተቃጠሉ ጊዜ፤ ነፍሶችም (ከየአካሎቻቸው ጋር) በተቆራኙ ጊዜ፤

የባህሮች መቃጠል በውሃ መሞላታቸው ወይም መቀጣጠልና መፈንዳታቸው ሊሆን ይችላል። የነፍሶች መቆራኘት ዳግም ከሞት በመቀስቀስ ከየአካሎቻቸው ጋር መገናኘታቸው ወይም ደግሞ ከየመሰሎቻቸው ጋር መሰባሰባቸው ሊሆን ይችላል።

وَإِذَا ٱلۡمَوۡءُۥدَةُ سُئِلَتۡ ٨ بِأَيِّ ذَنۢبٖ قُتِلَتۡ ٩

[1] **በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሚገኙና የሰው ልጆች እንደ ውድና እንደ ብርቅ የሚያዩአቸው አለማዊ ጸጋዎች የዚያን ቀን የማንንም ትኩረት የማይስቡ ይሆናሉ። (ተርጓሚው)**

‹‹ከነሕይወቷ የተቀበረች እንስት በምን ወንጀል እንደተገደለች በተጠየቀች ጊዜ››

በዘመነ መሐይምነት የሰው ልጅ ነፍስ ከመርከሱ የተነሳ ሴትን ልጅ ከነ ሕይወቷ መቅበር እጅግ የተስፋፋ ባህል ነበር። ይህን የሚያደርጉት ነውርን ወይም ድህነትን በመፍራት ነበር። የመቅበሩ ስራ እጅግ አሰቃቂና ጨካኝ በሆነ መልኩ ይፈጸማል። ከዚህ ውጭ በሌሎች መንገዶችም ሴትን ያዋርዷታል።

ኢስላም ሲመጣ ይህን እኩይ ባህል አወገዘ። ከለከለውም። ከከባድ ወንጀሎችም ፈረጀው። በእለተ ቂያማ የሚደረግ ምርመራ ዋነኛ ክፍልም አደረገው። በዚህ አስፈሪ ሁኔታ መሐል መጠቀሱም ክብደቱን ያመለክታል። ‹‹የዚያን ቀን ከነሕይወቷ የተቀበረች እንስት ለምን እንደተገደለች ትጠየቃለች።›› ሲል አወጀ። እርሷ ከተጠየቀች ቀባሪዋስ?

وَإِذَا ٱلصُّحُفُ نُشِرَتۡ

(የሥራ) መዛግብት በተገለው ጊዜ፣

የስራ መዝገቦችም ይገለጻሉ። ይፋ ይሆናሉ። ድብቅ መሆናቸው ያከትማል። ይህ መሆኑ ለነፍስ እጅግ ታላቅ መከራ ነው። ባለቤቱ ሊያወሳቸው እንኳ የሚያፍርባቸው ስንት ወንጀሎች ተደብቀዋል? ያኔ ግን ይፋ ይሆናሉ።

ይህ የቀልብ ሚስጥር መገለጽ በዩኒቨርሱም ውስጥ ተመሳሳይ ክስተት ይጎዳኘዋል።

﴿١٠﴾ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ كُشِطَتۡ

‹‹ሰማይ በተገሸለጠች ጊዜ››

መገሸለጥ መወገዷን ያመለክታል።

ከዚያ ቀን አስፈሪና ግዙፍ ሁነቶች መካከል የመጨረሻው እንዲህ ተገልጿል፡-

وَإِذَا ٱلْجَحِيمُ سُعِّرَتْ ﴿١٢﴾ وَإِذَا ٱلْجَنَّةُ أُزْلِفَتْ

‹‹ገሃነም በተቀጣጠለች፣ ገነትም በቀረበች ጊዜ››

ጀሃነም ትቀጣጠላለች- ነበልባሏና ግለቷ ይጨምራል። ጀነትም እንግዶቿን ለመቀበል ይፋ ትሆናለች። ይህ ሁሉ ክስተት ሲፈጸም እርሷ ቅርብ ናት። አማኞችን ለማስተናገድም ስንዱ ናት።

በዚህ ጊዜ ነፍስ ለዚህ ቀን ያዘጋጀችውን፣ ለምርመራው ያቀረበችውን ስራ ታውቃለች።

عَلِمَتْ نَفْسٌ مَّآ أَحْضَرَتْ ﴿١٤﴾

‹‹ነፍስ ሁሉ (ስለራ) ያቀረበችውን ታውቃለች።››

እያንዳንዷ ነፍስ ትርፍና ኪሣራዋን ትገነዘባለች፡ ካቀረበችው ነገር ኢምንት መቀየር፣ መጨመር ወይም መቀነስ እንደማትችል ትረዳለች። ሁሉም ነገር ተለውጧል። ሳይለወጥ የቀረው አላህ ብቻ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- በአንቀጾቹ የተዘረዘሩትን ሁለንተናዊና ግዙፍ የዩኒቨርሱ ስርዓት መናጋቶች ግለጽ፣
- ለዚህ የቂያማ ቀን ባህሪ ቁርአናዊ መረጃዎችን አቅርብ፣

አንቀጽ 15-29

﴿ فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلۡخُنَّسِ ١٥ ٱلۡجَوَارِ ٱلۡكُنَّسِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ إِذَا عَسۡعَسَ ١٧ وَٱلصُّبۡحِ إِذَا تَنَفَّسَ ١٨ إِنَّهُۥ لَقَوۡلُ رَسُولٖ كَرِيمٖ ١٩ ذِي قُوَّةٍ عِندَ ذِي ٱلۡعَرۡشِ مَكِينٖ ٢٠ مُّطَاعٖ ثَمَّ أَمِينٖ ٢١ وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجۡنُونٖ ٢٢ وَلَقَدۡ رَءَاهُ بِٱلۡأُفُقِ ٱلۡمُبِينِ ٢٣ وَمَا هُوَ عَلَى ٱلۡغَيۡبِ بِضَنِينٖ ٢٤ وَمَا هُوَ بِقَوۡلِ شَيۡطَٰنٖ رَّجِيمٖ ٢٥ فَأَيۡنَ تَذۡهَبُونَ ٢٦ إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ ٢٧ لِمَن شَآءَ مِنكُمۡ أَن يَسۡتَقِيمَ ٢٨ وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٩ ﴾ التكوير: ١٥ - ٢٩

‹‹ተመላላሽ (በቀን የሚጠፋና ሌሊት ላይ ብቅ የሚሉ) በሆኑት (ብርሃናማ) ከዋክብት እምላለሁ። ተንገሥገሥና የሚደበቁ በሆኑት (ከዋክብትም እምላለሁ)። በሌሊትም እምላለሁ፤ ፅልመቱ (ፍጡራንን) በሸፈነ ጊዜ፤ በንጋትም እምላለሁ፤ መተንፈስ (ብርሃንን መለገሥ) በጀመረ ጊዜ፤ እርሱ (ቁርአን) እጅግ የተከበረ መልዕክተኛ (ይዞት የመጣው) ቃል ነው። ኃያል፥ የዐርሽ ባለቤት ከሆነው (አምላክ) ዘንድም እጅግ ክቡር የሆነ (መልዕክተኛ ያመጣው ቃል ነው)። በዚያ ቦታ (በሰማየ ሰማያት ውስጥ) ከፍተኛ ተሰሚነት ያለውና ታማኝ (መልዕክተኛ ያመጣው ቃል ነው)። (ማንኑቱን ጠንቅቃችሁ የምታውቁትና) አብሯችሁ የኖረው ባልደረባችሁ (ሙሐመድ) እብድ አይደለም። (ሙሐመድ ጂብሪልን) በግልጽ አድማስ ውስጥ (በሚገባ) አይቶታል። እርሱ (ሙሐመድ) ሩቅ ሚስጥርን የሚነፍግ (መልዕክቱን የሚደብቅ) አይደለም። እርሱ (ቁርአን) የተረገመው ሰይጣን ቃልም አይደለም። (እንደረፋድ ፀሐይ ግልጽ የሆነ ጉዳና እያለ) ወደየት (አቅጣጫ) ትጓዛላችሁ? እርሱ (ቁርአን) በእርግጥም የዓለማት ማስታወሻ (መገሰጫ) ነው። ከመካከላችሁ (በቀጥተኛው መንገድ ላይ) መፅናት ለሚሻ ሰው (መገሰጫ) ነው። የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ካልሻ እናንተ አትሹም።›› (አንቀጽ 15-29)

አጠቃላይ ዓላማ

- ✓ የልቅና ባለቤት የሆነው አምላክ የማለባቸውን የዩኒቨርሱ ክስተቶች መዘርዘር
- ✓ የልቅና ባለቤት የሆነው አምላክ ጅብሪልን ያላቀበትን ነገር ማስታወስ
- ✓ አላህ ነቢዩን የገለጸበትን ባህሪ ማስታወስ
- ✓ እነዚህን ነገሮች ሁሉ የመግለጹን ጥበብ መረዳት

* * *

ይህ የምራፏ ክፍል ውብ በሆኑ የዩኒቨርሱ ክስተቶች በመማል ይወጠናል። የመሐላዎች ማረፊያዎች የወህዩ ባህሪና የአላህ መልእክተኛ ስብእና፣ እንዲሁም መልእክቱን የሚያደርሰው መላእክ ልቅና፣ የሰው ልጆች ከዚህ መልእክት አኳያ የሚኖራቸው አቋም ነው።

﴿ فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلۡخُنَّسِ ١٥ ٱلۡجَوَارِ ٱلۡكُنَّسِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ إِذَا عَسۡعَسَ ١٧ وَٱلصُّبۡحِ إِذَا تَنَفَّسَ ١٨ ﴾

‹‹ተመላላሽ (በቀን የሚጠፋና ሌሊት ላይ ብቅ የሚሉ) በሆኑት (ብርሃናማ) ከዋክብት እምላለሁ። ተንገሥጋሾችና የሚደበቁ በሆኑት (ከዋክብትም እምላለሁ)። በሌሊትም እምላለሁ፤ ፅልመቱ (ፍጡራንን) በሸፈነ ጊዜ፤ በንጋትም እምላለሁ፤ መተንፈስ (ብርሃንን መለገሥ) በጀመረ ጊዜ፤›› (አንቀጽ 15-18)

ተመላሾች የተባሉት ከዋክብት ናቸው። ሌሊቱ ጨለማውን መጠንሰሱ መጨለሙን ያመለክታል። ንጋቱ መተንፈሱ ሕያውነቱን ያሳያል። ንጋት ሕይወት አለው። ይተነፍሳል። የጠዋትን ወጋገን ማየት፣ በእርግጥም ለአስተዋይ ልቦና ሕይወት ኖሮት የሚተነፍስ አይነት ስሜት ያሰርጻል።

﴿ إِنَّهُۥ لَقَوۡلُ رَسُولٖ كَرِيمٖ ١٩ ذِي قُوَّةٍ عِندَ ذِي ٱلۡعَرۡشِ مَكِينٖ ٢٠ مُّطَاعٖ ثَمَّ أَمِينٖ ٢١ ﴾

‹‹እርሱ (ቁርአን) እጅግ የተከበረ መልዕክተኛ (ይዞት የመጣው) ቃል ነው። ኃያል፥ የዐርሽ ባለቤት ከሆነው (አምላክ) ዘንድም እጅግ ክቡር

የሆነ (መልዕክተኛ ያመጣው ቃል ነው)። በዚያ ቦታ (በሰማየ ሰማያት ውስጥ) ከፍተኛ ተሰሚነት ያለውና ታማኝ (መልዕክተኛ ያመጣው ቃል ነው)።›› (ኣንቀጽ 19-21)

ጅብሪል የተላቀውን የአምላክ ቃል ስለሚያደርስ የተላቀ ተብሏል። አምላኩ ‹‹የሐይል ባለቤት›› ሲል ገልጾታል። መልእክቱን ለማድረስ ብርቱ ጉልበት እንደሚያሻ በሚጠቁም መንገድ።

ከዓርሹ ባለቤት ዘንድ ‹‹ባለሟል››፣ በመላእክት አለም ደግሞ መልእክቱን ማድረስ ረገድ ‹‹ታማኝ›› የሆነ መልአክ ይህን መልእክት ለማድረስ ተመርጧል።

የእነዚህ ባህሪያት ድምር መልእክቱ የተላቀ፣ ግዙፍ፣ የመጠቀና ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታሉ። አላህ ለሰው ልጅ ያደረገውን እንክብካቤም ይጠቁማሉ። እንዲህ ዓይነት ባህሪ ያለውን መላእክት መልእክቱን ያደርሱለት ዘንድ በመምረጥ ወደተመረጡት ነብይ ወህይ እንዲያወርድ ማድረጉ የዚህ እንክብካቤው ትልቅ መገለጫ ነው።

ቃሉን ተሸክሞ የመጣው መላእክ ባህሪ ይህ ሲሆን፣ ለናንተ ያደረሰው ‹‹ባልንጀራችሁ (ሷሂቡኩም)›› ነው። ሙሉ እድሜውን ታውቁታላችሁ። ስለዚህም እውነትን ይዞላችሁ በመጣ ጊዜ ‹‹እብድ ነው›› ማለታችሁ አግባብ አይደለም።

﴿ وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجْنُونٍ ﴿٢٢﴾ وَلَقَدْ رَءَاهُ بِٱلْأُفُقِ ٱلْمُبِينِ ﴿٢٣﴾ وَمَا هُوَ عَلَى ٱلْغَيْبِ بِضَنِينٍ ﴿٢٤﴾ ﴾

‹‹(ማንነቱን ጠንቅቃችሁ የምታውቁትና) አብሯችሁ የኖረው ባልደረባችሁ (ሙሐመድ) እብድ አይደለም። (ሙሐመድ ጂብሪልን) በግልጽ አድማስ ውስጥ (በሚገባ) አይቶታል። እርሱ (ሙሐመድ) ሩቅ ሚስጥርን የሚነፍግ (መልዕክቱን የሚደብቅ) አይደለም።›› (ኣንቀጽ 22-24)

በትክክል የሚያውቋቸውን፣ የተስተካከለና አስተዋይ አእምሮ እንዳላቸው የተረዷቸውን የአላህ መልእክተኛ ‹‹እብድ›ነው፡፡ ‹‹ሰይጣን መልእክት ያስተላልፍለታል›› ሲሉ መተቸታቸው ይገርማል፡፡

ቁርአን በዚህ የምእራፏ ክፍል እጅግ ድንቅ እና ውብ፣ እጅግ ጥበባማ፣ እጅግ ማራኪ ስለሆነው ዩኒቨርስ በማስቃኘት ቁርአንም ይህን ውበት፣ ይህን ጥበብ ያለ አምሳያ ካስገኘው አካል የመነጨ መሆኑን አመላክታቸው፡፡ ይዞት የወረደውን መላእክ ባህሪ እና የተላከውን መልእክተኛ ስብእናም ነገራቸው፡፡

መልእክተኛው የሚያውቋቸው ስብእና ናቸው፡፡ እይታ በማይጭበረበርበት ግልጽ አድማስ ውስጥ ጅብሪልን በእርግጠኝነት አይተውታል፡፡ የመጣላቸውን ሩቅ ሚስጥር፣ አምላካዊ መልእክት በማድረስ ረገድም ታማኝ መሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡ እድሚያቸውን ሙሉ ከርሳቸው እውነትን እንጅ ሌላ አይታወቅም፡፡

﴿ وَمَا هُوَ بِقَوۡلِ شَيۡطَٰنٖ رَّجِيمٖ ﴿٢٥﴾ ﴾ التكوير: ٢٥

‹‹እርሱ (ቁርአን) የተረገመው ሰይጣን ቃልም አይደለም፡፡›› (አንቀጽ 25)

ሰይጣን እንዲህ ዓይነት የተስተካከለ ፍጹማዊ መልእክት አያስተላልፍም፡ ፡ በመቀጠልም‹ታዲያ ወደየት ትሄዳላችሁ?› በማለት የውግዘት ድምጸት ያለው ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፡፡ የተናገራችሁትን ቃል፣ የሰጣችሁትን ፍርድ የት ትጥሉታላችሁ? ወይም በሄዳችሁበት ቦታ ሁሉ እየተከተለ የሚገጥማችሁን እውነት ትታችሁ ወደየት ትሄዳላችሁ?

إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ

‹‹እርሱ የዓለማት መገሰጫ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡››

አሥ፣ የሕልውናቸውን ምንነት፣ ሚናቸውን፣ በዙሪያቸው ያለውን ዩኒቨርስ እውነታ የማስታወስ መልእክት ነው። የወረደውም ለዓለማት ነው። ገና ከመነሻው ጀምሮ ዓለማቀፋዊነቱን ያወጀ ጥሪ።

ኢስላማዊው ዳእዋ በጠላቶቹ የሚሳደድ በነበረበት በመካው ዘመን ነበር ይህ የታወጀው።

በመቀጠልም የመቀናት ጎዳና ለፈለገ ሰው ገርና ቀላል መሆኑን ይገልጽላቸዋል። ስለዚህም ስለራሳቸው ሁኔታ ተጠያቂዎች እነርሱው ናቸው። አላህ ይህን ገር ፍኖት ዘርግቶላቸዋል።

﴿ لِمَن شَآءَ مِنكُمۡ أَن يَسۡتَقِيمَ ٢٨ ﴾ التكوير: ٢٨

‹‹ከመካከላችሁ (በቀጥተኛው መንገድ ላይ) መፅናት ለሚሻ ሰው (መገሰጫ) ነው።›› (አንቀጽ 28)

የአላህን ቅን መመሪያ ተጠቅሞ፣ ወደ አላህ የሚያደርሰውን ቀጥተኛ መንገድ ተከትሎ መቀናት ለሚሻ ሁሉ መንገዱ ገር ተደርጓል። በሚገባ ተብራርቷል። ብሾርታዎች ሁሉ ተገፈዋል። አጠራጣሪ ነገሮች ሁሉ ተጠርገዋል። ሊቀርቡ የሚችሉ ምክንያቶች ሁሉ ተወግደዋል።

መቀናት እንደሚችሉ፣ ቀጥተኛው መሆን ገር እንደተደረገላቸው ካስገነዘበ በኋላ አንድን እውነታ አጸደቀ። እርሱም ከነርሱ ፈቃድ (መሺአ) ጀርባ የአላህ መሺአ የመኖሩ እውነታ ነው።

﴿ وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٩ ﴾ التكوير: ٢٩

‹‹የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ካልሻ እናንተ አትሹም።›› (አንቀጽ 29)

ይህን የገለጸው የነርሱ ፈቃድና ነጻነት የሁሉም ነገር መሠረት ከሆነው ከታላቁ መሽአ የተነጠለ እንደማይመስላቸው ይገነዘቡ ዘንድ ለማሰታወስ፤ የመስራት ነጻነት የተሰጣቸው፣ መቀናት የተገራላቸው ሁሉንም ነገር ባካበበው ሁለንተናዊ መሺአ ፈቃድ መሆኑን እንዳይዘነጉ ለማስቻል ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- የልቅና ባለቤት የሆነው አምላክ የማለባቸውን የዩኒቨርሱ ክስተቶች ግለጽ፣
- አላህ ጅብሪልን የገለጸበትን ባህሪ አሰታውስ፣
- ነቢዩን የገለጸበትን ባህሪም አሰታውስ፣
- አላህ እነዚህን ነገሮች ሁሉ የመግለጹን ጥበብ አብራራ።

* * *

ሱል ኢንፊጣር

አንቀጽ 1-9

﴿إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنفَطَرَتۡ ١ وَإِذَا ٱلۡكَوَاكِبُ ٱنتَثَرَتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ فُجِّرَتۡ ٣ وَإِذَا ٱلۡقُبُورُ
بُعۡثِرَتۡ ٤ عَلِمَتۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ وَأَخَّرَتۡ ٥ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ٦
ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ٧ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ٨ كَلَّا بَلۡ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ
٩﴾ الانفطار: ١ - ٩

‹‹ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤ ከዋክብትም ተበታትነው በወደቁ ጊዜ፤ ባሕሮችም በተደበላለቁ ጊዜ፤ መቃብሮችም በተገለባበጡ (ሙታን በተነሱ) ጊዜ፤ እያንዳንዷ ነፍስ (ከመልካምም ከክፉም) ያስቀደመችውንና ያቆየችውን ታውቃለች፡ የሰው ልጅ ሆይ! ፍፁም ቸር በሆነው ጌታህ (ላይ እንድታምፅ) ያነሳሳህ ምንድን ነው? በፈጠረህ፣ አካለ ሙሉ ባደረገህና ባስተካከለህም፥ በመረጠው ቅርፅና ውበት በፈጠረህም (ጌታህ ላይ እንድታምፅ ያነሳሳህ ምንድን ነው)? (የሰው ልጆች ሆይ! ከአመጽ) ታቀቡ! የመጪውን ዓለም መኖር ታስተባብላላችሁ።›› (ሱል ኢንፊጣር 1-9)

አጠቃላይ አላማዎች

- በአንቀጾቹ የተዘረዘሩትን የእለተ ቂያማ ክስተቶች መግለጽ
- አላህ ለሰው ልጆች የሰነዘረውን ሂስ ማብራራት

* * *

በእለተ ቂያማ ከሚከሰቱ የዩኒቨርሱስርዓት መናጋቶች መሐል የሰማይ መሰንጠቅ ተወስቷል። ከዚያ አስፈሪ ቀን ክስተቶች መሐል አንደኛው ይህ ነው። ይህን አስፈሪ ትእይንት የከዋክብት መበታተን ይጎዳኘዋል። ከዋክብት በምሕዋራቸው አስደናቂና አስፈሪ በሆነ ፍጥነት የሚምዘገዘጉ አካላት ናቸው። ፍጻሜውን ከአላህ ውጭ ማንም በማያውቀው በዚህ ሰፊ

ዩኒቨርስ ውስጥ ከምህዋራቸው አፈትልከው እንዳይወጡ፣ አቅጣጫም እንዳይስቱ በተፈጥሮ ሕግ ተይዘዋል።

የባህሮች መከፈትና መደባለቅ ገንፍለው እና ገደባቸውን ሁሉ ጥሰው የብስን ማጥለቅለቃቸው ሊሆን ይችላል። በመጣመር ውሃን ያስገኙ ንጥረ ነገሮች (ኦክስጅንና ናይትሮጅን) መነጣጠላቸው ሊሆንም ይችላል። እነዚህ ጋዞች ሲነጣጠሉ የሚፈጠረው ፍንዳታ (ተፍጂር) ሊሆንም ይችላል። በአሁኑ ዘመን የአቶሚክ እና የሐይድሮጅን ቦምቦች እንደሚያደርጉት አይነት ፍንዳታ። ወይም ደግሞ የሰው ልጅ ከሚያውቀውና ከለመደው የተለየ ክስተት ሊሆንም ይችላል።

መቃብሮችም ይገለባበጣሉ። ሙታንም ለምርመራ እና የስራቸውን ዋጋ ለመቀበል ካሸለቡበት የሞት ዓለም ይነሳሉ።

ያኔ፦ ***«ማንኛይቱም ነፍስ ያስቀደመችውንና የቆየችውን ታውቃለች።»***

ማለትም ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሰበሰበውን ወይም በምድር ዓለም የተወችውን የስራዋን ፋና፤ በምድር ዓለም የተጠቀመችውን፣ ለመጭውም ዓለም ያዘጋጀችውን ስራ ታውቃለች። በዚህ የዩኒቨርሱ አስደንጋጭ ክስተት መሐል ነፍስ የሰራችውን ማወቋ መጠቀሱ ልክ እንደ ዩኒቨርሱ መንኮታኮት በፍርሃት የሚንጥ ክስተት ነው።

* * *

ሕዋሳትንና ስሜትን፣ አእምሮንና ሕሊናን የሚያነቃውን ይህን ሁነት ከዘከረ በኋላ የሰው ልጅ ወደሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ይወርዳል። የሰው ልጅ ይህ ሁሉ መከራ ያለበት ሳይመስል ተዝናንቶና ተዘናግቶ፣ ደንዞና ረስቶ ከመኖሩ አኳያ አላህ ሂስና ዛቻ አዘል በሆነ መልእክት ልቦናውን ይነካዋል።

በመጀመሪያ የዋለለትን ውለታ፣ የለገሰውን ጸጋ፣ በተስተካከለ እና ባማረ አኳኋን እንደፈጠረው፣ ቢሻ ኖሮ ከዚህ በተለየ ገጽታ ሊያላብሰው ይችል እንደነበር ያስታውሰዋል።

‹‹አንተ ሰው ሆይ፣›› በማለት ከሰው ልጅ ስሪት ውስጥ ይበልጥ የተላቀውን፣ ከእንስሳ የተለየ የሚያደርገውን ውስጣዊ ገጽታ በመጥራት ያናግረዋል፡፡ በመቀጠልም ውብ እና የተላቀ የሆነውን ሂስ ይሰነዝርበታል፡፡

مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلْكَرِيمِ

‹‹ከቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ?››

መብቱን እንድታጓድል፣ ትእዛዙን ችላ እንድትል፣ ከርሱ ጋር በተያያዘ ስርዓት እንድታጣ የገፋፋህ ምንድን ነው? እርሱ ላንተ ቸር ሆኖ እያለ፣ በችሮታውና በጸጋው ያጥለቀለቀህ ሆኖ እያለ?

በመቀጠልም ከዚህ የአምላክ ችሮታ መሐል አንዱን ይጠቅሳል፡፡ እርሱም መፍጠሩና አካለ ሙሉ ማድረጉ ነው፡፡ በሌላ ገጽታና ቅርጽ ሊፈጥረው ይችል ነበር፡፡ በሰው ልጅ ስሪት ውስጥ ያለውን እየንዳንዱን ሴል የሚያርገፈግፍና ሕሊናውን የሚያነቃ፣ ቸሩ አምላኩ የተላቀ ሂስ እየሰነዘረበት፣ ጸጋውን እያስታወሰው እርሱ ግን ሐላፊነቱን በማንደል፣ ግዴታውን ባለመወጣት ባህሪ መቀጠሉ አግባብ እንዳልሆነ የሚያስታውስ እና የሚገስጽ መልእክት ነው፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- የቂያማን ትእይንቶች በአንቀጾቹ በተወሱት መልኩ ዘርዝር
- አላህ ለሰው ልጅ የሰነዘረውን ሂስ አውሳ

* * *

አንቀጽ 10-19

﴿ وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ١٠ كِرَامٗا كَٰتِبِينَ ١١ يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ١٢ إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٖ ١٣ وَإِنَّ ٱلۡفُجَّارَ لَفِي جَحِيمٖ ١٤ يَصۡلَوۡنَهَا يَوۡمَ ٱلدِّينِ ١٥ وَمَا هُمۡ عَنۡهَا بِغَآئِبِينَ ١٦ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٧ ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٨ يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٞ لِّنَفۡسٖ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ ١٩ ﴾ الانفطار: ١٠ - ١٩

‹‹በናንተ ላይ ተቆጣጣሪዎች (ተሹመውባችኋል)። (ከአላህ ዘንድ) የተላኩና ፀሐፊዎችም (የሆኑ ተቆጣጣሪዎች)። የምትፈጽሙትን (እያንዳንዱን ተግባር) ያውቃሉ። አማኞች ድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው። አመፀኞች ደግሞ ገሃነም ውስጥ ናቸው። በፍርዱ ቀን ከውስጧ ይገባሉ። ከርሷ መራቅ ፈፅሞ አይችሉም። ስለ ፍርዱ ቀን ምን የምታውቀው ነገር አለ? አንዲት ነፍስ ለሌላኛዋ አንዳች ነገር (መፈፀም) የማትችልበት ቀን ነው። የዚህን ቀን ሥልጣን የአላህ ብቻ ይሆናል።›› (አንቀጽ 10-19)

አጠቃላይ ዓላማ

- የሰውን ልጅ ክህደት ምክንያትና ውጤቱን ማስታወስ
- በአንቀጾቹ ውስጥ የተጠቀሱትን ዛቻዎችና ማባበያዎች፣ ቅጣቶችና ሽልማቶች ማብራራት

* * *

በመቀጠልም የሰው ልጅ እንዲቁልና ሐላፊነቱን እንዳይወጣ የሚያደርገውን ዋነኛ ምክንያት ጠቀሰ። እርሱም የምርመራውን ቀን ማስተባበል ነው። ስለምርመራው እና ስለ ምንዳውም አጽንኦት እና ብርታት ባለው ድምጸት አወሳ።

﴿ كَلَّا بَلۡ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ ٩ ﴾ الانفطار: ٩

‹‹(የሰው ልጆች ሆይ! ከአመጸ) ታቀቡ! የመጪውን ዓለም መኖር ታስተባብላላችሁ።›› (አንቀጽ 9)

‹‹ከልላ››የሚለው ቃል ያለበትን ሁኔታ ለማውገዝ እና በብርቱው ለመተቸት በተጠቀሰ ነው። ‹‹የፍርዱን ቀን ታስተባብላላችሁ›› ምርመራውን፣ የስራ ውጤት መሰጠቱን ትክዳላችላሁ። የመወቀሳችሁ ምክንያት፣ ሐላፊነትን ያለመወጣት ሰበብ ይህ ነው። የምርመራውን ቀን ያስተባበለ ቀልብ ለበጎ ነገር የተቀና፣ አምላኩን ለመታዘዝ የሚበጅ አይሆንም መጭውን ዓለም የስተባበለ ሰው ቀልቡ ሕያው፣ ሕሊናውም ንቁ አይደለም።

ወደ ፍርዱ ቀን፣ ወደ መጭው ዓለም የምትነዱ ሆናችሁ እያለ እርሱን ማስተባበላችሁ ይገርማል። እያንዳንዱ ስራችሁ ይመዘገባል። ወደፊትም ትመረመሩበታላችሁ። ተነጥሎ የሚቀር የለም።

﴿ وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ١٠ كِرَامٗا كَٰتِبِينَ ١١ يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ١٢ ﴾ الانفطار: ١٠ - ١٢

‹‹ብናንተ ላይ ተቆጣጣሪዎች (ተሾመውባችኋል)። (ከአላህ ዘንድ) የተላኩና ፀሐፊዎችም (የሆኑ ተቆጣጣሪዎች)። የምትፈጽሙትን (እያንዳንዱን ተግባር) ያውቃሉ።›› (አንቀጽ 10-12)

ጠባቂዎች የተሰጉት የሰውን ልጅ እንዲጎዳኙ፣ እንዲከታተሉ፣ ድርጊቶችንና ቃላቱን እንዲመዘግቡ ሐላፊነት የተሰጣቸው መላእክት ናቸው። የሰው ልጅ የሚሰራውን ሁሉ የሚያውቁ መላእክት ጠባቂዎች ዘወትር እንደማይለዩት ማወቁ ብቻ እንዲፈራ፣ ሕሊናው እንዲነቃ እና ስርዓት እንዲይዝ ለማድረግ በቂ ነው።

እነዚህ መላእክት ‹‹የተላቁ›› መሆናቸውን ማሰቡ ደግሞ ይበልጥ ያስፈራል። በእያንዳንዱ እንቅስቃሴውና ቅጽበቱ የተላቁ መላእክት ካጠገቡ ምንጊዜም ይገኛሉ። ስለዚህም እነዚህ ልቅና ያላቸው መላእክት በጥሩ ንግግርና ድርጊት ውስጥ እንጅ ሊያገኙት አይገባም።

በመቀጠልም አማኞችና ካህድያን የተላቁ መላእክት የመዘገቡትን ተንተርሶ ከሚደረግ ምርመራ በኋላ የሚያጋጥሟቸውን ፍጻሜዎች ገለጸ፡-

﴿ إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٖ ١٣ وَإِنَّ ٱلۡفُجَّارَ لَفِي جَحِيمٖ ١٤ يَصۡلَوۡنَهَا يَوۡمَ ٱلدِّينِ ١٥ ﴾

‹‹አማኞች ድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው። አመፀኞች ደግሞ ገሃነም ውስጥ ናቸው። በፍርዱ ቀን ከውስጧ ይገባሉ።›› (አንቀጽ 13-14)

አይቀሬ መጨረሻ፣ የማይለወጥ ፍጻሜው ። በጎ ሰዎች ድሎት ውስጥ ይሆናሉ። ካህድያን ወደ ገሐነም ያመራሉ። ‹ቢር›› ማለት መልካም ስራ ማለት ሲሆን፣ ደጋግመው መልካም ስራ በመስራት ባህሪያቸው ያደረጉት ‹‹አብራር›› ተሰኝተዋል። በጎ ስራ ሁሉንም መልካም ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። የዚህ ባህሪ ተቃራኒ ‹ፉጁር›› የሚለው ነው። ‹‹ፉጁር›› ያለ ይሉኝታና ስርዓት ወንጀልን መዳፈር ሲሆን፣ ለጀሃነም ተገቢ ሰው ያደርጋል።

‹‹የፍርዱ ቀን ይገቧታል›› ሲል እጣ ፈንታቸውን ይበልጥ ይገልጻል። ‹‹ከርሷ ራቂዎች አይደሉም።›› ሲልም ያጸናዋል። መጀመሪያውኑ ማምለጥ፣ ከገቡበት በኋላም ለቅጽበት እንኳ መውጣት አይችሉም።

የፍርዱን ቀን የሚያስተባብሉበት ሁኔታ በመኖሩ በርሱ ውስጥ እውን የሚሆኑ ክስተቶችን ከገለጸ በኋላ የመከሰቱን አይቀሬነት ተመልሶ ያወሳል። ግዝፈቱን እና የሰው ልጅ ስለርሱ ጉዳይ እውቀተ ቢስ መሆኑን በሚያሳይ ጥያቄ፤ ነፍስን አቅም አልባ በሚያደርግ፣ በዚያ ቀን እርስ በርስ የመረዳዳትን ተስፋ በሚያሟጥጥ የገለጻ ስልት፤ በዚያ እጅግ አስፈሪ ቀን የጉዳዮች ሁሉ ባለቤት አላህ ብቻ መሆኑን በሚያጎላ ድምጸት።

﴿ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٧ ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٨ ﴾

‹‹ስለ ፍርዱ ቀን ምን የምታውቀው ነገር አለ? ስለ ፍርዱ ቀን ምን የምታውቀው ነገር አለ? ›› (አንቀጽ 17-19)

እውቀተ ቢስነትን የሚያጎላ ጥያቄ ሲሆን፣ በቁርአን ውስጥ የተለመደ አገላለጽ ነው።ውስን የሆነው የሰው ልጅ ሊያውቀውና ሊደርስበት ከሚችለው በላይ እጅግ ግዙፍና ትልቅ መሆኑንም እንዲሰማን ያደርጋል፡ ፡ የጥያቄው መደጋገም ክብደቱን ይበልጥ ያጎላዋል። በዚህ ድባብ መሐል የሰውን ልጅ ፍጹማዊ አቅም አልባነት የሚያጎላ መልእክት ይከተላል፡-

يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٞ لِّنَفۡسٖ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ ١٩

‹አንዲት ነፍስ ለሌላኛዋ አንዳች ነገር (መፈፀም) የማትችልበት ቀን ነው።›

የዚያ ቀን የሰው ልጅ አቅሙን ሙሉ በሙሉ ያጣል።

وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ

‹የዚያን ቀን ሥልጣን የአላህ ብቻ ይሆናል።›

በዚህችም በመጭውም ዓለም የሁሉም ጉዳዮች ባለቤት እርሱ መሆኑ የታወቀ ነው። ግና ዝንጉዎችና የተቁለሉት በዚህች ዓለም ውስጥ የዘነጉት ይህ እውነታ በመጭው ዓለም ይገለጻል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- የሰውን ልጅ ክህደት ምክንቶችና ውጤቱንም አውሳ።
- በአንቀጾቹ ውስጥ የተካተተውን ማባበያና ማስፈራሪያ፣ ቅጣትና ሽልማት አብራራ።

* * *

አል-ሙጦፊፊን

አንቀጽ 1-6

﴿ وَيۡلٞ لِّلۡمُطَفِّفِينَ ١ ٱلَّذِينَ إِذَا ٱكۡتَالُواْ عَلَى ٱلنَّاسِ يَسۡتَوۡفُونَ ٢ وَإِذَا كَالُوهُمۡ أَو وَّزَنُوهُمۡ يُخۡسِرُونَ ٣ أَلَا يَظُنُّ أُوْلَٰٓئِكَ أَنَّهُم مَّبۡعُوثُونَ ٤ لِيَوۡمٍ عَظِيمٖ ٥ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٦ ﴾ المطففين: ١ - ٦

‹‹ለ“አል-ሙጦፊፊን” ወዮላቸው! ለነዚያ ከሰዎች በሚያስሰፍሩበት ወቅት የሚያስሞሉ፣ ለነርሱ (ለሰዎች) በሚሰፍሩላቸው ወይም በሚመዝኑላቸው ወቅት የሚያጉድሉ (ለሆኑት)። እነኝህ (ማፍ ፈጻሚዎች ከሞት በኋላ) እንደሚቀሰቀሱ አይገምቱምን? በታላቁ ቀን፤ ሰዎች (ሁሉ) ለዓለማት ጌታ (ፍርድ) በሚቆሙበት (ታላቅ) ቀን።›› (አንቀጽ 1-6)

አጠቃላይ ዓላማዎች

- አላህ ሙጦፊፊን ያላቸውን ወገኖች የገለጸባቸውን ባህሪያትና በነርሱ መገረሙን መግለጽ፣
- ቁርአን ይህን የስነ ምግባር እንከን ገና በመካ ዘመኑ የመቃኘቱን ምክንያት ማብራራት፣
- የተላቀው ቁርአን የወንጀለኞችን ባህሪ እና ፍጻሜ የገለጸበትን ሁኔታ ማብራራት
- የተላቀው ቁርአን የበጎ ሰሪዎችን ባህሪ፣ ምንዳና መመለሻ የገለጸበትን ሁኔታ ማብራራት
- አማኞች በካህድያን የሚደርሱባቸውን በዚህ ምእራፍ አናቅጽ የተጠቀሱ ሁከቶች ማብራራት
- የሁለቱንም ወገኖች ፍጻሜ መግለጽ

* * *

ይህ ምእራፍ ሕሊናን በማንቃት፣ ልቦናን በመናጥ በዓረቦችም ሆነ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ አዲስ ወደሆነ ክስተት ፊታቸውን ያዞራል። ይህም ክስተት ለምድር ሰማያዊ መልእክት መውረዱ፣ እንዲሁም ይህ መልእክት ያካተተው አዲስና ሁለንተናዊ ርእዮት ነው። ከዚህ በተጓዳኝ ኢስላማዊው ዳእዋ በመካ የታሪክ እርከን ካስተናገዳቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች መካከል ከፊሉን ያስቃኝናል።

የሚጀምረውም አላህ በ‹‹አል ሙጦፊፊን›› ላይ ያወጀውን ጦርነት ይፋ በማድረግ ነው።

وَيْلٌ لِّلْمُطَفِّفِينَ

ለ"አል-ሙጦፊፊን" ወዮላቸው!

‹‹ወዮላቸው›› (ወይል) የሚለው ቃል ጥፋትን ያመለክታል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ إِذَا ٱكْتَالُوا۟ عَلَى ٱلنَّاسِ يَسْتَوْفُونَ ﴿٢﴾ وَإِذَا كَالُوهُمْ أَو وَّزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ ﴿٣﴾ ﴾

‹‹ለነዚያ ከሰዎች በሚያስሰፍሩበት ወቅት የሚያስምሉ፣ ለነርሱ (ለሰዎች) በሚሰፍሩላቸው ወይም በሚመዝኑላቸው ወቅት የሚያጉድሉ (ለሆኑት)።›› (አንቀጽ 2-3)

ቀጣዮቹ ሦስት አናቅጽ በነዚህ ሰዎች ድርጊትና ባህሪ መገረምን ያዘሉ ናቸው። በዚህች ዓለም ሕይወት በሚፈጽሙት እያንዳንዱ ድርጊት ወደፊት እንደሚመረመሩ፣ ምርመራ በሚከናወንበትና የስራ ዋጋ በሚከፈልበት በታላቁ ቀን ከአላህ ፊት በአደባባይ መቅረባቸውን መዘንጋታቸው በእርግጥም ያስገርማል።

﴿ أَلَا يَظُنُّ أُو۟لَٰٓئِكَ أَنَّهُم مَّبْعُوثُونَ ﴿٤﴾ لِيَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿٥﴾ يَوْمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦﴾ ﴾

‹‹እነኝህ (ግፍ ፈጻሚዎች ከሞት በኋላ) እንደሚቀሰቀሱ አይገምቱምን? በታላቁ ቀን፤ ሰዎች (ሁሉ) ለዓለማት ጌታ (ፍርድ) በሚቆሙበት (ታላቅ) ቀን።›› (አንቀጽ 4-6)

መጦፊፎችን በዚህ መልኩ መካዊው የቁርአን ምእራፍ መጋፈጡ ትኩረትን የሚስብ ነገር ነው። መካዊ ምእራፎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት አጠቃላይ ከሆኑ የእምነት ጽነሰ ሐሳቦች ላይ ነው። ለምሳሌ የአላህን አንድነት፣ የመወህይንና የነብይነትን፣ የመጭውን ዓለም፣ የምርመራውን እና የስራ ዋጋ የመከፈሉን እውነታዎች ማጽደቅ ይጠቀሳሉ።።። ስነ ምግባራዊ አጀንዳዎችን በተመለከተ በጥቅሉ ለስነ ምግባር ንቁ የሆነ ሕሊና እንዲፈጠር ከመጣርና ስነ ምግባራዊ አጀንዳዎችን ከመሠረታዊ እምነት ጋር ከማገናኘት ባለፈ ወደ ዝርዝር የስነ ምግባር ትምህርቶች ውስጥ አይገባም። ከሚዛን ማጭበርበር ጋር የተያያዙም ሆኑ ከሌሎች ግንኙነቶች ጋር ትስስር ያላቸው አጀንዳዎች በዝርዝር የተቃኙት በኋላ ላይ፣ ማለትም ኢስላም ለሕይወት ካለው ሁለንተናዊ ርእዮት ላይ በታነጸ ኢስላማዊ መንግስት ጥላ ስር ለሚኖር ማሕበረሰብ ዝርዝር ሕግጋትን በገለጹ መዲናዊ ምእራፎች ውስጥ ነው። በመሆኑም ይህን ጉዳይ በተለይም በዚህች ምእራፍ መዳሰሱ ትኩረትን ይስባል። ብዙ ነገሮችንም ያመለክታል።

አንደኛ፡- ኢስላም በመካ ዘመኑ ከባላባቶች ለክት አልባ በሆነ ሁኔታ በይፋ የሚፈጸም ተጥፊፍ አጋጥሞት እንደነበር ያመለክታል። ያኔ የንግድን እንቅስቃሴ ሞኖፖል ሊባል በሚችል ሁኔታ የተቆጣጠሩት እነርሱ ነበሩ። እናም ትኩረት ሰጥቶ መሐየስ ተገቢ ነበር።

ሁለተኛ፡- የዚህን ዲን ባህሪና ሁለንተናዊነቱን፣ ሕይወትን ጥልቅና ጽኑ ከሆነ የስነ ምግባር መሠረት ላይ ለማነጽ ያለውን ብርቱ ፍላጎት ያመለክታል። እናም በንግድ ግንኙነት ውስጥ በይፋ የሚፈጸመውን ይህን ግልጽ በደል በእጅጉ ጠላ። የማሕበራዊውን ሕይወት ልዝም ያልጨበጠና በሕግ ሐይል፣ በመንግስት ስልጣን ማስተካከል የሚችልበት ሁኔታ ያልተመቻቸ ቢሆንም ገና ከመነሻው ድርጊቱን አወገዘ።

ይህ እውነታ ለመካ ባላባቶች ኢስላማዊውን ዳእዋ ከጅምሩ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እንዲጋፈጡት ያደረጋቸውን ምክንያት በከፊል እንድንገነዘብ ይረዳናል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ያመጡት አዲስ መልእክት በልቦና ውስጥ ብቻ የሚቀመጥ እንዳልሆነ ያለ ጥርጥር ተረድተዋል። ተጨባጭ ሕይወታቸው፣ ጥቅሞቻቸውና ማሕበራዊ ቦታዎቻቸው የቆሙባቸውን የጃሂልያ መሠረቶች የሚያፈራርስ የሕይወት ጎዳና መሆኑ ገብቷቸዋል። ይህም በመሆኑ ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር ከሂጅራ በፊትም ሆነ በኋላ በጽኑ ተዋግተውታል።

﴿ أَلَا يَظُنُّ أُوْلَٰٓئِكَ أَنَّهُم مَّبۡعُوثُونَ ٤ لِيَوۡمٍ عَظِيمٖ ٥ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٦ ﴾

‹‹እነኝህ (ግፍ ፈጻሚዎች ከሞት በኋላ) እንደሚቀሰቀሱ አይገምቱምን? በታላቁ ቀን፤ ሰዎች (ሁሉ) ለዓለማት ጌታ (ፍርድ) በሚቆሙበት (ታላቅ) ቀን።›› *(አንቀጽ 4-6)*

ሁኔታቸው ያስገርማል። ለዚያ ታላቅ ቀን መቀስቀስን፣ ሰዎች ከዓለማት ጌታ ፊት እንደሚቆሙ መገመት ብቻ እንኳ ከተጥፊፍ፣ የሰውን ገንዘብ ያለ አግባብ ከመብላት ለመታቀብ በቂ ነበር። ግና እንደማይቀሰቀሱ ያረጋገጡ ይመስል በዚህ እኩይ ድርጊታቸው መቀጠላቸው ግርምትን ይፈጥራል።

* * *

አንቀጽ 7-17

﴿ كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلۡفُجَّارِ لَفِي سِجِّينٖ ٧ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا سِجِّينٞ ٨ كِتَٰبٞ مَّرۡقُومٞ ٩ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١٠ ٱلَّذِينَ يُكَذِّبُونَ بِيَوۡمِ ٱلدِّينِ ١١ وَمَا يُكَذِّبُ بِهِۦٓ إِلَّا كُلُّ مُعۡتَدٍ أَثِيمٍ ١٢ إِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٣ كَلَّاۖ بَلۡۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ١٤ كَلَّآ إِنَّهُمۡ عَن رَّبِّهِمۡ يَوۡمَئِذٖ لَّمَحۡجُوبُونَ ١٥ ثُمَّ إِنَّهُمۡ لَصَالُواْ ٱلۡجَحِيمِ ١٦ ثُمَّ يُقَالُ هَٰذَا ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ١٧ ﴾

المطففين: ٧ - ١٧

‹‹(የመጭውን ዓለም መኖር ከመዘንጋት) ይታቀቡ! የከሓዲያን መዝገብ “ሲጂን” ውስጥ ነው። ስለ “ሲጂን” ምን የምታውቀው ነገር አለ? (የከሓዲያን እርኩስ ምግባር) የሰፈረበት መዝገብ ነው። የዚያን ቀን ለአስተባባዮች ወዮላቸው! ለነዚያ የፍርዱን ቀን መኖር ላስተባበሉ (ከሓዲያን)። (በክህደትና ጥመት) ወሰን አላፊ (የሆነና) ወንጀለኛ ብቻ እንጂ እርሱን (የፍርዱን ቀን መኖር) ምንም አያስተባብልም። (የፍርዱን ቀን መኖር የሚገልው የቁርአን) አንቀጾች በተነበቡለት ጊዜ፣ “(ይህ) የቀደምት (ሕዝቦች) አፈ-ታሪክ ነው” ይላል። በፍፁም፥ (ነገሩ ከሓዲያን እንደሚያስቡት አይደለም)፤ ይፈፅሙት የነበረው (ኃጢአት) ልቦቻቸውን ሸፈናቸው፥ (እናም ትክክለኛውን ጉዳና መመልከት ተሳናቸው፤ የክህደታቸው ሰበብ ይህ ነው።) (ከጥመታቸው) ይታቀቡ! እነርሱ በዚያን ቀን ከጌታቸው የተጋረዱ ናቸው። ከዚያም ገሃነም ገቢዎች ናቸው። ከዚያም “ይህ (ከሞት በፊት) ታስተ ባብሉት የነበረው (ቅጣት) ነው” ይባላሉ።›› *(አንቀጽ 7-17)*

* * *

ስለነርሱ ማተቱን ቀጥሏል። ከአላህ ዘንድ ያላቸውን ስፍራ፣ በሕይወት ውስጥ የሚያሳዩትን ባህሪ፣ ለታላቁ ቀን ሲቀሰቀሱ የሚጠብቃቸውን ሁኔታ ይተርካል። ለታላቁ ቀን እንደሚቀሰቀሱ አይገምቱም። ቁርአን ይህን ባህሪያቸውን ያወግዛል። ስራዎቻቸው የሚከተቡበት መዝገብ መኖሩን ይገልጻል። ይህንኑ ደጋግሞ ያጸናል። ‹‹ወዮላቸው›› ሲል ይዝትባቸዋል። የታተመ መዝገባቸው በሚገለጥበት ቀን ወዮላቸው፡-

﴿ كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلۡفُجَّارِ لَفِي سِجِّينٖ ٧ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا سِجِّينٞ ٨ كِتَٰبٞ مَّرۡقُومٞ ٩ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١٠ ﴾

‹‹(የመጭውን ዓለም መኖር ከመዘን ጋት) ይታቀቡ! የከሓዲያን መዝገብ "ሲጂን" ውስጥ ነው። ስለ "ሲጂን" ምን የምታውቀው ነገር አለ? (የከሓዲያን እርኩስ ምግባር) የሰፈረበት መዝገብ ነው። የዚያን ቀን ለአስተባባዮች ወዮላቸው!›› (አንቀጽ 7-10)

‹‹ፉጃር›› የሐጢአት ወሰኖችን ሁሉ ያለፉ፣ ለከቶችን ሁሉ የዘለሉ አመጸኞች ናቸው። መጽሐፋቸው ስራዎቻቸው የተጻፉባቸው መዝገቦች ናቸው። ስለዚህ መዝገብ የምናውቀው ነገር የለም። እንድናውቅም አንገደድም። ይህ መዝገብ በሲጂን ውስጥ እንደሚገኝ ይገልጻል። ከዚያም ክብደቱን የሚያጎላ ጥያቄ እንደተለመደው ይቀርባል። ከዚያም የወንጀለኞችን መዝገብ ባህሪ ‹‹የታተመ መዝገብ›› ሲል ይገልጸዋል። መዝገቡ የታተመ በመሆኑ በታላቁ ቀን እስኪገለጽ ድረስ ከውስጡ መጨመርም መቀነስም አይቻልም።

እውነታው ይህ ከሆነ በእርግጥም፡- ‹‹ለአስተባባዮች ወዮላቸው።››

ቀጥሎ ያስተባበሉትን ነገር ይገልጻል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ يُكَذِّبُونَ بِيَوۡمِ ٱلدِّينِ ١١ وَمَا يُكَذِّبُ بِهِۦٓ إِلَّا كُلُّ مُعۡتَدٍ أَثِيمٍ ١٢ إِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٣ ﴾ المطففين: ١١ - ١٣

‹‹ለነዚያ የፍርዱን ቀን መኖር ላስተባበሉ (ከሓዲያን)። (በክህደትና ጥመት) ወሰን አላፊ (የሆነና) ወንጀለኛ ብቻ እንጂ እርሱን (የፍርዱን ቀን መኖር) ምንም አያስተባብልም። (የፍርዱን ቀን መኖር የሚገልፁ የቁርአን) አንቀጾች በተነበቡለት ጊዜ፣ "(ይህ) የቀደምት (ሕዝቦች) አፈ-ታሪክ ነው" ይላል። (አንቀጽ 11-13)

ወሰን ማለፍና ሐጢአት የፍርዱን ቀን ወደ ማስተባበልና ከቁርአን ጋር በተያያዘ ስርዓት ወደ ማጣት ይመራሉ። እናም የዚህ ባህሪ ባለቤት ቁርአን በሚነበብለት ጊዜ ***የቀደምት (ሕዝቦች) አፈ-ታሪክ ነው*** ቢል

አይገርምም። ይህን ያለው የቀድሞ ሰዎች ታሪክ ትምህርት ሰጭ እንደሆነ፣ እንዲሁም የማይዛነፉትን የአላህ ተፈጥሯዊ ሕግጋት ለማብራራት ይረዳ ዘንድ እንደሚተረክ ባለመገንዘብ ነው።

ይህ አስተባባይነት እና ትእቢት ጠንካራ ትችት ያሻዋል። በመሆኑም ‹‹ከልላ›› (ይከልከል) የሚል ነቀፌታ ተሰንዝሮበታል። ‹‹ከልላ›› ነገሩ እነርሱ እንደሚሉት አይደለም።

በመቀጠልም የትእቢታቸውንና የማስተባበላቸውን፣ ሐቅን የመሸሻቸውን፣ ቀልቦቻቸው የታወሩበትን ትክክለኛ ምክንያት ይጠቅሳል፦

﴿ كَلَّا ۖ بَلْ ۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُوا يَكْسِبُونَ ﴿١٤﴾ ﴾ المطففين: ١٤

‹‹በፍፁም፥ (ነገሩ ከሐዲያን እንደሚያስ ቡት አይደለም)፤ ይፈፅሙት የነበረው (ኃጢአት) ልቦቻቸውን ሸፈናቸው፥ (እናም ትክክለኛውን ጐዳና መመልከት ተሳናቸው፤ የክህደታቸው ሰበብ ይህ ነው።)›› (ሱንቀጽ 14)

ሐጢአቶቻቸው ቀልቦቻቸውን ደፈኑ። ቀልብ ወንጀል ሲበዛበት ይደፈናል፡ ፡ ይጨልማል። ብርሃን እንዳይደርሰው ወይም እንዳያስተናግድ የሚከለክል ወፍራም ግርዶ ይቀመጥበታል። በሂደትም ስሜቱን እንዲያጣ ያደርገዋል። በመጨረሻም ይሞታል።

ኢብን ሐጀር፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢና ቢን ማጃህ ከአቡ ሁረይራ በተላለፈ ዘገባ እንዳወሱት ነብዩ (ሶ.ዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

‹‹አንድ ሰው ወንጀል ሲሰራ ከቀልብ ላይ ጥቁር ነጥብ ይደረግበታል። ሲቶብት ቀልቡ ይጸዳል። ወንጀል ሲያክል ደግሞ ጥቁረቱ ይጨምራል፡›› ቲርሚዚ ይህን ዘገባ ‹‹ሐሰኑን ሶሂህ›› ብለውታል። በነሳኢ ዘገባ መሠረትም፦ ‹‹አንድ ሰው ወንጀል ሲሰራ ከቀልቡ ላይ ጥቁር ነጥብ ይደረግበታል። ከሐጢአቱ ሲታቀብ፣ አላህን ምህረት ሲጠይቅና ከቶበተ ቀልቡ ይጸዳል። ወደ ወንጀሉ ከተመለሰ ደግሞ ጥቁረቱ ይጨምራል።

በመጨረሻም ቀልቡን በሙሉ ይሸፍነዋል። አላህ፡- ‹‹ይሰሩት የነበረው ሐጢአት ከቀልቦቻቸው ላይ መረገባቸው›› ያለው ይህንኑ ነው።
ሐሰን አልበስሪም፡- ‹‹ወንጀል ከወንጀል ላይ ሲነባበር ቀልብ ይታወርና ይሞታል።›› ብለዋል። የአስተባባዮችና የወንጀለኞች ሁኔታ ይህ ነው። የማስተባበልና የአመጽ ምክንያትም ይህ ነው።
በዚያ ታላቅ ቀን ከሚጠብቃቸው ቅጣት መሐል ከማስተባበል እና ከአመጽ ጋር ግንኙነት ያለውን ጠቀሰ፡-

﴿ كَلَّآ إِنَّهُمۡ عَن رَّبِّهِمۡ يَوۡمَئِذٖ لَّمَحۡجُوبُونَ ١٥ ﴾ المطففين: ١٥

‹‹(ከጥመታቸው) ይታቀቡ! እነርሱ በዚያን ቀን ከጌታቸው የተጋረዱ ናቸው።›› (አንቀጽ 15)
በዚህች ዓለም አምላክን እንዳያውቁ ሐጢአቶቻቸው ቀልቦቻቸውን ሸፈኑባቸው። በመጭው ዓለምም ለዚህ ጥፋት ተስማሚው ቅጣት የአላህን የተላቀ ገጽታ እንዳያዩ መታቀብ፣ ይህን ታላቅ ደስታ መነፈግ ነው። መንፈሳቸው ለስልሶና ጸድቶ በነርሱና በአላህ መካከል ያለው ግርዶ የተነሳላቸው ካልሆነ በቀር ሌሎች ሰዎች እርሱን የማየት እድል አያገኙም።
ከጌታቸው መጋረዳቸው ከቅጣቶች ሁሉ የከፋ ቅጣት፣ ጸጋዎችን ሁሉ ከመነፈግ የባሰ እቀባ ነው።

﴿ ثُمَّ إِنَّهُمۡ لَصَالُواْ ٱلۡجَحِيمِ ١٦ ﴾ المطففين: ١٦

‹‹ከዚያም ገሃነም ገቢዎች ናቸው።›› (አንቀጽ 16)
ወቀሳም ይከተላቸዋል። ወቀሳው ከገሐነም ይበልጥ ያሳምማል፡-

﴿ ثُمَّ يُقَالُ هَٰذَا ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ١٧ ﴾ المطففين: ١٧

‹‹ከዚያም “ይህ (ከሞት በፊት) ታስተ ባብሉት የነበረው (ቅጣት) ነው” ይባላሉ።›› (አንቀጽ 17)

* * *

አንቀጽ 18-28

﴿كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلۡأَبۡرَارِ لَفِي عِلِّيِّينَ ١٨ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا عِلِّيُّونَ ١٩ كِتَٰبٞ مَّرۡقُومٞ ٢٠ يَشۡهَدُهُ ٱلۡمُقَرَّبُونَ ٢١ إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٍ ٢٢ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ٢٣ تَعۡرِفُ فِي وُجُوهِهِمۡ نَضۡرَةَ ٱلنَّعِيمِ ٢٤ يُسۡقَوۡنَ مِن رَّحِيقٖ مَّخۡتُومٍ ٢٥ خِتَٰمُهُۥ مِسۡكٞۚ وَفِي ذَٰلِكَ فَلۡيَتَنَافَسِ ٱلۡمُتَنَٰفِسُونَ ٢٦ وَمِزَاجُهُۥ مِن تَسۡنِيمٍ ٢٧ عَيۡنٗا يَشۡرَبُ بِهَا ٱلۡمُقَرَّبُونَ ٢٨﴾ المطففين: ١٨ - ٢٨

‹‹በፍፁም፥ (ክሓዲያን ከአማኞች እኩል አይሆኑም።) የእውነተኞች መዝገብ "ዒሊይዩን" ውስጥ ነው። ስለ"ዒሊይዩን" ምን የምታውቀው ነገር አለ? (የአማኞች ጽድቅ ክንውን በክብር) የሰፈረበት መዝገብ ነው። (የአላህ) ባለሟሎች በቅርበት ይመለከቱታል። እውነተኞቹ አማኞች ድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው። (ከተንጣለሉ የክብር) አልጋዎች ላይ ሆነው (አላህንና የተዘጋጀላቸውን ወደር የለሽ ፀጋ) ይመለከታሉ። ከፊቶቻቸው ላይ የድሎት ነፀብራቅ ታስተውላለህ። የተጣራ እሽግ የወይን መጠጥ እንዲጠጡም ይደረጋል። ማሸጊያው ሚስክ ነው። የሚሽቀዳደሙ ሰዎች ለዚህ (ይህን ፀጋ ለመጉናፀፍ) ይሽቀዳደሙ። መበረግዣው ተስኒም ነው። (ተስኒም የአላህ ባለሟሎች) የሚጠጡባት ምንጭ ናት።›› (አንቀጽ 18-28)

* * *

በመቀጠል ሌላኛው ገጽ ይገለጻል። የበጎ ሰሪዎች ገጽ። ሁለት እውነታዎችን፣ ባህሪዎችንና ፍጻሜዎችን በንጽጽር ለማቅረብ።

‹ክልላ› ባለፈው ክፍል የተወሳውን አስተባባይነት ለማውገዝ እዚህም ላይ ተጠቅሷል። ከዚያም ስለበጎ ሰሪዎች በጽናት መተረኩን ይቀጥላል። የካህድያን መዝገብ ‹ሲጂን› ውስጥ መሆኑ የተወሳ ሲሆን የበጎ ሰሪዎች መዝገብ ደግሞ ‹ዒልይን› ውስጥ ነው። በጎ ሰሪዎች ሁሉንም አይነት መልካም ስራ የሚሰሩ ሲሆኑ፣ ወሰኖችን ሁሉ ከሚጥሱት አመጸኞች በተቃራኒ ጽንፍ ይገኛሉ። ‹ዒልይን› የሚለው ቃል ከፍታን ያመለክታል፡ ፡ ከዚህ በመነሳት ‹ሲጂን› የተሰኘው ውድቀትን እና ዝቅታን ማመልከቱን መረዳት ይቻላል።

ቀጥሎ አለማወቅን የሚያጎላውን እና ግዘፈትን የሚገልጸውን የተለመደ ጥያቄ ያቀርባል፡-

﴿ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا عِلِّيُّونَ ١٩ ﴾ المطففين: ١٩

‹‹ስለ“ዒሊይዩን” ምን የምታውቀው ነገር አለ?›› (አንቀጽ 19)

ከሰው ልጅ እውቀትና ግንዛቤ በላይ የሆነ ነገር ነው። የበጎ ሰሪዎችን መዝገብ ምንነት ወደ መግለጽ ይመለስና እንዲህ ይላል፡-

﴿ كِتَٰبٞ مَّرۡقُومٞ ٢٠ يَشۡهَدُهُ ٱلۡمُقَرَّبُونَ ٢١ ﴾ المطففين: ٢٠ - ٢١

‹‹(የአማኞች ጽድቅ ክንውን በክብር) የሰፈረበት መዝገብ ነው። (የአላህ) ባለሟሎች በቅርበት ይመለከቱታል።›› (አንቀጽ 20-21)

‹የታተመ› የሚለው ቃል ትርጉሙ በአንቀጹ ተወስቷል። እዚህ ላይ የአላህ ቅርብ ባለሟል የሆኑ መላእክት ይህን መዝገብ እንደሚመለከቱት ታክሎ ተገልጿል። አሠ፣በቅርበት ያዩታል። ከውስጡ የሰፈሩ በጎ ሰሪዎችና ባህሪያትም የሐሴቶቻቸው ምንጮች ይሆናሉ።

በመጠቀልም የዚህ የተከበረ መዝገብ ባለቤት የሆኑት በጎ ሰሪዎች በዚያ ታላቅ ቀን የሚታደሉትን ጸጋ ይዘክራል፡-

﴿ إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٍ ٢٢ ﴾ المطففين: ٢٢

‹‹እውነተኞቹ አማኞች ድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው።›› (አንቀጽ 22)

የአመጸኞች ማረፊያ ለሆነው ጀሃነም በንጽጽር የቀረበ ነው።[1]

﴿ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ٢٣ ﴾ المطففين: ٢٣

[1] በቃል አወቃቀር (ድምጸት) ደረጃ ሁለቱ ይመሳሰላሉ። የካህድያን ማረፊያ ‹ጀሂም›፣ የአማኞች ማረፊያ ‹ነዒም› (ተርጓሚው)

‹‹(ከተንጣለሉ የክብር) አልጋዎች ላይ ሆነው (አላህንና የተዘጋጀላቸውን ወደር የለሽ ፀጋ) ይመለከታሉ።›› (አንቀጽ 23)

በክብር ስፍራ ላይ ሆነው የሚሹትን ሳይቸገሩ ያያሉ። ያለ ድካም ይቃኛሉ። በዚህ ድሎት ውስጥ አካላዊም ስነ ልቦናዊም ደስታ ይጎናጸፋሉ። እናም የሐሴታቸውን ምልክት ሁሉም ሰዎች ያዩት ዘንድ ከገጽታቸው ላይ ይታያል። የድሎታቸው ብርሃን ከፊታቸው ላይ ይንጸባረቃል። ፦

﴿ تَعۡرِفُ فِي وُجُوهِهِمۡ نَضۡرَةَ ٱلنَّعِيمِ ٢٤ يُسۡقَوۡنَ مِن رَّحِيقٖ مَّخۡتُومٍ ٢٥ خِتَٰمُهُۥ مِسۡكٞ ﴾

‹‹ከፊቶቻቸው ላይ የድሎት ነፀብራቅ ታስተውላለህ። የተጣራ እሽግ የወይን መጠን እንዲጠጡም ይደረጋል። ማሸጊያው ሚስክ ነው። ›› (አንቀጽ 24-25)

‹ረሂቅ› ድፍርስ የሌለበት ንጹህ መጠጥ ማለት ነው። መታሸጉና ማሸጊያውም ሚስክ መሆኑ በእቃዎች የተሰናዳ፣ ይህም እቃ የታሸገ እንደሆነ ያመለክታል። ሊጠጣ ሲል ብቻ ይከፈታል። ይህ ገለጻ የእንክብካቤና የጥበቃ ድባብ ይፈጥራል። የመጠጡን ባህሪ ገልጾ ከመጨረሱ በፊት ተከታዩን መመሪያ ጣልቃ ያስገባል፦

﴿ وَفِي ذَٰلِكَ فَلۡيَتَنَافَسِ ٱلۡمُتَنَٰفِسُونَ ٢٦ ﴾ المطففين: ٢٦

‹‹ የሚሽቀዳደሙ ሰዎች ለዚህ (ይህን ፀጋ ለመጐናፀፍ) ይሽቀዳደሙ።›› (አንቀጽ 26)

ጥልቅ መልእክት ያለው መመሪያ ነው። በርካታ ነገሮችን ያመለክታል። ይህውም፦

‹መጡሬፎች የሚሽቀዳደሙት ርካሽ ለሆነ ዓለማዊ ጥቅም ሲሆን፣ እያንዳንዱ ሌላውን ለመቅደምና የበለጠውን ድርሻ ለማግኘት ይፈልጋል። ይህም በመሆኑ ጊዜያዊውን ዓለማዊ መደሰቻ ለማግኘት ወንጀል ይሰራል። ወሰን ያልፋል። ሐጢአት ይፈጽማል። በእርግጥ ይህ ርካሽና

ተወጋጅ ሽቀጥ ሊሸቀዳደሙበት የሚገባ አልነበረም። መሸቀዳደምስ የመጭውን ዓለም ጸጋና ክብር ለማግኘት፡-

﴿ وَفِي ذَٰلِكَ فَلۡيَتَنَافَسِ ٱلۡمُتَنَٰفِسُونَ ٢٦ ﴾ المطففين: ٢٦

‹‹የሚሸቀዳደሙ ሰዎች ለዚህ (ይህን ፀጋ ለመጐናፀፍ) ይሽቀዳደሙ።›› *(ሱንቀጽ 26)*

ሊሸቀዳደሙበት የሚገባ ዓላማ፣ ሊወዳደሩበት የሚገባ አድማስ፣ ሊበላለጡበት የሚያጓጓ ግብ ይህ ነው። ለመጭው ዓለም ጸጋ መሸቀዳደም- አንዳንድ የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ወገኖች እንደሚያስቡት- ምድርን ልማት አልባ የሚያደርግ አይደለም። ኢስላም ይህችን ዓለም የመጭው ዓለም ምርት መዝሪያ መስክ አድርጎ ይቆጥራታል። አላህን ከመፍራትና ከበጎነት ጋር ምድርን በማነጽና በማልማት የአምላክ ወኪልነትን ተግባር መወጣት የሙእሚን ትክክለኛ ተግባሩ ነው። ይህን ሲያደርግ ወደ አላህ ፊቱን ካዞረ ዓለማዊ ተግባሩ የሕልውናውን ዓላማ የሚያሳካ ዒባዳ ይሆንለታል።

* * *

ሱንቀጽ 29-36

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ أَجۡرَمُواْ كَانُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يَضۡحَكُونَ ٢٩ وَإِذَا مَرُّواْ بِهِمۡ يَتَغَامَزُونَ ٣٠ وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓاْ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِمُ ٱنقَلَبُواْ فَكِهِينَ ٣١ وَإِذَا رَأَوۡهُمۡ قَالُوٓاْ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ٣٢ وَمَآ أُرۡسِلُواْ عَلَيۡهِمۡ حَٰفِظِينَ ٣٣ فَٱلۡيَوۡمَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنَ ٱلۡكُفَّارِ يَضۡحَكُونَ ٣٤ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ٣٥ هَلۡ ثُوِّبَ ٱلۡكُفَّارُ مَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ٣٦ ﴾ المطففين: ٢٩ - ٣٦

‹‹እነዚያ አመፀኞች (በቅርቢቱ ዓለም ውስጥ) በአማኞች ይስቁ ነበር። (አማኞች) ባጠገባቸው ባለፉ ጊዜ በማፌዝ እርስ በርስ ይጠቃቀሱ ነበር። ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱት (በአማኞች በመቀለዳቸው በመርካት) በደስታ ተውጠው ነበር። (ምእመናንን) ባይዋቸው ጊዜ፦"እነኝህ ስህተት ውስጥ ናቸው" ይሉም ነበር። የነርሱን (ተግባር) ተቆጣጣሪዎች ሆነው አልተላኩም። ዛሬ (በዕለተ ትንሣዔ) አማኞች በከሓዲያን ይስቃሉ። (ከተንጣለሉ የክብር) አልጋዎች ላይ ሆነው (የከሓዲያንን ውድቀት) እየተመለከቱ። ከሓዲያን ለሥራቸው ተገቢውን ዋጋ አገኙን?››

(ሱንቀጽ 29-36)

* * *

አማኞች ከካህድያን በኩል በምድር ላይ የሚያገኛቸውን ስላቅና ትእቢት፣ ስም ማጥፋት እና ሌሎች መታወኮች ለማውጋት ስለመጭው ዓለም ድሎታቸው ያቀረበውን ረኸርም ገለጻ እንደመደላድል ተጠቀመበት።

ስለ መጭው ዓለም የአማኞች ድሎት ያቀረበውን ረኸርም ገለጻ እንደ መግቢያ ተጠቅሞ ከካህድያን የሚያገኛቸውን የስላቅ፣ የትእቢት፣ ስም የማጥፋትና ሌሎች ሁከቶች ተረከ።

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ أَجۡرَمُواْ كَانُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يَضۡحَكُونَ ٢٩ ﴾ المطففين: ٢٩

‹‹እነዚያ አመፀኞች (በቅርቢቱ ዓለም ውስጥ) በአማኞች ይስቁ ነበር።››
(ሱንቀጽ 29)

ነገሩ ‹‹በነበር›› ተተረከ። የፈጣኗንና ጠፊዋን ዓለም ገጾች ቁርአናዊው ገለጻ አጠፈ። አሁን ታዳሚዎች በመጭው ዓለም ውስጥ ናቸው። ለአማኞች የተዘጋጀውን ድሎት እያዩ። እናም በምድረ ዓለም የሆነውን ያስታውሳቸዋል። በአማኞች ይስቁ፣ በበጎ ሰዎች ይሳለቁ ነበር። አንድም ድሃና ከዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍል የመጡ ወይም ደግሞ የሚፈጸምባቸውን ግፍና መከራ ለመመከት አቅም የሚያንሳቸው በመሆናቸው፣ ወይም የባለጌዎችን ድርጊት በዝምታ እና በትእግስት ማሳለፍን በመምረጣቸው ያፌዙባቸው ነበር። የአማኞች ትእግስትና ‹‹ድክመት›› የካህድያንን የመሳለቅ ስሜት ያቀጣጥላል።

﴿ وَإِذَا مَرُّواْ بِهِمۡ يَتَغَامَزُونَ ٣٠ ﴾ المطففين: ٣٠

‹‹(አማኞች) ባጠገባቸው ባለፉ ጊዜ በማፈዝ እርስ በርስ ይጠቃቀሱ ነበር።›› (አንቀጽ 30)

በዓይናቸው ይጠቃቀሳሉ። ወይም በእጆቻቸው ይጠቋቆማሉ። አለያም እርስ በርስ የሚግባቡበትን የአካል እንቅስቃሴ ተጠቅመው በአማኞች ይሳለቃሉ።

ወራዳና ትንሽ ነፍሳቸውን በአማኞች በመሳለቅ እና እነርሱን በማወክ ካረኩ በኋላ በደስታ ስሜት ተሞልተው፣ በፈጸሟት ርካሽና ትንሽ ተንኮል ረክተው ወደቤተሰቦቻቸው ይመለሳሉ።

﴿ وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓاْ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِمُ ٱنقَلَبُواْ فَكِهِينَ ٣١ ﴾ المطففين: ٣١

‹‹ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚመለሱት (በአማኙ በመቀለዳቸው በመርካት) በደስታ ተውጠው ነበር።›› (አንቀጽ 31)

የሚቀጥለው ድርጊታቸው ደግሞ ይበልጥ ይገርማል፡-

﴿ وَإِذَا رَأَوۡهُمۡ قَالُوٓاْ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ٣٢ ﴾ المطففين: ٣٢

‹‹(ምእመናንን) ባይዋቸው ጊዜ፦ “እነኝህ ስህተት ውስጥ ናቸው” ይሉም ነበር።›› (አንቀጽ 32)

እነዚህ ካህድያንና ወንጀለኞች ስለመቀናትና ጥመት ከመናገራቸው፣ አማኞችንም ሲያዩ ወራዳ በሆነ መልኩ እየተጠቋቆሙ ‹‹እነዚህ ጠማሞች ናቸው።›› ከማለታቸው የበለጠ የሚያስገርም ነገር የለም።

ቁርአን በአማኞች ላይ የተሰነዘረውን ይህን ክስ ለመከላከል ወይም ቅጥፈትነቱን ለማጋለጥ አይሞክርም። ምክንያቱም ምላሽ የማያስፈልገው ከንቱ ንግግር ነውና። ይልቁንም በሰዎቹ እንዲህ ሲል በጣሙን ይሳለቃል፦

﴿ وَمَآ أُرۡسِلُواْ عَلَيۡهِمۡ حَٰفِظِينَ ٣٣ ﴾ المطففين: ٣٣

‹‹የነርሱን (ተግባር) ተቆጣጣሪዎች ሆነው አልተላኩም።›› (አንቀጽ 33)

አማኞችን እንዲከታተሉ፣ እንቅስቃሴያቸውን እንዲጠባበቁ፣ ድርጊቶቻቸውን እንዲመዘኑ አልተወከለም። ታድያ ይህን አባባል ከየት አመነጨት?

ካህድያን በምድረ ዓለም የነበሩበትን ሁኔታ መተረኩን በዚህ ስላቅ ይቋጫል። ትእይንቱንም እዚህ ላይ ያቆማል። መጋረጃውን ዘግቶ አማኞች ‹‹አሁን›› የሚገኙበትን ሐሴት ያስቃኛል፦

﴿ فَٱلۡيَوۡمَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنَ ٱلۡكُفَّارِ يَضۡحَكُونَ ٣٤ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ٣٥ ﴾

‹‹ዛሬ (በዕለተ ትንሣዔ) አማኞች በከሓዲያን ይሰቃሉ። (ከተንጣለሉ የክብር) አልጋዎች ላይ ሆነው (የከሓዲያንን ውድቀት) እየተመለከቱ።›› (አንቀጽ 34-35)

‹‹ዛሬ›› ካህድያን ከአምላካቸው ተጋርደዋል። ‹‹ዛሬ›› አማኞች በዘልዓለማዊ ድሎት ውስጥ በክበሩ አልጋዎች ላይ ሰፍረው ያሻቸውን በነጻነት በማየት ላይ ናቸው። ‹‹ዛሬ›› አማኞች በካህድያት ይስቃሉ። ቁርአን የስላቅ ድምጸቱን ይበልጥ አጉኖ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፦

﴿ هَلۡ ثُوِّبَ ٱلۡكُفَّارُ مَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ٣٦ ﴾ المطففين: ٣٦

‹‹ክሓዲያን ለሥራቸው ተገቢውን ዋጋ አገኙን?›› (አንቀጽ 36)

አዎ፣ ተመነዱን?፣ የስራቸውን ዋጋ አገኙን?፣ በእርግጥ ያገኙት የተለመደው ዓይነት (ምንዳ) (ሰዋብ) አይደለም። ምክንያቱም ‹‹ዛሬ›› ከጀሃነም ውስጥ ናቸው። ስለዚህም ምንዳቸው ይህ ቅጣት ነው። በዚህ ቦታ ላይ ‹ሰዋብ› የሚለውን ቃል መጠቀሙ የስላቅ የመጨረሻ ደረጃ ነው።

* * *

በመካው ዘመን የነበሩ ጥቂት ሙስሊሞች ከቁረይሾች ጥልቅና ብርቱ አሻራ የሚያሳርፍ ግፍና ጭካኔ ያስተናግዱ ነበር። ግና አምላካቸው ያለረዳት አልተዋቸውም። ማጽናናቱን፣ ማበርታቱን አልነፈጋቸውም። ከጣኦታውያን በሚደርስባቸው ግፍ የተሰማቸውን ሕመም እንዲህ በዝርዝር መተረኩ ብቻ የተሰበረ ቀልባቸውን ለመጠገን በቂ ነው። ሕመማቸውን የገለጸው አምላካቸው ቀልቦቻቸውን ያያል። ሕመሞቻቸውን ይረዳል። እነዲሁ ሜዳ ላይ አይተዋቸውም። ይህ ብቻ ለሙእሚን ቀልብ በቂው ነው። ሕመሙን ያሸርለታል። ቁስሉን ያክምለታል። ስብራቱን ይጠግንለታል።

ካህድያን አማኞችን እንዴት እንደሚሳለቁባቸው፣ እንዴት እንደሚያውኳቸው አምላካቸው ያያል። አይቶም በቁርአኑ ውስጥ አስፍሮታል። ስለዚህም እንግልታቸው ከርሱ ዘንደ ክብደት እና ግምት ተሰጥቶታል ማለት ነው። ለነርሱ ይህ ብቻ በቂ ነው። ቀልቦቻቸው የቱን

ያህል ቢቆስሉ፣ ሕመሙም ቢሰማቸው ይህን እውነታ መረዳታቸው ብቻ ለነርሱ በቂ ነው።

ከዚህ በላይ ደግሞ እነዚህ የቆሰሉ የሙእሚን ቀልቦች ጀነት ውስጥ ከአምላካቸው ዘንድ የሚጠብቃቸውን ጸጋ፣ በላይኛው ዓለም የተሰናዳላቸውን ክብር ያያሉ። በሌላ በኩል ጠላቶቻቸው በላይኛው ዓለም የሚጠብቃቸውን ውርደት፣ የጀሃነም ስቃይና ውድቀት ይመለከታሉ። ይህ ሁሉ ተዘርዝሮ እና ተብራርቶ ቀርቦላቸዋል። ይህ ሁሉ ለነርሱ ተጨባጭና ጥልቅ ሐሴትን ያጎናጽፋል።

በካህድያን የተለያዩ ወራዳ ስልቶች ይቀጡና ይሰቃዩ ለነበሩ አማኞች ከአምላክ ይወርድላቸው የነበረው መልዕክት የነርሱ ፍጻሜ ጀነት፣ የጠላቶቻቸው ደግሞ ጀሀነም መሆኑን ማብሰር ብቻ እንደነበር ማጤን ያስፈልጋል። በአንጻሩ ምድራዊ ድልና ስኬት በመካው የቁርአን ዘመን መጽናኛ እና ማበረታቻ ሆኖ አልቀረበም።

ቁርአን ቀልቦችን ለታላቅ ዓላማ ያዘጋጃቸው ነበር። እነዚህ ቀልቦች ያላቸውን ሁሉ እየሰጡና መከራን ሁሉ እየተሸከሙ በምላሹ ኢምንት ነገር የማይሹ፣ መጭውን ዓለም ብቻ የሚጠብቁ፣ የአላህን ፍቅር ብቻ ተስፋ የሚያደርጉ ፍጹም ጽኑ፣ ብርቱና ንጹህ እንዲሆኑ ይሻ ነበር። እነዚህ ቀልቦች እውን ሲሆኑና ሐላፊነታቸውን በሐቅ እየተወጡ መሆኑን ሲያውቅ ምድራዊ ድል ለገሳቸው። የድሉን ፍሬም በአደራ አስረከባቸው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ✓ ቁርአን አልሙጥፊፊንን የገለጸበትን ባህሪና በነርሱ የመደነቁን እውነታ አብራራ
- ✓ ቁርአን ይህን ክስተት መካ ውስጥ ለመቃኘት የተገደደበትን ምክንያት ዘርዝር
- ✓ ቁርአን የካህድያንን ባህሪ እና ፍጻሜ የገለጸበትን ሁኔታ አብራራ

- ✓ አላህ በጎ ሰሪዎችን እና ምንዳቸውን፣ አገራቸውን የገለጸበትን ሁኔታ አብራራ
- ✓ በጎ ሰሪዎች ከካህድያን በዚህች ዓለም የሚደርስባቸውን ሁከት ግለጽ
- ✓ የሁለቱንም ወገኖች ፍጻሜ ግለጽ
- ✓ አላህ በነዚህ አናቅጽ አማካይነት ሁለቱን ወገኖች በንጽጽር ማቅረቡን በተመለከተ የተሰማህን አካፍል።

* * *

አል ኢንሺቃቅ

አንቀጽ 1-15

﴿ إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنشَقَّتۡ ١ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ ٣ وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ٤ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٥ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦ فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ٧ فَسَوۡفَ يُحَاسَبُ حِسَابٗا يَسِيرٗا ٨ وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورٗا ٩ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهۡرِهِۦ ١٠ فَسَوۡفَ يَدۡعُواْ ثُبُورٗا ١١ وَيَصۡلَىٰ سَعِيرًا ١٢ إِنَّهُۥ كَانَ فِيٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورًا ١٣ إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ١٤ بَلَىٰٓۚ إِنَّ رَبَّهُۥ كَانَ بِهِۦ بَصِيرَۢا ١٥ ﴾ الانشقاق: ١ - ١٥

‹‹ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤ ለጌታዋ ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤ ምድርም በተለጠጠች ጊዜ፤ ከውስጧ ያሉትን ነገሮች ባራገፈችና ባዶ በሆነች ጊዜ፥ ለጌታዋም ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤ (በዚህ ወቅት የሰው ልጅ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ይገጥሙታል)። የሰው ልጅ ሆይ! ወደጌታህ (ጌታህን በሞት እስክተገናኘው ድረስ) ትለፋለህ፥ ትደክማለህ፤ (በመጨረሻም) ትገናኝዋለህ፤ (የልፋትህን ዋጋ ይሰጥሃል። መልካም ከሆነ ዕድለኛ ነህ፤ ክፉ ከሆነ ደግሞ ዕጣ ፋንታህ የከፋ ሆኗል)። (የሥራ) መዝገቡን በቀኝ እጁ የተሰጠ፥ ቀላል ምርመራ ይመረመራል። (አላህ በለገሠው ዐጋ ረክቶም) ወደ ቤተሰቦቹ በደስታ ይመለሳል። (የሥራ) መዝገቡን ከበስተኋላው በኩል የተሰጠ፥ (ሞትን በመመኘት) በቁጭት ይጮኻል። ከጋመች እሳት ውስጥ ይገባልም። (በዚህች ዓለም) ከቤተሰቦቹ መሀል ፈንጠዚያ ውስጥ (ዝንጉና ስለመጭው ሕይወት ቅንጣት የማያስብ) ነበር። በእርግጥም (ወደ ጌታው) እንደማይመለስ፥ (ከሞት በኋላ ዳግም እንደማይቀሰቀስ) ያስብ ነበር፤ (ለዚህም ነው ለክህደት የተዳረገው)። አዎ፣ (ከሞት በኋላ ዳግም ሕይወትን ይለግሰል፤ የሥራውን ዋጋም ይሰጣል።) ጌታው እርሱን (እያንዳንዱን ድርጊቱን) ዐዋቂ ነው። ›› *(አንቀጽ 1-15)*

* * *

አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ የዩኒቨርሱ ስርዓት የሚፋለስበትን ትእይንት በአንቀጾቹ በተተረከው መልኩ መግለጽ
- ✓ አላህ በዚህ ምእራፍ የሰውን ልጅ ያናገረበትን አጀንዳ መግለጽ

* * *

ምእራፉ ወደፊት ከሚከሰቱ የዩኒቨርሱ ስርዓት መፋለሶች መካከል የተወሰኑትን ይዘክራል። ግና የአንቀጾቹ ድምጸት የመፍራትንና የመታዘዝን ድባብ የሚፈጥር ነው። ሰማይና ምድር አምላካቸውን ያለ ተቃውሞ በፍርሃት ሲታዘዙ፣ ለፈቃዱ ያለ ማንገራገር ሲያድሩ እናነባለን፡-

﴿ إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنشَقَّتۡ ١ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ ٣ وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ٤ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٥ ﴾ الانشقاق: ١ - ٥

‹‹ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤ ለጌታዋ ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤ ምድርም በተለጠጠች ጊዜ፤ ከውስጧ ያሉትን ነገሮች ባራገፈችና ባዶ በሆነች ጊዜ፥ ለጌታዋም ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤ (በዚህ ወቅት የሰው ልጅ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ይገጥሙታል)።›› (አንቀጽ 1-5)

የአምላክን ልቅናና ልእልና፣ የፍጡራንን ታዛዥነት ስሜት በሚያሰፍን መልኩ የቀረበ መግቢያ፤ ‹‹የሰውን ልጅ›› ለማናገር፣ በልቦናውም ላይ አምላኩን የመፍራትን ስሜት ለማስረጽ፣ ፍጻሜውን ለማስታወስ ታልሞ የተዋቀረ መነሻ ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦ فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ٧ فَسَوۡفَ يُحَاسَبُ حِسَابٗا يَسِيرٗا ٨ وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورٗا ٩ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهۡرِهِۦ ١٠ فَسَوۡفَ يَدۡعُواْ ثُبُورٗا ١١ وَيَصۡلَىٰ سَعِيرًا ١٢ ﴾ الانشقاق: ٦ - ١٢

‹‹የሰው ልጅ ሆይ! ወደጌታህ (ጌታህን በሞት እስክተገናኘው ድረስ) ትለፋለህ፥ ትደክማለህ፤ (በመጨረሻም) ትገናኘዋለህ፤ (የልፋትህን ዋጋ ይሰጥሃል። መልካም ከሆነ ፅድለኛ ነህ፤ ክፉ ከሆነ ደግሞ ዕጣ ፋንታህ የከፋ ሆኗል)። (የሥራ) መዝገቡን በቀኝ እጁ የተሰጠ፥ ቀላል ምርመራ ይመረመራል። (አላህ በለገሠው ዐጋ ረክቶም) ወደ ቤተሰቦቹ በደስታ ይመለሳል። (የሥራ) መዝገቡን ከበስተኋላው በኩል የተሰጠ፥ (ሞትን በመመኘት) በቁጭት ይጮኻል። ከጋመች እሳት ውስጥ ይገባልም።›› *(አንቀጽ 6-12)*

* * *

የሰማይን መሰንጠቅ የሚመለከት መልእክት ከአሁን ቀደም ተላልፏል። እዚህ ላይ አዲስ የተወሳው አምላኳን ያለ ተቃውሞ መታዘዟ ነው።

﴿ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٢ ﴾ الانشقاق: ٢

‹‹ለጌታዋ ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤›› (አንቀጽ 2)

የጌታውን ትእዛዝ መስማቷን፣ እንድትቀደድም ባዘዛት ጊዜ መተዘዟንና ለፈቃዱ ማደሯን የሚያመለክት ነው።

﴿ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ ٣ ﴾ الانشقاق: ٣

‹‹ምድርም በተለጠጠች ጊዜ፤›› (አንቀጽ 3)

‹‹መለጠጧ›› ይገዛት በነበረው የዩኒቨርሱ ስርዓት ላይ ከሚደርሰው መናጋት የተነሳ መጠኗ ከወትሮው በተለየ መልኩ መስፋቱን ለማመልከት ነው።

﴿ وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ٤ ﴾ الانشقاق: ٤

‹‹ከውስጧ ያሉትን ነገሮች ባራገፈችና ባዶ በሆነች ጊዜ፥›› (አንቀጽ 4)

ምድርን ሕያውነት የሚያላብስ ገለጻ ነው። ከውስጥ ያሉ ነገሮችን እያወጣች ስትጥል፣ ስታራግፍና ስትወረውር ይስልልናል።

ከውስጧ ብዙ ነገሮች አሉ። ርዝመቱን አላህ እንጅ ሌላ ማንም በማያውቀው ዘመን ውስጥ ወደ ሆዷ የከተተቻቸው እጅግ በርካታ እንስሳት፣ በውስጧ ያዘለቻቸው ማእድናት፣ ውሃዎችንና አላህ ብቻ እንጅ ማንም የማያውቃቸው ሚስጥራት ይጠቀሳሉ። ይህንን ሸክሟን ተሸክማ ከትውልድ ትውልድ፣ ከዘመን ዘመን ስትሸጋገር ኖራለች። በዚህች ቀን ግን ይህን ሁሉ ታራግፋለች። ወደ ውጭ ተፍታም ባዶ ትሆናለች።

﴿ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٥ ﴾ الانشقاق: ٥

ለጌታዋም ትእዛዝ ባደረች ጊዜ፥ ማደርም ይገባታል፤ (በዚህ ወቅት የሰው ልጅ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ይገጥሙታል)።›› (አንቀጽ 5)

ሰማይ የአምላኳን ትእዛዝ እንደሰማችው ምድርም ትሰማለች። ለፈቃዱ ታድራለች። ትእዛዙን ትፈጽማለች። ይህን ማድረግ እንደሚገባትም ታውቃለች።

በዚህ ዓይነቱ የታዛዥነትና የፍርሃት ድባብ መሐል ተከታዩ ጥሪ ተላለፈ፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦ ﴾ الانشقاق: ٦

‹‹የሰው ልጅ ሆይ! ወደጌታህ (ጌታህን በሞት እስክተገናኘው ድረስ) ትለፋለህ፥ ትደክማለህ፤ (በመጨረሻም) ትገናኘዋለህ፤ (የልፋትህን ዋጋ ይሰጥሃል። መልካም ከሆነ ዕድለኛ ነህ፤ ክፉ ከሆነ ደግሞ ዕጣ ፋንታህ የከፋ ሆኗል)።›› (አንቀጽ 6)

የሰው ልጅ ሆይ፣ በምድር ላይ የምታሳልፈውን የሕይወት ጉዞ በልፋት፣ በትግልና በድካም ታሳልፋለህ። በመጨረሻም ወደ ጌታህ ትደርሳለህ። ከትግልና ከድካም በኋላ መመለሻ ወደርሱ ነው። የሰው ልጅ ሆይ፣ በምድር ላይ ረፍት ፈጽሞ አታገኝም። ረፍት የሚገኘው ከወዲያኛው ዓለም ነው። እርሱንም የሚያገኘው አምላኩን የታዘዘና ለፈቃዱ ያደረ ብቻ ነው።

በምድር ላይ ሁሉም ሰው ያለ ልዩነት ይለፋል፣ ይደክማል። ከጌታቸው ዘንድ ሲደርሱ ግን ፍጻሜያቸው ይለያያል።

በመቀጠል በዚህች ዓለም ጉዞ የሚኳትኑ የሰው ልጆች ከብዙ ድካም በኋላ ጉዟቸውን ሲያጠናቅቁ የሚያጋጥማቸውን ነገር ይዘክራል፡-

﴿ فَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ۝٧ فَسَوْفَ يُحَاسَبُ حِسَابًا يَسِيرًا ۝٨ وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ مَسْرُورًا ۝٩ ﴾ الانشقاق: ٧ - ٩

‹‹(የሥራ) መዝገቡን በቀኝ እጁ የተሰጠ፥ ቀላል ምርመራ ይመረመራል። (አላህ በለገሠው ፀጋ ረክቶም) ወደ ቤተሰቦቹ በደስታ ይመለሳል።›› (አንቀጽ 7-9)

መዝገቡን በቀኝ እጁ የሚቀበለው ያመነና በጎ የሰራ፣ አላህም ስራውን የወደደለት፣ መዳንንም የጻፈለት ስኬታማና ደስተኛ ሰው ነው። ቀላል ምርመራ ይመረመራል። ከምር የሆነ መተሳሰብ አያጋጥመውም። ከአላህ መልእክተኛ የተላለፈ አንድ ሐዲስ የቀላልን ምርመራን ትርጉም የብራራል።

አኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ‹‹የምር የሆነ ምርመር ያጋጠመው ሰው ለቅጣት ይዳረጋል።› አሉ። እኔም፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ አላህ ‹‹በእርግጥ ቀላል ምርመራን ይመረመራል›› አላለምን? ስል ጠየቅኳቸው። ‹‹ይህማ ምርመራ አይደለም። የስራ

መዝገብ መቅረቡን የሚያመለክት ነው። የቂያማ ቀን የተመረመረ ሰው መቀጣቱ አይቀሬ ነው።›› በማለት መለሱልኝ።

አኢሻ እንዲህ ስትል አስተላልፋለች፡- ‹የአላህ መልእክተኛ በአንድ ሶላታቸው፡- ‹‹አላህ ሆይ፣ ቀላል ምርመራ መርምረኝ።›› ሲሉ ሰማኋቸው። ሶላታቸውን ሲያጠናቅቁ ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ቀላል ምርመራ ምንድን ነው?›› በማለት ጠየቅኳቸው። ‹መዝገቡ ቀርቦ ይታያል። ያለ መተሳሰብም እንዲያልፍ ይደረጋል። አኢሻ ሆይ፣ የዚያን ቀን የተመረመረ ጠፋ።›› አሉ።

መዝገቡን በቀኝ እጁ የተቀበለ ሰው የሚደረግለት ቀላል ምርመራ ይህ ነው። ከዚያም ይድናል። ቀድመውት ጀነት ወደገቡ ቤተሰቦቹም ተደሳች ሆኖ ይመለሳል። ከዚህ በተቃራኒ አቅጣጫ በክፉ ስራው የሚቀጣውን፣ መዝገቡንም እየጠላው የሚቀበለውን ወገን እናገኛለን፡-

﴿ وَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهْرِهِۦ ﴿١٠﴾ فَسَوْفَ يَدْعُوا۟ ثُبُورًا ﴿١١﴾ وَيَصْلَىٰ سَعِيرًا ﴿١٢﴾ ﴾

‹‹(የሥራ) መዝገቡን ከበስተኋላው በኩል የተሰጠ፣ (ሞትን በመመኘት) በቁጭት ይጮኻል። ከጋመች እሳት ውስጥም ይገባል።›› (አንቀጽ 10-12)

መዝገብን ከጀርባ በኩል መቀበል ከአሁን በፊት በቁርአን ያልተነገረ አዲስ ገለጻ ነው። በግራ እጅ የሚቀበለው ሰው ከጀርባው በኩል ሊቀበል ይችላል። ሰውየው የስራ መዝገቡን ፊት ለፊት ለመቀበል ያልወደደና ያፈረ ይመስላል። የምድር ላይ ሕይወቱን በልፋት ያሳለፈ፣ ወደ ጌታው የሚያደርሰውን መንገድ በጥፋትና በሐጢአት ሲኳትን የኖረ ተስፋ ቢስ ሚስኪን ፍጻሜውን ያውቃል። መመለሻውን ይጋፈጣል። በቁጭት ይቃጠላል። ከአደጋ ይታደገው ዘንድም ጥፋትን ይጠራል። ሌላ ጠባቂ አጥቶ ጥፋትን እንዲያድነው ሲማጸን፣ የመጨረሻ ምኞቱ ጥፋት ሲሆን አስቡት። በመጨረሻም አይቀሬ ፍጻሜውን ይጋፈጣል። ***ከጋመች እሳት ውስጥም ይገባል***።

ጥፋት ከቅጣት ይታደገው ዘንድ የሚማጸነው እድለ ቢስ ፍጻሜው ይህ ይሆናል። በዚህ ተስፋ አስቆራጭ ትእይንት መሐል ይህ እድለ ቢስ ለዚህ መከራ እንዲዳረግ ምክንያት የሆነውን ያለፈ ታሪክ ይቃኛል፦

በምድር ላይ፦ ***«ብቤተሰቦቹ መሐል ተደሳች ነበር።»***

إِنَّهُۥ كَانَ فِىٓ أَهْلِهِۦ مَسْرُورًا ﴿١٣﴾

ከዚያች ቅጽበት በኋላ ያለውን ዓለም ረስቶ፣ የመጭውን ዓለም ሁኔታ ዘንግቶ። እርሱን ከስሌቱ ውስጥ ሳያስገባ፣ ስንቅም ሳያዘጋጅላት።

إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ﴿١٤﴾

«ወደ አላህ እንደማይመለስ አሰቦ ኖሯል።»

በመጨረሻ በጉዞው ማጠናቀቂያ ወደ አምላኩ እንደሚመለስ አስቦ ቢሆን ኖሮ ጥቂት ስንቅ ባዘጋጀ፣ ለምርመራውም አንዳች በጎ ስራ ባስቀመጠ ነበር።

﴿ بَلَىٰٓ إِنَّ رَبَّهُۥ كَانَ بِهِۦ بَصِيرًا ﴿١٥﴾ ﴾

«አዎ፣ (ከሞት በኋላ ዳግም ሕይወትን ይለገሳል፤ የሥራውን ዋጋም ይሰጣል።) ጌታው እርሱን (እያንዳንዱን ድርጊቱን) ዐዋቂ ነው።» (ሱንቀጽ 15)

እንደማይመለስ ገመተ። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ሆኖ አገኘው። ጌታው ስለርሱ ሁሉንም ነገር ጠንቅቆ ያውቃል። እንቅስቃሴዎቹንና እርምጃዎቹን ያውቃል። በጉዞው መጨረሻ ላይ በአላህ እውቀት ስር ወዳለው ፍጻሜው ባመራ ጊዜም የነበረው ሁኔታ ይህን ይመስላል።

* * *

አንቀጽ 16-25

﴿ فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلشَّفَقِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ وَمَا وَسَقَ ١٧ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا ٱتَّسَقَ ١٨ لَتَرۡكَبُنَّ طَبَقًا عَن طَبَقٖ ١٩ فَمَا لَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٢٠ وَإِذَا قُرِئَ عَلَيۡهِمُ ٱلۡقُرۡءَانُ لَا يَسۡجُدُونَ ۩ ٢١ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُكَذِّبُونَ ٢٢ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا يُوعُونَ ٢٣ فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ٢٤ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ مَمۡنُونِۭ ٢٥ ﴾

በ“ሸፈቅ” እምላለሁ! በሌሊትም እምላለሁ፤ (በወስጡ) በሰበሰበውም። በጨረቃም እምላለሁ፤ ምሉዕ በሆነች ጊዜ። ከአንድ እርከን ወደ ሌላ እርከን ትሸጋገራላችሁ። (አጋሪዎች) ለምን (በአላህ) አያምኑም? በነርሱ ላይ ቁርአን በሚነበብላቸው ወቅት (ለምን) አይሰግዱም? በእርግጥም እነዚያ የካዱ ሰዎች (በትንሣዔ) ያስተባብላሉ፤ (ለዚህም ነው የአላህን ትእዛዝ የማይፈጽሙት)። አላህ ልቦቻቸውን ውስጥ የቋጠሩትን (ሚስጥር) ዐዋቂ ነው። (ሙሐመድ ሆይ!) አሳማሚ በሆነ ቅጣት አርዳቸው። በአንጻሩ እነዚያ ያመኑትና መልካም የሠሩት የማይቋረጥ ምንዳ አላቸው።›› (አንቀጽ 16-25)

* * *

ትልቅና ጥልቅ ተጽእኖ ካዘለው ከዚህ ቅኝት በኋላ የሚኖሩበትን ዩኒቨርስ ከፊል ገጽታ ያስቃኛቸዋል። ዝንጉዎች በመሆናቸው ፍጥረተ ዓለሙ የሚመራበት ስርዓት የሚያመማለክተውን ጥልቅ እውነታ ዘንግተዋል።

﴿ فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلشَّفَقِ ١٦ وَٱلَّيۡلِ وَمَا وَسَقَ ١٧ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا ٱتَّسَقَ ١٨ ﴾

‹‹በ“ሸፈቅ” እምላለሁ! በሌሊትም እምላለሁ፤ (በወስጡ) በሰበሰበውም። በጨረቃም እምላለሁ፤ ምሉዕ በሆነች ጊዜ።›› (አንቀጽ 16-18)

አላህ የማለባቸው እነዚህ የፍጥረተ ዓለሙ ከፊል ገጽታዎች የሰከነ ትእይንትና አስፈሪ ግርማን የተላበሱ ናቸው። ወጋገን ጸሐይ ከጠለቀች በኋላ ያለው የሰከነና አስፈሪ ጊዜ ነው። ከጸሐይ መጥለቅ በኋላ የሰው ልጅ ስነ ልቦና ጥልቅ ከሆነ ቁዘማ ውስጥ ይሰጥማል።

‹‹ሌሊቱ እና የሰበሰበው ሁሉ›› -የተሸከመው ሁሉ- አንድም ሳይቀር፡፡

ጨረቃም ሙሉ በምትሆንበት ሌሊት ማራኪና የሰከነ ብርሃኗን ቁልቁል ወደ መሬት ስትረጭ ልዩ የሐሴት ስሜት ትፈጥራለች፡፡

እነዚህን የተፈጥሮ ከፊል ክስተቶች ቁርአን በፍጥነት ይቃኛቸዋል፡፡ ትኩረት የማይቸራቸውን የሰው ልጅ ቀልብም በነርሱ አማካይነት ያናግራል፡፡ ሕሊናን ለማንቃትም በመሐላው ያወሳቸዋል፡፡

﴿لَتَرۡكَبُنَّ طَبَقًا عَن طَبَقٖ ١٩﴾ الانشقاق: ١٩

‹‹ከአንድ እርከን ወደ ሌላ እርከን ትሸጋገራላችሁ።›› (አንቀጽ 19)

የተሰመረላችሁን ተፈጥሯዊ መስመር ተከትላችሁ ከአንድ ሁኔታ ወደ ሌላ ትሸጋገራላችሁ፡፡ የተለያዩ የሕይወት እርከኖችን ታልፋላችሁ፡፡ እያንዳንዱ እርከን ወደ ሌላው ያሸጋግራችኋል፡፡ በቅብብሎሹ መጨረሻ ጌታችሁን ትገናኛላችሁ፡፡ በዚህ ቅኝት ድባብ ውስጥ በነዚያ በማያምኑ ሰዎች ሁኔታ የመገረምን ድምጸት ያዘለ መልእክት ይከተላል፡-

﴿فَمَا لَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٢٠ وَإِذَا قُرِئَ عَلَيۡهِمُ ٱلۡقُرۡءَانُ لَا يَسۡجُدُونَ ٢١﴾

‹‹(አጋሪዎች) ለምን (በአላህ) አያምኑም? በነርሱ ላይ ቁርአን በሚነበብላቸው ወቅት (ለምን) አይሰግዱም?›› (አንቀጽ 20-21)

እውነትም የማያምኑት ምን ነክቷቸው ነው? ወደ እምነት የሚያመላክቱ ሁነቶች የሰውን ልጅ ቀልብ በሁሉም አቅጣጫዎች ያሳድዳሉ፡፡፡ የትም ቢሆን አይተውትም፡፡ በብዛት ወደርሱ ይጎርፋሉ፡፡ በእውነት ሚዛን ብዙ፣ ጥልቅ፣ ጠንካራና ከባድ ከመሆናቸው የተነሳ የሰውን ልጅ በሁሉም አቅጣጫዎች ከበውታል፡፡ መፈናፈኛና ማምለጫ አሳጥተውታል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ለምን አያምኑም? ቁርአን ካነበቡስ ለምን አይሰግዱም?

ለተፈጥሯቸው ቅርብና ቀላል በሆነ መንገድ ያናግራቸዋል፡፡ በነፍሶቻቸውም በአድማሱም ውስጥ በተረጨት እምነትን ጠቋሚ በሆኑ

ክስተቶች ቀልቦቻቸውን ያንኳኳል። የዩኒቨርሱን ፈጣሪ የመፍራት እና እርሱን የመታዘዝ ስሜቶቻቸውን ሁሉ ይቀሰቅሳል።

የአላህ ፍርሃትና ታዛዥነት አብይ መገለጫ ለርሱ መስገድ ነው።

በእርግጥም አለማመናቸው ይገርማል። ይህን እዚህ ላይ ያቆምና የካህድያንን ድርጊትና ባህሪ ወደ ማብራራቱ ይገባል።

﴿ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُكَذِّبُونَ ﴿٢٢﴾ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا يُوعُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾

‹‹በእርግጥም እነዚያ የካዱ ሰዎች (በትንሣዔ) ያስተባብላሉ፤ (ለዚህም ነው የአላህን ትእዛዝ የማይፈጽሙት)። አላህ በልቦቻቸው ውስጥ የቋጠሩትን (ሚስጥር) ዐዋቂ ነው።›› (አንቀጽ 22-23)

ማስተባበል ባህሪያቸው ነው። በቀልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ክፋት፣ ተንኮል እና ለማስተባበል ያበቃቸውን ግፊት አላህ ጠንቅቆ ያውቃል።

ቀጥሎ ስለነርሱ ማውጋቱን ትቶ ፊቱን ወደ አላህ መልእክተኛ በማዞር እንዲህ ይላቸዋል፦

﴿ فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ﴿٢٤﴾ ﴾ الانشقاق: ٢٤

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) አሳማሚ በሆነ ቅጣት አርዳቸው።›› (አንቀጽ 24)

አስደሳች ያልሆነ፣ ቀልብ በደስታ የማያስተናግደውብስራት።

አማኞች የሚጠብቃቸውን ስኬትም አያይዞ ያቀርባል።

﴿ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ مَمۡنُونٍ ﴿٢٥﴾ ﴾ الانشقاق: ٢٥

‹‹በአንጻሩ እነዚያ ያመኑትና መልካም የሠሩት የማይቋረጥ ምንዳ አላቸው።›› (አንቀጽ 25)

‹‹የማይቋረጥ ምንዳ››፣ የተባለው በዘልዓለማዊው ሐገር የተሰናዳላቸው የማይቋረጥ ድሎት እና ጸጋ ነው።።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ✓ በአንቀጾቹ የተወሱትን የዩኒቨርሱ ስርዓት መናጋቶች ዝርዝር
- ✓ አላህ በዚህች ምእራፍ የሰውን ልጅ ያናገረበትን አጀንዳ አብራራ።።

* * *

አል ቡሩጅ

አንቀጽ 1-11

﴿ وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡبُرُوجِ ١ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡمَوۡعُودِ ٢ وَشَاهِدٖ وَمَشۡهُودٖ ٣ قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ٤ ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ إِذۡ هُمۡ عَلَيۡهَا قُعُودٞ ٦ وَهُمۡ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ شُهُودٞ ٧ وَمَا نَقَمُواْ مِنۡهُمۡ إِلَّآ أَن يُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَمِيدِ ٨ ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٩ إِنَّ ٱلَّذِينَ فَتَنُواْ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ ثُمَّ لَمۡ يَتُوبُواْ فَلَهُمۡ عَذَابُ جَهَنَّمَ وَلَهُمۡ عَذَابُ ٱلۡحَرِيقِ ١٠ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡكَبِيرُ ١١ ﴾ البروج: ١ - ١١

‹‹የ«ቡሩጅ» ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ። በተቀጠረው ቀንም (በዕለተ-ትንሣዔም) እምላለሁ። በመስካሪዎችና በሚመሰከርባቸውም። የጉድጉ ባለቤቶች ተረገሙ፤ የማገዶዋማዋ እሳት (ባለቤቶች)። በርሷ (በእሳቷ) ዙሪያ በተቀመጡ ጊዜ፤ በአማኞች ላይ የሚፈጽሙትን (ዘግናኝ የወንጀል ድርጊት) ለመመልከት። (ግፈኞች) ከነርሱ (ለአሰቃቂ የግፍ ተግባር ከተዳረጉት አማኞች) አሸናፊ፥ የምስጋናና ውዳሴ ባለቤት በሆነው አላህ ማመናቸውን እንጂ ሌላ ምንም አልጠሉም። (ወንጀለኞቹ) በዚያ የሰማያትና የምድር የበላይ ገዥነት ለርሱ ብቻ በሆነው አላህ (ማመናቸው ብቻ ነበር።) አላህ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ ነው። እነዚያ የሴትና የወንድ አማኞችን የፈተኑ (እምነታቸውን ለማስለቀቅ በእሳት በማቃጠል ያሰቃዩ) እና ያልተፀፀቱ ወገኖች የገሃነም ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል። አቃጣይ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። እነዚያ ያመኑትና መልካም ተግባራትን የፈፀሙ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ተዘጋጅተውላቸዋል። ይህ ታላቅ ስኬታማነት ነው።›› (አንቀጽ 1-11)

* * *

አጠቃላይ ዓላማዎች

- ✓ አማኞችን የጨፈጨፉና ያጠፉ አምባ ገነኖች አስከፊ ፍጻሜ፣ እንዲሁም ይህን ለማሳየት የቀረቡ ናሙናዎችን ማወቅ
- ✓ በሰው ልጅ ዓለማዊ ሕይወትና በአላህ ችሎታ፣ ፈቃድና ፍትህ አግባብ በመንዙ መካከል ያለውን ትስስር መረዳት።

* * *

ይህ አጭር ምእራፍ ከዓቂዳዊ እይታዎችና ከእምነታዊ አመለካከት መሠረቶች ውስጥ ታላላቅ ጉዳዮችን ይቃኛል። ምእራፉ በቀጥታ የተመለከተው የጉድጓዱ ባለቤቶችን (አስሐበል ኡኽዱድ) ታሪክ ነው። ይህውም ከነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) መነሳት በፊት የነበሩ አማኞች (አሐዳውያን ክርስትያኖች ናቸው ተብሏል።) እጅግ አምባገነን፣ ጨካኝ እና ክፉ በሆኑ ጠላቶቻቸው መፈተናቸውን ይተርካል። ሐይማኖታቸውን እንዲተው ተጠየቁ። እነርሱ ግን አሻፈረን አሉ። እምነታቸውንም አጥብቀው ያዙ። አምባገነኖችም ጉድጓድ ቆፈሩ። ከውስጧም እሳት አነደዱ። አማኞችንም ወደ እሳቷ ወረወሩ። አማኞች እየተቃጠሉ ሞቱ። በእኩያን ባለስልጣናት የተጠራው ሕዝብ ትእይንቱን ይመለከት ነበር። እኩዮችም አማኞች ሲቃጠሉ እየተመለከቱ ይዝናኑ፣ ይጫወቱ፣ ይደሰቱ ነበር።

* * *

﴿وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡبُرُوجِ ١﴾ البروج: ١

የ"ቡሩጅ" ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ።›› (አንቀጽ 1)

ምእራፉ በዚህ መሐላ ይጀምራል። ‹ቡሩጅ› በሆነችው ሰማይ። ‹‹ቡሩጅ›› የታላላቅ ኻላኔቶች እና ከዋክብት ምህዋሮች ሊሆኑ ይችላሉ። የግዙፉ ሰማይ የታነጹ ግንቦች እንደሆኑ ገለጻው ይጠቁማል። ወይም ደግሞ ኻላኔቶች በሚሽከረከሩ ጊዜ የሚሻገሯቸው የተለያዩ እርከኖች ሊሆኑም

ይችላሉ፡፡ እዚህ ቦታ ላይ መነሳታቸው የግዘፈቱን ድባብ የመፍጠር ዓላማ አለው፡፡

﴿ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡمَوۡعُودِ ٢ ﴾ البروج: ٢

‹‹በተቀጠረው ቀንም (በዕለተ-ትንሣዔም) እምላለሁ፡፡›› (አንቀጽ 2)

የዚህች አለም ክስተቶች ፍርድ የሚሰጥበት፣ አላህ እንደሚመጣ የቀጠረው፣ ሰዎችን እንደሚመረምርና የስራቸውን ዋጋ እንደሚሰጥበት የቀጠረው ቀን ነው፡፡ የባለጋራዎችንና የፍትህ ፈላጊዎችን ጉዳዮች ለዚህ ቀን በቀጠሮ አስተላልፏል፡፡

وَشَاهِدٖ وَمَشۡهُودٖ

በመስካሪዎችና በሚመሰከርባቸውም፡፡ (አንቀጽ 3)

በዚያ ቀን ስራዎች ሁሉ ይቀርባሉ፡፡ ፍጡራን ይቀርባሉ፡፡ ሁሉም ነገር ለእይታ ግልጽ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሰዎች ትእይንቱን ይከታተላሉ፡፡

ሦስቱም የተማለባቸው ነገሮች፣ ማለትም ቡሩጃማ ሰማይ፣ የቀጠሮው ቀን፣ ተመልካችና የሚታዩ ነገሮች ተደምረው ቀጥሎ የሚጠቀሰው አጀንዳ ከፍተኛ ትኩረት እና ክብደት እንደተቸረው ያመለክታሉ፡፡ የግዘፈትን ድባብም ይፈጥራሉ፡፡ ቀጥሎም የጉድጓድ ባለቤቶች ታሪክ በጥቂት ቃላት ይጠቀሳል፡-

﴿ قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ﴾

‹‹የጉድቡ ባለቤቶች ተረገሙ፤›› (አንቀጽ 4)

በጉድጓዱ ባለቤቶች ላይ እርግማን በማወጅ ታሪኩ ይወጠናል፡፡ ገለጻው ቁጣን ያሳያል፡፡ ድርጊቱን በፈጸሙት ወገኖች ላይ የታጋሹን አምላክ እርግማን ፣ ቁጣና ቅጣት የሚያስከትለው ይህ ድርጊት በጣም አስከፊ መሆኑን ያመለክታል፡፡

﴿ ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ ﴾

‹‹የማገዶዋማዋ እሳት (ባለቤቶች)።›› (አንቀጽ 5)

የድርጊቱ ፈጻሚዎች ጉድጓድ ቆፈሩ። ከውስጧም እሳት አቀጣጠሉ። አማኞችንም ወደ ውስጡ ወረወሩ።

﴿ إِذۡ هُمۡ عَلَيۡهَا قُعُودٞ ٦ وَهُمۡ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ شُهُودٞ ٧ ﴾ البروج: ٦ - ٧

‹‹ባርሷ (በእሳቷ) ዙሪያ በተቀመጡ ጊዜ፣ በአማኞች ላይ የሚፈጽሙትን (ዘግናኝ የወንጀል ድርጊት) ለመመልከት።›› (አንቀጽ 6-7)

ጉድጓድ ቆፍረው፣ እሳት አቀጣጥለው የሚማግዷቸውን አማኞች ስቃይ ከአጠገባቸው ሆነው እየተመለከቱ ይደሰቱ የነበሩበትን ሁኔታ የሚከስት ገለጻ ነው።

ይህን ያደረጉት፣ አማኞች አንዳች ወንጀል ወይም ጥፋት ኖሮባቸው አይደለም።

﴿ وَمَا نَقَمُواْ مِنۡهُمۡ إِلَّآ أَن يُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَمِيدِ ٨ ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٩ ﴾ البروج: ٨ - ٩

‹‹(ግፈኞች) ከነርሱ (ለአሰቃቂ የግፍ ተግባር ከተዳረጉት አማኞች) አሸናፊ፣ የምስጋናና ውዳሴ ባለቤት በሆነው አላህ ማመናቸውን እንጂ ሌላ ምንም አልጠሉም። (ወንጀላቸው) በዚያ የሰማያትና የምድር የበላይ ገዥነት ለርሱ ብቻ በሆነው አላህ (ማመናቸው ብቻ ነበር።) አላህ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ ነው።›› (አንቀጽ 8-9)

የአማኞች ወንጀል ይህ ነው። የሚሻውን ሰሪ፣ ሐያልና በሁሉም ሁኔታዎች ለምስጋና ተገቢ፣ የሰማያትና የምድር ባለቤት፣ ሁሉንም ነገር ተመልካች፣ የጉድጓዱን ባላቤቶች ድርጊትና የአማኞችን ስቃይ ያየና የተከታተለ በሆነው አምላክ ማመናቸው ብቻ ነው። ገለጻው አማኞችን

ያጸናል። ለወንጀለኞችም ዛቻ አዘሏል። ‹‹አላህ ድርጊቱን ተመልክቷል፣ የተፈጸመውን ሁሉ አይቷል። ይህንንም ይመሰክራል›› ነው መልእክቱ። ምስክርነት በአላህ በቃ!

የክስተቱ ትረካ የድርጊቱን አስከፊነትና የታዳሚዎችን ጥፋት አግዝፎ በማሳየት ልቦና እንዲጸየፋቸው በሚያደርጉ ጥቂት አናቅጽ ተተርኮ እዚህ ላይ ይጠናቀቃል። ትረካው በተጨማሪም ፈተናን ያሸነፈ እምነት፣ ብኽርታን ድል የነሳን ዓቂዳ በማስተዋወቅ ልቦናን በድንቅታ ይሞላል።

አማኞች እምነታቸውን ለሸንፈት ዳርገው ሕይወታቸውን ማዳን ይችሉ ነበር። ግና ይህ ቢሆን ኖሮ ከመጭው ዓለም በፊት በዚህች ዓለም በጣም ይከስሩ ነበር። እነርሱ ብቻ ሳሆኑ የሰው ልጅ ባጠቃላይ የከፋ ኪሣራ ይደርስበት ነበር። ይህን ትልቅ መልእክት ይገድሉታል። ሕይወት ያለ እምነት ርካሽ፣ ያለ ነጻነት አስጸያፊ፣ አምባገነኖች ከአካል አልፈው መንፈስን ሲቆጣጠሩ እጅግ ወራዳ የመሆኗን መልእክት ያወድሙታል።

ስለዚህም በጽናት በመሞታቸው በምድር ላይ ይህን እጅግ ታላቅ መልእክት አትርፈዋል። አካላቸውን ለእሳት ቃጠሎ ሰጥተው ይህን የላቀ እውነታ ታድገውታል። በእሳት ይበልጥ እንዲጸዳና እንዲጥር አድርገውታል። በተጨማሪም ከአምላካቸው ዘንድ ለነርሱ ትልቅ ዋጋ፣ ለጠላቶቻቸው ደግሞ አስከፊ ቅጣት ተሰናድቷል፦

إِنَّ ٱلَّذِينَ فَتَنُواْ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ ثُمَّ لَمۡ يَتُوبُواْ فَلَهُمۡ عَذَابُ جَهَنَّمَ وَلَهُمۡ عَذَابُ ٱلۡحَرِيقِ

‹እነዚያ የሴትና የወንድ አማኞችን የፈተኑ (እምነታቸውን ለማስለቀቅ በእሳት በማቃጠል ያሰቃዩ) እና ያልተፀፀቱ ወገኖች የገሃነም ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል። አቃጣይ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። ›› (አንቀጽ 11)

በምድር ላይ የተከሰተው የታሪኩ መቋጫ፣ የጉዞው መጠናቀቂያ አይደለም። ትእይንቱ ይቀጥላል።

‹‹እነዚያ አማኞችን የፈተኑ፣ የቀጡና ያንገላቱ፣ በክፋታቸውም የቀጠሉ፣ ወደ አላህ በተውባ ያልተመለሱ አቃጣይ የጀሃነም ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል።››

ሁለቱ የእሳት ቃጠሎዎች ከስም በቀር ፍጹም የሚመሳሰሉ አይደሉም። የዚህች ዓለም እሳት በፍጡራን፣ የመጭው ዓለም ግን በአምላክ የተቀጣጠሉ ናቸው። የዚህች ዓለም እሳት ከቅጽበት በኋላ ይከስማል። የመጭው ዓለም እሳት ግን ዘልዓለማዊ ነው።

አላህ ለነዚያ ላመኑት እና በጎ ስራ ለሰሩት ያለው ውዴታ በጀነት ይገለጻል፡-

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡكَبِيرُ

‹‹እነዚያ ያመኑትና መልካም ተግባራትን የፈፀሙ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ተዘጋጅተውላቸዋል። ይህ ታላቅ ስኬታማነት ነው።›› (አንቀጽ 11)

እውነተኛ ስኬት፣ ትክክለኛ መዳን ይህ ነው። ከመጭው ዓለም እሳት መዳን በራሱ ትልቅ ስኬት ነው። በዚህ ላይ ከስሮቿ ወንዞች የሚፈሱባትን ጀነት ማግኘት ሲታከልበት አቻ አይገኝለትም።

በዚህ መቋጫ የታሪኩ ፍጻሜ ይሆናል። ትክክለኛ መቋጫ ነው። ለክስተቱ የተሰጠው የመጀመሪያ ትንተና በመካ ውስጥ በነበሩት፣ እንዲሁም በየትኛውም ዘመንና ቦታ ለፈተናና ለስቃይ በሚጋለጡ መእሚኖች ልቦና ውስጥ ማጽናት የሚሻው እውነትም ይህ ነው።

* * *

አንቀጽ 12-22

﴿ إِنَّ بَطۡشَ رَبِّكَ لَشَدِيدٌ ١٢ إِنَّهُۥ هُوَ يُبۡدِئُ وَيُعِيدُ ١٣ وَهُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلۡوَدُودُ ١٤ ذُو ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡمَجِيدُ ١٥ فَعَّالٞ لِّمَا يُرِيدُ ١٦ هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡجُنُودِ ١٧ فِرۡعَوۡنَ وَثَمُودَ ١٨ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي تَكۡذِيبٖ ١٩ وَٱللَّهُ مِن وَرَآئِهِم مُّحِيطُۢ ٢٠ بَلۡ هُوَ قُرۡءَانٞ مَّجِيدٞ ٢١ فِي لَوۡحٖ مَّحۡفُوظِۭ ٢٢ ﴾

البروج: ١٢ - ٢٢

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) የጌታህ አያያዝ (ብቀላ) እጅግ የበረታ ነው። መጀመሪያ ፍጡራንን ከምንም ያስገኘው እርሱ ብቻ ነው፤ ዳግም (ሕይወትን) መመለስም (ከሞት በኋላ መቀስቀስም) አይሳነውም። እርሱ ምሕረተ ብዙና እጅግ አፍቃሪም ነው። የዐርሹ ባለቤት፤ የተላቀውም (አምላክ) ነው። ያሻውን መፈፀም የሚችል (ኃያል አምላክ)። የሠራዊቶች ወሬ ደርሶሃልን? የፈርዖንና የሠሙድ? እነዚያ የካዱት ሰዎች በአስተባባይነት እንደፀኑ ናቸው። አላህ ከበስተኋላ አካቢቸዋል፤ (ደካሞችና በቁጥጥሩ ሥር ናቸው። የትም አያመልጡም)። እርሱ የተከበረ ቁርአን ነው። በተጠበቀ ሰሌዳ ውስጥ (ሠፍሯል)›› (አንቀጽ 12-22)

* * *

የቁርአን ትንተና ይቀጥላል።

﴿ إِنَّ بَطۡشَ رَبِّكَ لَشَدِيدٌ ١٢ ﴾ البروج: ١٢

‹‹ የጌታህ አያያዝ (ብቀላ) እጅግ የበረታ ነው።›› (አንቀጽ 12)

እዚህ ላይ የአላህ አያያዝ ብርታት መዘከሩ ከተተረከው የጭከኔ ታሪክ ጋር ይጣጣማል። የጉድጓዱ ባለቤቶችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች አማኞች የተቀጡበትን ሁኔታ ብርቱ አድርገው ያስባሉ። ብርቱ አያያዝስ የሰማያት እና የምድር ባለቤት የሆነው አምላክ አያያዝ። ብርቱ ቅጣትስ የርሱ ቅጣት።

﴿ إِنَّهُۥ هُوَ يُبۡدِئُ وَيُعِيدُ ١٣ ﴾ البروج: ١٣

‹‹መጀመሪያ ፍጡራንን ከምንም ያስገኘው እርሱ ብቻ ነው፣ ዳግም (ሕይወትን) መመለስም (ከሞት በኋላ መቀስቀስም) ኣይሳነውም።›› (ኣንቀጽ 13)

መጀመሪያ መፈጠርንና ከሞት መነሳትን የሚያመለክት ቢሆንም በእያንዳንዱ ቅጽበት የሚስተዋል ተአምር ነው። አላህ ሁሌም ሕይወት ይለግሳል። ሁሌም የሞቱትን ሕያው ያደርጋል።

﴿ وَهُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلۡوَدُودُ ١٤ ﴾ البروج: ١٤

‹‹እርሱ ምሕረተ ብዙና እጅግ አፍቃሪም ነው።›› (ኣንቀጽ 14)

ምህረት ወሰን የለሽ እዝነትንና ችሮታን ያመለክታል። ሁሌም ክፍት የሆነና ተውባ ለሚያደርጉት ምንጊዜም የማይዘጋ በር ነው። ሐጢአት የቱን ያህል ቢገዝፍም፣ ወንጀል የቱን ያህል ቢተልቅም። ፍቅር (ውዴታ) ደግሞ አምላካቸውን ከሁሉም ነገር ያስበለጡና የመረጡ አማኞች የሚታደሉት ስጦታ ነው።

ለስላሳና ጣፋጭ፣ ውብና የላቀ ማጽናኛ። ከዚህ ሽልማት አንጻር ጠፊውን ሕይወታቸውን ለመስዋእትነት ማቅረባቸው፣ የተሸከሙት ጊዜያዊ ስቃይና መከራ ሁሉ ኢምንት ነው። የዚህን አምላካዊ ፍቅር ጠብታ እንኳ ለማግኘት፣ ይህን ተወዳጅ መጽናኛ ለመስማት የሚከፈል ማንኛውም ዓይነት መስዋእትነት እዚህ ግባ ሊባል የማይችል፣ ክብደት እና ግምት የማይሰጠው አናሳ ነው።

﴿ ذُو ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡمَجِيدُ ١٥ ﴾ البروج: ١٥

‹‹የዐርሹ ባለቤት፣ የተላቀውም (ኣምላክ) ነው።›› (ኣንቀጽ 15)

አዋጅ፣ የዚህን አምላክ ፍቅር ጠብታ ከመታደል አንጻር የዚህች ዓለም ሕይወት ርካሽ ነው። ሕመሟ እና ስቃይዋም ቀላል ነው። ውድ ነገሮች ሁሉ ዋጋ ቢስ ናቸው።

﴿ فَعَّالٞ لِّمَا يُرِيدُ ١٦ ﴾ البروج: ١٦

‹‹ያሻውን መፈፀም የሚችል (ኃያል አምላክ)።›› (አንቀጽ 16)

ይህ ባህሪው ሁሌም ይደጋገማል። በስርዓትና በጽናትም ይሰራል። የአምላክ ፈቃድ ገደብ የለውም። ያሻውን ይመርጣል። ያሻውን ያከናውናል። ሁሌም ይህን ያደርጋል። ባህሪው ይህ ነው። አንዳንድ ጊዜ እርሱ ለሚያውቀው ጥበብ ሲል አማኞች በዚህች ምድር ድል እንዲያገኙ ይፈቅዳል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ፈራሹ ገላ ጠፍቶ እምነት ፈተናን እንዲያሸንፍ እርሱ ለሚያውቀው ጥበብ ይፈቅዳል። አንዳንድ ጊዜ ወንጀለኞችን በምድር ላይ ይቀጣል። ሌላ ጊዜ ለቀጠሮው ቀን ያቆያቸዋል። ይህ ሁሉ ለጥበብ ነው። የሻውን ሰሪ የመሆኑ ናሙና እነሆ ቀጥሎ ተመልክቷል፦

﴿ هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡجُنُودِ ١٧ فِرۡعَوۡنَ وَثَمُودَ ١٨ ﴾

የሠራዊቶች ወሬ ደርሶሃልን? የፈርዖንና የሠሙድ?› (አንቀጽ 17-19)

አላህ ‹ሰራዊት› ሲል የጠራቸው ብርታታቸውን ለመግለጽ ነው። የነርሱ ወሬ፣ አምላክህ በነርሱ ላይ ምን እንደፈጸመ ደርሶሐልን? የሁለት ቀንደኛ ሐጢአተኞች ታሪክ ተወሳ። በባህሪያቸውም በፍጻሜያቸውም የተለያዩ። በፊርዓውን ታሪክ ፊርዓውን ከነሰራዊቱ ጠፍቶ፣ የእስራኤል ልጆች ድነው አላህ በምድር ላይ ለተወሰነ ጊዜ ምቾትንና የበላይነትን እንደሰጣቸው እናነባለን። በአንጻሩ ሰመዶችን አላህ አንድም ሳያስቀር አጥፍቶ ሷሊህና ጥቂት ተከታዮቹ ብቻ መዳናቸውን እናነባለን። ከሐጢአተኞች መትረፋቸው ብቻ እንጅ ከዚያ በኋላ በምድር ላይ ንግስና

ወይም የበላይነት እንዳገኙ አልተተረከም። ስለዚህም ሁለት ዓይነት የአላህን ፈቃድ የሚያሳዩ ናሙናዎች ናቸው።

እነዚህ ሁለት ታሪኮች የየትኛውም የዳእዋ ፍጻሜ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ናሙናዎችን ይዘዋል። ሌላ ሦስተኛ ናሙናም የዚህ ምእራፍ አብይ አጀንዳ በሆነው የጉድጓዱ ባለቤቶች ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። ቁርአን መካ ውስጥ ለነበሩ ጥቂት አማኞች እና ለሁሉም ዘመናት አማኞች እነዚህን ናሙናዎች ያቀርባል።

﴿ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي تَكۡذِيبٖ ١٩ وَٱللَّهُ مِن وَرَآئِهِم مُّحِيطُۢ ٢٠ ﴾ البروج: ١٩ - ٢٠

‹‹እነዚያ የካዱት ሰዎች በአስተባ ባይነት እንደወኑ ናቸው። አላህ ከበስተኋላ አካቢቸዋል፤ (ደካሞችና በቁጥጥሩ ሥር ናቸው። የትም አያመልጡም)።›› (አንቀጽ 19-20)

የካህድያን ሁኔታ ይህው ነው። በአስተባባይነት ውስጥ ይኖራሉ። በዚህ ባህሪ አምሽተው ያነጋሉ። አላህ በችሎታውና በእውቀቱ ዙሪያቸውን አካቢቸዋል። እነርሱ ግን ይህን ዘንግተዋል።

﴿ بَلۡ هُوَ قُرۡءَانٞ مَّجِيدٞ ٢١ فِي لَوۡحٖ مَّحۡفُوظِۭ ٢٢ ﴾ البروج: ٢١ - ٢٢

‹‹እርሱ የተከበረ ቁርአን ነው። በተጠበቀ ሰሌዳ ውስጥ (ሠፍሯል)›› (አንቀጽ 21-22)

በልቅና የከበረ መጽሐፍ። ከአላህ መጽሐፍ ይበልጥ የላቀና ከፍ ያለ ሌላ ነገር ሊኖር ይችላልን? እርሱም በተጠበቀ ስሌዳ ውስጥ ነው። በማንኛውም ጉዳይ ውሳኔው የመጨረሻ ነው። ቃሉ የተጠበቀ ነው። ቁርአን የጉድጓድ ባለቤቶችን ታሪክ እና ከበስተጀርባ ያዘለውን እውነታ በተመለከተ መልእክቱን አስተላልፏል። ውሳኔውን ሰጥቷል። ትክክለኛውን ትንታኔ አስቀምጧል። በዚህ ረገድ የመጨረሻው ቃልም የርሱ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- አማኞችን ያሰቃዩ ወገኖችን ፍጻሜ ምን እንደሆነ በአንቀጾቹ በተብራራው መልኩ ግለጽ፡፡ ናሙናዎችንም አቅርብ፡፡
- የሰው ልጅ ሕይወት በአላህ ፈቃድ፣ ችሎታና ፍትህ ስር የመገዙን እውነታ አብራራ፡፡

* * *

አል ጧሪቅ

አንቀጽ 1-10

﴿ وَٱلسَّمَآءِ وَٱلطَّارِقِ ﴿١﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلطَّارِقُ ﴿٢﴾ ٱلنَّجۡمُ ٱلثَّاقِبُ ﴿٣﴾ إِن كُلُّ نَفۡسٖ لَّمَّا عَلَيۡهَا حَافِظٞ ﴿٤﴾
فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ مِمَّ خُلِقَ ﴿٥﴾ خُلِقَ مِن مَّآءٖ دَافِقٖ ﴿٦﴾ يَخۡرُجُ مِنۢ بَيۡنِ ٱلصُّلۡبِ وَٱلتَّرَآئِبِ ﴿٧﴾ إِنَّهُۥ عَلَىٰ رَجۡعِهِۦ
لَقَادِرٞ ﴿٨﴾ يَوۡمَ تُبۡلَى ٱلسَّرَآئِرُ ﴿٩﴾ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٖ وَلَا نَاصِرٖ ﴿١٠﴾ ﴾ الطارق: ١ - ١٠

‹‹በሰማይ እምላለሁ፤ በሌሊት ጉብኚውም። ስለሌሊት ጉብኚው ምን የምታውቀው ነገር አለ? ጨለማን ሰንጣቂ ኮከብ ነው። ተቆጣጣሪ (መላእክት) የሌሉበት አንድም ሰው የለም። የሰው ልጅ ከምን እንደተፈጠረ ያስተውል! የተፈጠረው ከተስፈንጣሪ ውሃ (የዘር ፈሳሽ) ነው። ከ"ሱልብ" እና ከ"ተራኢብ" መካከል የሚወጣ ከሆነ (የዘር ፈሳሽ)። እርሱ (በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያስገኘው አምላክ) ሊመልሰው (ከሞት በኋላ ዳግም ሊቀሰቅሰው) ችሎታ አለው፤ ሚስጥሮች በሚገለፁበት ቀን። (በዚያ ወቅት) ለርሱ (ለሰው ልጅ) ምንም ዓይነት ኃይልና ረዳት አይኖረውም።›› አንቀጽ 1-10

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) አላህ በምእራፏ መጀመሪያ ላይ የገለጻቸውን የተፈጥሮ ክስተቶችና የእምነት እውነታዎች ማብራራት
2) ከሰው ልጅ መነሻ ጋር የተያያዘውን የአላህ ጥበብ ማስተንተን
3) ከሞት በማስነሳቱ ሂደት የአላህን ችሎታ ማብራራት
4) በመጭው ዓለም ወደ አላህ ለመመለስ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ

* * *

ምእራፉ የተወጠነችባቸው መሐላዎች የዩኒቨርሱን ትእይንቶችና ኢማናዊ እውነታዎች ይዘዋል። በሰማይና በሌት ጉብኚው በመማል ይወጠናል። በመቀጠልም በቁርአናዊው የገለጻ ስልት የተለመደውን ጥያቄ ያቀርባል።

﴿ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلطَّارِقُ ۝٢ ﴾ الطارق: ٢

‹‹ስለሌሊት ጉብኚው ምን የምታውቀው ነገር አለ?›› (አንቀጽ 2)

ከሰው ልጅ የእውቀት ወሰን ባሻገር መሆኑን ለመጠቆም ይህ ጥያቄ ተሰንዝሯል። ከዚያም ምንነቱን ይገልጻል፡-

﴿ ٱلنَّجۡمُ ٱلثَّاقِبُ ۝٣ ﴾ الطارق: ٣

‹‹ጨለማን ሰንጣቂ ኮከብ ነው።›› (አንቀጽ 3)

ከነዚህ መሐላዎች በኋላ እያንዳንዱ ነፍስ ጠባቂ እንዳለባት ይገልጻል፡-

﴿ إِن كُلُّ نَفۡسٖ لَّمَّا عَلَيۡهَا حَافِظٞ ۝٤ ﴾ الطارق: ٤

‹‹ተቆጣጣሪ (መላእክት) የሌለበት አንድም ሰው የለም።›› (አንቀጽ 4)

ይህ ጠባቂ ሥራዎቹን እንዲመዘግብ፣ ጥበቃም እንዲያደርግላት በአላህ ተወክሏል። ስለዚህ ስርዓት አልባነት የለም። የሰው ልጅ በምድር ላይ ያለ ጠባቂ አልተተወም። ያለ ተቆጣጣሪ ያሻውን ይሰራ፣ የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ አልተለቀቀም። የቁጥጥር ስልት ተዘርግቷል። ስራዎች በጥንቃቄ ይመዘገባሉ። ይህን ምዝገባ ተንተርሶም ምርመራ ይከናወናል።

ከዚያም የአላህን ችሎታ ወደሚያሳይ ሌላ ቅኝት ይገባል።

﴿ فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ مِمَّ خُلِقَ ۝٥ خُلِقَ مِن مَّآءٖ دَافِقٖ ۝٦ يَخۡرُجُ مِنۢ بَيۡنِ ٱلصُّلۡبِ وَٱلتَّرَآئِبِ ۝٧ ﴾

‹‹የሰው ልጅ ከምን እንደተፈጠረ ያስተውል! የተፈጠረው ከተስፈንጣሪ ውሃ (የዘር ፈሳሽ) ነው። ከ“ሱልብ” እና ከ“ተራኢብ” መካከል የሚወጣ ከሆነ (የዘር ፈሳሽ)።›› (አንቀጽ 5-7)

አሥ፣ የሰው ልጅ መነሻውን ይመልከት፡፡ ከምን እንደተፈጠረ እና አሁን ያለበትን ሁኔታ ያስተውል፡፡ ከተስፈንጣሪ ፈሳሽ ተፈጥሯል፡፡ በመነሻውና አሁን ባለበት ሁኔታ መካከለ ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ በተስፈንጣሪ ሚና እጅግ ረቂቅ አካላዊ የነርቭ፣ የአእምሮና ስነ ልቦናዊ ቅንብር ባለው፣ የማወቅና የማሰብ ክህሎት በተሰጠው የሰው ልጅ መካከል ሰፊ ርቀት አልለ፡፡ ይህ ርቀት ደካማ የሆነው ፈሳሽ እጅግ ድንቅ ወደሆነ የሰው ልጅ እንዲለወጥ የሚያደርግ ሌላ ውጫዊ አካል እንዳለ ያመለክታል፡፡ በመሐላ ለማረጋገጥ የተከጀለው የመጀመሪያው እውነታ ይህ ሲሆን፣ ቅኝቱ ለሁለተኛውም እውነታ መነሻ ይሆናል፡፡ እርሱም ጣኦታውያን ያስተባብሉት የነበረው ከሞት በኋላ የመነሳት ጉዳይ ነው፡፡

﴿ إِنَّهُۥ عَلَىٰ رَجۡعِهِۦ لَقَادِرٞ ٨ يَوۡمَ تُبۡلَى ٱلسَّرَآئِرُ ٩ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٖ وَلَا نَاصِرٖ ١٠ ﴾ الطارق: ٨ - ١٠

‹‹እርሱ (በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያስገኘው አምላክ) ሊመልሰው (ከሞት በኋላ ዳግም ሊቀሰቅሰው) ችሎታ አለው፣ ሚስጥሮች በሚገለፁበት ቀን፡ (በዚያ ወቅት) ለርሱ (ለሰው ልጅ) ምንም ዓይነት ኃይልና ረዳት አይኖረውም፡፡›› (አንቀጽ 8-10)

አሥ፣ መጀመሪያ ያስገኘውና የተንከባከበው አምላክ ከሞት በኋላ ወደ ሕይወት መመለስ፣ ከበሰበሰ በኋላ ማደስ አይሳነውም፡፡ አምላክ የሰውን ልጅ የፈጠረበት ሁኔታ ችሎታውን ብቻ ሳይሆን መርጦ ማስተናበሩን ያመለክታል፡፡

በእርግጥም የተደበቁ ሚስጥሮች በሚገለጹበት፣ በይፋ በሚነገሩበት ቀን ይቀሰቅሰዋል፡፡ (ቀስቅሶም ይመረምረዋል፡፡ መርምሮም የስራ ዋጋውን ይሰጠዋል፡፡)

﴿ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٖ وَلَا نَاصِرٖ ١٠ ﴾ الطارق: ١٠

‹‹(በዚያ ወቅት) ለርሱ (ለሰው ልጅ) ምንም ዓይነት ኃይልና ረዳት አይኖረውም፡፡››(አንቀጽ 10)

የሰው ልጅ በራሱ ሐይል የለውም። ሌላ ረዳትም የለውም።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) በምእራፉ መወጠኛ ላይ የተማለባቸውን የተፈጥሮ ክስተቶችና የእምነት እውነታዎች አብራራ

2) በነፍሶቻችሁ ውስጥ አትመለከቱምን?› በአንተነትህ ውስጥ ያለውን የአላህ ረቂቅ የአፈጣጠር ጥበብ አስተነተንክን?

3) ከሞት በኋላ በማስነሳቱ ሂደት የአላህን ችሎታ አብራራ

4) በመጭው ዓለም ከአላህ ፊት ለመቅረብ እየተዘጋጀህ ነውን? ምን አዘጋጀህ?

* * *

አንቀጽ 11-17

﴿ وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلرَّجۡعِ ١١ وَٱلۡأَرۡضِ ذَاتِ ٱلصَّدۡعِ ١٢ إِنَّهُۥ لَقَوۡلٞ فَصۡلٞ ١٣ وَمَا هُوَ بِٱلۡهَزۡلِ ١٤ إِنَّهُمۡ يَكِيدُونَ كَيۡدٗا ١٥ وَأَكِيدُ كَيۡدٗا ١٦ فَمَهِّلِ ٱلۡكَٰفِرِينَ أَمۡهِلۡهُمۡ رُوَيۡدَۢا ١٧ ﴾ الطارق: ١١ - ١٧

‹‹ዝናባማ በሆነችው ሰማይ እምላለሁ። (በቡቃያዎች) ተሰንጣቂ በሆነችው መሬትም እምላለሁ። እርሱ (ቁርአን እውነትን ከሐሰት) የሚለይ ቃል ነው፤ ቀልድ አይደለም፤ (ከውስጡ ቁም ነገር ብቻ እንጅ ቀልድ የለበትም።) እነርሱ (መካውያን አጋሪዎች) ሴራ ያውጠነጥናሉ። እኔም ተንኮላቸውን አመክናለሁ፤ እበቀላቸዋለሁም። ከሓዲያንን ቀን ስጣቸው፥ (ለመጥፋታቸው አትቸኩል)፤ ጥቂት ጊዜ ታገሣቸው።›› (አንቀጽ 11-17)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) አላህ ከምእራፏ መጨረሻ ላይ የማለባቸውን ነገሮች ማስታወስ

2) ከአላህ ጠላቶች ጋር የሚደረገውን ጦርነት ባህሪ መገንዘብ

* * *

የሰውን ልጅ ከሞት መነሳት እና ለፍርድ መቅረብ በተመለከተ ምን አልባትም በቀልብ ውስጥ ጥቂት የጥርጣሬ ቅሪት ይኖር እንደሁ እርሱን ለመጠራረግ አጽንኦት ሰጥቶ ይናገራል። በቁርጥ ያስገነዝባል። በመሐላ ይበልጥ ያጸናዋል፦

﴿ وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلرَّجۡعِ ١١ وَٱلۡأَرۡضِ ذَاتِ ٱلصَّدۡعِ ١٢ إِنَّهُۥ لَقَوۡلٞ فَصۡلٞ ١٣ وَمَا هُوَ بِٱلۡهَزۡلِ ١٤ ﴾

‹‹ዝናባማ በሆነችው ሰማይ እምላለሁ። (በቡቃያዎች) ተሰንጣቂ በሆነችው መሬትም እምላለሁ። እርሱ (ቁርአን እውነትን ከሐሰት) የሚለይ ቃል ነው፤ ቀልድ አይደለም፤ (ከውስጡ ቁም ነገር ብቻ እንጅ ቀልድ የለበትም።)›› (አንቀጽ 11-14)

የመመላለስ ባለቤት ዝናብ ሲሆን በሰማይ ላይ ዘወትር ይመላለሳል። ቡቃያም ምድርን ሰንጥቆ ሲወጣ ዘወትር ይስተዋላል። ሁለቱም

የእጽዋት ሕይወት መነሻ ትእይንቶች ናቸው። ውሃ ከሰማይ ይወርዳል። ቡቃያዋም ምድርን ትሰነጥቃለች።

በነዚህ በሁለቱ ክስተቶች በመማል ከሞት መቀስቀስንና መመርመርን የሚያጸድቀው ይህ ንግግር እንዲሁም ቁርአን ባጠቃላይ እውነትን ከሐሰት የሚለይ፣ ቀልድም ያልተቀላቀለበት፣ የትኛውንም ጥርጣሬና ክርክር የሚያስቀር ቁርጥ ቃል መሆኑን አላህ በአጽንኦት ይገልጻል።

በዚህ ቁርጥ ቃል ድባብ ስር የንግግሩን አቅጣጫ ወደ አላህ መልእክተኛ እና መካ ውስጥ በጣኦታውያን ሁከት እና ሴራ ይሰቃዩ ወደነበሩ ጥቂት አማኞች በማዞር የካህድያን ሴራ ኢምንትና ጊዜያዊ፣ ከነርሱ ጋር የሚደረገው ጦርነትም በርሱ እጅና በአመራሩ ስር መሆኑን በመገለጽ ‹ታገሱ፣ ተርጋጉ›› ሲል ያጸናቸዋል። ያረጋጋቸዋል።

﴿ إِنَّهُمۡ يَكِيدُونَ كَيۡدٗا ١٥ وَأَكِيدُ كَيۡدٗا ١٦ فَمَهِّلِ ٱلۡكَٰفِرِينَ أَمۡهِلۡهُمۡ رُوَيۡدَۢا ١٧ ﴾

‹‹እነርሱ (መካውያን አጋሪዎች) ሴራ ያውጠነጥናሉ። እኔም ተንኮላቸውን አመክናለሁ፤ እበቀላቸዋለሁም። ከሓዲያንን ቀን ስጣቸው፤ (ለመጥፋታቸው አትቸኩል)፤ ጥቂት ጊዜ ታገሣቸው።›› (አንቀጽ 15-17)

እነርሱ ያሴራሉ። አላህም ሴራቸውን እየተከታተለ ያመክናል። የጦርነቱ ባህሪ ይህን ይመስላል። ስለዚህም ለካህድያን ጥቂት ጊዜ ስጣቸው። ፍጻሜያቸውን ለማየት መቸኮል አያስፈልግም። የትግሉን ባህሪ እና ምንነቱን ተረድተሐል። ይህ ላንተ በቂ ነው። ጊዜ ከማግኘታቸው በስተጀርባ የላቀ ጥበብ መኖሩ እሙን ነው። ጥቂት ጊዜ ብቻ። የዱንያን እድሜ በሙሉ በሕይወት እንዲቆዩ ቢደረግ እንኳ ጥቂት ጊዜ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) አላህ ከምእራፉ መጨረሻ ላይ የማለባቸውን ነገሮች አውሳ።
2) ከአላህ ጠላቶች ጋር የሚደረገውን ጦርነት ትክክለኛ ባህሪ ግለጽ።

ምእራፍ ሁለት

አልሐዲሱ ሸሪፍ

የመጀመሪያው ሐዲስ

ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው

‹‹ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የነያውን ያገኛል፡፡ ስደቱ ወደ አላህ እና ወደ መልእክተኛው የሆነ ስደቱ ወደ አላህና መልእክተኛው ነው፡፡ ሊያገኛት ወዳለማት ዱንያ ወይም ሊያገባት ወደ ፈለጋት እንስት የተሰደደ ስደቱ ወደተሰደደበት ነገር ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አጠቃላይ ዓላማ

1) የዚህን ሐዲስ ክብደት ማብራራት፣
2) የኒያን ትርጉም ማስታወስ
3) በሁሉም ስራዎች ንያን ለአላህ ብቻ ማድረግና ማጥራት ያለውን ጠቀሜታና ክብደት መረዳት
4) የዚህን ሐዲስ መልእክት ምን ያህል ገቢራዊ እያደረገው እንደሆነ ማጤን

የሐዲሱ ክብደትና ጠቀሜታ

ሐዲሱ እጅግ ከፍተኛ ክብደት ከሚሰጣቸው ሐዲሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የእስልምና ሐይማኖት መሰረት ነው፡፡ አብዛኛው የእስልምና አህካሞች የሚሽከረከሩት በዚህ ሐዲስ ዙሪያ ነው፡፡ ኢማም አቡ ዳውድና ሻፊዒ፡- ‹ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው፣ ከሚለው ሐዲስ ውስጥ የእውቀት ሲሶው ይካተታል፡፡›› ብለዋል፡፡ ምክንያቱም ሰውየው በጎ ስራ የሚሰራው በቀልቡ፣ በአካሉና በምላሱ ሲሆን፣ የቀልብ ስራ (ኒያ) የሦስቱ አንድ ክፋይ ስለሆነ ነው፡፡

የቃላት ትርጉም እና መልእክት

ኒያት፡- ኒያት የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ሲሆን ማሰብ ማለት ነው፡፡ ሰፋ ባለ ትርጉሙ ሰውየው አንዳች ጥቅም ለማግኘት ወይም ጉዳትን ለመከላከል ይረዳኛል ወዳለው ስራ ልቦናው መነሳሳቱ ነው፡፡ በሸሪዓው ቴክኒካዊ አጠቃቀም መሠረት ደግሞ እንዲህ ተተርጉሟል፡-

‹‹ቀልብ የአላህን ውዴታ በመፈለግና ትእዛዙን ለመፈጸም ሲል አንድን ተግባር ለማከናወን መፍቀዱ (መወሰኑ) ነው፡፡

ስደት (ሂጅራ) ፡- ስርዎ ቃሉ ‹‹ሐጀረ›› ሲሆን ትርጉሙም አንድን ቦታ ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ነው፡፡ በሸሪዓው አጠቃቀም መሠረትም ለእምነት ተስማሚ ያልሆነን አስጊ ወይም የክህደት አገር ለቅቆ ሰላማዊ ወደሆነ አገር መሰደድ ነው፡፡ ከፊል ሶሐቦች መካን ለቀው ወደ ሐበሻ እንደተሰደዱት፡፡ እንዲሁም የክህደትን ሐገር በመተው ወደ ኢማን ሐገር መጓዝም ስደት ይባላል፡፡

ወደ አላህ፡- የርሱ ውዴታ ወደሚገኝበት አገር አስቦና ወስኖ መጓዝ ስደቱ ወደ አላህና ወደ መልእክተኛው ነው፡፡ ይቀበሉታል፡፡ ይመነዱታልም፡፡

ሊያገኛት ላሰባት ዱንያ፡- ሊያገኛት ላለማት ዱንያዊ ዓላማ ሲል የተሰደደ

አጠቃላይ መልእክት

ይህ ሐዲስ ለስራ መስተካከል ኒያን መመዘኛ አድርጎ ያቀርባል፡፡ ኒያ ከተስተካከለ ስራም ይስተካከላል፡፡ ኒያ ከተበላሸ ስራም ይበላሻል፡፡ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ስራ የተባለ ሁሉ›› ማለታቸው፡- ‹‹ስራ የሚስተካከለው ወይም ተቀባይነት የሚያገኘው›› ማለታቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ኢማም አቡ ሐኒፋ ሐዲሱን የተረዱት በዚህ መልክቱ ነው፡፡ ከስራዎች መካከል ነጃሳን ማስለቀቅ፣ የተቀማን ገንዘብ መመለስ፣ ስጦታን ማድረስና መሰል ተግባራት ለትክክለኛነታቸው የኒያ መስፈርት አያስፈልጋቸውም፡፡ ግና

ምንዳ ያስገኙ ዘንድ ወደ አላህ በመቃረብ ኒያ መከናወን ይኖርባቸዋል። ልክ እንደዚሁ አንድ ሰው ከአላህ ምንዳን በመከጀል እንስሳውን ቢመግብ ምንዳ ያገኛል። ግና ኒያው ንብረቱን መንከባከብ ከሆነ ምንዳ አይኖረውም። ከዚህ ምድብ ውስጥ የሙጃሂድ ፈረስ የተለየ ብይን ይሰጠዋል። ለጅሃድ ተግባር ከመደባት እርሱ እንድትጠጣ ሳይፈልግ ብትጠጣ እንኳ ምንዳ ያገኛል። በሶሂህ አልቡኻሪ ውስጥ ይህ ተጠቅሷል። ለሚስት የሚደረግ እንክብካቤም እንደዚሁ ነው። እንደዚሁ ሌላ ነገር ከነያ ግን አያገኝም።።።

ኒያ የተደነገገው የልምድ ክንውኖችን ከኢባዳ ለመለየት ነው። ወይም ደግሞ የኢባዳዎችን የተለያዩ ደረጃዎች ለመለየት ነው።

በመጀመሪያው ምሳሌ ከመስጊድ ውስጥ መቀመጥን ይመስል ነው። እረፍት በመፈለግ መስጊድ ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል። በዚህ ጊዜ ነገሩ ኢባዳ አይደለም። ኢዕቲካፍ ከነያ ደግሞ ኢባዳ ይሆንለታል። ይህን ልዩነት የፈጠረው ኒያ ነው። መታጠብም እንደዚሁ ነው። ለንጽህና ብሎ ካከናወነው ኢባዳ አይሆንም። በአንጻሩ አምልኮ ከነያበት ኢባዳ ይሆንለታል። እዚህም ላይ ልዩነቱን ያመጣው ኒያው ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፣ ለይዩልኝ፣ ለዘር ክብር እና ለጀግንነት ስለሚጋደሉ ሰዎች፡- ‹‹በአላህ መንገድ የተፋለመው የትኛው ነው?›› ተብለው ተጠይቀው ‹‹የአላህ ቃል የበላይ ትሆን ዘንድ የተገጋደለው፣ በአላህ መንገድ የተፋለመው እርሱ ብቻ ነው።›› በማለት መመለሳቸው ይህንኑ ይጠቁማል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

የሁለተኛው ምሳሌ፡- የኢባዳን የተለያዩ ደረጃዎች ለመለየት የኒያን ጠቀሜታ የሚያሳይ ሲሆን፣ አንድ ሰው የዙህርን ሶላት አስቦ ወይም ሱንና ለመስገድ አስቦ 4 ረከዐዎችን ሊሰግድ ይችላል። ልዩነቱን የፈጠረው ኒያ ብቻ ነው።

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ስደቱ ወደ አላህና ወደ መልእክተኛው የሆነ›› ማለታቸው ኒያና ዓላማውን ለመግለጽ ሲሆን፡- ‹‹ወደ አላህና

ወደ መልእክተኛው ይሆናል›› ማለት በሸሪዓው ብይን ይህው ዓላማው ተቀባይነት ያገኛል ማለት ነው።

ሊያገኛት ወዳለማት ዱንያ ወይም ሊያገባት ወደፈለጋት እንስት የተሰደደ ስደቱ ወደ ተሰደደበት ነገር ነው።›

ይህን አባባል የተናገሩበትን መነሻ በተመለከተ አንድ ታሪክ ተላልፏል። ይህውም የስደትን ምንዳ አስቦ ሳይሆን ኡም አልቀይስ የተባለች እንስት ለማግባት በመፈለግ ከመካ ወደ መዲና ተሰደደ። በዚህ የተነሳ ‹‹የኡም ቀይስ ስደተኛ›› ተባለ። (ጦበራኒ)

ጋብቻ ሸሪዓው ጽድቅ ከቸራቸው ነገሮች መካከል አንዱ ሆኖ እያለ እንዴት ከዱንያዊ ዓላማ ሊካተት ቻለ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። መልሱም ሰውየው የስደቱ አላማ እንስት ማግባት መሆኑን በግልጽ አሳውቆ አልተሰደደም። የስደቱን እውነተኛ ዓላማ በመደበቅ ለአላህና ለመልእክተኛው ሲል የተሰደደ በማስመሰሉ ለዚህ ስመሳይነቱ ነቀፌታ የተገባው ሆኗል።

‹‹ስደቱ ወደተሰደደበት ነገር ነው።›› ለምሳሌ በሐጅ ጊዜ ንግድንና ሐጅን ነይቶ ከቤቱ የወጣ ምንዳ አያገኝም ማለት ነው። ግና ይህ የሚሆነው የመጀመሪያ መነሻው፣ ወደ ሐጅ የቀሰቀሰው ዓይነተኛ ዓላማ ንግድ ከሆነ ነው። ዋነኛ ፍላጎቱና ኒያው ሐጅ ሆኖ እግረ መንገዱን ንግድ ቢያስብ ግን ምንዳ አይቀርበትም። ባይሆን ለሐጅ ብቻ አስቦ ቢሆን ኖሮ ከሚያገኘው ምንዳ ይጎድልበታል። ሁለቱንም በጣምራ አስቦ ከተጓዘ ደግሞ ምንዳ የማግኘት እድል ይኖረዋል። ምክንያቱም ስደቱ ለዱንያ ብቻ አይደለምና ምንዳ ሊያገኝም ይችላል። ምክንያቱም የአኼራን ስራ ከዱንያ ስራ ጋር ቀላቅሏልና። ሐዲሱ ብይኑን ያስተላለፈው ኒያን እና ዓላማን መሰረት አድርጎ በመሆኑ ሁለቱንም በጣምራ የነያ ዱንያን ብቻ ነይቷል ሊባል አይችልም። ልዑል የሆነው አላህ ይበልጥ አዋቂ ነው።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁም ነገሮች

- በጎ ስራ ለመስራት አስቦ በሽታ፣ ሞት እና መሰል አስገዳጅ ሁኔታዎች ያሰበውን ከመፈጸም ቢያሰናክሉት በኒያው ብቻ ምንዳ ያገኛል።
- ተግባር ያለ ኒያ ፋይዳ የለውም። ኒያ ግን ያለ ተግባር ምንዳ የሚያስገኝበት ሁኔታ አለ። ኒያ ለስራ ያለው ፋይዳ ነፍስ ለአካል ያላትን ፋይዳ ያህል ነው። አካል ያለ ነፍስ ሕልውና አይኖረውም። ነፍስ ደግሞ ያለ አካል በዚህ ዓለም መገለጽ አትችልም።
- ሐዲሱ በበጎ ስራዎቻችንና በኢባዳዎቻችን በመጭው ዓለም ምንዳ፣ በዚህች ዓለም ደግሞ ስኬት እናገኝ ዘንድ ኢኽላስ እንዲኖረን ያስተምረናል።
- ጠቃሚና በጎ የሆነ ስራ ሁሉ በኒያ፣ በኢኽላስና የአላህን ውዴታ በመሻት ሲፈጸም ኢባዳ ይሆናል።
- ኒያና ኢኽላስ ይኖርህ ዘንድ ሁሌም ጉጉና ትጉ ሁን።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) ‹‹ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው›› የሚለውን ሐዲስ ክብደት አብራራ።
2) የኒያን ቋንቋዊ እና ሸሪዓዊ ትርጉም ግለጽ
3) ኒያን ለአላህ ብቻ ማድረግ (ኢኽላስ) ያለውን ፋይዳ ዘርዝር
4) ሰውየው ምንዳ የሚያገኘው በኒያው መሠረት ነው። የምትሰራቸው በጎ ስራዎች ሁሉ ለአላህ ብቻ እንዲሆኑ ጥረት ታደርጋለህን? ይህን ጥረትህን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ጥቀስ።
5) የዚህን ሐዲስ መልእክት ምን የህል እየሰራህበት እንደሆነ አስረዳ።
6) የዚህን ሐዲስ መልእክት በገቢር ለማዋል ራስህን እንዴት እንደምታለማምድ አብራራ

ሁለተኛ ሐዲስ

ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን

ዑመር እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

ከአላህ መልእክተኛ ጋር ተቀምጠን እያለ ልብሱ በጣም የነጸና ጸጉሩ በጣም የጠቆረ አንድ ሰው መጣ። የጉዞ ምልክት አይታይበትም። ከመካከላችንም የሚያውቀው ሰው የለም። ከነቢዩ አጠገብ ተቀመጠ። ጉልበቶቹን ወደ ጉልበቶቻቸው አስጠጋ። መዳፎቹን ከጭኖቹ ላይ አኖረ። ‹‹ሙሐመድ ሆይ፣ ስለ ኢስላም ንገረኝ?›› ሲልም ጠየቀ። የአላህ መልእክተኛም ‹‹ኢስላም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድ መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከርህ፣ ሶላትን ደንቡን አሟልተህ መስገድህ፣ ዘካ መስጠትህ፣ ረመዷን መጾምህና የአላህንም ቤት ወደርሱ የመንገዝ አቅም ካለህ ሐጅ ማድረግህ ናቸው›› አሉት። ‹‹እውነት ብለሃል›› አላቸው። በድርጊቱ ተገረምን። ይጠይቃቸዋል፣ እውነት ብለሃል ይላቸዋልም። ‹‹ስለ ኢማን ንገረኝ?›› ሲልም ጠየቃቸው። ‹‹በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጽሐፍት፣ በመልእክተኞች፣ በመጨረሻው ቀንና በቀደር ደግም ይሁን ክፉ ማመንህ ነው›› በማለት መለሱለት። ‹‹እውነት ብለሃል›› አላቸው። ‹‹ስለ ኢህሳን ንገረኝ?›› በማለትም ጠየቃቸው። ‹‹አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው። አንተ ባታየውም እርሱ ያይሐል›› አሉት። ‹‹ስለ ጊዜዋ (ስለ ትንሳኤ) ንገረኝ?›› አላቸው። ‹‹ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ ስለ እርሷ አዋቂ አይደለም›› አሉት። ስለ ምልክቶቿ ንገረኝ?›› አላቸው። ‹‹ባዶ እግራቸውን እና እርቃን የሆኑ ድሃ ፍየል ጠባቂዎች በሕንጻ ግንባታ ሲፎካከሩ ማየትህ ነው›› አሉት። ከዚያም ሄደ። ጥቂት ጊዜ ቆየን። ነቢዩም ‹‹ዑመር ሆይ፣ ይህ ጠያቂ ማን እንደሆነ ታውቃለህ?›› አሉኝ። ‹‹አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ›› አልኳቸው። ‹‹ጅብሪል ነው። ሐይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ወደናንተ ዘንድ መጣ።›› (ሙስሊም)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) የዚህን ሐዲስ ክብደት ማብራራት

2) ኢስላም፣ኢማንና ኢህሳን ምን እንደሆኑና የቂያማን ምልክቶች ማብራራት

3) ከሐዲሱ የሚገኙ ፋይዳዎችን መዘርዘር

የሐዲስ ክብደትና ጠቀሜታ

ኢብን ደቂቅ አል ዒዲ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

ይህ ሐዲስ ግልጽም ስውርም የሆኑ ስራዎችን መሠረቶች ያካተተ ትላቅ ሐዲስ ነው፡፡ የሸሪዓ እውቀቶች ሁሉ ወደርሱ የሚያደርሱ፣ የርሱ ምንዛሬዎች ናቸው፡፡ የሱንናን እውቀት ሁሉ ሰብስቦ ይዟል፡፡ ለሱንና እውቀት ልክ እንደ እናት ማለት ነው፡፡ የፋቲሐ ምእራፍ የቁርአንን ዓይነተኛ መልእክቶች ሁሉ የያዘች በመሆኗ ‹‹የቁርአን እናት›› እንደተሰኘችው ሁሉ ይህም ሐዲስ የሌሎች ሐዲሶች መልእክቶች ሁሉ አስኳል ከመሆኑ አኳያ ‹‹የሱንና እናት›› ሊሰኝ ይችላል፡፡

የቃላት ትርጉምና መልእክት

መዳፎቹን በጉልበቶቹ ላይ አኖረ፡- ከራሱ ጉልበቶች ላይ በማኖር ስርዓት ያለው አቀማመጥ ተቀመጠ፡፡ በነሳኢ ዘገባ መሠረት ደግሞ ‹‹እጆቹን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጉልበቶች ላይ አስቀመጠ፡፡›› የሚል ተወስቷል፡፡ ግና የመጀመሪያው ዘገባ የተሻለ ጥራት ያለው ነው፡፡

በድርጊቱ ተገረምን፡፡ ይጠይቃል፣ ‹‹እውነት ተናገርክ›› ሲልም ይደመድማል፡- የአዋቂ አይነት ጥያቄ እየጠየቀ ‹‹እውነት ብለሐል›› በማለት መልሱን ያጸድቃል፡፡ ወይም ጥያቄው አላዋቂ ያስመስለዋል፡፡ መልሶቹን ማጽደቁ ደግሞ አዋቂነቱን ያመለክታል፡፡

‹‹በአላህ ማመንህ››፡- ኢማን በቋንቋ ደረጃ ልቦና አንድን ነገር በማያጠራጥር ሁኔታ መቀበሉን አመልካች ሲሆን፣ በሸሪዓው ደግሞ

ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ያመጡትን መልእክት ሙሉ በሙሉ መቀበል ነው።

የቂያማ ምልክቶች፡- ቂያማ ከመከሰቷ በፊት ቀድመው የሚታዩ ምልክቶች ናቸው።

ባሪያ ጌታዋን ትወልዳለች፡- ትርጉሙም ቂያማ ሲቃረብ ከእንስት ባሪያ የመውለድ ልምድ ይበዛል። ልጆቹ ልክ እንደ አባቶቻቸው ነጻ ሰዎች ስለሚሆኑ የእናቶቻቸው ጌቶች (ባለቤቶች) ይሆናሉ። በሕግ ደረጃ የአባት ባሪያ ባለቤትነቱ ወደ ልጅ ይሸጋገራል። ከዚህ አኳያ ልጇ ጌታዋ ይሆናል።

ጥቂት ጊዜ ቆየሁ፡- በሌላ ዘገባ እንደተወሳው ለሦስት ቀናት ያህል ከነቢዩ ርቄ ቆይቼ አገኘኋቸው።

አጠቃላይ መልእክት

ኢስላም ምንድን ነው?፡- ኢስላም ማለት በቋንቋ ደረጃ ለአላህ መታዘዝ እና እጅ መስጠት ማለት ነው። በሸሪዓው ትርጉሙ መሠረት ደግሞ ከአምስት መሠረቶች ላይ የታነጸ ሐይማኖት ነው። እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እና ሙሐመድም መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን ደንቡን አሟልቶ መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ የረመዷንን ወር መጾም፣ እንዲሁም አቅሙ ላለውና መንገጎና ስንቅ፣ እንዲሁም ለሐጅ ደርሶ እስኪመለስ የቤተሰቡን ቀለብ የሚችል ሰው በእድሜ ልክ አንድ ጊዜ የአላህን ቤት መሐጀጅ ናቸው።

ኢማን ምንድን ነው?፡- ኢማን በቋንቋ ደረጃ አንድን ነገር እውነት ብሎ መቀበል ሲሆን፣ በሸሪዓው አተረጓጎም መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ያጠቃልላል። የአላህን ሕልውና አንድነት እና አጋር የሌለው መሆኑን ማመን፣

መላኢካ የሚባሉ፣ የአላህ የተላቁ ባሮች የሆኑ፣ የታዘዙትን ያለ ተቃውሞ የሚፈጽሙ፣ ከብርሃን የተሰሩ፣ የማይበሉ፣ ጾታ የሌላቸው፣

የማይራቡ፣ ቁጥራቸውን ከአላህ ውጭ ሌላ ማንም የማያውቃቸው የአላህ ፍጡራን እንዳሉ ማመን፤

ከአላህ በተወረዱ መለኮታዊ መጽሐፍት ማመንና ሳይበረዙና ሳይከለሱ በፊት የአላህ ሸሪዓዎች እንደነበሩ መቀበል፤

አላህ የሰው ልጆችን ወደ ቅን ጎዳና ለመምራት በመረጣቸውና መለኮታዊ መጽሐፍትን ባወረደላቸው የአላህ መልእክተኞች ሁሉ ማመን፤ እንዲሁም መልእክተኞች ከሐጢአት የተጠበቁ ሰዎች መሆናቸውን ማመን።

በመጭው ዓለም መኖር፣ አላህ ሰዎችን ከመቃብር ለማስነሳት በዚህች ዓለም የሰሩትን ስራ እንደሚመረምር፣ መርምሮም መልካም ከሆነ እንደሚመነዳቸው፣ ክፉ ከሆነም እንደሚቀጣቸው ማመን፤

በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ የሚከሰት ማናቸውም ነገር በአላህ ውሳኔና ፈቃድ፣ እንዲሁም እርሱ ለሚያውቀው ጥበብ እንደሚከሰት ማመን፤

የእምነት መሠረቶች እነዚህ ናቸው። በነርሱ ያመነ ዳነ። ስኬታማም ሆነ። ያስተባበላቸው መንገድ ሳተ። ከሰረም።

ኢህሳን ምንድን ነው?፦ አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ፣ ማለትም አላህን በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) በተሟላ አኳኋን (ኢትቃን) እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው። ይህን ባትችል እንኳ እርሱ ካንተ የሚመነጨ ኢምንትም ይሁኑ ትልቅ ነገሮች ሁሉ እንደሚያይ ማስታወስ ይገባሐል። ሙስሊም ባሰፈሩት ዘገባ፦ ‹‹አላህን እንደምታየው አድርገህ መፍራትህ ነው›› የሚል ቃል ሰፍሯል።

ቂያማና ምልክቶቿ

ቂያማ የምትከሰትበትን ትክክለኛ ጊዜ ከአላህ ውጭ የሚያውቅ የለም። ከፍጡራኑ ለአንዱም፣ ለመልእኩም ይሁን ለመልእክተኛው አላካፈለም። ለዚህም ነው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጅብሪልን፦ ‹‹ተጠያቂው ከጠያቂው የተሻለ

እውቀት የለውም፡፡›› ያሉት፡፡ ይህም ሆኖ ቂያማ ከመከሰቷ በፊት እውን የሚሆኑ አንዳንድ ምልክቶችን ነግረውታል፡፡

1) የዘመን መበላሸት፣ የስነ ምግባር መዳከም፣ ብዙዎች ልጆች ወላጆቻቸውን ያንገላታሉ፡፡ ይቃረኗቸዋል፡፡ ከነርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነትም ጌታ ከባሪያው ጋር ያለው ዓይነት ይሆናል፡፡

2) ነገሮች የተገላቢጦሽ ይሆናሉ፡፡ አጀንዳዎች ይደበላለቃሉ፡፡ በመሆኑም ርካሽና ወራዳ ሰዎች የሕዘቦች መሪ ይሆናሉ፡፡ ሐላፊነቶች ተገቢ ላልሆኑ ሰዎች ይሰጣሉ፡፡ በሰዎች እጅ ገንዘብ ይበዛል፡፡ አባካኝነትም ይበረክታል፡፡ ሰዎች በሚገነቧቸው ሕንጻዎች ርዝመት፣ ባሏቸው ቁሳቁሶች ይፎካከራሉ፡፡ በድህነት እና በችግር ውስጥ በሌሎች ምጽዋትና ድጋፍ ይኖሩ የነበሩ ዘላኖች፣ ፍየል ጠባቂዎችና መሰል ዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሰዎች የበላይ፣ የጉዳዮቻቸው ተቆጣጣሪዎች ይሆናሉ፡፡

ከሐዲሱ የሚቀሰሙ ትምህርቶች

ስለ እውቀት መጠየቅ፡- ሙስሊም ለዱንያው ወይም ለአኼራው የሚጠቅመውን ብቻ ይጠይቃል፡፡ ጥቅም አልባ የሆኑ ነገሮችን የመጠየቅም ይታቀባል፡፡ ከአንድ የትምህርት ስብስብ ላይ የተገኘና ታዳሚዎች ሊያውቁት ይገባል የሚለው ጉዳይ ያለው፣ ያን ጉዳይ ከመካከላቸው አንዱ ካልጠየቀ፣ እርሱ ቢያውቀው እንኳ- በመጠየቅ በመልሱ ተሳታፊዎች እንዲጠቀሙ ሊያደርግ ይገባል፡፡ የማያውቀውን ነገር የተጠየቀ ‹‹አላውቀውም›› በማለት የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ማድረጉ ጥንቁቅነቱን፣ አላህን ፈሪነቱንና አዋቂነቱን ያመለክታል፡፡

ጥያቄና መልስ፡- ከጥንት እስከ ዛሬ ውጤታማ የማስተማር ስልት ነው፡ ፡ በነቢዩ ሐዲሶች ውስጥ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል ተስተውሏል፡፡ ምክንያቱም ጥያቄ የአድማጮችን ስሜት ይስባል፡፡ ትክክለኛውን መልስ ለመስማትም አእምሯዊና ስነ ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡

አለባበስንና ገጽታን ማሳመር፡- ወደ መስጊድና ዒልም ወደሚሰጥበት ቦታ ሲሄዱ አለባበስን ማሳመር፣ የአቀማመጥ ስርዓትን መጠበቅ፣ ለመምህርና ለተማሪ ስርዓታማ ግኑኝት መገዛት ተገቢ ነው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የሐዲሱን አስፈላጊነት እና ክብደት አብራራ።
2) የኢስላም፣ የኢማን፣ እና የኢህሳንን ትርጉምና ይዘት፣ እንዲሁም የቂያማን ምልክቶች የአላህ መልእክተኛ ከሰጡት ማብራሪያ አኳያ ዘርዝር
3) በሐዲሱ ውስጥ የመማር ማስተማር ስርዓት ተቀምጧል። ይህን ስርዓት እና ከነርሱ ምን እንደተማርክ ግለጽ።
4) በሐዲሱ ውስጥ ለስኬታማ የማስተማር ሂደት ጠቃሚ የሆነ አንድ ስልት ተጠቁሟል። እርሱን አውሳ። በተጨባጭ ግላዊ ሕይወትህ ውስጥ ትጠቀምበታለህን? አብራራ።
5) ኢስላም ተከታዮቹ መልካም ገጽታ እንዲኖራቸው ማበረታታቱን የሚጠቁም መልእክት በዚህ ሐዲስ ውስጥ ሰፍሯል። አብራራ።

* * *

ሦስተኛ ሐዲስ

የእስልምና መሠረቶችና ታላላቅ ምሰሶዎች

የአላህ መልእክተኛ ተከታዩን ሲናገሩ ሰምቻለሁ በማለት አብደላህ ቢን ዑመር ቢን አል'ኻጣብ አስተላልፈዋል፡- ‹‹እስልምና ከአምስት መሠረቶች ላይ ታንጿል፡፡ እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና መሐመድም መልእክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ የአላህን ቤት መሐጀድና የረመዳንን ወር መጾም ናቸው፡፡ ›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ኢስላም የታነጸባቸውን መሠረቶች ማዘርዘር

2) እነዚህን መሠረቶች እያንዳንዳቸውን ማብራራት

3) በእስልምና የኢባዳን ዓላማ መግለጽ

4) ከሐዲሱ ምን እንደተማሩ ማስረዳት

5) ይህ ሐዲስ በስራዎቹ ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እንዳሳደረ ማስረዳት፡፡

አጠቃላይ መልእክት

የእስልምና ግንብ፡- የአላህ መልእክተኛ () እርሳቸው ያመጡትንና ሰዎች ከክህደት ክልል ወጥተው፣ ከእሳት ርቀው፣ ለጀነት ተገቢ የሚሆኑበትን መለኮታዊ መልእክት በጽኑ መሠረት ላይ በታነጸ ግንብ መስለውታል፡፡ ይህ ግንብ የቆመባቸውን መሠረቶችንም ዘርዝረዋል፡-

1) ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና መሐመድም የርሱ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር፡፡ ትርጉሙም የአላህን ሕልውናና አንድነት ማጽደቅ፣ እንዲሁም የነቢዩ መሐመድን ነብይነት እና ተልእኮ መቀበል ነው፡፡ ይህ መሠረት ለሌሎች የእስልምና ምሰሶዎች እንደ

መሠረት የሚቆጠር ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ላኢላሐ ኢለላህ ያለ ጀነት ገባ።›› (በዛር የዘገቡት ሶሂህ ሐዲስ)

2) ሶላትን ደንቡን አሟልቶ መስገድ፡- ትርጉሙ ሶላትን ደንቡንና ወቅቱን ጠብቆ፣ መስፈርቶችን አሟልቶ፣ ግዴታዎችን፣ ሱንናዎችን እና አደቦችን በትክክል አከናውኖ፣ በስብእና ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያሳድርና ከእኩይ ድርጊቶች እንዲርቅ ሊያደርግ በሚችልበት አኳኋን መስገድ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَۖ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِۗ ﴾ العنكبوت: ٤٥

‹‹ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከፀያፍና እኩይ አድራጐቶች ትጠብቃለችና።›› (አል አንከቡት 45)

3) ዘካ መስጠት፡- የግዴታ መጠን (ኒሷብ) የደረሰ እና ዘካ ለመክፈል መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ያሟላ ገንዘብ ያለው ሰው ለድሆችና ለሌሎች ተገቢ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከዚያ ከገንዘቡ የተወሰነ መጠን መስጠቱ ዘካ ይባላል።

4) ሐጅ፡- በሐጅ ወራት፣ ማለትም በሸዋል፣ በዙል ቂእዳ፣ እና በዙል ሂጃ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ውስጥ የአላህን ቤት ለመጎብኘት በመሻት ተጉዞ የአላህ መልእክተኛ ያብራሩትን ስርዓት መፈጸም ሐጅ ይባላል። ሐጅ ለግለሰብም ሆነ ለማሕበረሰብ በርካታ ፋይዳዎችን የሚያስገኝ፣ በአካልና በገንዘብ የሚፈጸም ኢባዳ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ በተለያዩ ሐገሮች ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች እንዲገናኙ ጥሩ አጋጣሚ የሚፈጥር ታላቅ አለማቀፋዊ ኢስላማዊ ጉባኤ ነው። ይህም ስለሆነ የሐጅ ምንዳ ትልቅ ሆኗል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹ተቀባይነት ያገኘ ሐጅ ከጀነት ውጭ ሌላ ምንዳ የለውም።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሐጅ ግዴታ የተደረገው በ6ኛው ዓመተ ሂጅራ በተከታዩ የቁርአን መልእክት ነው፡-

﴿ وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلۡبَيۡتِ مَنِ ٱسۡتَطَاعَ إِلَيۡهِ سَبِيلٗاۚ ﴾ آل عمران: ٩٧

‹‹ ቤቱን -ወደርሱ መንገዝ ለሚችሉ ሁሉ- ይጐበኙ ዘንድ አላህ በሰዎች ላይ ግዴታ አድርንል።›› (አሊ ዒምራን 97)

5) ረመዷን መጾም፡- የረመዷን ጾም በሁለተኛው ዓመተ ሂጅራ በተከታዩ የቁርአን መልእክት ግዴታ ተደረገ፡-

﴿ شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ ﴾ البقرة: ١٨٥

‹‹(የረመዷን ወር ለሰው ዘር መመሪያ የሆነው፥ (መለኮታዊ) አመራርና (እውነት ከሐሰት) ለመለየት የሚያስችሉ ግልጽ አናቅጽ የሰፈሩበት ቁርአን የወረደበት (ወር) ነው። ከመካከላችሁ በዚህ ወር ውስጥ የተገኘ (ወሩን) በጾም ማሳለፍ አለበት።›› (አል በቀራህ 185)

ጾም ነፍስን የሚያጸዳ፣ መንፈስን የሚያመጥቅ፣ ለአካላዊ ጤንነትም ጠቃሚ የሆነ ኢባዳ ነው። የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲል በትክክል ያከናወነው ወንጀሉ ይማርና ጀነትም ይገባ ዘንድ ሰበብ ይሆንለታል፡

* * *

በዚህ ሐዲስ የተወሱት የእስልምና ዋናዋና መሠረቶች ሲሆኑ፣ ማሟያዎች ለምሳሌ ሱናዎችና የሚወደዱ ነገሮች የግንቡ ማስዋቢያዎች ናቸው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ማለታቸው በሐዲስ ተመልክቷል፡-

‹‹ኢማን ከሰባ በላይ ቅርንጫፎች አሉት። ከፍተኛ ላኢላሐ ኢለላህ የሚለው ሲሆን ዝቅተኛው ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ ነው።››

የኢባዳ ዓላማ፡- ኢስላም ከኢባዳ የሚፈልገው ላያዊ ገጽታውን ወይም ቅርጹን ሳይሆን ዓላማውን እና አስኳሉን ነው። ሶላት ከመጥፎ ነገሮች

ካላቀበች፣ ጾምም ባለቤቱን ከውድቅ ንግግርና ስራ ካልታደገ፣ ሐጅና ዘካም ለይዩልኝና ይስሙልኝ ከተፈጸሙ ፋይዳ የላቸውም። ይህ ማለት ግን እነዚህን ኢባዳዎች ፍሪያቸው ካልታየ አናከናውናቸው ማለት ሳይሆን በኢኽላስና ዓላማቸውን በሚያሳካ አኳኋን ለመፈጸም መትጋት እንዳለብን ለማሳየት ነው።

የኢማን ዘርፎች፡- ኢስላም ማለት በሐዲሱ ውስጥ የተወሱት ነገሮች ብቻ አይደሉም። ሐዲሱ በነዚህ የተወሰነው የተለየ ክብደትና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ክንውኖች ስለሆኑ ነው። እስልምና ከነዚህ ሌላ በርካታ በጎ ምግባራትን አካቷል። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ኢማን ከሰባ በላይ ዘርፎች አሉት።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

የሐዲሱ ጠቀሜታ፡- ኢስላም እምነት ብቻ ሳይሆን ተግባርም ጭምር መሆኑን ይህ ሐዲስ ያስተምራል። ስራ ያለ እምነት ጠቀሜታ እንደሌለው ሁሉ እምነትም ያለ ስራ ሕልውና የለውም።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) ኢስላም የተገነባባቸውን መሠረቶች ዘርዝር
2) የእያዳንዳቸውን ትርጉምና መልእክት አብራራ
3) በእስልምና የኢባዳን ዓላማ አብራራ
4) ከዚህ ሐዲስ የተማርከውን ቁም ነገር አስረዳ
5) ይህ ሐዲስ በስራዎችህ ላይ ምን የህል ተጽእኖ እንዳሳደረ ግለጽ፣

* * *

አራተኛ ሐዲስ

የሰው ልጅ አፈጣጠር እርከኖችና ፍጻሜው

አቡ አብዱረህማን አብደላህ ቢን መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከናንተ አንዳችሁ በእናቱ ሆድ ውስጥ ለ40 ቀናት የዘር ፈሳሽ፣ ለዚሁ ያህል ጊዜ የረጋ ደም፣ ለዚሁ ያህል ጊዜም የተላመጠ ስጋ ሆኖ ይቆያል። ከዚያም አላህ መላኢካ ልኮ ነፍስ ያስገባለታል። መላኢካው አራት ተግባራትን እንዲያከናውን ማለትም ሲሳዩን፣ እድሜውን፣ ስራውንና እድለ ቢስ ወይም እድለኛ መሆኑን እንዲመዘግብ ይታዘዛል። ብቸኛ አምላክ በሆነው አላህ እምላለሁ፣ ከናንተ አንዳችሁ የጀነት ሰዎችን ስራ ሲሰራ ይቆይና በርሱና በሷ መካከል የአንድ ክንድ ያህል ርቀት ሲቀረው የተጻፈው ይቀድመውና የእሳት ሰዎችን ስራ በመስራት ወደርሷ ይገባል። ከናንተ አንዳችሁም የእሳት ሰዎችን ስራ ሲሰራ ይቆይና በርሷና በርሱ መካከል የአንድ ክንድ ያህል ርቀት ሲቀረው የተጻፈው ይቀድመውና የጀነት ሰዎችን ስራ በመስራት ወደርሷ ይገባል።››

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) የሰውን ልጅ አፈጣጠር የተለያዩ እርከኖች ማስታወስ
2) አላህ የፍጡራኑን ሁኔታ፣ ሳይፈጥራቸው በፊት የማወቁ እውነታ ማብራራት
3) ለመልካም ፍጻሜ እንደሚያበቃንና ከክፉ ፍጻሜ እንዲጠብቀን አላህን መለመን
4) ይህን ሐዲስ በገቢር ለማዋል ማከናወን ያለበትን ተግባር መዘርዘር፣

የሐዲሱ አስፈላጊነትና ክብደት

የሰውን ልጅ ጠቅላላ ሁኔታ በውስጡ ያካተተ ታላቅ ሐዲስ ነው። ይህውም መነሻውን፣ ፍጻሜውንና በመካከላቸው ያለውን የሕይወቱን ሁኔታ ይሏል። መነሻው አፈጣጠሩ ሲሆን፣ ፍጻሜው እድለቢስ ወይም እድለኛ መሆኑ ነው። በመካከላቸው ያለው ሕይወቱ ደግሞ የሚሞትበት ቀን፣ በሕይወት ውስጥ የሚያከናውናቸው ተግባራት እና ሲሳዩ ናቸው።

አጠቃላይ መልእክት

በማሕጸን ውስጥ የጽንስ የሚያልፍባቸው እርከኖች፡- ይህ ሐዲስ እንደሚያመለክተው ጽንስ በ120 ቀናት ውስጥ በሦስት እርከኖች ያልፋል። በመጀመሪያዎቹ አርባ ቀናት የዘር ፈሳሽ እንደሆነ ይቆያል። በቀጣዮቹ አርባ ቀናት የረጋ ደም ይሆናል። በሦስተኛው አርባ ቀናት የተላመጠ ስጋ ቅርጽ ይይዛል። ከ120 ቀናት በኋላ መላኢካ ‹‹ሩህ›› ያስገባለታል። በሐዲሱ የተወሱትን አራት መልእክቶችም ይጽፋል።

አላህ የሰውን ልጅ ‹‹ሁን›› ብሎ መፍጠር እየቻለ በነዚህ እርከኖች እንዲያልፍ የማድረጉ ጥበብ የሰው ልጅ አፈጣጠር በዙሪያው እንዳለው ሰፊ ዩኒቨርስ የምክንያትና ውጤትን ስርዓት ተከትሎ እነዲሄድ ለማድረግ ሲሆን፣ ይህ የአላህን ችሎታ ይበልጥ ገላጭ ነው።

በተጨማሪም አላህ ለባሮቹ በሁሉም ጉዳዮቻቸው እርጋታ እንዲማሩ፣ ከችኮላ እንዲርቁ ለማስተማር ያደረገው ነው። የሰው ልጅ ውስጣዊ ምሉእነትን የሚጎናጸፈው ልክ እንደ አካላዊ እሱነቱ በሂደት እና የተለያዩ እርከኖችን አልፎ መሆኑን ሐዲሱ ያስተምራል። የስብእና እድገቱም ልክ እንደ አካሉ የተለያዩ እርከኖንና የእድገት ደረጃዎችን ማለፉ የግድ ነው።

የነፍስ መነፋት፡- ጽንሱ ነፍስ የሚዘራው ከተጸነሰ ከ120 ቀናት በኋላ መሆኑን ዑለሞች ተስማምተዋል። 4 ወራትን አጠናቆ ከ5ኛው ወር መግቢያ ላይ መሆኑ ነው። ይህ እውነታ ከተሞክሮ ይታወቃል። ከዚህ ግንዛቤ ላይ በርካታ ፊቅሐዊ ብይኖች (አህካሞች) ይታነጻሉ። ለምሳሌ ‹‹አስቲልሐቅ››፣ የቀለብ ሁኔታ ወዘተ። ጽንሱ በዚህ ጊዜ መንቀሳቀስ

ይጀምራል ተብሎ ስለሚታመን። ባሏ የሞተባት እንስት አራት ወራት ከ10 ቀናት የእፎይታ ጊዜ (ኢዳ) እንድትጠብቅ የመደረጉ ጥበብም ይህ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ የእርግዝና ምልክት ባይታይባት እንኳ ማሕጸኗ ጽንስ መያዙ ወይም አለመያዙ ይታወቃል።

‹‹ሩህ›› የሰው ልጅ ሕያው የሚሆንበት ረቂቅ ነገር ሲሆን፣ ምንነቱን አላህ ብቻ የሚያውቀው ነገር መሆኑ በቁርአን ተነግሯል፡-

﴿ وَيَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلرُّوحِۖ قُلِ ٱلرُّوحُ مِنۡ أَمۡرِ رَبِّي وَمَآ أُوتِيتُم مِّنَ ٱلۡعِلۡمِ إِلَّا قَلِيلٗا ٨٥ ﴾ الإسراء: ٨٥

‹‹ስለ ሩሕ (መንፈስ) ይጠይቁሃል። "ሩሕ የጌታዬ (እርሱ ብቻ የሚያውቀው) ጉዳይ ነው። ከእውቀት ጥቂትን እንጅ አልተሰጣችሁም።" በል።›› (አል ኢስራእ 85)

ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል፡-

‹‹የዘር ፈሳሽ ከማሕጸን ላይ ሲያርፍ መልአኩ በመዳፉ ይይዘውና፡- ይጸነሳል ወይስ አይጸነስም? በማለት አምላክን ይጠይቀዋል። አይጸነስም ካለው ደም አድርጎ ወደ ማህጸን ይወረውረዋል። ጽንስም አይሆንም። ይጸነሳል ካለው ደግሞ፡- ወንድ ነው ሴት? እድለኛ ነው እድለ ቢስ? ሲሳዩና የሚሞትበት ጊዜና ቦታስ? በማለት ይጠይቃል። ወደ እናት መዝገቡ ሂድ። ይህን ሁሉ እዚያው ታገኛለህ፣ ይባላል። ይሄድና ያገኘዋል። ይቀዳዋልም። ባህሪውን ሁሉ አስርጾ እስኪያጠናቅቅ ድረስ መዝገቡ ከርሱ ጋር ይቆያል።

ለዚህም ነው እድለኛነት ከመወለድ በፊት የሚገኝ እጣ ፈንታ ነው የሚባለው።

አላህ የፍጡራኑን ሁኔታ ከመፈጠራቸው በፊት ያውቃል፡- ሙእሚን ወይም ካሐዲ፣ በጎ ወይም አመጸኛ፣ እድለቢስ ወይም እድለኛ መሆናቸው በአላህ እውቀትና ፈቃድ ስር ያሉ ነገሮች ናቸው። የሰዎች እጣ ፈንታ ቀድሞውኑ መጻፉን የሚያመለክቱ ሐዲሶች በርካታ ናቸው።

ቡኻሪ አሊ ቢን አቢ ጧሊብን ዋቢ አድርገው ባሰፈሩት ዘገባ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እያንዳንዷ ነፍስ በጀነት ወይም በእሳት ውስጥ ቦታዋ ተዘጋጅቷል። እድለኛ ወይም እድለ ቢስ የመሆኗ ነገርም ተጽፏል።››

አንድ ሰውም፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ስለዚህ ምንም ነገር መስራት ትተን በመቀመጥ የተጻፈውን እንጠባበቅን?›› ሲል ጠየቃቸው። ‹‹ስሩ። ሁሉም ለተፈጠረለት እጣ ፈንታ የተገራ ነው። እድለኞች የበጎ ሰዎችን ስራ ለመስራት የተገሩ ናቸው። እድለ ቢሶች ደግሞ የመጥፎ ሰዎችን ስራ ለመስራት የተገሩ ናቸው።›› አሉና ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፡-

﴿ فَأَمَّا مَنْ أَعْطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ۝٥ وَصَدَّقَ بِٱلْحُسْنَىٰ ۝٦ ﴾ الليل: ٥ - ٧

‹‹(ገንዘቡንም፥ ሕይወቱንም ለአላህ) የሰጠና (የአላህን ቅጣትና ቁጣ) የፈራ፤ በ"አል-ሑስና" ያመነም፣›› (አልለይል 5-6)

ይህም ሆኖ ግን የአላህ እውቀት የሰውን ልጅ መርጦ የመስራት ነጻነትና ችሎታ አይቃረንም፡ ምክንያቱም እውቀት ወደፊት የሚሆነውን ከሳች እንጅ በሰውየው ላይ አንዳች ተጽእኖ የሚያደርግ አይደለም። አላህ እምነትንና በጎ ስራን አሟል። ከክህደትና ከወንጀልም ከልክሏል። ይህ፣ የሰውን ልጅ መርጦ የመስራት ነጻነት ያረጋግጣል። ካልሆነማ የአላህ ትእዛዝና እቀባ ጨዋታ ይሆናል። ይህ ደግሞ ፈጽሞ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَنَفْسٍ وَمَا سَوَّىٰهَا ۝٧ فَأَلْهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقْوَىٰهَا ۝٨ قَدْ أَفْلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ۝٩ وَقَدْ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ۝١٠ ﴾ الشمس: ٧ - ١٠

‹‹በነፍስና አስተካክሎ (ኢስላማዊ ተፈጥሮ አስይ5) በፈጠራት፤ አመጽዋን (የጥመትን ጐዳና) እና ፍርሃትዋን (የጽድቅን ፍኖት) ባሳወቃት (አምላክ) እምላለሁ። (ነፍሱን አላህን በማምለክና ከኃጢአት

በማቀብ) ያዐዳት ስኬታማ ሆኑ። (በኃጢአት) የሸፈናት ከሰረ።››› (አል ሸምስ 7-10)

በቀደር ማመካኘት፦ አላህ በርሱ እንድናምንና እንድንታዘዘው አዞናል። ከክህደትና ከወንጀልም ከልክሎናል። የእኛ ሐላፊነት ይህ ነው። በኛ ላይ የተጻፈውንና የተወሰነውን ነገር በተመለከተ ሚስጥር በመሆኑ የምናውቀው ነገር የለም። በርሱ ጉዳይም ተጠያቂነት የለብንም። ስለዚህም መንገድ የሳቱ ወገኖች፣ ካህድያንና ወንጀለኞች ለጥፋታቸው የአላህን ውሳኔና ፈቃድ (ቀደር)፣ እንዲሁም ጥፋቱ ከመከሰቱ በፊት ቀድሞ የጻፈው መሆኑን በምክንያትነት ሊያቀርቡ አይገባም።

﴿ وَقُلِ ٱعۡمَلُواْ فَسَيَرَى ٱللَّهُ عَمَلَكُمۡ وَرَسُولُهُۥ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۖ ﴾ التوبة: ١٠٥

‹‹ሥሩ፤ አላህ ሥራችሁን ያያል። መልዕክተኛውና አማኞችም (እንዲሁ ምግባሮቻችሁን ይመለከታሉ)።››› (አል ተውባህ 105)

የተወሰነው ነገር እውን ከሆነ በኋላ ግን በቀደር ማመካኘት ይፈቀዳል። ምክንያቱም ሙእሚን የአላህን ውሳኔ በጸጋ ይቀበላል፣ በዚህ ባህሪውም ውስጣዊ መረጋጋትንና እርካታን ያገኛል።

አንድ ሰው በጎ ስራዎችን ወይም ክፉ ስራዎችን ሁሉ ሲሰራ ቢታይ እንኳ ጀነት ወይም እሳት መግባቱን በእርግጠኝነት መናገር እንደማይቻል ሐዲሱ ያመለክታል። ስለዚህም ፍጻሜ የማይታወቅ በመሆኑ በበጎ ስራ መኮፈስና መመካት አግባብ አይደለም። እያንዳንዱ ሰው መልካም ፍጻሜ ይሰጠው ዘንድ አላህን መለመን፣ ከክፉ ፍጻሜ እንዲጠብቀውም ዘወትር መማጸን ይገባዋል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) በሐዲሱ የተብራራውን የሰው ልጅ የአፈጣጠር እርከኖች አውሳ

2) የሰው ልጅ አፈጣጠር በሐዲሱ በተጠቀሰው መልክ በእርከን የመሆኑ ጥበብ ምንድን ነው?

3) የሰው ልጅ በተለያዩ እርከኖች ከመፈጠሩ እውነታ ምን እንማራለን?

4) ባሏ የሞተባት እንስት የእፎይታ ጊዜ (ኢዳ) አራት ወራት ከ10 ቀናት የመሆኑ ሚስጥር ምንድን ነው?

5) በዚህ ሐዲስ እንደተገለጸው የስራዎች ምንነት ከፍጻሜያቸው ላይ መሆኑን አስረዳ

6) ይህን ሐዲስ በማወቅህ የቀሰምከው ተጨባጭ ትምህርት ምንድን ነው?

* * *

አምስተኛ ሐዲስ

እኩይ ነገሮችንና አዳዲስ ፈጠራዎችን ማውገዝ

የአማኞች እናት አኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በዚህ በጉዳያችን ውስጥ የርሱ አካል ያልሆነን አዲስ ነገር የጨመረ ጭማሬው ውድቅ ነው፡፡››

በሙስሊም ዘገባ መሠረትም፡- ‹‹የኛ ፈቃድ የሌለበትን አዲስ ስራ የሰራ ተግባሩ ውድቅ ነው፡፡›› ተብሎ ተዘግቧል፡፡

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ኢስላም መከተል (ኢቲባእ) ወይም አዳዲስ ፈጠራዎችን መጨመር (ኢብቲዳእ)፣ መሆኑን ተማሪው እንዲያስረዳ፣
2) ተቀባይነት የሌላቸውን ተግባራት እንዲያብራራ
3) ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራት እንዲያብራራ
4) ይህን ሐዲስ በሕይወቱ ውስጥ ወደ ተግባር እንዴት መቀየር እንዳለበት እንዲያብራራ

አጠቃላይ መልእክት

ኢስላም ‹‹ኢቲባእ›› እንጅ ‹‹ኢብቲዳእ›› አይደለም፡- የአላህ መልእክተኛ በዚህ ሐዲሳቸው እስልምናን ከጽንፈኞች አጥባቂነት እና ከበካዮች ግድፈት ጠብቀውታል፡፡ ሐዲሱ በጥቂት ቃላት እጅግ ጥልቅና ሰፊ መልእክት የማስተላለፍ ክህሎታቸውን ያስመሰከሩበት ነው፡፡ ነጃህና ፈላህ የሚገኘው ከአላህ መልእክተኛ መመሪያ ላይ ምንም ነገር ሳይጨምሩና ሳያጠባብቁ በመከተል መሆኑን የሚደነግጉ በበርካታ የቁርአን አናቅጽ ለዚህ ሐዲስ መነሻዎች ናቸው፡፡ ለአብነት ያህል አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ ﴾ آل عمران: ٣١

በላቸው፦ "አላህን የምታፈቅሩ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ያፈቅራችኋል፤" (አሊ ዒምራን 31)

መስሊም ባሰፈሩት ዘገባ እንደተወሳው የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘወትር በንግግራቸው መሐል እንዲህ ይሉ ነበር፦

‹‹ከንግግሮች ሁሉ በላጩ የአላህ ኪታብ ሲሆን፣ ከመመሪያዎች ሁሉ በላጩ የነቢዩ መሐመድ መመሪያ ነው። ከነገሮች ሁሉ መጥፎ አዲስ ፈጠራዎች ናቸው። ፈጠራዎች ሁሉ ቢድዓ ሲሆኑ፣ ቢድዓ ሁሉ ደግሞ ጥመት ነው።››

ውድቅ ተግባራት፦ የሸሪዓው ባለቤት ፈቃድ የሌለባቸውን ተግባራት ሁሉ ይህ ሐዲስ በግልጽ ውድቅ አድርጓል። ጥሬ መልእክቱ ስራን ሁሉ ከሸሪዓው አህካም አኳያ ብቻ መመዘን፣ በቁርአንና እና በሱንና ትእዛዛትና እቀባዎች ብቻ መወሰን የግድ እንደሆነ ያመለክታል። ስራዎች ከሸሪዓው ወሰን መውጣታቸውና በርሱ አለመገዛታቸው ፍጹም ጥመት መሆኑን ያረጋግጣል።

ተቀባይነት ያላቸው ተግባራት፦ ከሸሪዓው መንፈስ የማይወጡ፣ ከድንጋጌዎቹ ወይም ከመሠረታዊ መርሆዎቹ ዋቢ ሊመዘዝላቸው የሚችሉ ተግባራት ውድቅ አይደሉም። ተቀባይነት አላቸው። የሚያስመሰግኑም ናቸው። ሶሐቦች እንዲህ ዓይነት በርካታ ተግባራትን ፈጽመዋል። ፈቅደዋቸዋል። ተቀባይነታቸውንም በጋራ ውይይት (ኢጅማእ) አጽድቀዋል። የዚህ ጉልህ ምሳሌ በአቡበክር ዘመን ቁርአን በአንድ መጽሐፍ መሰብሰቡና በዑስማን ዘመን ይህ ቁርአን ተባዝቶ፣ ከሊቃውንት ጋር በሁሉም የእስልምና ግዛቶች እንዲሰራጭ መደረጉ ነው።የአላህን ሸሪዓ የሚቃረኑ አዳዲስ ተግባራት መጥፎ ቢድዓዎችና ጥመቶች ሲሆኑ፣ ሸሪዓውን የማይቃረኑት፣ ከርሱ ጋር የሚጣጣሙት፣ በርሱ ሚዛን ተቀባይነት ያላቸው አዳዲስ ክንውኖች ግን ምስጋናና ጽድቅ የሚቸራቸው ናቸው። ከመካከላቸው የሚወደዱ ተግባራት አሉ። የወል

ግዴታ (ፈርዶል አይን) የሚሆኑም አሉ። ለዚህ ነው ኢማም ሻፊዒ እንዲህ ሲሉ የተናገሩት፡-

‹‹ቁርአንን፣ ሱንናን፣ ኢጅማእን ወይም አሰርን የሚቃረን አዲስ ፈጠራ ሁሉ ጥመት የሆነ ቢድዓ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውንም ያልተቃረነ አዲስ በጎ ተግባር ሁሉ ግን የሚመሰገን ቢድዓ ነው።››

የሐዲሱ ጠቀሜታ፡- ከሸሪዓው ጋር የማይጣጣም አዲስ ፈጠራ (ቢድዓ) የፈጠረ ወንጀሉን እርሱ ይሸከማል። ስራውም ተቀባይነት የለውም። ቅጣትም ይገባዋል።

ክልክል ነገሮች ሁሉ መጥፎ መሆናቸውን፤ ኢስላማዊው ሸሪዓም ጉድለት የሌለበት ሙሉ መሆኑን ሐዲሱ ያመለክታል።

* * *

ምእራፍ ሦስት

ዓቂዳ

በአላህ ማመን

አጠቃላይ ዓላማ ስድስቱን የኢማን መሠረቶች ማስተዋወቅ

ዝርዝር አላማዎች

1) የኢማንን ትርጉምና አስፈላጊነት ማብራራት

2) ስድስቱን የኢማን መሠረቶች ማብራራት

የኢማን ትርጉምና አስፈላጊነት

አጠቃላይ ዓላማ

1) የኢማንን ትርጉም ማብራራት

2) አስፈላጊነታቸውን ማብራራት

የኢማን ትርጉም

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيۡنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٢٨٥ ﴾ البقرة: ٢٨٥

‹‹መልዕክተኛው (ሙሐመድ ሶ.ዐ.ወ) ከአላህ ወደርሱ በተወረደለት መልዕክት አመኑ። አማኞችም (እንዲሁ አመኑ)። "ሁሉም በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጻሕፍትና በመልዕክተኞች፥ በመካከላቸው ምንም ልዩነት አናደርግም (ከፊሎቹን አምነን በከፊሎቹ አናስተባብልም)" ያሉ ሲሆን፥ አመኑ። ጥሪህን ተቀብለናል፥ ለትዕዛዝህ አድረናል። ምሕረትህን እንሻለን። ጌታችን ሆይ! መመለሻም ወደ አንተ ነው - አሉ።››› (አል በቀራህ 285)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ ءَامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلۡكِتَٰبِ ٱلَّذِي نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَٱلۡكِتَٰبِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِن قَبۡلُۚ وَمَن يَكۡفُرۡ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ فَقَدۡ ضَلَّ ضَلَٰلَۢا بَعِيدًا ١٣٦ ﴾ النساء: ١٣٦

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው፥ በመልዕክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍም፥ ከዚህ በፊት ባወረደው መጽሐፍም እመኑ። በአላህ፣ በመላእክቱ፥ በመጽሐፍቱ፥ በመልዕክተኞችም፥ በመጨረሻው ቀንም የካደ (ከእውነት) በእጅጉ ርቋል።›› (ሱል ኒሣእ 136)

እውቅ በሆነው የጅብሪል ሐዲስ ውስጥ ጅብሪል በደዊን ተመስሎ ወደነቢዩ በመምጣት ስለ ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን በጠየቃቸው ጊዜ ኢማንን እንዲህ አብራርተውለታል፡-

‹‹በአላህ፣ በመላኢኮች፣ በመጽሐፎች፣ በመልእክተኞችና በቀደቀደር - በጎም ሆነ ክፉ- ማመንህ ነው።›› (ሙስሊም)

ከላይ ከተወሱት የቁርአን አናቅጽና የሐዲስ ዘገባ እንደምንረዳው ኢማን ስድስት ጽንሰ ሐሳቦችን አካትቷል። እነርሱም

<u>አንደኛ</u>፡- አላህን፣ የላቁ ስሞቹንና ባህሪያቱን፣ የሕልውናውን መርሆዎች፣ የልእልናውን መገለጫዎች ማወቅ፤

<u>ሁለተኛ</u>፡- ከእይታ ባሻገር ያለውን ድብቅ ዓለም፣ በውስጡ ያዘላቸውን በመላኢኮች የሚወከል የበጎ ሐይል፣ በኢብሊስና በአጋሮቹ ሰይጣናት የሚወከል የክፉ ሐይል፣ እንዲሁም የዚሁ ድብቅ ዓለም አካል የሆኑትን አጋንንትና መናፍሳት ማወቅ፤

<u>ሦስተኛ</u>፡- የእውነትንና የሐሰትን፣ የበጎና የክፋትን፣ የሐላልና የሐራምን፣ የጥሩና የመጥፎን ወሰኖች ለማበጀት አላህ ያወረዳቸውን መጽሐፍት ማወቅ፤

<u>አራተኛ</u>፡- የመቀናት ተምሳሌት ይሆኑ ዘንድና የሰው ልጆችን ወደ ቅን ጎዳና እንዲመሩ አላህ የመረጣቸውን ነብያትና መልእክተኞች ማወቅ፤

<u>አምስተኛ</u>፡- መጭው ዓለም፣ ከሞት መቀስቀስ፣ ምንዳ ወይም ቅጣት፣ ጀነት ወይም እሳት የመኖሩን እውነታ ማወቅ፤

<u>ስድስተኛ</u>፡- ዩኒቨርሱ የሚመራበት የቀዲቀደር ስርዓት መኖሩን ማወቅ[1]

ኢማን ማለት እውቀት ወይም የልቦና እምነት ብቻ ሳይሆን የአንደበት ምስክርነትንና ተግባርን ያካትታል። ይህን ሁለንተናዊ የኢማን ይዘት የሚያብራሩ የቁርአን አናቅጽና የሐዲስ ዘገባዎች በርካታ ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ثُمَّ لَمۡ يَرۡتَابُواْ وَجَٰهَدُواْ بِأَمۡوَٰلِهِمۡ وَأَنفُسِهِمۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ ١٥ ﴾ الحجرات: ١٥

‹‹አማኞች እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው (በጥልቅ) ያመኑት፥ ቅንጣት ጥርጣሬም የሌለባቸውና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውም፥ በነፍሶቻቸውም የሚታገሉት ብቻ ናቸው። እውነተኞቹ እነርሱ ብቻ ናቸው።›› (ሱል ሁጁራት 15)

﴿ إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتۡ قُلُوبُهُمۡ وَإِذَا تُلِيَتۡ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتۡهُمۡ إِيمَٰنٗا وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٢ ﴾ الأنفال: ٢

‹‹(እውነተኛ) አማኞች እነዚያ አላህ ሲወሳ ልቦናዎቻቸው በፍርሃት የሚርዱት፥ አንቀጾቹ በሚነበቡ ጊዜም እምነትን የሚጨምሩላቸው፥ በጌታቸው (ብቻም) የሚመኩት ናቸው።›› (ሱል አንፋል 2)

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣›› ተብሎ መእሚን የተጠራባቸው እና ‹‹መእሚን ማለት›› በሚል ቃል ተወጥነው የኢማንን መስፈርት የሚያብራሩ የቁርአን መልእክቶች ብዙዎች ሲሆኑ እነርሱን ማስተንተንና ማስተዋል ተገቢ ነው። ይህን የኢማን ይዘት ከሚያብራሩ ሐዲሶች መካከል ኢብን ዑመር ያስተላለፉት ይገኝበታል። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

[1] ሸህ ሰይድ ሳቢቅ፣ አልዓቃኢዱል ኢስላሚያ

‹‹ደግ ስራው ያስደሰተውና መጥፎ ስራው ያስከፋው ሰው መኣሚን ነው።›› (አህመድ)

ኡባደት ቢን ሷሚት እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በላጩ ኢማን የትም ቦታ ብትሆን አላህ ካንተ ጋር እንዳለ ማወቅህ ነው።›› (ጦበራኒ)

አብደላህ ቢን ዑመር እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሐያእ (ይሉኝታ) የኢማን ዘርፍ ነው።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አነስ እንዳስተላለፉት ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።››› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ሹረይህ አልካእቢ እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፡-

‹‹በአላህ እምላለሁ አለመነም።›› በማለት ሦስት ጊዜ ተናገሩ። ‹‹ይህ ሰው ማን ነው?›› ተብለው ሲጠየቁ፡- ‹‹ጎረቤቱ ተንኮሉን የማያምነው ሰው›› በማለት መለሱ። (ቡኻሪ)

ቁርአንና ሐዲስ ያስተማሩት ኢማን፣ መንገድ የሳቱ ሐይማኖቶች፡- ‹‹እውር ሆነህ እመን››፣ ‹‹አእምሮህን ዝጋና ተከተለኝ›› የሚሉት አይነት አእምሯችንን ቆልፈን የምንቀበለው እውር እምነት አይደለም። ይልቁንም ግዙፉን ዩኒቨርስ እና በውስጡ ያካተታቸውን ወደ እምነት የሚጠሩ ጥበቦች በጥልቀት ከማጤንና ከማስተንተን የሚመነጭ ነው።

ለ) የኢማን አስፈላጊነትና ክብደት

በአላህ ማመን በርካታ በጎ ስሜቶችን ያሰርጻል። ሕሊናን ለደግ ስራ ያነቃቃል። ራስን የመቆጣጠርን ክህሎት ያጎናጽፋል። ለላቁ ዓላማዎች ያነሳሳል። ከአጓጉል ድርጊቶችም ያርቃል።

በመላኢኮች ማመን ከነርሱ ጋር ለመመሳሰል መጣርን፣ ለሐቅና ለሰናይ መተባበርን ይጋብዛል። ጥንቁቅና ንቁም ያደርጋል። መላኢኮች ካጠገቡ

እንዳሉ የታሰበው ሰው መልካም ነገር እንጅ ክርሱ አይመነጭም። ለላቀ ዓላማ እንጅ አይንቀሳቀስም።

መለኮታዊ መጽሐፍትን ማወቅ የሰው ልጅ ውጫዊና ውስጣዊ ምሉእነትን ይጎናጸፍ ዘንድ እንዲገዝበት አላህ ያሰመረለትን ቅን ጎዳና ማወቅ ነው።

መልእክተኞችን ማወቅ፡- ፈለጋቸውን መከተል፣ ባህሪያቸውን መውረስ፣ እነርሱን አርአያ (Role Model) ማድረግ ማለት ነው። ምክንያቱም እነርሱ የመልካም እሴትና አላህ ለሰው ልጅ ያለመለት ጸእድ ሕይወት ተምሳሌቶች ናቸውና።

የመጭውን ዓለም ሕልውና ማወቅ፡- በጎ ነገር ለመስራት እና ከክፋት ለመታቀብ ግፊት በማሳደር ወደር አይገኝለትም።

በቀጂ ቀደር ማመን፡- ችግሮችንና እንቅፋቶችን ለማለፍ የሚያስችል ወሰን አልባ ጉልበት ይለግሳል። ይህ እምነት በልቦና ውስጥ ካለ ግዙፍ ክስተቶች ሁሉ ኢምንት ሆነው ይታያሉ።

ከላይ የሰፈረው ገለጻ በጉልህ እንደሚያመለክተው ኢማን ዓላማው ስብእናን ማስተካከል፣ ነፍስን ማጽዳትና ፊትን ወደ ላቀ አርአያ ማዞር ነው። ይህ አይነቱ ኢማን ለግለሰቦች ሕይወት ነው።እርሱ ካለ መልካም ሕይወት ይኖራሉ። እርሱ ከሌለ ደግሞ መንፈሳቸው ይሞታል። ኢማን መንገድ አመላካች ብርሃን ሲሆን፣ ያለርሱ የሰው ልጅ እውር ነው። መንገድ ስቶ በሕይወት ጥሻዎች ውስጥ ይወሸቃል። በጥመት ሸለቆዎች ውስጥ ይጠፋል።

﴿ أَوَمَن كَانَ مَيۡتٗا فَأَحۡيَيۡنَٰهُ وَجَعَلۡنَا لَهُۥ نُورٗا يَمۡشِي بِهِۦ فِي ٱلنَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُۥ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ لَيۡسَ بِخَارِجٖ مِّنۡهَاۚ كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلۡكَٰفِرِينَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٢٢ ﴾

‹‹ሕይወት አልባ የነበረና ሕይወትን የለገሰነው፥ በሰዎች መካከል (ፈሩን ሳይስት) የሚጓዝበትንም ብርሃን የሰጠነው መውጣት ከማይችልበት ጽልመት ውስጥ ካለው ጋር እኩል ነውን? ለነዚያ

ለካዱት ሰዎች (እኩይ) ምግባራችሁ -እንደዚሁ- መልካም ሆኖ ታያቸው።›› *(አል አንዓም 122)*[1]

ይህም ብቻ አይደለም፡፡ ኢማን ማለት ከመላ የዩኒቨርሱ አካላት፣ ከአላህና እንዲሁም ዩኒቨርሱን ከሚገዛው ሕግና ስርዓት ጋር መገናኘት ማለት ነው፡፡ ከአላህ ጋር የተሳሰረ፣ በርሱ ያመነ፣ ትእዛዙን የተከተለ፣ ከዩኒቨርሱ ጋር በመገናኛ፣ በጎ ተጽእኖውን በማስተናገድና ተጽእኖ በማሳደር በዚህችም በቀጣዩም ዓለማት በደስታ ይኖራል፡፡

﴿ فَمَنِ ٱتَّبَعَ هُدَايَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشۡقَىٰ ١٢٣ ﴾ طه: ١٢٣

‹‹መመሪያዬን የተከተለ መንገድ አይስትም። እንግልትም አይደርስበትም።›› (ጣሃ 123)

ሰውየው ከአላህ ጋር ካልተሳሰረ ከዩኒቨርሱ ጋር ያለው ግንኙነትም ይቋረጣል፡፡ ነፍሱም ለርሱ እና ከርሱ ለሚመነጩት ነሮች ሁሉ ባይተዋር ትሆንናለች፡፡ ይህም ሲሆን በዚህችም በመጭውም ዓለም ደስታ ቢስ ይሆናል፡፡

﴿ وَمَنۡ أَعۡرَضَ عَن ذِكۡرِي فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةٗ ضَنكٗا وَنَحۡشُرُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ أَعۡمَىٰ ﴾

“ግና ከመልዕክቴ ያፈገፈገ ሕይወቱ ጭንቅ የበዛበት ይሆናል። በትንሳኤ ቀንም እውር አድርገን እንቀሰቅሰ ዋለን።›› *(ጣሃ 124)*

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የኢማንን ይዘትና ባህሪ አብራራ

2) የኢማንን ክብደትና አስፈላጊነት አብራራ

[1] አልአቃኢደል ኢስላሚያህ

የኢማን መሠረቶች

በዑመር ቢን አልኸጧብ የተላለፈው እውቁ የጅብሪል ሐዲስ የዘረዘራቸውን ስድስቱን የኢማን መሠረቶች ከአሁን ቀደም መጠቆማችን ይታወሳል። ጅብሪል ‹ስለ ኢማን ይንገሩን› በማለት የአላህን መልእክተኛ በጠየቃቸው ጊዜ እንዲህ ሲሉ መመለሳቸው ይታወሳል፡-

‹‹ኢማን ማለት በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጽሐፍቶች፣ በመልእክተኞች፣ በመጭው ዓለምና በቀዷ ቀደር -ደግም ሆነ ክፉ- ማመንህ ነው።›› (ሙስሊም)

ቀጥሎ ሁሉንም የኢማን መሠረቶች በተናጠል እንመለከታቸዋለን። ዓላማቸውንና በጎ ተጽእኗቸውንም እንቃኛለን።

የመጀመሪያው መሠረት- በአላህ ማመን

መግቢያ

በአላህ ማመን ማለት አላህ የሁሉም ነገር ለቤትና ፈጣሪ መሆኑን ማመን (ተውሂድ ሩቡብያ)፣ ሶላት፣ ጾም፣ ዱዓእ፣ ተስፋ ማድረግ፣ መፍራት፣ መዋረድ፣ መተናነስና ሌሎችም ኢባዳዎች ለርሱ ብቻ እንደሚገቡ ማመን (ተውሂዱል ኡሉህያ)፣ እንዲሁም ከጎደሎ ባህሪያት የጸዳና በምሉእ ባህሪያት የሚገለጽ አምላክ መሆኑን ማመን (ተውሂዱል አስማእ ወሲፋት) ናቸው።

በአላህ ማመን በሦስት መስክ ብቸኝነቱን መቀበልን ይጠይቃል። በመፍጠርና በመንከባከብ ስልጣኑ (ሩቡብያ)፣ አምልኮ ለርሱ ብቻ መሆኑ (ዑሉህያ) እና የምሉእና የላቁ ባህሪያት ባለቤት መሆኑ (አስማእ ወሲፋት)።

የተውሂድ አይነቶች

አንደኛ፡- ተውሂድ ሩቡብያ

አጠቃላይ ዓላማዎች

ሀ) ትርጉሙን መረዳት

ለ) ይዘቱን መገንዘብ

ሐ) ተውሂደል ሩቡብያን ለማጽናት የሚረዱ ተግባራዊ እርምጃዎችን በከፊል ማብራራት

ሀ) **የተውሂደ ሩቡብያን ጥቅል ትርጉም፡-** አላህ የሁሉም ነገር ፈጣሪ፣ ተንከባካቢና አስተናባሪ መሆኑን እና ከርሱ ሌላ ይህን ማድረግ የሚችል አካል እንደሌለ በእርግጠኝነት ማመን፡፡

ለ) **የተውሂደ ሩቡብያ ይዘት፡-** የፍጡራን ፈጣሪና ባለቤት፣ ሕይወት ለጋሽ፣ ገዳይ፣ ጠቃሚ፣ ጎጅ፣ የችሎታ ባለቤት፣ የሚሰጥም የሚነሳም አላህ ብቻ መሆኑን፣ መፍጠርም ማዘዝም የርሱ ብቻ ስልጣን መሆኑን ማመን፡፡

ይህ የተውሂድ ክፍል ለሌሎች የተውሂድ ዓይነቶች ሁሉ መሠረት ነው። ይህ ተውሂድ ሲረጋገጥና ሲጸና አላህን በፍጹም መተናነስና ፍርሃት የማምለክ ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ለምስጋና፣ ለመታወስ፣ ለመለመን፣ ተስፋ ለመደረግና ለመፈራት ተገቢው አላህ ብቻ ነው፡፡ አምልኮ የመፍጠርም ሆነ የማዘዝ ስልጣን ሁሉ ባለቤት ከሆነው አካል ውጭ ለሌላ ለማንም ተገቢ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ፈጣሪና ባለቤት የሆነው አካል የላቁና ምሉእ ባህሪያት ይገቡታል፡፡ እንዲህ ዓይነት ባህሪያት ለዓለማት ጌታ እንጅ ለሌላ ተገቢ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም ሕያው፣ ሰሚ፣ ተመልካች፣ ቻይ፣ ተናጋሪ፣ የፈለገውን ሰሪ፣ በንግግሩም ሆነ በስራው ጥበበኛ ያልሆነ አካል የፍጡራን ፈጣሪ፣ ባለቤትና አስተናባሪ ሊሆን አይችልምና፡፡ ይህም

በመሆኑ ቁርአን ተውሂደ ሩቡብያን በበርካታ ቦታዎች ላይ ሲያወሳ እናነባለን።

ከምስጋና ጋር አያይዞ እንዲህ ማለቱን ሙስሊም በእያንዳንዱ የሶላት ረከዓዎች ውስጥ ያነባል፡-

﴿ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴾ الفاتحة: ١ - ٥

‹‹ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው፥ ለዓለማት ጌታ።›› (አል ፋቲሐ 2-5)

እንዲህም ይላል፡-

﴿ فَلِلَّهِ ٱلۡحَمۡدُ رَبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَرَبِّ ٱلۡأَرۡضِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٣٦ ﴾ الجاثية: ٣٦

‹‹ምስጋና ለአላህ ይሁን። ለሰማያትና ለምድር ጌታ፤ ለዓለማት ጌታ።›› (አል ጃሲያህ 36)

እርሱን ብቻ የበጎ ምግባር ዓላማ ከማድረግ ጋር አያይዞም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢ ﴾ الأنعام: ١٦٢

“ስግደቴም፥ የማቀርበው መስዋእትም፥ ሕይወቴም፥ ሞቴም የዓለማት ጌታዬ የሆነው የአላህ ነው።” በልም፤ (አል አንዓም 162)

ከላቁ ሰሞቹና ባህሪያቱ ጋር በተያያዘም የሰማያትና የምድር፣ እንዲሁም በመካከላቸው ያሉ ፍጡራን ጌታ፣ ባለቤትና አስተናባሪ በመሆኑ የሚገለጸውን የአላህ ፈጣሪነት (ሩቡብያ) ከላቁ ስሞቹና ባህሪያቱ ጋር አያይዞ ቁርአን ሲቀያየቀርብ እናነባለን። ተከታዩን የአላህ ቃል አስተንትን፡-

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ

بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ﴿٢٥٥﴾ ﴾ البقرة: ٢٥٥

‹‹አላህ (ብቸኛ አምላክ ነው፤) ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። ሕያውና ራሱን ቻይ ነው። ማንጐላጀትም እንቅልፍም አይዘውም። በሰማይም በምድርም ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ የርሱ ናቸው። ከርሱ ዘንድ ያለርሱ ፈቃድ የሚያማልድ ማን ነው? (ፍጡራኑ) በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚገጥሟቸውን ነገሮች ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። እርሱ የፈቀደውን ያህል ቢሆን እንጅ ከእውቀቱ ቅንጣት ያህሉን አይደርሱበትም። ዙፋኑ ከሰማያትና ከምድር ሰፋ። እነርሱን (ሰማያትንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ፍጡራኑን) መጠበቁ አይሳነውም። ከፍ ያለና ልዕል (አምላክ) ነው።›› (አልበቀራህ 255)

ተውሂድ ሩቡብያን ለሌሎች የተውሂድ ዘርፎች መሠረት ከመሆኑ ጋር በአላህ የማመንን ጽንሰ ሐሳብ በተሟላ መልኩ ለመገንዘብ ብቻውን በቂ አይደለም። አላህ የሁሉም ነገር ፈጣሪና አስተናባሪ መሆኑን አምነው እርሱን በብቸኝነት የማያመልኩና ከርሱ ጋር ሌላን አካል የሚያጋሩ፣ እንዲሁም ለላቁ ስሞቹና ባህሪያቱ ብቸኛው ተገቢ አካል መሆኑን የማይቀበሉ ወገኖች ተውሂድ ሩቡብያን ማጽደቃቸው አይጠቅማቸውም። ከክህደት ክልል አውጥቶም ወደ እምነት ክልል አያስገባቸውም። ጣኦታውያን የአላህን የሁሉም ነገር ፈጣሪነት የሚያጸድቁ ቢሆንም እርሱን በብቸኝነት ማምለኩን ስላልወደዱና ምሉእና የተላቁ ስሞችና ባህሪያት ብቸኛ ሊያደርጉት ስላልፈቀዱ ጣኦታዊ ሆነው መቀጠላቸውን አላህ ይናገራል፡-

﴿ وَمَا يُؤۡمِنُ أَكۡثَرُهُم بِٱللَّهِ إِلَّا وَهُم مُّشۡرِكُونَ ﴿١٠٦﴾ ﴾ يوسف: ١٠٦

‹‹ብዙዎቹ አጋሪዎች ሆነው እንጅ፥ በአላህ አያምኑም።›› (ዩሱፍ 106)

መጃሂድ ይህችን አንቀጽ አስመልክተው ሲናገሩ፡-

‹‹በአላህ ማመናቸው፣ አላህ ፈጥሮናል፣ ሲሳይ ለግሶናል፣ ይገድለናል፣ ማለታቸው ሲሆን፣ ይህ እምነታቸው በርሱ ከማጋራታቸውና ሌላን አካል ከማምለካቸው ጋር የተቀላቀለ ነው።››

እናም አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ መሆኑን ያጸደቁ ሁሉ በአምልኮ ወይም በስሞቹና በባህሪያቱ እርሱን ብቸኛ ያደርጋሉ ማለት አይደለም። አብዛኛዎቹ ሰዎች የፈጣሪን ሕልውናና ጌትነት፣ እንዲሁም በፍጡራን ላይ ያለውን የጌትነት ስልጣን አያስተባብሉም። የአብዛኛዎች ክህደት መሠረት ከርሱ ውጭ ሌላን አካል ማምለካቸው ነው።››

ሐ) ይህን የተውሂድ ዘርፍ ለማጽናት የሚረዱ ስልቶች፡-

⇒ በተለየ መልኩ ማስተንተንን የሚጋብዙ የቁርአን አናቅጽን በማስተንተን ማንበብ፣

⇒ የአላህን ፍጥረታት ጥበብ ለመረዳት የሚያስችል ጉዞ፣

⇒ የአላህን ፍጥረታት ተአምራትና የቁርአንን ሳይንሳዊ ተአምራት የሚያብራሩ የሸህ ዘንዳኒንና የዶክተር ዘግሉል አልነጃርን ካሴቶች ማየት

⇒ የሰውን ልጅ ድንቅ የአፈጣጠር ጥበብ ማስተንተን፡-

﴿ وَفِيٓ أَنفُسِكُمۡۚ أَفَلَا تُبۡصِرُونَ ٢١ ﴾ الذاريات: ٢١

‹‹በነፍሶቻችሁም ውስጥ (እንዲሁ ተአምራት አሉት።) አታስተውሉምን?›› (አል ዛሪያት 21)

⇒ ስለ ባህር፣ ስለ መሬት ነውጥ፣ ስለ እሳተ ጎመራ እና ስለ አስትሮኖሚ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ካሴቶችን ማየት፣

⇒ ይህንን የእውቀት መስክ የሚያጎለብቱ መጽሐፍትን ማንበብ

ሁለተኛ- ተውሂደል ኡሉሂያ

ሀ) የተውሂደል ኡሉሂያን ጥቅል ትርጉምና ይዘት መረዳት

ለ) ተውሂደ ኡሉህያ ግድ የሚያደርጋቸውን ሐላፊነቶች ማብራራት

ሀ) የተውሂደል ኡሉህያ ትርጉምና ይዘት፡- እውነተኛው አምላክ አላህ ብቻ መሆኑንና ከርሱ ሌላ አምላክ እንደሌለ በእርግጠኝነት ማመን፣ አምልኮዎችንም ለርሱ ብቻ ማዋል ነው።

የአምልኮን (ኢባዳን) ትርጉም ኢማም ኢብን ተይሚያህ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ኢባዳ ማለት ከፍጹማዊ ፍቅር የሚመነጭ ፍጹማዊ ታዛዥነት ነው።››

እንዲህ ሲሉም አክለዋል፡-

‹‹ሙወሂዶችን ከጣኦታውያን የሚለየው የተውሂድ አይነት ይህ ሲሆን፣ በመጭው ዓለምም ለምንዳ ወይም ለቅጣት የሚያበቃው ይህ የተውሂድ ክፍል ነው። ይህን የተውሂድ ክፍል ያልፈጸሙ ከጣኦታውያን ይፈረጃሉ።››[1]

ይህ የተውሂድ ክፍል የአላህ መልእክተኞች ዳእዋ መሠረት ነው። እርሱን ለማብራራት መጻሐፍት ወርደዋል። ይህን የተውሂድ ዘርፍ ለየወገኖቹ ያላስተማረ አንድም የአላህ መልእክተኛ የለም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥ ﴾

<<ከአንተ በፊት መልዕክተኛን አልላክንም፦ «እነሆ፥ ከኔ ሌላ አምላክ የለም። ስለሆነም (በብቸኝነት) አምልኩኝ።» የሚል መልዕክት የምናወርድለት ቢሆን እንጅ።>>

ለ) **ግድ የሚያደርጋቸው ሐላፊነቶች፡-** ኢባዳን ሁሉ ለአላህ ብቻ ማዋል፣ ቀልቦቻችንን ከአላህ ውጭ ካለ አካልና አቅጣጫ ማጽዳት

[1] ሪሳቱል ሐሰናህ ወሰይኢህ፣ ቢን ተይሚያህ።

ሲሆን፣ ይህ ጽንሰ ሐሳብ በርካታ ቁም ነገሮችን ያካተተ ነው። ከብዙው በጥቂቱ፡-

1) ለአላህ ፍጹማዊ ፍቅርን መለገስ፣ ማለትም ሰውየው ልክ እንደ አላህ የሚወደው ወይም በፍቅር ከአላህ የሚያስቀድመውን ሌላ አካል መያዝ የለበትም። ይህን ያደረገ ከጣኦታውያን ይፈረጃል፡-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِ ۗ ﴾ البقرة: ١٦٥

‹‹ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን (አማልክት አድርገው) የሚይዙ አሉ። (ሙእሚኖች) አላህን የሚወዱትን ያህል ይወዷቸዋል። እነዚያ ያመኑት ለአላህ የበረታ ፍቅር አላቸው።›› (አል በቀራህ 165)

ከሙእሚን ዘንድ በዚህች ዓለም የየትኛውም ነገር ፍቅር ከአላህ ፍቅር ቀጥሎ የሚመጣ ነው። የአላህ ፍቅር ከሁሉም ፍቅሮች በላይ ነው። ይህም በመሆኑ የትኛውም ነገር ከአላህ ፍቅር ጋር ተቃርኖ ከተገኘ ሙእሚን እርሱን ከመሰዋት አያመነታም። ምድራዊ እሴቶችን ከአላህና ከመልእክተኛው ፍቅር የሚያስቀድሙ ወገኖችን አላህ እንዲህ ሲል አስጠንቅቋል፡-

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَٰلٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٍ فِى سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٢٤﴾ ﴾ التوبة: ٢٤

“አባቶቻችሁን፣ ልጆቻችሁን፣ ወንድሞቻችሁን፣ የትዳር ጓደኞቻችሁን፣ ዘመዶቻችሁን፣ የሰበሰባችኋቸውን ጥሪቶች፣ መክሰሩን የምትፈሩትን ንግድና የምትወዷቸውን ቤቶቻችሁን ከአላህ፣ ከመልዕክተኛውና በርሱ መንገድ ከመታገል አብልጣችሁ የምትወዱ ከሆናችሁ አላህ የራሱን ውሳኔ እስኪያስተላልፍ ድረስ ተጠባበቁ። አላህ አመፀኞችን አይመራምና።” በላቸው። (አል ተውባህ 24)

2) ከአላህ ውጭ ሌላ አካል ማድረግ በማይችላቸው ነገሮች አላህን ብቻ መማጸን፣ በርሱ ብቻ መመካትና እርሱን ብቻ ተስፋ ማድረግ ግዴታ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ وَلَا تَدۡعُ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكَ وَلَا يَضُرُّكَۖ فَإِن فَعَلۡتَ فَإِنَّكَ إِذٗا مِّنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٠٦ ﴾

ከአላህም ሌላ የማይጠቅምህንና የማይጐዳህን አታምልክ። ይህን ካደረግክ (ለሐሰት አማልክት ካጐበደ ድክ)፥ ያንየ አንተ በእርግጥ ከበደለ ኞች ትሆናለህ። (ዩኑስ 106)

﴿ وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٢٣ ﴾ المائدة: ٢٣

(ትክክለኛ) አማኞች ከሆናችሁ በአላህ ተመኩም። (አል ማኢዳህ 23)

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱلَّذِينَ هَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ يَرۡجُونَ رَحۡمَتَ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٢١٨ ﴾ البقرة: ٢١٨

‹‹እነዚያ ያመኑት፥ እነዚያም የተሰደዱትና በአላህ መንገድ የታገሉት የአላህን እዝነት የመጐናፀፍ ተስፋ ያላቸው እነርሱ ናቸው። አላህ እጅግ መሓሪና አዛኝ ነው።›› (አል በቀራህ 218)

3) አላህን ብቻ መፍራት፦ ከፍጡራን አንዳቸውም በነጻ ፈቃዳቸው ሊጎዱኝ ይችላሉ ብሎ የፈራ ሰው በአላህ ላይ አጋርቷል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ فَإِيَّٰيَ فَٱرۡهَبُونِ ٥١ ﴾ النحل: ٥١

‹‹ እኔን ብቻ ፍሩኝ።" አለ።›› (አል ነህል 51)

﴿ وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يُرِدۡكَ بِخَيۡرٖ فَلَا رَآدَّ لِفَضۡلِهِۦۚ يُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦۚ وَهُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ١٠٧ ﴾ يونس: ١٠٧

‹‹አላህ አንዳች ክፉ ነገር እንዲያገኝህ ቢያደርግ፥ ከአላህ ውጭ የሚያነሳልህ ማንም የለም። መልካም ነገር ቢያቅድልህም ማንም ችሮታውን ማስቀረት አይቻለውም። በርሱ (በችሮታው) ከባሮቹ የሚሻውን ይለያል። እርሱ መሓሪም አዛኝም ነውና።›› (ዩኑስ 107)

4) እንደ ስለት፣ ሩኩእ፣ ሱጁድ፣ ጾምና ጠዋፍ ያሉ አካላዊ የአምልኮ ተግባራት፣ እንዲሁም እንደ ኢስቲግፋርና ሶላት (ነዝር) ያሉ በአንደበት የሚፈጸሙ ዒባዳዎችን ለአላህ ብቻ ማድረግ ግዴታ ነው። ከነዚህ ወይም ከሌሎች አምልኮዎች መካከል አንዳቸውንም ከአላህ ውጭ ለሌላ አካል ያዋለ በአላህ ላይ አጋርቷል፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُۚ وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱفۡتَرَىٰٓ إِثۡمًا عَظِيمًا ٤٨ ﴾ النساء: ٤٨

‹‹አላህ ለርሱ ተጋሪ መደረጉን (ሽርክን) ፈጽሞ አይምርም። ከዚህ ባሻገር ያሉትን (ጥፋቶች) ግን ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህ የሚያጋራ በእርግጥም የከበደ ኃጢአት ፈጽሟል።›› (አል ኒሣእ 48)[1]

ሦስተኛ- ተውሂደል አስማ ወሲፋት

ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ) ይህን የተውሂድ ዘርፍ ማብራራት

ለ) ዓላማውን መረዳት

ሐ) የአላህን ስሞች ትርጉም ማወቅና በአእምሮ ማሰታወስ

ሀ) **ተውሂደል አስማ ወሲፋት ትርጉምና ይዘት፡-** አላህ በምሉእ ባህሪያት የሚገለጽ፣ ከነደሉ ባህሪያት ሁሉ የጠራና በዚህ ረገድ ከፍጡራን ሁሉ የተለየ መሆኑን በእርግጠኝነት ማመን፤ አላህ ወይም መልእክተኛው ያጸደቋቸውን በቁርአንና በሱንና የተገለጹ የአላህ ስሞችና

[1] ያለፈው ምንጭ

ባህሪያት የቃላት አወቃቀራቸው ወይም ትርጉማቸውን ሳይለውጡ (ተሕሪፍ)፣ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ሳያደርጉ (ተእጢል)፣ በምናብ ቅርጽ ሳያስይዙ (ተክይፍ) ወይም ከፍጡራን ባህሪያት ጋር ሳያመሳስሉ (ተሽቢህ) እንደወረዱ መቀበል ግዴታ ነው።

ይህ ማብራሪያ ሦስት መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦችን የያዘ ሲሆን፣ አንዱንም ያጓደለ ይህን የተውሂድ ዘርፍ አላሟላም።

<u>አንደኛ</u>፡- አላህን ከፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ወይም ከጎደሎ ባህሪያት ማጽዳት፣

<u>ሁለተኛ</u>፡- በቁርአንና በሱንና የተገለጹ የአላህ ባህሪያትን ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ፣ የቃል ወይም የትርጉም ለውጥ ሳያደርጉ (ተእዊል)፣ ወይም ውድቅ ሳያደርጉ (ተእጢል) እንደወረዱ መቀበል፣

<u>ሦስተኛ</u>፡- እነዚህን ባህሪያት ምናባዊ ቅርጽ ለማስያዝ ከመሞከር መታቀብ።

ለ) **ግዴታዎች፡-** የአላህን ባህሪያት ከርሱ ምሉእነት ጋር በሚጣጣሙ ትርጉሞቻቸው መረዳት፤ ይህውም ከፍጡራን ማመሳሰል (ተሽቢህ)፣ ይዘታቸውን ማራቆት (ተእጢል)፣ መልእክታቸውን ማዛባት (ተእዊል) ወይም በምናብ ቅርጽ ለማስያዝ መሞከር (ተክይፍ) ያልታከለበትን ትክክለኛ ትርጉማቸውን መቀበል፤ ኢማም ሻፊዒ የተናገሩትን ተከታዩን ጽንሰ ሐሳብ ማጽደቅ ነው፡-

‹‹በአላህ፣ ከአላህ በመጣው መልእክት፣ እርሱ በፈቀደው ትርጉሙና ይዘቱ አምኛለሁ።››.

ሐ) **የአላህ ስሞች፡-** አላህ በቁርአኑ እንዲሁም መልእክተኛው በሱንናቸው የአላህን መልካም ስሞች አስተዋውቀውናል። እነርሱም የአላህን ባህሪያት ለማስተዋወቅ የሚረዱ ስሞች ሁሉ ናቸው። የአላህን ስሞችና ባህሪያት መልእክት አጠቃልሎ የያዘው ቃል ‹አላህ› የሚለው ሲሆን፣ አምላካችንን የምንጠራው፣ የምናስታውሰው፣ የምናመልከው፣ የምንለምነው እነዚህን ስሞቹን ተጠቅመን ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَلِلَّهِ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰ فَٱدۡعُوهُ بِهَاۖ﴾ الأعراف: ١٨٠

‹‹ለአላህ መልካም ስሞች አሉት። ስለ ሆነም በነርሱ ተማፀኑት።›› *(አል አዕራፍ 180)*

አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ዘጠና ዘጠኝ ስሞች አሉት፡፡ እነርሱን በአእምሮው የያዘ ጀነት ገባ፡፡››[1]

መ) የአላህ መልካም ስሞች ትርጉም

ስም	ትርጉም
አላህ	የሁለንተናዊ አምላካዊ ባህሪያት ባለቤት የሆነን አካል የሚያመለክት ስም ነው፡፡
አል-ረህማን (ሩህሩህ)	ሙእሚንም ካሐዲም ለሆኑ ፍጡራን እዝነቱ ሰፊና ትልቅ
አልረሂም (አዛኝ)	ከስራ እጥፍ ድርብ የላቀ ምንዳ የሚሰጥ (ለሙእሚኖች በተለየ ሁኔታ በጎ ዋይ እና አዛኝ)
አል መሊክ (ንጉስ)	በግዛቱ ያሻውን የሚፈጽም ንጉስ
አልቁዱስ (የተቀደሰ)	በስሜት ሕዋሳት ሊደረስበት ወይም በምናብ ሊታሰብ ከሚችል ባህሪ ሁሉ የጸዳ
አል ሰላም (ሰላም)	ከነውር እና ከጉድለት የጸዳ፤ ሰላሙን በፍጡራኑ ላይ የሚያሰፍን
አል ሙእሚን (አማኝ)	ራሱ፣ መጽሐፍቱና መልእክተኞቹ ስለርሱ የተናገሩትን የሚያጸድቅ
አል ሙሐይሚን	በምሉእ ችሎታው ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር

[1] ቡኻሪ፣ ሙስሊም፣ ነሣኢ፣ ቢን ማጃህ

(ተቆጣጣሪ)	
አል ዓዚዝ (ሐያል)	አቻ የለሽ ሐያልና አሸናፊ
አል ጀባር	ፈቃዱን በሐይል የሚፈጽም፣ ጠጋኝ እና ፈዋሽ
አል ሙተከቢር (ኩሩ)	የልዕልና ባህሪያቱ ብቸኛ ባለቤት፣ ከጉድለትና አንዳች ነገር ከመከጀል የጸዳ
አል ኻሊቁ (ፈጣሪ)	ፍጡራንን በፈቃዱ ካልነበሩበት ያስገኘ
አል በርሩ (የድንቅ ፈጠራ ባለቤት)	ለባሮቹ የተለያዩ ገጽታዎችን በማላበስ አንዱ ከሌላው እንዲለይ ያደረገ ጠቢብ
አል ሙሰዊሩ (ቅርጽ ለጋሽ)	ለእያንዳንዱ ፍጡር የተለየ ቅርጽ የሰጠ
አል ገፋር (መሐሪ)	መጥፎ ድረጊትን በዱንያ የሚሸፍን፣ በመጭው ዓለም ደግሞ ይቅር የሚል
አል ቀሐር (አሸናፊ)	አምባነገኖችን ሁሉ የሚያሸንፍ
አል ወሃቡ (ሰጭ)	በችሮታው የሚያንበሸብሽ
አል ረዛቅ (ሲሳይን ለጋሽ)	ሲሳዮችን የፈጠረና ወደ ፍጡራኑ የሚያደርስ
አል ፈታሁ (ከፋች)	ለባሮቹ የችሮታውን ካዝናዎች የሚከፍት
አል ዓሊሙ (አዋቂ)	በእውቀቱ ሁሉንም ነገር ያካበበ
አል ቃቢዱ (ነሽ)	ከፍጡራኑ ለሚሻው፣ የፈለገውን ነገር የሚነሳ
አል ባሲጥ (ሰጭ)	ሚስጥራቱን ለሚሻው አካል የሚያካፍል
አልኻፊድ (ዝቅ አድራጊ)	ካህድያንና ወንጀለኞችን ዝቅ የሚያደርግ
አል ራፊዕ (ከፍ	ወዳጆቹን ከፍ የሚያደርግ

አድራጊ)	
አል ሙኢዙ (ክብር ለጋሽ)	እርሱን ለሚታዘዙ አማኞች ክብር የሚለግስ
አል ሰሚዑ (ሰሚ)	ድምጾች የማያመልጡት
አል በሲሩ (ተመልካች)	ፍጡራንን ሁሉ የሚመለከት
አል ሐኪም (ፈራጅ)	የነገሮችና የፍርዶች ሁሉ መመለሻ
አል ዓድል (ፍትህ)	በግዛቱ ውስጥ ነውር ወይም ጉድለት የሌለበት
አልለጢፍ (አዛኝ)	ለባሮቹ የሚያዝን
አል ኸቢር (እውቀተ ሰፊ)	ግልጽም ስውርም የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚያውቅ
አል ሐሊም (ታጋሽ)	ለቅጣት የማይቸኩል
አል ዐዚም (ታላቅ)	ከአእምሮ ግንዛቤና ችሎታ በላይ የሆነ
አል ገፉር (መሐሪ)	ጠላቱን የሚምርና ተውበትን የሚቀበል
አል ከቢር (ታላቅ)	ከአልባሌ ነገሮች የጠራ
አል ሐፊዝ (ጠባቂ)	ፍጡራንን ከመናጋት የሚጠብቅ
አል ሙቂት (ቀላቢ)	ለፍጡራን ቀለባቸውን የሚፈጥር እና የሚያከፋፍል
አል ሐሲብ (በቂ)	የፍጡራንን ጉዳይ ያለ ተጋሪ የሚያከናውን፣ ለጉዳያቸው በቂ
አል ጀሊል (ልዑል)	ልእልናውና ምሉእነቱ የላቀ
አል ከሪም (ቸር)	ስጦታው የማይነጥፍ
አል ረቂብ (ተቆጣጣሪ)	ፍጡራንን የሚያውቅና የሚከተታተል

አል ሙጂብ (ዱዓን ተቀባይ)	ዱዓን ተቀባይ
አል ዋሲዕ (ሰፊ)	ከሰማያትና ከምድር የሰፋ
አል ሐኪም (ጥበበኛ)	ከምሉእነቱና ከልቅናው ጋር የሚቃረኑ ተግባራትን ከመፈጸም የጠራ
አል ወዱድ (ተወዳጅ)	የፍጡራኑን ውዴታ ለማግኘት የሚተጋ
አል መጅዱ	በማንነቱም ሆነ በስራዉ የላቀ፣ ችሮታውም ብዙ፡ ፡
አል ባኢስ (ቀስቃሽ	ሙታንን ለምርመራ የሚቀሰቅስ
አል ሸሂድ	ግልጽም ስውርም የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉ የሚመለከት
አል ሳዲቅ (እውነተኛ)	ሁሉንም ነገር በጥበብ የፈጠረ
አል ወኪል (ወኪል)	የሁሉንም ጉዳዮች ሐላፊና ከዋኝ፡፡
አል ቀዊይ (ጠንካራ)	ምንም ነገር የማይሳነው
አል መቲን (ጽኑ)	ምንም ነገር የማያሸንፈው
አል ወሊይ (አለኝታ)	በወዳጆቹ ተወዳጅ፣ የነርሱ ረዳትና አለኝታ
አል ሐሚድ (ምስጉን)	ለምስጋናና ለውዳሴ ተገቢ
አል ሙህሲ	ጥቃቅን ጉዳዮች የማያመልጡትና ታላላቆች የማይሳኑት (በጥንቃቄ መዘጋቢ)
አል ሙብዲዑ	ፍጡራንን መጀመሪያ ካልነበሩበት ያስገኘ (ጀማሪ)
አል ሙኢዱ	ፍጡራንን ወደ ሞት የሚመልስ (መላሽ)
አል ሙህይ	የበሰበሱ አጥንቶችን ሕያው የሚያደርግ

አል ሙሚት	ነፍስን ከአካል በመነጠል የሚገድል
አል ሐዩ	ዘልዓለማዊ ሕይወት ያለው (ሕያው)
አል ቀዩሙ	ሁሉንም ነገር ያለ ረዳት የሚያከናውን (ራሱን ቻይ)
አል ዋጅድ	የሚፈልገውን ሁሉ ማግኘት የሚችል (አግኝ)
አል ማጅድ	የተላቀ ችሮታና በጎ ምግባር ባለቤት
አል ዋሂድ	በማንነቱም፣ በባህሪውም፣ በስራውም መሰል የለሽ (ብቸኛ)
አል ሰመድ	ጉዳዮች የሚከጀሉበት (መጠጊያ)
አል ቃዲር	ፍጡራኑን በመፍጠር ብቸኛ
አል ሙቅተዲር	የሻውን ነገር የሚወስን
አል ሙቀዲሙ	ነብያትን፣ ወዳጆቹንና ከፍጡራን የሚሻውን የሚያስቀድም
አል ሙአኺር	ጠላቶቹን (ከእዝነቱ) በማራቅ የሚያዘገይ
አል አወል	ሁሉንም ነገር የቀደመ
አል አኺሩ	ፍጡራን ከጠፉ በኋላ ወደኋላ የሚቀር
አል ዛሂር	በምልክቶቹ፣ በተአምራቱና በአድራጎቱ ሕልውናው ግልጽ
አል ባጢኑ	ከእይታ የተሰወረ፣ ሚስጥራትን ሁሉ አዋቂ
አል ዋሊ	የነገሮች ባለቤት፣ በችሮታው ውለታ የሚውል፣ መከራን የሚከላከል።
አል ሙተዓሊ	ደረጃው ከፍ ያለ፣ የዓርሽ ባለቤት፣ በክብሩና

	በሕልውናው የላቀ
አል በር	ለለመኑት ቸር
አል ተዋቡ	ከባሮቹ ተውበትን የሚቀበልና ሐጢአትን ይቅር የሚል
አል ሙንተቂም	ቅጣቱ የሚፈራ፣ እዝነቱ በፍርሃትና በተስፋ የሚከጀል
አል ዓፍው	ወንጀልን የሚያብስ፣ ጥፋትንና ወንጀልን የሚያልፍ
አል ረኡፍ	ለባሮቹ በጣም አዛኝ
ዙልጀላሊ ወልኢክራም	የልእልናዎችና የልቅናዎች ሁሉ ባለቤት፣ ከፍጡራኑም የላቀ።
አል ሙቅሲጡ	ፍትህ አስፋኝ (ፍትሃዊ)
አል ጃሚዑ	በማንነቱ፣ በባህሪውና በስራው ምሉእ ባህሪያትን ሁሉ የሰበሰበ (ሰብሳቢ)
አል ገንይ	በማንነቱ፣ በሕልውናውም ሆነ በስራው አንዳች ነገር የማይከጅል (ሐብታም)
አል ሙግኒ	ከባሮቹ ለሚሻው ሰው የሚሰጥ
አል ማኒዑ	ባሮቹን ለመጠበቅ መከራን የሚያስቀርና ለፈተና ችሮታውን የሚያቅብ
አድዲሩ	ከባሮቹ የሚሻውን የሚጎዳ፣ የጉዳት ባለቤት
አል ናፊእ	የመጥቀም ባለቤት፣ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ
አል ኑር	በተውሂዱ የእውነተኞችን ልቦናዎች የሚያበራ
አል ሐዲ	ሁሉንም ነገር የፈጠረና የመራ

አል በዲዕ	ጥበበ ረቂቅ ፈጣሪ
አል ባቂ	ዝንተ ዓለም የሚኖር
አል ዋሪሱ	በሰማያትና በምድር ያሉ ፍጡራን ሁሉ ባለቤት፣ የሁሉም ነገር ጌታ፣ ሲሳይ ለጋሽና አዛኝ
አል ረሺድ	እርሱን ለሚታዘዙና ለሚገዙ ሰዎች ቅኑን ጎዳና አመላካች
አል ሰቡር	ጊዜ የሚሰጥ፣ የሚታገስ፣ የማይቸኩል፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) በአላህ የማመንን ትርጉም ግለጽ፡፡
2) የተውሂድ ዓይነቶችን አብራራ
3) በአላህ የማመንን በጎ ፍሬዎች ዘርዝር
4) የተውሂድ ሩቡብያን ትርጉም ግለጽ
5) የተውሂድ ሩቡብያን መልእክትና ይዘት አብራራ
6) ተውሂድ ሩቡብያን በልቦና ውስጥ ለማስናት የሚረዱ ተግባራዊ እርምጃዎችን በከፊል ዘርዝር
7) የተውሂደል ኡሉሀያን ጥቅል ትርጉም ግለጽ
8) ተውሂደል ኡሉህያ የሚያስከትላቸውን ሐላፊነቶችና ግዴታዎች በከፊል ዘርዝር
9) የተውሂደል አስማ ወሲፋትን ጥቅል ትርጉም ግለጽ
10) የአላህ ባህሪያት ዓይነቶችንና ከነኝህ ባህሪያት ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን ዘርዝር
11) የአላህን ስሞች ይዘት አብራራ
12) የአላህን ስሞችና ያዘሉትን ትርጉም አብራራ

* * *

ምእራፍ አራት

ቆይታ ከአላህ መልእክተኛ ታሪክ

የተመረጡት ነብይ ታሪክ

የዘር ሐረጋቸው፣ አወላለዳቸው እና የልጅነት ዘመን

አጠቃላይ ዓላማ

1) የነቢዩን ዘር ሐረግና አወላለዳቸውን ማወቅ፣

2) አላህ ለመልእክተኛው ያደረገላቸውን እንክብካቤና ጥበቃ ማብራራት፣

3) የቲም የሆኑበትን እና አጎታቸውና አያታቸው እንዲሞቱ የተደረገበትን ጥበብ ማብራራት፣

4) የነቢዩን አርአያነት በመከተል ሐላል ሪዝቅ ብቻ መፈለግን ማበረታታት፣

5) ተማሪው ለራሱ የበጎ ስነ ምግባር ስልጠና እንዲሰጥ ማበረታታት

6) ተማሪው ከዚህ የነቢዩ ታሪክ ክፍል የቀሰማቸውን ትምህርቶች ምን ያህል ወደተግባር እንደለወጣቸው ማጤንና ማብራራት፣

የዘር ሐረጋቸው፡- ሙሐመድ የአብደላህ ልጅ፣ የአብዱል ሙጦሊብ ልጅ፣ የሐሽም ልጅ፣ የመናፍ ልጅ፣ የፈህር (ቁረይሽ) ልጅ፣ የማሊክ ልጅ፣ የነድር ልጅ፣ የኪናነህ ልጅ፣ የአድናን ልጅ፣ የአላህ ነብይ እስማኤል ልጅ፣ የአላህ ወዳጅ የኢብራሂም ልጅ።

አላህ ከጥሩ ጎሳ መረጣቸው። የመሐይምነት ዘመን ቆሻሻ ወደ ዘር ግንዳቸው አልገባም።

ሙስሊም እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ከእስማኢል ልጆች ኪናናን፣ ከኪናናህ ልጆች ውስጥም ቁረይሽን፣ ከቁረይሽ ሐሽምን፣ ከበኒ ሐሽም በኩል ደግሞ እኔን መርጧል።›› (ሙስሊም)

አወላለዳቸው፡- የተወለዱት የዝሆን አመት (ዓመል ፊል) በመባል በሚታወው ዘመን ነው። ይህም ዓመት አብረሃት ካእባን ለማፍረስ

የሞከረበት ዓመት ነበር። አላህም እጅግ በሚያስደንቅ ጥበብና ተአምር ሐሳቡን አምክኖታል። ይህ በቁርአን ታሪክ ተወስቷል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) በዚሁ አመት በወርሃ ረቢአል አወል 11ኛው ቀን በእለተ ሰኞ እንደተወለዱ ዘገባዎች ያመለክታሉ።

አስገራሚ ጅምርና ግልጽ በረከት፡- አባት አልባ ሆነው ተወለዱ። እናታቸው እርሳቸውን የሁለት ወር እርጉዝ እያለች አባታቸው ሞቱ። አያታቸው አብዱል ሙጦሊብም የማሳደግ ሐላፊነቱን ወሰዱ። በያኔዎቹ አረቦች ባህል መሠረትም ከበኒ ሰእድ ጎሳ የሆነችና ሐሊመት ቢንት አቢ ዙዓይብ የምትባል እንስት ታሳድጋቸው ዘንድ ተሰጣት።

የታሪክ ጸሐፊዎች እንደሚስማሙት ያኔ የበኒ ሰእድ ቀዬ በድርቅ የተመታበት አመት ነበር። የእንስሳት ጋቶች ነጥፈዋል። አዝርእቱ ደርቀዋል። ነቢዩ ሙሐመድ ከሐሊማ ቤት ካረፉበት እና ጡቷን መጥባት ከጀመሩበት ቅጽበት አንስቶ ግን የሐሊማ ቤት በበረከት ተሞላ፡ ፡ ፍየሎቿ ጠግበውና ጋቶቻቸው በወተት ተሞልቶ ይመለሱ ጀመር።

በበኒ ሰእድ መስክ ላይ እያሉ የተከሰተው የደረታቸው መቀደድ አላህ ለትልቅ ሐላፊነት እንደመረጣቸው የሚጠቁም የነብይነት ምልክት ነበር። አነስ ቢን ማሊክን ዋቢ በማድረግ ሙስሊም እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ በልጅነታቸው ዘመን ከሕጻናት ጋር በመጫወት ላይ እያሉ ጅብሪል መጣና ያዛቸው። አጋደማቸውም። ደረታቸውንም ሰነጠቀው። ልቦናቸውንም አወጣ። የረጋ ደም የሚመስል ነገርም ከውስጡ አስወገደ። ‹‹ይህ የሰይጣን ድርሻ ነው›› አለም። በወርቅ ሳህን ውስጥ አድርጎም በዘምዘም ውሃ አጠበው። ከዚያም እንደነበር ጠገነውና ወደቦታው መለሰው። ልጆችም ወደ ሐሊማ ቤት እየሮጡ ሄደው ‹‹መሐመድ ተገደለ›› በማለት ተናገሩ። ሲመጡ የነቢዩ ፊት ገርጥቶ አገኙት። አነስ፡- ‹‹የዚህን ክስተት ፋና ከነቢዩ ደረት ላይ አይቻለሁ።›› ሲሉ ተናግረዋል። ከልባቸው ውስጥ የረጋ ደም የሚመስል ነገር መወገዱ እርሳቸውን ከልጅነት አጓጉል ባህሪያት አርቆ፣ ቁም ነገረኛ፣ ጽኑ፣ ሚዛናዊና ውብ ባህሪያት የተላበሱ ለማድረግ ነው።አላህ በጣም እንደሚጠበቃቸው እና

እንደሚንከባከባቸው፣ ሰይጣንም እርሳቸውን የመተናኮል አቅም እንዳይኖረው መደረጉን ለማመልከትም ጭምር ነው።[1]

ይህ ክስተት ሐሊማ ሕጻኑን ወደቤተሰቦቹ እንድትመልስ ምክንያት ሆነ። ያኔ የተላቁት ነብይ እድሜ አምስት አመት ነበር። ስድስት አመት ሲሞላቸው እናታቸው አሚና ሞተች። አያታቸው ሊያሳድጓቸው ወሰዷቸው። ስምንት ዓመት ሲሞላቸው አያታቸው ሞቱ። የማሳደጉን ሐላፊነትም አጎታቸው አቡ ጧሊብ ወሰዱ።

የላቀ እጣ ፈንታ

አስራ ሁለት አመት ሲሞላቸው አጎታቸው አቡ ጧሊብ ወደ ሻም ለንግድ እርሳቸውን አስከትለው ወጡ። ቅፍለቱ በስራ ከተባለ ቦታ ላይ ሲያርፍ ቡሐይራ የተባለን አንድ መነኩሴ ለመነጋገኘት ጎራ አለ። ሰውየው የክርስትና ሐይማኖትና መጽሐፍት አዋቂ ነው። ነቢዩን በትኩረት አስተዋላቸው። በጥንቃቄ አጠናቸው። አናገራቸውም። ከዚያም ወደ አቡ ጧሊብ በመዞር፡- ‹‹ይህ ልጅ ምንህ ነው?› አላቸው። ‹ልጄ ነው›› አሉት። (አቡ ጧሊብ በጣም ስለሚወዷቸው ልጄ በማለት ነበር የሚጠሯቸው።) ቡሐይራም፡- ‹‹ልጅህ አይደለም። የዚህ ልጅ አባት በሕይወት ሊኖር አይችልም።›› ሲል ተናገረ። አቡ ጧሊብም፡- ‹‹የወንድሜ ልጅ ነው።›› አሉ። ‹‹አባቱ ምን ሆነ?›› ሲል ጠየቃቸው። ‹ተረግዞ እያለ ሞተ።› አሉ። ‹‹እውነት ብለሐል። በአስቸኳይ ወደሐገሩ ይዘህው ተመለስ። አይሁዶች እንዳያገኙት ተጠንቀቅ። በአላህ እምላለሁ። ካገኙት ይተናኮሉታል። ለታላቅ ደረጃ የሚበቃ ልጅ ነው።›› አላቸው። አቡ ጧሊብም ፈጥነው ወደ መካ መለሱት።

እንጀራ ፍለጋ

የአላህ መልእክተኛ ለወጣትነት እድሜ ሲደርሱ እንጀራ ፍለጋ መሮጥ ጀመሩ። ፍየል ጥበቃ የጥረታቸው መጀመሪያ ነበር። በኋላ ላይ፡- ‹‹ለመካ ሰዎች በቀራሪጥ (ክፍያ)ፍየል እጠብቅ ነበር።› ሲሉ ተናግረዋል፡

[1] ፊቅሁ ሲራ -በዶክተር ረመዷን ቡጢ

አላህ ያደረገላቸው ጥበቃ

ከወጣትነት አንጉል ድርጊቶችና ጨዋታዎች ሁሉ አላህ ጠብቋቸዋል፡፡ስለ ራሳቸው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹በመሐይምነት ዘመን ወጣቶች ይፈጽሟቸው የነበሩ ድርጊቶችን ለመፈጸም ያሰብኩት ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ በነዚህም ጊዜያት አላህ ያሰብኩትን እንዳላደርግ አቀበኝ፡፡ ከዚያ በኋላ በመልእክተኛነት እስኪልከኝ ድረስ ተመሳሳይ ድርጊት አስቤ አላውቅም፡፡ ይህውም አንድ ቀን በሌሊት በመካ ከፍታማ ቦታዎች ላይ ፍየል አብሮኝ ይጠብቅ ለነበረ ልጅ፡- ፍየሌን ጠብቅልኝ፡፡ ልክ እንደወጣቶች መካ ውስጥ ስጫወት ልደር›› አልኩት፡፡ ‹‹ይሁን›› አለኝ፡፡ወደ መካ ወረድኩ፡፡ እዚያ እንደደረስኩ ከአንድ ቤት ውስጥ ዘፈን ሰማሁ፡፡ ምንድን ነው? በማለት ስጠይቅ፣ የሰርግ ዘፈን እንደሆነ ተነገረኝ፡፡ ቁጭ ብዬ ማድመጥ ስጀምር አላህ ጆሮዬን ደፈነው፡፡ ጥልቅ እንቅልፍም ወሰደኝ፡፡ ከእንቅልፍ ያነቃኝ የረፋዱ ጸሐይ ግለት ነበር፡፡ ወደ ባልንጀራየም ተመለስኩ፡፡ ስለ አዳሩ ጠየቀኝ፡፡ የሆነውን ነገርኩት፡፡ በሌላ ሌሊትም ተመሳሳይ ሙከራ አደረግኩ፡፡ ልክ የመጀመሪያው ሌሊት ዓይነት ሁኔታ አጋጠመኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ያን ዓይነት ሐሳብ አስቤ አላውቅም፡››

በአላህ ብቻ መመካት

የፍጡራን ፈርጥ ለየት ያለ የሕይወት ጅማሬ፣ አላህ ቀልባቸው ከርሱ ውጭ በሌላ አካል እንዳይንጠለጠል እንደፈለገ ያመለክታል፡፡ በአባት፣ በእናት፣ በአያት ወይም በአጎት፣ በገንዘብ፣ በስልጣን ወይም በሌላ ነገር እንዳይመኩ የፈለገ ይመስላል፡፡ ይህ ስሜት ለሙስሊም ባጠቃላይ እና ለዳኢ በተለይ ለስብእናው ስሪት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከሚንከባከባቸው ክንድ ወይም ድሎት ከሚለግሳቸው ሰው ገንዘብ አርቆ አላህ ብቻ ሊጠብቃቸው እና ሊንከባከበው በመሻት ይህን አደረገ፡፡ ይህ ሲሆን፣ ‹‹አባቴ›› በማለት ፋንታ ‹‹አምላኬ›› ይላል፡፡ ነፍሳቸውም ወደ ገንዘብ ወይም ክብር፣ ወደ አያት ቅድመ አያቶች ንግስናና ስልጣን

ወደማስመለስ ስሜት አትዘነበልም። ሰዎችም የዱንያ ክብር ከነብይነት የተቀደሰ ደረጃ ጋር አይቀላቀልባቸውም።

ይህም በመሆኑ መልእክተኛው ነብይ ነኝ ያሉት ዓለማዊ ክብርና ጥቅም ለማግኘት ወይም በዘመናችን አገላለጽ ‹በሐይማኖት ለመነገድ› ነው የሚባሉ ክሶች ሁሉ የሚቆሙበት መሠረት አጡ። አለማዊያንና አምላክ የለሾች በቅን የዳአዋ ሰዎች ላይ ይህን ክስ በየዘመናቱ ሲሰነዘሩት ይደመጣል።

ጠቃሚ ትምህርቶች

ገና በለጋ እድሚያቸው እንጀራ ፍለጋ ያሳዩት ትጋት ሦስት ጠቃሚ ትምህርቶችን አካቷል።

1) አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ ያላበሳቸውን ውብ ባህሪና ረቂቅ ስሜት ያሳያል። አጎታቸው የተሟላ እንክብካቤ ያደርጉላቸው ነበር። ልክ እንደ አባት ያዝኑላቸው ነበር። ይህም ሆኖ ግን መልእክተኛው ሰርተው ማደር እንደሚችሉ ሲሰማቸው ወደ ስራ ተሰማሩ። የአጎታቸውን የገንዘብ ቀዳዳዎች ያቅማቸውን ያህል ለመሸፈን ጥረት አደረጉ። ከስራቸው የሚያገኙት ገቢ ምንም ያህል አነስተኛ ቢሆንም እንኳ ኩሩ ስብእናቸው፣ ያቅሙን ያህል ከመጣር የማይሰስተው ባህሪያቸው ወደ ስራ መራቸው። የአጎታቸው ውለታ ለመመለስና የተግባር ምስጋና ለማድረስ ይህን አደረጉ።

ስለዚህም አንተም ልክ እንደርሳቸው ጥንቁቅና ኩሩ ሁን። ‹‹ራስህን ባንገትህ ተሸከም።››

2) አላህ ለባሪያው በምድር ላይ የሚወድለትን የሕይወት ዓይነት የሚያብራራ አጋጣሚ ነው። ይህውም አላህ ቢፈልግ ኖሮ ለነቢዩ ገና ከሕይወታቸው መጀመሪያ ጀምሮ ኑሯቸውን ድሎታማ በማድረግ እንጀራ ፍለጋ ከመኳተን መታደግ ይችል ነበር። ግና ለሰው ልጅ መልካሙ ገንዘብ ለሕብረተሰቡ በሚሰጠው አገልግሎት ወይም በጥረቱ የሚያገኘው መሆኑን፣ ሳይሰራ እና ሳይለፋ፣ ለሚኖርበት ማሕበረሰብ

ቅንጣት በጎ ነገር ሳያደርግ፣ ስራ ፍትቶና እጁን አጣጥፎ ተቀምጦ የሚያገኘው ገንዘብ ደግሞ መጥፎ መሆኑን በጥበቡ ሊያስተምረን ስለከጀለ ነው።

በመሆኑም ልክ እንደ ተወዳጁ ነብይ ሐላል ስራዎችን ብቻ ሰርተህ ገንዘብ ለማግኘት ጉጉና ትጉ ሁን።

3) ዳዒ የኑሮ መሠረቱ ዳእዋ ሲሆን፣ ወይም በሰዎች ስጦታና ምጽዋት ላይ ሲመሠረት ዳእዋው ክብደትና ግምት ያጣል።

﴿ يَٰقَوۡمِ لَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ أَجۡرًاۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَى ٱلَّذِي فَطَرَنِيٓۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٥١ ﴾

“ወገኖቼ ሆይ! ለዚህ (ጥሪዬ) ክፍያ አልጠይቃችሁም። ምንዳ የምሻው ከዚያ ከፈጠረኝ (አምላክ) ብቻ ነው። አታስተውሉምን?” (ሁድ 51)

መልእክተኛው የሰዎች ውለታ በአንገታቸው ዙሪያ ተጠምጥሞ ሐቅን ይሉኝታ ሳይዛቸው በድፍረት እንዳይናገሩ የሚያደርጋቸው አንድም አጋጣሚ በነብይነት ከመላካቸው በፊትም ሆነ በኋላ በሕይወታቸው ውስጥ እንዲኖር አላህ አልፈቀደም።

ስለዚህም ለራስህ እና ለዳእዋው ክብር ቀናኢ ሁን። ለምትሰጠው የዳእዋ አገልግሎት ከሰዎች ምንዳም ሆነ ምስጋና አትሻ። የእስልምና ዳእዋ ልክ እንደ አንበሳ ኩሩና ቁጥብ፣ እንደ ዳመና ውሃ ንጹህ መሆኑን እወቅ።

ፍጹም ሰዋዊ ስብእና

ነቢዩ ሙሐመድ እንደ ማንኛውም ሰው ሰዋዊ ባህሪን የተላበሱ፣ ሰዋዊ ስሜቶችና ፍላጎቶች ያሏቸው መሆኑ ጥርጥር የለውም። በማንኛውም ወጣት ላይ የሚስተዋሉ ተፈጥሯዊ ዝንባሌዎች ነበሩባቸውም። ይህም እውነት ከሌሎች ሰዎች የተለዩ እንዳልሆኑ ያመለክታል። ልክ እንደ ሌሎች ወጣቶች በጨዋታ የሚያሳልፉት ጊዜ ቢኖራቸው ይፈልጋሉ። ይህ ተፈጥሯዊ ስሜት መጥፎ አይደለም። ይሁንና አላህ ይህን ተከትሎ ከሚመጣና ከበጎ ስነ ምግባሮች ለምሳሌ፣ የዘልዓለማዊው አምላካዊ ሽሪዓ

መምህር ከመሆናቸው ጋር ከማይጣጣሙ አንጉል አጋጣሚዎች ጠበቃቸው።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) አላህ መልእክተኛውን ከመልካም እና ንጹህ ጎሳ መረጣቸው። የመሐይምነት ዘመን ቆሻሻ ወደ ዘር ግንዳቸው አልገባም። ይህን ሐሳብ አብራራ።

2) አላህ ለመልእክተኛው ያደረገላቸውን እንክብካቤና ጥበቃ አብራራ። ከዚህ እይታ ምን ተማርክ?

3) በነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ስብእና ላይ ካደረግከው ጥናት አኳያ እንጀራ ፍለጋ መትጋት ያለውን ጠቀሜታ አብራራ።

4) ልቦና በአላህ ብቻ መንጠልጠሉ ያለውን ጠቀሜታ ከተማርከው ትምህርት አኳያ- ግለጽ፣

5) ከዚህ የነቢዩ ታሪክ ክፍል ያገኘህውን ትምህርት በተግባር ለማዋል ያለህን ዝግጁነት አብራራ።

የፉጁር ጦርነትና የፉዱል ስምምነት

አጠቃላይ ዓላማ

1) የፉጁር ጦርነትን ምንነት ማብራራት፣

2) ሒልፈል ፉዱል በመባል የሚታወቀውን ስምምነት ከነ ምክንያቱ ማብራራት

3) ተማሪው በደልን እንዲከላከል እና መብትን ለባለ መብቶቹ እንዲመልስ ማበረታታት

4) ከሐርበል ፉጁር እና ከፉዱል ስምምነት የሚገኙ ትምህርቶችን እንዲዘረዝር

5) እነዚህን ትምህርቶች በተግባር ለማዋል ያለውን ዝግጁነት እንዲያስረዳ

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እድሜያቸው 14 ሲሞላ ‹ሐርበል› ፉጁር በተባለው ጦርነት ላይ ተሳተፉ። የኪናናህና የቁረይሽ ጎሳ በአንድ ወገን፣ የቀይስ ጎሳ በሌላ ወገን ተሰልፈው ያደረጉት ጦርነት ነው። ለአረቦች እጅግ አስፈሪ ጦርነት ነበር። የተቀደሰችውን የመካን ከተማ ክብር የገሰሰ ስለነበር እለቱ “የውመል ፉጁር” (የአመጽ ቀን) ተባለ። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

‹‹በዚያ ጦርነት ላይ ለአጎቶቼ ቀስት እየሰበሰብኩ አቀብል ነበር።

ያኔ የአስራ አራት ወይም የአስራ አምስት አመት ልጅ እንደነበሩ ከፊል ዘገባዎች ያመለክታሉ። ሌሎቹ ደግሞ የ20 አመት ልጅ መሆናቸውን ዘግበዋል። የመጀመሪያው ሐሳብ ሚዛን ይደፋል። ምክንያቱም በጦርነቱ ወቅት የነበራቸው ሚና ቀስት እየሰበሰቡ ማቀበል መሆኑ ልጅ እግር እንደነበሩ ያመለክታል። ይህ ተሳትፎ ከልጅነታቸው ጀግንነትን እንዲማሩና የውጊያ ልምድ እንዲቀስሙ አደረጋቸው። ይህ ጦርነት እንደሌሎች የአረቦች ጦርነቶች ሁሉ በኢምንት ምክንያት የተነሳ ነው። ከዚያም የዘረኝነት እሳት አቀጣጠለው። የኢስላም ብርሃን ልቦናዎቻቸውን አስማምቶ ይህን ጥመት እስኪያስወግድላቸው ድረስ እንደዚሁ ነበሩ።

ቁረይሾች ከፉጁር ጦርነት እንደተመለሱ ፉዱል ለተባለው ስምምነት ተጠራሩ። ስምምነቱ ከቁረይሽ ባላባቶች መካከል አንዱ በነበረው በጀድዓን ቢን ተይሚ ቤት ውስጥ ተፈጸመ። የስምምነቱ ይዘት መካ ውስጥ ተበድሎ ያገኙትን ማንኛውም ሰው -የከተማዋ ነዋሪ ይሁንም አይሁን- ከጎኑ ቆመው በደሉን ለማካካስ የተስማሙበት ነበር። የአላህ መልእክተኛ ከአጎቶቻቸው ጋር በመሆን በስምምነቱ ላይ ተሳትፈዋል። አላህ በመልእክተኝነት ከላካቸው በኋላ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡-

‹‹በአብደላህ ቢን ጀድአን ቤት ውስጥ ከተደረገው ስምምነት ላይ ተገኝቻለሁ። ከዚያ ሳልገኝ ቀርቼ በልዋጩ ቀይ ግመል ቢሰጠኝ

የምመርጥ አይደለሁ፡፡ በእስልምና ውስጥ ሆኜም ወደዚያ ስምምነት ብጋበዝ ግብዣውን እቀበላለሁ፡፡››

ምክንያቱም እርሳቸው የተላኩት መልካም ስነ ምግባራትን ለማሟላት ነው፡፡ የስምምነቱ ይዘትም የመልካም ስነ ምግባር አካል ነው፡፡ ኢስላም የስምምነቱን አብይ ይዘት ያጸድቃል፡፡ ይህ ስምምነት በርካታ ሰዎችን ከበደል ታድጓል፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የፉጃር ጦርነትን ምንነት አብራራ
2) ሒልፈል ፉዱል በመባል የሚታወቀውን ስምምነት ከነ ምክንያቱ አብራራ
3) የዚህን ስምምነት ልቅና የሚያሳየውን የነቢዩ ሐዲስ አውሳ
4) ከሒልፈል ፉዱል ስምምነት ከምናገኛቸው ትምህርቶች መካከል ዋነኛው፡- ‹‹ከተበዳይ ጎን መቆምና በደሉን ማካካስ›› ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለህን የግል ተሞክሮ ማካፈል ትችላለህን?
5) የአላህ መልእክተኛ በፉጃር ጦርነትና በፉዱል ስምምነት ላይ እንዲሳተፉ ያደረጋቸውንና በበርካታ ሰዎች ስብእና ላይ የማይታየውን መልካም ባህሪ ጥቀስ፡፡

እመት ኹዲጃን ማግባታቸው

አጠቃላይ ዓላማ

1) ተማሪው የነቢዩንና የኹዲጃን የጋብቻ ታሪክ እንዲያስታውስ
2) በትዳር ጓደኛ አመራረጥ ረገድ የመልእክተኛውን አርአያነት እንዲከተል
3) ከነቢዩና ከኹዲጃ የጋብቻ ታሪክ የሚገኙ ትምህርቶችን እነዲዘረዝር

4) እነዚህን ትምህርቶች ወደ ተግባር ለመለወጥ ያለውን ዝግጁነት እንዲያብራራ

* * *

ኢብን ሂሻም እንደዘገቡት ኸዲጃ ማሕበራዊ ክብር እና ሃብት የነበራት ነጋዴ እንስት ናት። ወንዶችን በሽርክና ታስነግዳለች። የአላህለ መልእክተኛ ሐቀኝነትና ታማኝነት እንዲሁም መልካም ስብእና ስትሰማ ወደርሳቸው መልእክት በመላክ ገንዘቧን ይዘው ለንግደ ወደ ሻም እንዲሄዱ ጠየቀቻቸው። ለሌሎች ከምትሰጠው በላይ ገንዘብም ልትሰጣቸውና መይሰራህ የተባለ አገልጋይዋን ከርሳቸው ጋር ልትልክ ቃል ገባች።

ነቢዩ ጥያቄዋን ተቀበሉ። ገንዘቧንም ይዘው ከአገልጋይዋ ከመይሰራህ ጋር ወደ ሻም ተጓዙ። ጉዟቸው የተሳካ ነበር። እጥፍ ድርብ ትርፍ ይዘው ወደ ኸዲጃ ተመለሱ። ገንዘቡንም በታማኝነት አስረከቡ። መይሰራህ የነቢዩን መልካም ስብእናና ውብ ባህሪ ሲያይ ልቦናው በአድናቆትና በክብር ተሞላ። ያየውንም ለኸዲጃ አወጋት። እርሷም በነቢዩ ታማኝነት ተደነቀች። በርሳቸው ሰበብ ያገኘችው በረከትም ሳያስገርማት አልቀረም። ይህ ሁኔታ ለጋብቻ እንድትጠይቃቸው አነሳሳት። ሐሳቧን አቀረበችላቸው። እርሳቸውም ተቀበሏት። አጎቷን አምር ቢን አሰድን በአጎታቸው በአቡ ጧሊብ በኩል አስጠየቁ። አቡ ጧሊብ የጋብቻ ጥያቄውን ያቀረቡት በሚከተለው ንግግር ነበር፦

‹‹የኢብራሂም ዝርያ፣ የቤቱ ጠባቂ፣ የሐጃጆች አገልጋይ ላደረገን አምላክ ምስጋና ይድረሰው። ይህ የወንድሜ ልጅ መሐመድ በገንዘብ በኩል ድሃ ቢሆንም በመልካም ስብእናና በአስተዋይነት ከየትኛውም ወንድ ሚዛን ይደፋል። ገንዘብ ደግሞ አላፊና ጠፊ ነገር ነው። ከዚህ በተጨማሪም መሐመድ ታላቅ እድል ያለው ሰው ነው። ልቅናችሁን በመሻትም ኸዲጃን ለጋብቻ ጠይቋታል። ይህን ያህል ጥሎሽም ይጥላል።››

የኸዲጃ ቤተሰቦች ተስማሙ። ጋብቻውም ተፈጸመ። ያኔ የእርሳቸው እድሜ 25 ዓመት ሲሆን፣ የርሷ ደግሞ 40 ዓመት ነበር። ኸዲጃ እርሳቸውን ከማግባቷ በፊት ሁለት ባሎችን አግብታ ፈትታለች።

መሠረት አልባ ሂስ

ነቢዩ ከኸዲጃ ጋር ያደረጉት ጋብቻ ለስጋዊ ሐሴት ብዙም ትኩረት የማይሰጡ እንደነበሩ ያመለክታል። እንደሌሎች የእድሜ እኩዮቻቸው ወጣቶች ስጋዊ ደስታን የሚሹ ቢሆን ኖሮ በእድሜ ከርሳቸው የምታንስ፣ ቢያንስ ቢያንስ የእድሜ እኩያቻውን ያገቡ ነበር።

እርሷን ለማግባት የወሰኑት ክብሯንና መልካም ስብእናዋን ተመልክተው ነበር። በዘመነ መሐይምነት ንጹህና ከአንጉል ድርጊት የተጠበቀች እንደነበረች ተመስክሮላታል። (የአንተም የትዳር ጓደኛ ምርጫ የነብይህን አርአያነት የተከተለ ይሁን።)

ይህ ጋብቻ እመት ኸዲጃ በ56 ዓመት እድሜያቸው እስከሞቱበት እለት ድረስ ቀጥሏል። ነቢዩም ሌላ ሴት የማግባት ሐሳብ ሳይኖራቸው እድሚያቸው 50ዎቹን ተሻገረ። ወንድ ልጅ ብርቱ የወሲብ ፍላጎቱን ለማርካት ሲል ብዙ ሚስቶችን ለማግባት የሚከጅለው ከ25-50 ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ መሆኑ ይታወቃል።

ነቢዩ መሐመድ () በኸዲጃ ላይ ሌላ ሴት የመደረብ ሐሳብ ሳያድርባቸው ይህን የእድሜ ክልል አለፉ። ቢፈልጉ ኖሮ በርካታ እንስቶችን ያገኙ ነበር። የሕብረተሰቡ ባህልም ይደግፋቸውዋል። ኸዲጃ አግብታ የፈታች እና በእድሜም የርሳቸው እጥፍ ልትባል የምትችል ሆና እያለ ቢያገቧትም ከርሷ ጋር ሌላ እንስት ሳያገቡ አብረዋት ኖረዋል።

ይህ እውነታ ለእስልምና የበረታ ጥላቻ ያላቸው ሚሽነሪዎችና ኦሪየነታሊስቶች፣ እንዲሁም የነርሱ አገልጋይ፣ የአስተሳሰባቸው አቀንቃኝ የሆኑ አምላክ የለሾችና አለማዊያን የሚሰነዝሩትን ክስ ባዶ የሚያስቀር ነው። እነዚህ ወገኖች የአላህን መልእክተኛ ጸታዊ ስሜት ያጠቃቸው አድርገው ለመሳል ጥረዋል። ዓላማቸው እውነትን መፈለግ

ሳይሆን እምነትን ማናጋት፣ የርሳቸውን አርአያነት ጥላሸት መቀባትና የወሲብ ስሜትን እሳት ማቀጣጠል በመሆኑ ሂሳቸው አያስገርምም።

ለስጋዊ ስሜቱ ተገዥ የሆነ ሰው እንደ አረቢያ ባለ በብክለት የተከበበ ክልል ውስጥ እየኖረ፣ በዙሪያው በሚተራመሰው የብክለት ማእበል ሳይሳብ እስከ 25 ዓመት እድሜው ንጹህና ጥብቅ ሆኖ ሊኖር አይችልም።

ከዚያ በኋላም በእጥፍ እድሜ የምትበልጠውን ፈት ሴት ለማግባት፣ ብሎም በዙሪያው ወዳሉ በርካታ እንስቶች አይኑን ሳይጥል፣ የፈለጋትን ሴት ለማግኘት ያለውን ሰፊ እድል ሳይጠቀም እድሜውን ሙሉ ከአዛውንት ሚስቱ ጋር ለመኖር አይፈቅድም።

ከኸዲጃ ሕልፈት በኋላ አኢሻን እና ሌሎች እንስቶችን ማግባታቸው በነቢዩ ሙሐመድ ልቅናና በምሉእ ባህሪያቸው ላይ ያለንን እምነት የሚያጠናክሩ ሰበቦችንና ጥበቦችን ያዘሉ ናቸው። የጋብቻዎች ምክንያቶች ምንም ይሁኑ ምን የእስልምና ጠላቶች እንደሚያናፍሱት ስጋዊ ስሜቱን ለማስተናገድ ሊሆን ፈጽሞ አይችሉም። ነቢዩ ይህ ፍላጎት ቢኖራቸው ኖሮ ሊያስተናግዱበት በሚችሉበት ተፈጥሯዊ ጊዜ ባስተናገዱት ነበር። በዚያ ላይ ያኔ ከየትኛውም ሐሳብና ሐላፊነት ነጻ ስለነበሩ ይህን ጥሪ ለማስተናገድ እንቅፋት የሚሆናቸው ነገር አልነበረም።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የአላህን መልእክተኛና የኸዲጃን የጋብቻ ታሪክ አውሳ።

2) ከዚህ የጋብቻ ታሪክ ውስጥ በአርአያነት ለመከተል ጠቃሚ የሆነው ገጽታው የትኛው ነው?

3) በዚህ የጋብቻ ሕይወት ውስጥ ያገኘህውን ትምህርት በገቢር ለማዋል ምን ያህል ተዘጋጅተሐል?

በካእባ ግንባታ መሳተፋቸው

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ተማሪው የተቀደሰውን የአላህ ቤት ክብር እንዲረዳ

2) በሕብረተሰቡ ጉዳዮች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን፣

3) የመልእክተኛውን ጥበብና ብስለት እንዲያውቅ፣

4) የአላህን መልእክተኛ አርአያነት በመከተል በማሕበራዊ ተሳትፎው መልካም እና አዎንታዊ እንዲሆን፣

5) የአላህ መልእክተኛ በካእባ ግንባታ ከመሳተፋቸው ታሪክ ውስጥ የሚቀሰሙ ጠቃሚ ትምህርቶችን እንዲዘረዝር፣

* * *

ካእባ በአላህ ስም፣ አላህን በብቸኝነት ለማምለክ የተገነባ የመጀመሪያው ቤት ነው። አባታችን ኢብራሂም ከጣኦት አምልኮ ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ ካደረጉ በኋላ ከአላህ በሆነ ትእዛዝ ካእባን አነጹ።

﴿ وَإِذۡ يَرۡفَعُ إِبۡرَٰهِـۧمُ ٱلۡقَوَاعِدَ مِنَ ٱلۡبَيۡتِ وَإِسۡمَٰعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧ ﴾ البقرة: ١٢٧

‹‹ኢብራሂምና ኢስማዒል (ተከታዩን ፀሎት እየደረጉ) የቤቱን መሠረት ከፍ ባደረጉ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፦"ጌታችን ሆይ! (ይህንን ተግባራችንን) ተቀበለን። አንተ ሰሚም፥ ዐዋቂም ነህ።" (አል በቀራህ 127)

ካእባ ከዚህ በኋላ ለብዙ አደጋዎች ተጋልጧል። ነቢዩ በነብይነት ከመላካቸው ከጥቂት አመታት በፊት መካን ያጥለቀለቀው ሐይለኛ ጎርፍ ይጠቀሳል። የአላህ መልእክተኛ በነብይነት ከመላካቸው በፊት ካእባን ለማደስ በተደረገው ጥረት ላይ በንቃት ተሳትፈዋል። በትከሻቸው ድንጋይ

እየተሸከሙ ያቀብሉ እንደነበር ተዘግቧል። ያኔ እድሜያቸው 35 ዓመት እንደነበር ዘገባዎች ያመለክታሉ።

ቡኻሪ እንደዘገቡት ጃቢር ቢን አብደላህ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

ካእባ በሚገነባ ጊዜ ነቢዩ እና አጎታቸው አባስ ድንጋይ ያቀብሉ ነበር። አባስም ለነቢዩ ‹‹ሸርጥህን ከአንገትህ ላይ ደልድለህ ተሸከም›› አላቸው። ነቢዩም እንደተባሉት ሲያደርጉ ራሳቸውን ስተው ወደቁ። ዓይናቸው ወደ ላይ ተንጋጠጠ። ‹‹ሸርጡን አቀብሉኝ›› አሉና ከወገባቸው ላይ ታጠቁት።[1]

ጥቁሩን ድንጋይ ወደ ቦታው የመመለስን ክብር ለማግኘት በጎሳዎች መካከል የተነሳውን ውዝግብ በማፍታቱ ሂደትም ነቢዩ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ውዝግቡ ወደ ጦርነት ሊያመራ ተቃርቦ ነበር። የበኒ አብዱዳርና የበኒ ዓድይ ጎሣዎች በደም የተሞላ ገበታ አቅርበው ለክብራቸው በጋራ ለመፋለም እጃቸውን ከገበታው ውስጥ በማስገባት ቃል ተገባቡ። ቁረይሾች ውዝግቡን ለመፍታት ለአራት ወይም ለአምስት ቀናት ቢቀመጡም አልተሳካላቸውም። በመጨረሻም አቡ ኡመየተል መኽዙሚ የተባለ ሰው፡- ‹‹ወገኖቼ ሆይ፣ አትወዛገቡ። ሁላችሁም የምትስማሙበትን ሰው ዳኛ አድርጉ።›› ሲል ሐሳብ አቀረበ። ‹‹በተቀደሰው ካእባ በር መጀመሪያ ለሚገባው ሰው ዳኝነት እናድራለን።›› ሲሉም ተስማሙ። ያ ሰው ታማኙ ሙሐመድ ሆኑ። ‹‹ይህ ታማኝ የሚሰጠንን ብይንስ በደስታ እንቀበላለን።› አሉ። ጉዳዩን አጫወቷቸው። እርሳቸውም ኩታቸውን ዘረጉ። ሁሉም ጎሳዎች የኩታውን ጫፍ እንዲይዙ አዘዙ። ድንጋዩን አነሱና ከኩታቸው ላይ አስቀመጡት። እንዲያነሱትም አዘዟቸው። ከሚቀመጥበት ቦታ ላይ ሲደርስ እርሳቸው ድንጋዩን ያዙና አስቀመጡት። ይህ ክስተት የነቢዩን አዎንታዊ ስብእና፣

[1] አላህ ይህን ያደረገው ሐፍረተ ገላቸውን ሌላ ሰው እንዳያየው ለመከላከል ነው። ይህ ክስተት እኒህ ሰው ለታላቅ ጉዳይ የታጩ መሆናቸውን አመላካች ነበር።

ጥበባቸውንና የላቀ ደረጃቸውን ያሳያል። ታዲያ ወገኖቻቸው መልእክታቸውን ላለመቀበል ለምን ያን ያህል አንገራገሩ?

የአላህ መልእክተኛ ተቀጣጥሎ የነበረውን የጦርነት እሳት ማጥፋታቸው አራት እውነታዎችን ይከስትልናል፡-

አንደኛ፡- አምንታዊነት የነቢዩ ሙሐመድ ስብእና መሠረታዊ አካል ነው፡ ፡ በካእባ ግንባታም ሆነ በሌሎች የማሕበረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ያሳዩት የነበረው የላቀ ተሳትፎ ከዚህ ባህሪያቸው የመነጨ ነው።

ሁለተኛ፡- ጉዳዮችን የሚያስኬዱበትን፣ ችግሮችን የሚፈቱበትን እጅግ አስደናቂ ጥበብ ያሳያል። በተለይም ይህን በጥበብ የከበረ የሽምግልና ሂደት ያከናወኑት በመካከላቸው ውዝግብ በተነሱባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ብዙ ደም ከመፍሰሱ በፊት እርቅ በማያወርዱ ጎሳዎች መሐል መሆኑ ደግሞ ለድርጊታቸው የበለጠ ድምቀት ይሰጠዋል።

ሦስተኛ፡- ከቁረይሾች ዘንድ የነበራቸውን የላቀ የክብር ደረጃ ያመለክታል፡ ፡ ‹ታማኙ› በሚል ማእረግ ይጠሯቸው ነበር። በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ ነበሩ።

አራተኛ፡- ከአላህ ዘንድ መልእክት ወርዶላቸው እርሱን ማድረስ በጀመሩ ጊዜ የነዚህ ወገኖቻቸው ልቦች በክህደት መሞላታቸው፣ በማስተባበልና በማወክ ጥረያቸውን ማስተናገዳቸው በጣም ያስገርማል። በየትኛውም ቦታና ዘመን የሚገኙ የእውነት ተጣሪዎችን የሚቀናቀኑ ወንጀለኞችን እኩይ ባህሪም በጉልህ ያሳያል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የተቀደሰው የአላህ ቤት የእስልምና ጎህ ከመፈንጠቁ በፊት በአረብ ጎሳዎች ልቦና ውስጥ የነበረውን ቦታ አብራራ፣

2) የአላህ መልእክተኛ በነብይነት ከመላካቸው በፊት የነበራቸውን አምንታዊ ስብእና የሚያሳዩ ክስተቶችን አውሳ

3) ነቢዩ በነብይነት ከመላካቸው በፊት በማሕበረሰባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ተሳተፉ? አጋጣሚዎችን ጥቀስ?

4) የእውነትን ጥሪ ክፉኛ የሚጠሉ ወገኖች፣ ዳዒው ከነርሱ ዘንድ ታማኝ እና እውነተኛ ቢሆንም እንኳ፣ ጥሪውን የሚያስተናግዱበትን ሁኔታና ባህሪያቸውን ግለጽ።

5) የአላህ መልእክተኛ በካእባ ግንባታ ላይ ከመሳተፋቸው ታሪክ የቀሰምካቸውን ትምህርቶች ዘርዝር።

* * *

ምእራፍ 5

የሶሐቦች ቅንጭብ ታሪክ

አቡበክር ሲዲቅ

ጦልሐ ቢን ዑበይዲላህ
ዙበይር ቢን አልዓዋም

አቡበክር ሲዲቅ

(ከሂጅሪያ በፊት 51 እስከ 13 ሂጅሪያ)

(ከ573-633 ዓ.ል)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ተማሪው የአቡበክር ሲዲቅን ጉልህ ባህሪያት እንዲያስታውስ፣

2) አሰላለማቸውን እንዲያስታውስ፣

3) ከአቡበክር ድንቅ ስብእና መገለጫዎች ውስጥ የተወሰኑትን እንዲያብራራ፣

4) ከአቡበክር የሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚቀሰሙ ትምህርቶችን እንዲዘረዝር፣

5) የአቡበክርን ስብእና በማጥናቱ ያገኛቸውን ጥቅሞች እንዲያስረዳ።

ታሪካቸው ባጭሩ

የነቢዩ ኽሊፋ የሆኑት አብደላህ ቢን አቡ ቁሐፋህ ኡስማን ቢን አሚር አልቁረይሺይ አልተሚሚ አቡበክር ሲዲቅ የገዘሆኑ ክስተት እውን በሆነ በሁለት አመት ከስድሰት ወሩ ተወለዱ።

ነቢዩ ሙሐመድ በነብይነት ከመላካቸው በፊት አቡበክር ባልንጀራቸው ነበሩ። ከነብይነት በኋላም ቀድመው ሰለሙ። በመካው የዳእዋ ዘመን አብረዋቸው ሆኑ። ወደ መዲና ሲሰደዱ፣ በዋሻው ታሪክና ከዚያ በኋላ እስኪሞቱ ድረስ ከርሳቸው አልተለዩም።

በተቡክ ዘመቻ የሙስሊሞችን አርማ ተሸካሚ ነበሩ። በዘጠነኛው ዓመተ ሂጅራ ነቢዩ በሕይወት እያሉ የሐጅ ስርዓትን መርተዋል። ከርሳቸው ሞት በኋላም እርሳቸውን ተክተው የሙስሊሞች ኽሊፋ ሆነዋል። የነቢዩ ሙሐመድ ምትክ (ኽሊፊቱ ረሱሊላህ) የሚል ማእረግም በሙስሊሞች አግኝተዋል።

ኢብን ኢስሐቅ ‹‹ሲረቱል ኩብራ›› በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዳወሱት አቡበክር በወገኖቻቸው ዘንድ ተወዳጅ እና ተግባቢ ሰው ነበሩ፡፡ በቁረይሽ የዘር ሐረግና ታሪክ እውቀትም አቻ አይገኝላቸውም፡፡ ጸባዬ መልካም ነጋዴ ነበሩ፡፡ ሰዎች የርሳቸውን እውቀት፣ ተሞክሮና መልካም ባህሪ በመሻት በጣም ይቀርቧቸው ነበር፡፡ ከርሳቸው ጋር መቀማመጥንም ይወዱ ነበር፡፡

አቡበክር ይበልጥ የሚቀርቧቸውንና የሚያምኗቸውን ሰዎች ወደ እስልምና ጋበዙ፡፡ በርሳቸው እጅ፣ ዑስማን፣ ጦልሐ፣ዙበይር፣ ሰእድ እና አብዱረህማን ቢን አውፍ ሰለሙ።

የእቁብ ቢን ሱፍያን በታሪክ ዘገባቸው እንዳወሱት፣ አቡበክር ሲሰልሙ አርባ ሺህ (የወርቅ ሳንቲሞች) ነበሯቸው፡፡ ወዲያውኑ በአላህ መንገድ መጸወቱት፡፡ ለአላህ ሲሉ ስቃይና መከራ ያስተናገዱ ሰባት ባሪያዎችን ገዝተው ነጻ ለቀቁ፡፡ እነርሱም ቢላል፣ ዓሚር ቢን ፉሐይራህ፣ ዚኒራህ፣ ነህዲያውና ልጇ፣ የበኒ ሙኡመል እንስት አልጋይና ኡም ዓቢስ ናቸው፡፡

አስማ ቢን ዘይድ አባታቸውን ጠቅሰው እንዳስተላለፉት አቡበክር እውቅ ነጋዴ ነበሩ፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ በነብይነት ሲላኩ አቡበክር አርባ ሺህ የወርቅ ሳንቲሞች ነበሯቸው፡፡ ባሪያዎችን እየገዙ በመልቀቅና የተቸገሩ ሙስሊሞችን በመርዳት ሐብታቸውን ወጭ አደረጉ፡፡ ወደ መዲና ሲሰደዱ 5 ሺህ (ፍራንክ) ብቻ ቀራቸው፡፡ እርሱንም መዲና ውስጥ መጸወቱት፡፡

ቡኻሪ እንደዘገቡት አምር ቢን አልዓስ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ከርስዎ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ ሰው ማን ነው?›› በማለት ጠየቅኳቸው፡፡ ‹አዒሻ› አሉኝ፡፡ ‹ከወንድስ›› አልኳቸው፡፡ ‹‹አባቷ›› አሉኝ፡፡ ቀጥሎም ሌሎች ሰዎችን አወሱ፡፡ አብደላህ ቢን ጃእፈር እንዲህ ብለዋል፡-

ወዳጃችን አቡበክር፣ መልካም፣ እጅግ ሩህሩህና አዛኝ ኸሊፋችን ናቸው፡፡

ኢብራሂም ኑኸኢ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አቡበክር በጣም አዛኝ ስለነበሩ ‹አዋህ› ተብለው ተጠሩ።››

በ11ኛው ዓመተ ሂጅራ በወርሃ ጀማዱል ኡላ ሰኞ ቀን በ63 ዓመት እድሜያቸው ይህችን ዓለም በሞት ተሰናበቱ።

ባህሪያቸው

በጃሂልያ ዘመን ከቁረይሾች መሐል በዘር ሐረግና በታሪክ እውቀት ወደር አይገኝላቸውም። ውጤታማ ነጋዴም ነበሩ። በመልካም ባህሪና በችሮታ ይታወቃሉ። ወገኖቻቸው ይወዷቸዋል። አስካሪ መጠጥ አይጠጡም፣ ጣኦት አያመልኩም። ስብእናቸውን የሚያጎድፍ አንዳች ድርጊት ሲፈጽሙ አልተስተዋሉም። ቆዳቸው ነጭና አካላቸው ሸንቃጣ፣ የፊታቸው ስጋ መጠነኛ ነበር። ዓይኖቻቸው ገባ፣ ግንባራቸው ወጣ ያሉ ነበሩ። ጸጉረ ብዙ፣ የተስተካከለ ቁመና ባለቤት ነበሩ።

ሰዎች በጃሂልያ ዘመን የአቡበክርን መልካም ስብእና እና ታማኝነት በማወቃቸው ‹አልሲዲቅ›› (እውነተኛው) በሚል ቅጽል ስም ጠሯቸው። በታማኝነታቸው ቁረይሾችን በመወከል ይፈጣጠሙ ነበር። ቁረይሾች እርሳቸው ያጸደቁትን ያጸድቃሉ። ሌላ ሰው ያጸደቀውን ግን ተቀብለው ለመተግበር ያንገራግራሉ።

አሰላለማቸው

ከነብይነት በፊት የመልእክተኛው ባልደረባ ነበሩ። አላህ ነቢዩን በመልእክተኝነት ሲያልቃቸው ወደ እስልምና መጀመሪያ የጋበዙት አቡበክርን ነበር። እርሳቸውም ሳያመነቱ እስልምናን ተቀበሉ። የአላህ መልእክተኛ ይህን በማስመልከት ሲናገሩ፦

‹‹የትኛውም ሰው ወደ እስልምና ስጋብዘው ይከብደዋል። ለመቀበልም ያመነታል። አቡበክር ሲቀር። እርሱ ግን ወዲያውኑ እንደጠራሁት ሳያመነታ ተቀበለኝ።››[1]

[1] ሲረት ቢን ሂሻም

በተለያዩ የዳእዋው እርከኖች ውስጥ ከአላህ መልእክተኛ ሳይነጠሉ፣ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ እያደረጉላቸው፣ ለአምላክና ለነብዩ ጥሩና አማኝ፣ ለሐይማኖታቸው ቀናኒ ሆነው ኖረዋል። በዚህ ሂደትም የነቢዩ የስደት ጉዞ ተጋሪ፣ የዋሻ ውስጥ ባልደረባ እንዲሆኑ ያስቻሏቸውን በርካታ መከራዎች አስተናግደዋል። ገንዘባቸውን ሁሉ ለእስልምና ዳእዋ ሳይሰስቱ ችረዋል። ከአላህ መልእክተኛም ‹‹የአቡበክር ገንዘብ የጠቀመኝን ያህል በማንም ገንዘብ አልጠቀመኝም።›› የሚል ምስክርነትአግኝተዋል።[1]

የዚህ ሁኔታ የአላህን መልእክተኛ እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ደግፈው ለቀልባቸውም ይበልጥ ቅርብና ለኽሊፋነትም ይበልጥ ብቁ ሶሐባ ለመሆን ታደሉ። በዚህ ረገድ ታላቁ ነቢይ የሰጡት ምስክርነት ከበቂ በላይ ነው። እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በባልደረባነትና በገንዘብ ከማንም በላይ የደገፈኝ አቡበክር ነው። ከአምላኬ ውጭ የመጨረሻውን ፍጹማዊ ፍቅር የምለግሰው ሰው ቢኖር ኖሮ ያ ሰው አቡበክር ይሆን ነበር። ቢሆንም የእስልምና ወንድማማችነት እና ፍቅር አስተሳስሮናል።›› (ቡኻሪ፣ሙስሊምና ቲርሚዚ)

ልቅናቸውን የሚገልጹ ምስክርነቶች

የአቡበክርን ልቅና ከሚያሳዩ ዘገባዎች መካከል አቡ ሰኢድ ያስተላለፉት ይገኝበታል። እንዲህ ብለዋል፡-

ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ፡- ‹‹አላህ አንድን ባሪያውን ከዚህች ዓለም ሕይወትና ከርሱ ዘንድ ካለው ጸጋ ሲያስመርጠው ከአላህ ዘንድ ያለውን መረጠ።›› በማለት ሲናገሩ አቡበክር አለቀሱ። ለቅሷቸው አስገረመን። ለካስ ምርጫ የተሰጣቸው መልእክተኛው ኖረዋል። አቡበክርም ከማንኛችንም ቀድመው ይህን ተረድተዋል። መልእክተኛውም እንዲህ ብለዋል፡-

[1] አህመድ፣ አቡ ሐቲምና ቢን ማጃህ

‹‹በባልደረባነትና በገንዘብ ከማንም በላይ የደገፈኝ አቡበክር ነው። ከአምላኬ ውጭ የመጨረሻውን ፍጹማዊ ፍቅር የምለግሰው ሰው ቢኖር ኖሮ ያ ሰው አቡበክር ይሆን ነበር። ቢሆንም የእስልምና ወንድማማችነት እና ፍቅር አስተሳስሮናል።›› (ቡኻሪ፣ሙስሊምና ቲርሚዚ)

‹‹‹‹በባልደረባነትና በገንዘብ ከማንም በላይ የደገፈኝ አቡበክር ነው። ከአምላኬ ውጭ የመጨረሻውን ፍጹማዊ ፍቅር የምለግሰው ሰው ቢኖር ኖሮ ያ ሰው አቡበክር ይሆን ነበር። ቢሆንም የእስልምና ወንድማማችነት እና ፍቅር አስተሳስሮናል፡የአቡበክር በር ሲቀር ሁሉም በሮች ይዘጋሉ። ›› (ቡኻሪ፣ ሙስሊምና ቲርሚዚ)

በሌላ ዘገባ እንደተወሳው እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከአምላኬ ውጭ ፍጹማዊ ፍቅር የምለግሰው ሰው ቢኖር ኖሮ ያ ሰው አቡበክር ይሆን ነበር። ይህም ሆኖ ወንድሜና ባልደረባዬ ነው። አላህ ባልደረባችሁን ፍጹማዊ ወዳጁ (ኸሊል) አድርጎታል።›› (ቡኻሪ፣ ሙስሊምና ቲርሚዚ)

በአላህና በመልእክተኛው ማመን

አቡበክር የመጀመሪያው ሙስሊም እንዲሆኑና የአላህ መልእክተኛ የሚናገሩትን ሁሉ ቅንጣት ሳይጠራጠሩና ሳያመነቱ እንዲቀበሉ የረዳቸው ይህ እምነታቸው ነው። በኢስራእ እና ሚእራጅ ሐዲስ ውስጥ ያሳዩትን እጅግ አንጸባራቂ አቋም አስተውል። የአላህ መልእክተኛ ለባልደረቦቻቸውና ለቁረይሾች በዚያች ሌሊት ያጋጠማቸውን ኩነት ባጫወቷቸው ጊዜ እምነቱ ደካሞች ከእስልምና እስከ መውጣት ደረሱ። ቁረይሾችም በአላህ መልእክተኛ ተሳለቁ። አቡበክር ስለዚህ እንግዳ ክስተት የሚኖራቸውን አቋም ለማወቅም አቡ ጀህል ወደርሳቸው ሄደ። ነቢዩ የተናገሩትንም አጫወታቸው። እርሳቸውም በፍጹም መተማመንና በእርጋታ፡- ‹‹በእርግጥ ይህን ተናግረዋልን?›› በማለት ጠየቁ። አቡ ጀህልም ‹አዎ› ሲል መለሰ። እርሳቸውም፡- ‹‹ሙሐመድ ይህን ከተናገረ እውነቱን ነው።›› አሉ። አቡ ጀህልና አብረውት የነበሩት ባልደረቦቹም፡-

‹‹በአንድ ቀን ሌሊት ወደ በይተል መቅዲስ ሄጀ ሳይነጋ በፊት ተመለስኩ ማለቱን አምነህ ትቀበላለህን?›› አሏቸው፡፡ አቡበክር የሚከተለውን አስገራሚ መልስ ሰጡ፡-

‹‹ከዚህ ይበልጥ እንግዳ የሆነ ነገር ተናግሮ አምኜዋለሁ፡፡ ጧር ማታ ከሰማይ መልእክት እንደሚወርድለት ነግሮኝ ተቀብየዋለሁ፡፡›› አሉ፡፡ ወደ ነቢዩ (ሶ.ወ.ወ) በመሄድም የኢስራእን ታሪክ ሰሙ፡፡ ‹፣አንተ የአላህ መልክተኛ መሆንህን እምሰክራለሁ፡፡›› በማለትም የሰሙትን ሳያመነቱ መቀበላቸውን አረጋገጡ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

የመጨረሻውን የምጥቀት ጫፍ የደረሰ ኢማን፣ የዚህ እምነት ባለቤት የኢስላም ታላላቅ ሰዎች ፈርጥ ቢሆኑ ምኑ ያስገርማል!

መስዋእትነት

አቡበክር ነፍሳቸዉንና ገንዘባቸውን ለእስልምና ዳእዋ መሰዋታቸው የጽኑ እምነታቸው አይቀሬ ውጤት ነው፡፡ ኢማን ወደ ቀልብ ሲገባ ለመስዋእትነት ያነሳሳል፡፡ እንደ አቡበክር አይነት እጅግ ጽኑና ጥልቅ እምነት ከሆነስ?!

አቡበክር ራሳቸውን ለመስዋእትነት አቅርበው የአላህን መልእክተኛ የታደጉባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ አንድ ቀን ቁረይሾች ከካእባ መስክ ላይ የአላህን መልእክተኛ ለማነቅ ሙከራ ሲያደርጉ አቡበክር ተከላከሉላቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩን ትተው ከርሳቸው ላይ በመረባረባቸው ራሳቸውን ስተው እስኪወድቁ ድረስ ደበደቧቸው፡፡ አፍንጫቸውን ከአይናቸው ወይም ከጉንጫቸው መለየት እስኪያዳግት ድረስ ክፉኛ ቆሰሉ፡፡ ሰዎች አፋፍሰው ወደቤታቸው ወሰዷቸው፡፡ ራሳቸውን ሲያውቁ መጀመሪያ ያቀረቡት ጥያቄ፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ በምን ሁኔታ ውስጥ ናቸው?›› የሚል ነበር፡፡[1]

[1] ሲረቱ ነበዊያህ ዘይኒ ደህላን፡፡

ከመልእክተኛው ጋር ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜም ተመሳሳይ መስዋእትነት ከፍለዋል። ቁረይሾች አግኝተው ሊገድሏቸው ብርቱ ጥረት አድርገዋል። በዚህ ጊዜ የአቡበክር አቋም እጅግ አስገራሚ ነበር። ቁረይሾች ከዋሻው በር ላይ ቆመው በነበረ ጊዜ የተናገሩትን ድንቅ ቃል እንመልከት፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ አንደኛቸው ወደ እግሩ ስር ቢያይ ይመለከተናል።› መልእክተኛው ግን ባልደረባቸውን እንዴት እንደሚያጸኑ ያውቁ ነበር። እንዲህ አሉ፡-

‹‹አቡበክር ሆይ፣ አላህ አብሯቸው ባለ ሁለት ሰዎች ስጋት አይግባህ።››

አቡበክር ገንዘባቸውን ሁሉ ለእስልምና ዳእዋ መስዋእት አደረጉ። አኢሻ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አቡበክር 40 ሺህ (የወርቅ ፍራንክ) ለዳእዋ መጸወቱ። የአላህ መልእክተኛ ለአስቸጋሪው የተቡክ ዘመቻ ጦርነት ትጥቅና ስንቅ እንዲዘጋጅ ባልደረቦቻቸውን በጠየቁ ጊዜ ሶሐቦች ገንዘቦቻቸውን እየያዙ መጡ። ኡስማን ብዙ ገንዘብ አመጣ። ዑመር ግማሽ ሐብታቸውን መጸወቱ። አቡበክር ደግሞ ሙሉ ገንዘባቸውን ሰጡ። የአላህ መልእክተኛም፡- ‹‹አቡበክር ሆይ፣ ለቤተሰቦችህ ምን አስቀረህ?›› ሲሏቸው። ‹‹አላህንና መልእክተኛውን›› ሲሉ መለሱ። (ቲርሚዚ)

ብልህነትና ቆራጥነት

በጃሂልያ ዘመን ወገኖቻቸው ጣኦት ለማምለክ ሲጋፉ እርሳቸው አንድም ጊዜ እንኳ ለጣኦታት ለመስገድ ካለመፍቀዳቸው፣ ወገኖቻቸው በአስካሪ መጠጥ ሲነከሩ እርሳቸው ግን ኢምንት እንኳ ካለመጎንጨታቸው የበለጠ ብልህና አስተዋይ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነገር የለም። ጣኦት አምልኮ ቂልነት እና ጥመት፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣትም ውድቀትና ውርደት መሆኑን በብሩህ አእምሯቸው ተረድተዋል።

ምን ያህል ጀግናና ቆራጥ እንደሆኑ ለማሳየት የአላህ መልእክተኛ በሞቱና ከፊል ዓረቦች በኢስላማዊው ስርዓት ላይ ባመጹ ጊዜ ያሳዩአቸው አስደናቂ የጀግንነት አቋሞች በቂ ናቸው።

ነቢዩ በሞቱ ጊዜ ሶሐቦች እጅግ ከማዘናቸው የተነሳ ከፊሎቹ አንደበታቸው ተሳሰረ። ሌሎችም ከተቀመጡበት መነሳት ተሳናቸው። ዑመርም ‹‹ነብዩ አልሞቱም።ይመለሳሉ።›› እስከማለት ደረሱ። አቡበክር ግን እንደሚሞቱት መልእክተኛውም ሌሎች ሰዎች መሞታቸውን አወጁ፡ ፡ የዑመርን ንግግር ሐየሱ። ሶሐቦችን አረጋጉ። የሚከተለውን የአላህ ቃልም አስታወሱ፡-

﴿ وَمَا مُحَمَّدٌ إِلَّا رَسُولٌ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِ ٱلرُّسُلُۚ ﴾ آل عمران: ١٤٤

‹‹ሙሐመድ ከበፊቱ (በርካታ) መልዕክተኞች ያለፉ የሆነ መልዕክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም።›› (አሊ ዒምራን 144)

የአመጽ (ሪዳህ) ክስተቱን የተቆጣጠሩበት ሁኔታም በወሳኝና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ የሚላበሱትን ፍጹም ጀግንነት ያሳያል። ያኔ አላህ የአቡበክርን ቀልብ በሐቅ ላይ ባያጸና እና የጽኑ ነብያትን ቆራጥነት ባያላብሳቸው ኖሮ ተከስቶ የነበረው ፈተና ገና ለጋ የነበረውን የእስልምና ሕንጻና መንግስቱን ባወደመው ነበር። ይህም ስለሆነ ነው አቡበክር ከአላህ መልእክተኛ በኋላ ሁለተኛው የእስልምና መንግስት መስራች ተብለው የሚወደሱት።

ትህትናና ቁጥብነት

እንደ አቡበክር ያለ ታላቅ ስብእና ስልጣን አያታልለውም። ከኢስላማዊው አደብና ስነምግባር አያወጣውም። እናም በኸሊፋነት ዘመናቸው ልክ እንደ ቀድሞው ለስላሳና አዛኝ፣ ለሕዝባቸው ጉዳይም ቀናኢ ሆነው ቀጠሉ። ተከታዩ ታሪክ አቡበክር በኸሊፋነት ዘመን የነበራቸውን ትህትና ለማሳየት ጥሩ ምስክር ነው፡-

አቡበክር ለአላውንትና ረዳት አልባ እንስቶች ዘወትር ጠዋት ፍየል ያልቡ ነበር። ኸሊፋ በሆኑ ጊዜ አንዲት የመንደራቸው እንስት፡- ‹‹ከእንግዲህ አቡበክር ፍየሎቻችንን አያልብልንም›› አለች። አቡበክር ይህን ማለቷን ሲሰሙ፡- ‹‹በአላህ እምላለሁ፣ እንደወትሮው ሁሉ ማለቤን እቀጥላለሁ። የኖርኩበትን መልካም ባህሪ አላህ እንደማይቀይርብኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ›› አሉ።

የዓለማችን ታላላቆች ለክብራቸው እንዲያጎበድዱ የሚያደርግ አንጸባራቂ አቋም ነው። ከስጋዊ ስሜቶችና ዝንባሌዎች በላይ በመምጠቅ የኡምማውን መብትና አስፈልጎት የማስታወስ፣ ክብሩንና ገንዘቡን የሚጠብቅለት ታላቅነት ነው።

የአቡበክር ዙህድ

የአቡበክርን ዙህድ[1] ከሚያሳዩ ክስተቶች መሐል ኢማም አህመድ፣ አኢሻን ጠቅሰው የዘገቡት ታሪክ ይገኝበታል። እንዲህ ብላለች፡-

‹‹አቡበክር ሲሞቱ አንዲት ዲናር ወይም ዲርሃም አልተውም። ከመሞታቸው በፊት ገንዘባቸውን በሙሉ ወደ በይተል ማል (የሙስሊሞች የገንዘብ ግምጃ ቤት) አስገብተውት ኖሯል።››

ዑርወት እንዳስተላለፉት አቡበክር ኸሊፋ በተደረጉ ጊዜ ያላቸውን እያንዳንዷን ዲርሃምና ዲናራቸውን ወደ ሙስሊሞች በይተል ማል አስገቡ። ‹‹በዚህ ገንዘብ እነግድ ነበር። አሁን ግን ኸሊፋቸው ሲያደርጉኝ መነገድ አልቻልኩም።››አሉም።

አሚእ ቢን ሳኢብን በመጥቀስ ቢን ሰእድ እንደዘገቡት አቡበክር ኸሊፋ በተደረጉ ማግስት ጠዋቱኑ በርካታ ኩታ በትከሻቸው ተሸክመው ሲሄዱ ዑመር ተመለከቷቸው። ‹‹የት እየሄድክ ነው?›› ሲሉም ጠየቋቸው። ‹‹ወደ ገበያ›› በማለት መለሱ። ‹‹የሙስሊሞች ሐላፊ ተደርገህ እያለ ሐላፊነትህን ትተህ ገበያ ውስጥ ምን ትሰራለህ?› ሲሉም ጠየቋቸው።

[1] ዙህድ ማለት ለዓለማዊ ጸጋና ድሎት አለመጓጓት ነው።

‹‹ቤተሰቦቼን ምን ላበላ ነው?›› አሉ አቡበክር፡፡ ‹‹አቡ ዑደይዳህ ቀለብ ይወስንልሐል፡፡›› አሏቸው፡፡ ተያይዘው ወደ አቡዑበይዳህ ዘንድ ሄዱ፡፡ እርሳቸውም፡- ‹‹አንድ ሙሐጅር የሚበቃውን ቀለብ፣ ሳይበዛም ሳያንስም፣ እቆርጥልሐለሁ፡፡ ለክረምትና ለበጋ የሚሆን ልብስም እገዛልሃለሁ፡፡ እርሱ ሲነትብ ትመልሰውና በልዋጩ ሌላ ትወስዳለህ፡፡›› አሉ፡፡ በየቀኑ ግማሽ ፍየል ወሰኑላቸው፡፡ ገላቸውን የሚሸፍኑበት እራፊ ጨርቅም ሰጧቸው፡፡

በበጎ ነገሮች ሁሉ ቀዳሚ

አቡ ሁረይራ እንዳስትላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ከናንተ ውስጥ ጾም ይዞ ያነጋ ማን ነው?›› በማለት ጠየቁ፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹እኔ›› አሉ፡፡ ‹‹ከናንተ ውስጥ ጀናዛን የሸኘ ማን ነው?›› ሲሉም ጠየቁ፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹እኔ››አሉ፡፡ ‹‹ዛሬ ምስኪንን ያበላ ማን ነው?›› አሉም፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹እኔ››አሉ፡፡ ‹‹በሽተኛ የጠየቀስ ማን ነው?›› ሲሉ፣ አቡበክር ‹‹እኔ›› አሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛም፡- ‹‹እነዚህ በጎ ድርጊቶች ከአንድ ሰው ላይ አይሰባሰቡም፣ ያ ሰው ጀነት የገባ ቢሆን እንጅ፡፡፡›› አሉ፡፡(ሙስሊም)

‹‹ጅብሪል መጣና እጁን ይዞ ተከታዮቼ የሚገቡበትን የጀነት በር አሳየኝ፡፡›› አሉ፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹ከርስዎ ጋር ሆኘ ባየው እወድ ነበር፡፡›› አሏቸው፡ ነቢዩም፡- ‹‹አቡበክር ሆይ፣ ከኡመቴ ውስጥ መጀመሪያ ጀነት የምትገባው አንተ ነህ፡፡›› አሏቸው፡፡ (አቡ ዳውድ)

የአላህ ፍራቻ እና ጥንቃቄ

አቡበክር አንድ ባሪያ ነበራቸው፡፡ ዘወትር ጠዋት እየወጣ ስራ በመስራት ገንዘብ ያገኛል፡፡ አንድ ቀን ምግብ ይዞ መጣ፡፡ አቡበክርም አንድ ጉራሽ ተመገቡለት፡፡ ባሪያውም በመሐይምነት ዘመን ለፈጸመው የጥንቆላ ተግባር ከተሰጠው ክፍያ ያገኘው ምግብ እንደሆነ ነገራቸው፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹ልታጠፋኝ ተቃርበህ ነበር፡፡›› አሉና ጣታቸውን ወደ ጉሮሯቸው በመላክ እንዲያስመልሳቸው ሞከሩ፡፡ አልወጣ ብሎ አስቸገራቸው፡፡ ‹‹በውሃ እንጅ አይወጣም›› ሲሏቸው በሳህን ውሃ

እንዲቀርብላቸው አደረጉና እርሱን እየጠጡ የበሉትን ሁሉ አስመለሱ። ‹‹አላህ ይዘንልዎት። ለአንዲት ጉርሻ ይህን ያህል ራስዎን ያንገላታሉን?›› ተባሉ።‹‹ነፍሴ ከአካሌ ካልተነጠለች ይህች ጉርሻ የማትወጣ ቢሆንም እንኳ ነፍሴን ከማውጣት ወደኋላ አልልም። የአላህ መልእክተኛ፡- በሐራም ምግብ የበቀለ ስጋ እሳት ለርሱ ይበልጥ የተገባ፣ ነው ሲሉ በመስማቴ በዚህ ጉርሻ አማካይነት ከአካሌ አንዳች ነገር እንዳይበቅል ስለፈራሁ ነው።›› አሉ።[1]

የአምላካቸውን ከለላነት መምረጣው

ቡኻሪ እንደዘገቡት አኢሻ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

‹ወላጆቼ ሙስሊም ሆነው እንጅ አላውቃቸውም። የአላህ መልእክተኛ ጠዋትና ማታ ከኛ ዘንድ የሚመጡ ሆነው እንጅ አንድምቀንአላለፈም።››

መስሊሞች መካ ውስጥ እንግልት ሲበዛባቸው አቡበክር ወደ ሐበሻ ለመሰደድ መካን ጥለው ወጡ። ‹‹በርከል ገማድ›› ከተባለ ቦታ ሲደርሱ ኢብን ዱግኒያህ አገኛቸው። የጎሣ አለቃ ነው። ‹‹የት እየሄድክ ነው?›› ሲልም ጠየቃቸው። ‹‹ወገኖቼ ከአገር አስወጡኝ›› አገር ላገር እየተዘዋወርኩ አምላኬን ማምለክ እፈልጋለሁ።›› ሲሉ መለሱ። ኢብን ዱግኒያህም፡- ‹‹አቡበክር ሆይ፣ አንተን የመሰለ ሰው አገር ጥሎ አይወጣም። እንዲወጣም አይደረግም። አንተ ችግረኛን የምትረዳ፣ ዝምድናን የምትቀጥል፣ ችግርን የምትጋራ፣ እንግዳ የምታስተናግድ፣ ከባለ መብት ጎን የምትቆም ሰው ነህ። ስለዚህ እኔ ከለላ እሆንሐለሁ። ተመለስና እዚያው ከአገርህ ውስጥ ጌታህን አምልክ›› አላቸው። ወደ መካ ተመለሱ። ቢን ዱግኒያህም አብሯቸው ሄደ። ማታ ላይ የቁረይሽ ባላባቶችን በየቤታቸው እየዞረ፡- ‹‹አቡበክር ከአገር የሚወጣ ወይም እንዲወጣ የሚደረግ ሰው አይደለም። ችግረኛን የሚታደግን፣ ዝምድናን የሚቀጥልን፣ ችግርን የሚጋራን፣ እንግዳ የሚንከባከብንና ከተበዳይ ጎን

[1] በይሐቂ እንደዘገቡት (አል ሁልያህ 2/31)

የሚቆምን ሰው ከአገር ታስወጣላችሁን?›› ሲል ወቀሳቸው፡፡ ቁረይሾች ለአቡበክር ከለላ መሆኑን ተቀበሉ፡፡ ግና እንዲህ ሲሉ አስጠነቀቁት፡-

‹‹ለአቡበክር አምላክን ቤቱ ውስጥ ብቻ እንዲያመልክና እንዲሰግድ ንገረው፡፡ በቤቱ ውስጥ ያሻውን ነገር ያንብብ፡፡ እኛን ግን እያወከን፣ እነዚህን ነገሮች በይፋ ከፈጸመ ሴቶቻችንና ልጆቻችን እንዳይፈተኑ እንሰጋለን፡፡››

ኢብን ዱግኒያህ ለአቡበክር ይህንኑ ነገራቸው፡፡

አቡበክር ጌታቸውን ከቤታቸው ውስጥ ማምለካቸውን ቀጠሉ፡፡ ሶላት በይፋ አይሰግዱም። ቁርአንም ከቤታቸው ውጭ አይቀሩም፡፡ በኋላ ግን ከካእባ ግቢ ውስጥ የመስገድ ሐሳብ መጣላቸው፡፡ ይህንኑ አደረጉ፡፡ ከርሱ ውስጥም መስገድና ቁርአን መቅራት ጀመሩ፡፡ የጣኦታውያን እንስቶችና ሕጻናትም በአግራሞት ይመለከቷቸው ጀመር፡፡ አቡበክር አልቃሽ ሰው ነበሩ፡፡ ቁርአን ሲቀሩ በለቅሶ ይንፈቀፈቃሉ፡፡

ይህ ድርጊታቸው የቁረይሽ ባላባቶችን አስደነገጠ፡፡ ለቢን ዱግኒያህም እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ፡-

‹‹አቡበክር አምላኩን ከቤቱ ውጭ ላያመልክ ቃል አስገብተን ከለላ ትሆን ዘንድ ፈቅደን ነበር፡፡ እርሱ ግን ቃሉን ጥሶ በካእባ ግቢ ውስጥ መስገድ እና መቅራት ጀምሯል፡፡ ሴቶቻችንና ልጆቻችን እንዲፈተኑ ስለማንሻ ከልክለው፡፡ ከቤቱ ውስጥ ብቻ ማምለክ ከፈለገ ይችላል፡፡ አምልኮውን ይፋ ማድረግ የሚፈልግ ከሆነ ግን ከለላነትህን መልስለት። የሰጠንህን ቃል ማፍረስ አንሻም፡፡ በይፋ እንዲያመልክም አንፈቅድለትም፡፡››

አኢሻ እንዳስተላለፉት ቢን ዱግኒያህ ከአቡበክር ዘንድ መጣና፡- ‹‹እኔና አንተ የተጋባነውን ቃል ታውቃለህ፡፡ ስለዚህም በቃልህ መሠረት ከቤትህ ውስጥ ብቻ አምልክ። ካልሆነ ከለላነቴን መልስልኝ፡፡ ከለላዬ እንዲጣስና ዓረቦችም ይህን ጉድ እንዲሰሙ አልሻም፡፡›› አለ፡፡ አቡበክርም፡- ‹‹ከለላነትህን መልሸልሐለሁ፡፡ ከእንግዲህ የአላህን ከለላነት ብቻ እሻለሁ፡፡ ›› አሉ፡፡

ከአቡበክር ሌላ ይህን የጀግንነት አድራጎት ማን ሊፈጽም ይችላል። በዚህ ድንቅ አቋም ሊዋብ የሚችለው የአቡበክር ስብእና ብቻ ነው። በአላህ ላይ የነበራቸው እምነት ይህን ያህል ጽኑና ጠንካራ ነበር። የክህደት ሐይሎች ዙሪያውን ከበው ሊያጠፏቸው ባሰፈሰፉበት ወቅት አላህ ከየትኛውም ፍጡር የላቀ፣ ከሰላው የሚከጀል፣ ተስፋ የሚጣልበት ብቸኛ ሐይል መሆኑን፣ አላህ የረዳውን የሚያሸንፈው እንደሌለ በጥልቅ ተረዱ።

በኸሊፋነት ዘመን

አቡበክር ኸሊፋ የሆኑት ሙስሊሞች በነብያቸው ሞት ምክንያት ግራ በተጋቡበት አስፈሪ ወቅት ነው። በወቅቱ ከፊል አረቦች ከእስልምና አፈንግጠዋል። ሌሎች ከመልእክተኛው በኋላ ለማንም ላለማደር ወስነዋል። ሮሞች ሂጃዝን ለመውረር በዝግጅት ላይ ናቸው። የሮሞችን ጥቃት ለመመለስ የአላህ መልእክተኛ ያዘጋጁት የኡሳማ ጦር ጉዞውን ለመቀጠል ከመዲና አፋፍ ላይ ሆኖ ትእዛዝ ይጠባበቃል። በዚህ ሁሉ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ኸልፋ የተደረጉት አቡበክር ሐላፊነታቸውን በሚገባ ተወጡ።

አፈንጋጮችን አደብ ለማስያዝ ቆራጥ ውሳኔ ወሰኑ። ሌሎች ሶሐቦች የጦርነቱን ሐሳብ ባይደግፉም እርሳቸው ግን በዚሁ ሐሳባቸው ጸኑ። በኋላ ላይ ግን ሶሐቦች የርሳቸውን ሐሳብ ደገፉ። በአላህ በረከትም እስልምናን በአረቢያ ውስጥ እንደ አዲስ ለማጽናት ተመሙ። አላህ የለገሳቸው ድል ታላቅ ነበር። የአመጽ እንቅስቃሴውን በእንጭጩ ቀጨት።

የኡሳማንም ጦር የአላህ መልእክተኛ ወዳሰማሩት ግንባር አዘመቱ። ይህ ጦር እስልምናን ለማስፋፋትና ሕዝቦችን ነጻ ለማውጣት የተገኙ ድሎች ሁሉ መነሻ ሆነ። የአስተዳደር ፖሊሲያቸው ኸሊፋ በተደረጉ ጊዜ ያሰሙት ተከታዩ ንግግር ነበር፦

‹‹እኔ በናንተ ላይ ተሹሚያለሁ። ይህ ማለት ግን ከናንተ ብልጫ አለኝ ማለት አይደለም። በጎ ከሰራሁ አግዙኝ። ክፉ ከሰራሁ አስተካክሉኝ።

እውነት መናገር አደራን መጠበቅ ሲሆን፣ መዋሸት ደግሞ ክህደት ነው። ከናንተ መካከል ደካማው መብቱን እስካሟላለት ድረስ ከኔ ዘንድ ጠንካራ ነው። ከናንተ ዘንድ ጠንካራው ግዴታውን እንዲወጣ እስካደርገው ድረስ ከኔ ዘንድ ደካማ ነው። ሰዎች በአላህ መንገድ መፋለምን ሲተው አላህ ውርደትን ያከናንባቸዋል። በአንድ ሕዝብ ውስጥ ዝሙት ከተስፋፋ አላህ ሁሉንም በቅጣቱ ያጠቃልላቸዋል። አላህንና መልእክተኛውን እስከታዘዝኩ ድረስ ታዘዙኝ። የአላህን እና የመልእክተኛውን ፈቃድ ስጥስ ግን ልትታዘዙኝ አይገባም።››[1]

አቡበክር የአስተዋይ ልቦና፣ የሩቅ አሳቢ አእምሮ ባለቤት ነበሩ። በዘመናቸው ያሉ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ ከማየት፣ በጥልቀት ከማስተዋል የመነጨ ንግግራቸው የልብ ብርታትን፣ ፍጹም መተማመንና ጽኑነትን የተላበሰ ነው።

የኸሊፋነት ዘመናቸው ጥቂት ቢሆኑም እጅግ አስደናቂና ታላላቅ በሆኑ ስኬቶች የተሞሉ ናቸው። የአቡበክር ብልህነት በበርካታ አጋጣሚዎች ተስተውሏል። በተለይም እጅግ ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች። ታላቅ ሰው ታላላቅ አቋሞችን ያስመዘግባል።

ቁርአንን የመሰብሰብ ድንቅ ተግባር

በየማማ ጦርነት ወቅት በርካታ የቁርአን አዋቂዎች የመገደላቸውን ዜና አቡበክር በሰሙ ጊዜ ዑመር አብረዋቸው ነበሩ። በዚህ ጦርነት በርካታ የቁርአን አዋቂዎች ተገድለዋል። ‹‹በሌሎች ጦርነቶችም ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሮ አዋቂዎቻችን እንዳያልቁ እሰጋለሁ። ስለዚህም በነቢዩ ዘመን የተጻፉ የቁርአን ጽሑፎች እንዲሰበሰቡ ብታደርግ መልካም ይመስለኛል።›› አሉ።

አቡበክርም፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ያላደረጉትን ነገር እንዴት እኔ አደርገዋለሁ?›› ሲሉ ጠየቁ። ዑመርም፡- ‹‹በአላህ እምላለሁ ይህን

[1] አልሙሂብ ጦበሪ እንዳሉት ይህ ሐዲስ በቡኻሪ ውስጥ ሙንቀጢእ በሆነ ሰነድ ተዘግቧል።

ብታደርግ መልካም ነው።›› አሉ። ዑመር አቡበክርን ደጋግመው ጎተጎቱ። በመጨረሻም አቡበክር በሐሳቡ ተስማሙ። ዘይድ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ አቡበክር እንዲህ አሉኝ፦

‹‹አንተ አስተዋይ ወጣት ነህ። በመጥፎ ነገር አንጠረጥርህም። ለአላህ መልእክተኛ ቁርአን ሲወርድላቸው እየተከታተልክ ትጽፍ ነበር። ስለዚህም የተጻፉ የቁርአን መልእክቶችን በአንድ አሰባስብ›› አሉኝ። በአላህ እምላለሁ፣ ይህን ሐላፊነት ከሚያሸክሙኝ ተራራ እንድገፋ ቢየዙኝ እመርጥ ነበር።

‹‹የአላህ መልእክተኛ ያላደረጉትን እንዴት እናንተ ታደርጋላችሁ?›› አልኳቸው። አቡበክርም ‹‹በአላህ እምላለሁ፣ በጎ ነገር ይመስለኛል።›› አሉኝ። ደጋግመውም ጎተጎቱኝ። በመጨረሻ በሐሳባቸው ተስማማሁ።

በተለያዩ ቁሳቁሶች ላይ ተጽፎ የነበረውን ቁርአን ከያለበት ተከታትዬ ሰበሰብኩት። የአልተውባህን የመጨረሻ አናቅጽም ከኹዘይማህ ቢን ሳቢት ዘንድ አገኘሁት።

﴿ لَقَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ عَزِيزٌ عَلَيۡهِ مَا عَنِتُّمۡ حَرِيصٌ عَلَيۡكُم بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ ١٢٨ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَقُلۡ حَسۡبِيَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُۖ وَهُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡعَظِيمِ ١٢٩ ﴾ التوبة: ١٢٨ - ١٢٩

‹‹ከናንተ ውስጥ የሆነ፣ ችግራችሁ የሚያሳስበውና (ለስኬታችሁ) ጉጉ የሆነ፣ (ለአማኞችም) እጅግ ርኅሩኅና አዛኝ መልዕክተኛ መጣላችሁ። ፊታቸውን (ከዚህ መልዕክት) ካዞሩ፦ “አላህ በቂዬ ነው። ከርሱ ሌላ አምላክ የለም። በርሱ ብቻ ተመካሁ። እሱ የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው።” በላቸው። (አል ተውባህ 128-129)[1]

[1] ይህ ሐዲስ ሐሰኑን ሶሂህ ደረጃ ያለው ነው።

ዘመን ተሻጋሪ መልእክቶቻቸው

1) ሰዎች ሆይ፣ በአላህ እምላለሁ፣ ጠላቶቻችሁ ቢበዙ፣ ወዳጆቻችሁ ቢያንሱና ሰይጣን በሙሉ ሐይሉ ቢዘምትባችሁም እንኳ አላህ ይህን ሐይማኖት የሐይማኖቶች ሁሉ የበላይ ያደርገዋል። ጣኦታውያን ይህን ቢጠሉም። ንግግሩ እውነት፣ ቃል ኪዳኑም የማይታበል ነው።

﴿ بَلۡ نَقۡذِفُ بِٱلۡحَقِّ عَلَى ٱلۡبَٰطِلِ فَيَدۡمَغُهُۥ فَإِذَا هُوَ زَاهِقٞۚ وَلَكُمُ ٱلۡوَيۡلُ مِمَّا تَصِفُونَ ١٨ ﴾

‹‹እውነትን ሐሰት ላይ በእርግጥ እንጥላለን። ያፈራርሰዋልም። (ሐሰት) በባሕሪው ጠፊ ነውና። እናንተ ግን -(በኛ ላይ) ለምትለጥፉት (ቅጥፈት)- ወዮላችሁ።›› (አል አንቢያእ 18)

2) ሰዎች ሆይ፣ የተላቀውን አላህን በሁሉም ጉዳዮችና ሁኔታዎች እንድትፈሩት፣ በምትወዱትም በምትጠሉትም ሁኔታ ሐቅን አጥብቃችሁ እንድትይዙ እመክራችኋለሁ። ከእውነት የበለጠ በጎ ወሬ የለም። የዋሸ ወነጀለ። የወነጀለ ጠፋ። ኩራትን አደራ ተጠንቀቁ። ከአፈር ተፈጠሮ ወደ አፈር የሚመለስ ሊኮራ አይገባውም።

3) አዋጅ፣ እያንዳንዱ ጉዳይ መቋጠሪያ ውል አለው። እርሱን ያገኘ በቂው ነው። ለአላህ የሰራ አላህ ይበቃዋል። ብርቱና ቆጣቢዎች ሁኑ። ቁጠባ እጅግ ጠቃሚ ባህሪ ነው። እነሆ፣ ራሱን የማይቆጣጠር ሰው ዲንም ኢማንም የለውም። ኒያ የሌለው ስራ የለውም። አዋጅ፣ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ የጅሃድን ምንዳ የሚከር መልእክት አለ። ሙስሊም በዚህ እድል ብቸኛ ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል። ጅሃድ አላህ ያመላከተው ንግድ ነው። በርሱ አማካይነት ሰዎችን ከኪሣራ ይታደጋል። በዚህችም በመጭውም ዓለም ክብር ያጎናጽፋቸዋል።››

የኸሊፋው ኹጥባ

አላህን እንድትፈሩ፣ ተገቢውን ውዳሴ እንድታደርሱለት፣ ፍርሃትን ከጉጉት እድታጣምሩ፣ አጥብቃችሁና አዘውትራችሁ እንድትለምኑት

እመክራችኋለሁ። አላህ ዘከሪያንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲህ ሲል አወድሷል፦

﴿إِنَّهُمۡ كَانُواْ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلۡخَيۡرَٰتِ وَيَدۡعُونَنَا رَغَبٗا وَرَهَبٗاۖ وَكَانُواْ لَنَا خَٰشِعِينَ ٩٠﴾ الأنبياء: ٩٠

‹‹እነርሱ (ነቢያት) ለመልካም ሥራ ይሮጡ ነበር። በጉጉትና በፍርሃትም ይጠሩን ነበር። ፍፁም ታዛዦቻችንም ነበሩ።›› (አል አንቢያእ 90)

የአላህ ባሮች ሆይ፣ አላህ ነፍሳችሁን መዋሱን እወቁ። ከናንተ ቃል ኪዳን ተቀብሏል። ጠፊና ጥቂት የሆነውን ዘልዓለማዊና ብዙ በሆነው ገዝቷችኋል። እነሆ፣ የአላህ መጽሐፍ ማስደመሙ አያልቅም። ብርሃኑም አይከስምም። ስለዚህም መልእክቱን አምናችሁ ተቀበሉ። በምክሩም ተጠቀሙ። ለጽልመታማው ቀን ብርሃን አድርጉት። አላህ የፈጠራችሁ ለአምልኮ ነው። ስራችሁን ይመዘግቡ ዘንድም የተላቁ የመላእክት ጸሐፊዎችን በናንተ ላይ ወክሏል። የምትሰሩትን ሁሉ ያውቃሉ። የአላህ ባሮች ሆይ፣ ለናንተ የተሰወረው የምትሞቱበት ቅጽበት ካጠገባችሁ ሆኖ ታነጋላችሁ፣ ታመሻላችሁ። ለአላህ በሆነ ስራ ላይ ሆናችሁ ሞት እንዲወስዳችሁ ማድረግ የምትችሉ ከሆነ ይህንኑ አድርጉ። በአላህ እገዛ ብቻ እንጅ ይህን ማድረግ አትችሉም። እድሚያችሁ አልቆ ወደ ክፉ ስራችሁ ከመመለሳችሁ በፊት በበጎ ስራ ተሽቀዳደሙ። ከሰዎች መሐል ራሳቸውን ረስተው እድሚያቸውን ለሌላ የሰጡ ይገኛሉ። እንደነርሱ እንዳትሆኑ አስጠነቅቃችኋለሁ። እባካችሁን ፍጠኑ፣ በጣም ፍጠኑ። ከኋላችሁ ፈጣን አባራሪ (ሞት) እያሳደዳችሁ ነው። ቅጣቱም ፈጣን ነው።››[1]

በጎ ነገር አላህን በመታዘዝ ብቻ

አላህ በጎ ነገርን እንዲሁ እንዲሰጥ፣ ከክፉም እንዲሁ እንዲከላከል የሚያስገድደው የዝምድና ትስስር ስለሌለው ይህ እድል የሚገኘው

[1] አልሁልየህ 1/35

እርሱን በመገዛት እና ትእዛዙን በመፈጸም ብቻ ነው። ከበስተኋላው ጀሃነምን የሚያስከትል መልካም ነገር መልካም አይደለም። ጀነትን የሚያስከትል መጥፎ ነገርም መጥፎ አይደለም።››[1]

ለምትካቸው ያስተላለፉት ኑዛዜ

አቡበክር ከሞት አፋፍ ላይ በሆኑ ጊዜ ዑመርን ጠሩና እንዲህ ሲሉ መከሯቸው፡-

‹‹ዑመር ሆይ፣ አላህን ፍራ። አላህ በቀን ካልሆነ በሌሊት የማይቀበለው ስራ አለው። ፈርድን እስክትወጣ ድረስ ሱናን አይቀበልም። በእለተ ቂያማ ሚዛናቸው የሚከብድላቸው ሰዎች ይህን እድል ያገኙት በዚህች ዓለም ሐቅን በመከተላቸው ነው። ሐቅ የስራ ሚዛናቸውን አከበደው። ነገ ሐቅ የሚቀመጥበት ሚዛን ሊከብድ ተገባው። በእለተ ቂያማ ሚዛናቸው የሚቀልባቸው ሰዎች ይህ የሆነባቸው በዚህች ዓለም ሐሰትን በመከተላቸው ነው። ሐሰት ስራቸውን አቀለለው። ነገ ሐሰት የሚቀመጥበት ሚዛን ሊቀል ተገባው። አላህ የጀነት ሰዎችን ሲያወሳ ከስራዎቻቸው መካከል ይበልጥ መልካሙን አወሳ። ግድፈቶቻቸውንም አለፈ። እነርሱን ሳስታውስ፡- ‹‹ከነርሱ ሳልሆን እንዳልቀር፡›› የሚል ስጋት ያድርብኛል። የእሳት ሰዎችን ሲያወሳም ከስራዎቻቸው መሐል ይበልጥ ክፉውን አብሮ አወሳ። ጥሩውን ስራቸውን መለሰባቸው። እነዚህንም ሳስታውስ፡- ‹‹ከነርሱ እንደማልሆን ተስፋ አደርጋለሁ›› እላለሁ። በፍርሃትና በተስፋ መሐል መሆን ተገቢ ነው። በአላህ ላይ መመጻደቅም ከእዝነቱ ተስፋ መቁረጥም ተገቢ አይደለም። ይህን ምክሬን ከሰራህበት ወዳንተ መምጣቱ አይቀሬ ከሆነው ሞት ይበልጥ ተወዳጅ ሩቅ እንግዳ አይኑርህ። ካልሰራህበት ደግሞ ከሞት ይበልጥ የምትጠላው ሩቅ እንግዳ አይኑርህ።››[2]

---

[1] አል ሁልየህ 1/36

[2] ያለፈው ምንጭ

በጸጋ መሸንገል

የአማኞች እናት አኢሻ አዲስ ልብስ ለበሰች። ወደርሱ እያየችም ተኩራራች። አቡበክርም፡- ‹‹ምን እያየሽ ነው? አላህ ወዳንች እያየ አይደለም።›› አሏት። ‹‹ለምን?›› አለቻቸው። እንዲህ አሉ፡- ‹‹አንድ ሰው በዓለማዊ ጌጥ ምክንያት ኩራት ወደቀልቡ ከገባ ያን ጌጥ እስኪተወው ድረስ አላህ ይጠላዋል።››

አኢሻ ልብሷን ወዲያውኑ አወለቀች። መጸወተችውም። አቡበክርም፡- ‹‹ምን አልባት ይህ ድርጊትሽ ወንጀልሽን ያብስልሽ ይሆናል።›› አሉ።[1]

የአላህን ጸጋ በመግለጽና በርሱ በመኮፈስ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ተገቢ ነው። የአላህን ጸጋ መግለጽ በቁርአንና በሐዲስ እንደተነገረው ለርሱ ችሮታ እውቅና መስጠትና ማጽደቅ ሲሆን፣ መኮፈስ ደግሞ ሐቅን ወደ መተው፣ ጸጋን ወደ መካድና በሰዎች ላይ ወደ መኩራት የሚያደርስ ድርጊት ነው።

አቡበክር ሲሞቱ ሐብት ንብረት አልተውም። ለሐላፊነታቸው ከሚሰጣቸው ጥቂት ገንዘብ በላይም ከሙስሊሞች ንብረት አልወሰዱም። የሚገርመው ባለቤታቸው ጣፋጭ ነገር መግዛት ፈልጋ ገንዘብ አጣች። ‹‹ከቀለባችን እየቀናነስኩና እየቆጠብኩ አጠራቅሜ ልግዛ›› በማለት ወሰነች። ከቀለባቸው ቆጥባም ጣፋጭ የሚያስገዛትን ገንዘብ አጠራቀመች። አቡበክር ይህን ድርጊቷን ሲሰሙ፡- ‹‹ከሙስሊሞች በይተል ማል ከሚያስፈልገን በላይ እየወሰድን ነበር ማለት ነው።;›› አሉና ባለቤታቸው ቆጥባ ታስቀምጠው የነበረውን ያህል ገንዘብ ከደሞዛቸው ቀነሱ።

አቡበክር በአራተኛው አመተ ሂጅራ በወርሃ ጀማዱል አኺር 11ኛ ቀን ሰኞ ቀን ይህችን ዓለም በሞት ተሰናበቱ። አላህ ይዘንላቸው። ከርሳቸውና ከልጆቻቸው፣ እንዲሁም የሰው ልጆች ፈርጥ ከሆኑት ከነቢዩ

[1] አል ሁልየህ 1/37

መሐመድ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከባልደረቦቻቸው ጋር በዘልዓለማዊው ሐገር ውስጥ ያገናኘን።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የአቡበክር ሲዲቅን መልካም ባህሪያት አውሳ።

2) አሰላለማቸውን አስታውስ

3) ከአቡበክር ባህሪያት ውስጥ ስሜትህን ይበልጥ የሳቡትን ዘርዝር

4) ከሰይድና አቡበክር ሲዲቅ የሕይወት ታሪክ የሚቀሰሙ ትምህርቶችን ዘርዝር

5) የአቡበክርን ስብእና ማጥናትህ ያስገኘልህን ፋይዳ ዘርዝር።

6) በተግባራዊ ሕይወትህ ውስጥ ተጽእኖ ያሳደሩብህን የአቡበክር ንግግሮች ግለጽ።

* * *

ጦልሐ ቢን ኡበይዱላህ

(ከሂጅራ በፊት 28-36 ሂጅሪያ)

(516-656 ዓ.ል)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ተማሪው የጦልሐ ቢን ዑበይዲላህን መልካም ባህሪያት እንዲያስታውስ፣
2) ጦልሐ በኡሁድ ዘመቻ ላይ ያስመዘገበውን ጀግንነት እንዲያስታውስ፣
3) የጦልሐን ፍጻሜ እንዲያሰታውስ
4) ከጦልሐ ቅንጭብ ታሪክ የሚቀሰሙ ትምህርቶችን እንዲዘረዝር

ታሪኩ ባጭሩ

ጦልሐ፣ የኡበይዱላህ ልጅ፣ የኡስማን ልጅ፣ የአምር ልጅ፣ የከእብ ልጅ፣ የተሚም ልጅ፣ የሙራህ ልጅ፣ የከእብ ልጅ። ከአላህ መልእክተኛ ጋር ሙራህ ቢን ከእብ በተባለ አያታቸው ላይ፣ ከአቡበክር ጋር ደግሞ ከእብ ቢን ሰእድ በተባለው በኩል በዝምድና ይገናኛሉ። የጦልሐ እናት ሰህባህ ቢንት ሐድረሚ ትባላለች።

ኢብን ደሐክ እንደዘገቡት ጦልሐ ቢን ዑበይዲላህ እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

የኡሁድ ዘመቻ እለት የአላህ መልእክተኛ ‹‹በጎው ጦልሐ›› በአሺረህ ዘመቻ ላይ ደግሞ፡- ‹‹ጦልሐቱል ፈያድ›› እንዲሁም በሁነይን ዘመቻ ጊዜ፡- ‹‹ጦልሐቱል ጀዋድ›› በሚሉ ቅጽሎች ጠርተውታል። ጦልሐ በጣም ብልህ ነበሩ። ስለ አሰላለማቸው እንዲህ ሲሉ አውግተዋል፡-

ከበስራ ገበያ ተገኘሁ። አንድ መነኩሴ ከቤተ አምልኮው ውስጥ ሆኖ፡- ‹‹ከገበያተኞች መሐል ከሐረም (መካ) የመጣ ሰው ካለ ጠይቁ።›› አለ።

‹‹እኔ የመጣሁት ከዚያ ነው›› አልኩ። ‹‹አህመድ ተከሰተን?›› አለ። ‹‹አህመድ ማን ነው?›› ስል ጠየቅኩት። ‹‹ቢን አብደላህ፣ ቢን አብዱል መጦሊብ፣ ነብይ በሚሆን ጊዜ መጠሪያ ስሙ ይህ ሲሆን፣ የመጨረሻው ነብይ ነው። መነሻውም ሐረም መካ ነው። የተምር ዛፍና ጥቋቁር አለቶች ወዳሉባት ምድረ በዳ መሬትም ይሰደዳል። ፈጥነህ ተከተለው።›› አሉ። ንግግሩን ከልቦናዬ ውስጥ ገባ። ፈጥኜም ወደ መካ ተመለስኩ። አዲስ የተከሰተ ነገር እንዳለ ስጠይቅም፡- ‹‹ታማኙ መሐመድ ቢን አብደላህ ነብይ ነኝ እያለ ነው። አቡበክር ተከታዩ ሆኗል፡ ፡›› አሉኝ። እንዲህ ስል ከራሴ ጋር አወጋሁ፡-

‹‹በአላህ እምላለሁ፣ መሐመድና አቡበክር በመጥፎ ነገር ላይ አይሰማሙም። መሐመድ እድሜው አርባ ዓመት ደርሷል። ከዚህ ቀደም ውሸት ሰምተንበት አናውቅም። በሰዎች ላይ ለመዋሸት ያልደፈረ በአላህ ላይ ለመዋሸት አይደፍርም።››

ከዚያም ወደ አቡበክር ሄድኩ። ‹‹ይህን ሰው ተከተልከውን?›› ስል ጠየቅኩት። ‹‹አዎ፣ አንተም ሂድና አግኘው። ተከተለውም። ወደ እውነት ነው የሚጣራው።›› አለኝ። ‹‹ጦልሐ ለአቡበክር መነሱኬው የነገረውን አወጋቸው። ተያይዘው ወደ አላህ መልእክተኛ ሄዱ። እስልምናንም ተቀበሉ። በጉዞው ያጋጠመውንም ነገራቸው።

ነውፈል ቢን ኹወይሊድ የአቡበክርንና የጦልሐን መስለም ሲሰማ ሁለቱንም ያዛቸው። ጀአንድ ገመድም ጠፈራቸው። የበኒ ተሚም ጎሳ አልታደጋቸውም። ነውፈል ‹‹የቁረይሽ አንበሳ›› በሚል ቅጽል ነበር የሚታወቀው። ከዚህ ክስተት የተነሳ አቡበክር እና ጦልሐ ‹‹ተጣማሪዎች››[1] ተብለው ተጠሩ። ጦልሐ በዚህ አኳኋን እስልምናን በመቀበል ቀዳሚ ሆነ። በእርግጥ የሰፊ ንግድና የብዙ ሐብት ባለቤት ነበር። ግና ለበጎ ነገር ሌሎችን ቀደመ።

[1] በአንድ ገመድ ተጣምረው ስለታሰሩ።

የኡሁድ ንስር

በኡሁድ ዘመቻ ቁረይሾች በከፍተኛ ሁኔታ ተዘጋጅተው በነቢዩ መሐመድና በተከታዮቻቸው ላይ ተመመዉባቸው። በታላቁ የበድር ዘመቻ የደረሰባቸውን ብርቱ ሽንፈትና ውድመት ለመበቀል ቋምጠዋል። በዚህ ዘመቻ ድል ማግኘት እንዳለባቸውም ወስነዋል። ለዚህም ሲባል ከሙስሊሞች በተሰነዘረባቸው ብርቱ በትር ተስፋ ያልቆረጡ ጽኑና ጀግና ጦረኛቻቸውን አሰልፈው በሙስሊሞች ላይ ቁጣቸውን አዘነቡ። ይህም ሆኖ በመጀመሪያ ድል አልቀናቸውም። የሙስሊሞችን ጠንካራ ጥቃት መቋቃምም ሳይችሉ ቀርተው፣ በድንጋጤ ተውጠው ከጦርነቱ መስክ አፈገፈጉ። ሙስሊሞች በካህድያን ላይ የደረሰውን ውርደት እና ማፈግፈጋቸውን ሲመለከቱ ተቻኩለው መሣሪያ አስቀመጡ። ምክንያቱም የጦርነቱ ውሎ አድክሟቸው አካላቸው ዝሏል። ከጋራው ላይ ሆነው ጠላትን በቀስት እንዲከላከሉ የተመደቡ ቀስተኞችም ከምርኮው የድርሻቸውን ለማግኘት ስፍራቸውን ትተው ወረዱ።

የጥንት ሰዎች እንደሚሉት ‹‹ጦርነት ማታለ›› ነውና ቁረይሾች በድንገት ከበቧቸው። የጦርነቱን ልጓምም ተቆጣጠሩት። በዚህ የጦርነት ረመጥ ውስጥ ከሁለቱም ወገኖች በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ተገደሉ። ሙስሊሞች በተፈጠረው ድንገተኛ ነገር እና በጠላት ፈጣን እና ጠንካራ ጥቃት ግራ ተጋቡ።

በዚህ ፈታኝ ወቅት ጦልሐ የአላህን መልእክተኛ ተመለከተ። ነቢዩ ወድቀው በአደጋ ተከበዋል። ሰይፎች ወደርሳቸው ዞረዋል። የተራቡ ውሾች ሊበሏቸው አሰፍስፈዋል። በሁሉም አቅጣጫዎች የፈረሶች ድምጽ ያስገመግማል። ወንጀለኛ እጆች ሊያጠቋቸው ተዘርግተዋል። ግና አንድ ሐይል ይህን የጠላት ጦር ሰንጥቆ መጣ። ነብዩንም ከእኩያን ጥቃት ታደገ። ይህ ሐይል በአንድ ብርቱና ጀግና ሰው የተመሰለ ነው። ያ ሰው ጦልሐ ቢን ኡበይዲላህ ይባላል። በግራ እጁ የአላህን መልእክተኛ ያዘ። ወደ ደረቱም አስጠጋቸው። የሰይፉን እጀታ በቀኙ ይዞም ከወዲያ ወዲህ

ያወናጭፈው ጀመር። እርሱ ሰይፉን ባንቀሳቀሰ ቁጥር አንገቶች ከአካላቸው እየተነጠሉ ልክ እንደ ዛፍ ቅጠል በዙሪያው ረገፉ።

ሕያው ሰማዕት

አቡበክር የጦልሐን የኡሁድ ውሎ በሚያምር ቋንቋ ገልጸውታል። ልጃቸው አኢሻ ባስተላለፉት ዘገባ እንዲህ ብለዋል፦

አቡበክር የኡሁድን ዘመቻ ሲያወሱ እንዲህ ይሉ ነበር፦
‹‹ቀኑ የጦልሐ ቀን ነበር። ከነቢዩ ዘንድ ቀድሜ ደረስኩ። ለኔና ለአቡኡበይዳህ ወንድማችሁን እርዱት››አሉን። ጦልሐን ማለታቸው ነበር። ከሰባ ቦታዎች ላይ በጦር፣ በቀስትና በሰይፍ ተወግቶ፣ ጣቶቹም ተቆርጠው አገኘነው። እገዛም አደረግንለት።››
የአላህ መልእክተኛ ከዚያ ቀን በኋላ ስለ ጦልሐ ሲናገሩ፦ ‹‹ሞቶ በምድር ላይ የሚራመድ ሰው ማየት የፈለገ ጦልሐ ቢን ኡበይዱላህን ይመልከት።››› ይሉ ነበር። አላህ ጦልሐንና መሰሎቹን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፦

﴿ مِّنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ رِجَالٞ صَدَقُواْ مَا عَٰهَدُواْ ٱللَّهَ عَلَيۡهِۖ فَمِنۡهُم مَّن قَضَىٰ نَحۡبَهُۥ وَمِنۡهُم مَّن يَنتَظِرُۖ وَمَا بَدَّلُواْ تَبۡدِيلٗا ٢٣ ﴾ الأحزاب: ٢٣

‹‹ከአማኞች መካከል ለአላህ የገቡትን ቃል የፈፀሙ ወንዶች አሉ። ከፊሎቹ መስዋዕት ሆነዋል። ከፊሎቹም (መስዋእትነትን በመጠባበቅ ላይ ናቸው። (ቃላቸውን) ፈጽሞ አልለወጡም።›› (አል አህዛብ 23)
የጦልሐ አስተዋጽኦ ቁሳዊ ብቻ አልነበረም። አላህ የሰጠውን ገንዘብ ለዳእዋው በገፍ እንደቸረው ሁሉ ነፍሱንም ችሯል። በውጊያው መስክ ከፊት በመሰለፍ የአላህን መልእክተኛና ሐይማኖቱን ከጥቃት ታድጓል።

ነፍሱን የሚቸር በእውነቱ
ሰዎች ሁሉ ሲሰስቱ
የነፍስ የሕይወት ሰጦታ
አቻ የለሽ ችሮታ

ጦልሐ የምርጥ ስብእና ባለቤት ነው። እርሱ አብዱረህማን ቢን አውፍና ኡስማን ቢን አፋን በዘመነ መሐይምነት ባለጸጋዎች ነበሩ። አንዳች ማሕበራዊ ቦታ ያለው ሰው በተለምዶ ሐብቱንና ክብሩን ከአደጋ ላይ በማጥል ጉዳይ ውስጥ ላለመሳተፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል። እነዚህ ስብእናዎች ግን ለዱንያ ሳይጓጉ እስልምናን ተቀበሉ። የዚህች ዓለም ብልጭልጭ አላታለላቸውም። ለመጭው ዓለም ስኬት ተጠቀሙበት። ለእስልምና ዳእዋ መሳካት ሐብታቸውን ያለ መሰሰት መጸወቱ። ይህ ከመሆኑ አኳያ አላህ በመጭው ዓለም ጸጋውን ያለ ገደብ ቢሰጣቸው የሚገርም አይደለም።

በመጭው ዓለም ጀነት እንደሚገቡ የተሰጣቸው ምስክርነት ብቻ ለውለታቸው በቂ ምላሽ ነው።

የጦልሐ ቸርነት

የጦልሐ ቸርነት እስከ ጥግ የደረሰ ነበር። ይህን ባህሪውን ከባለቤቱ ከሱዓዳ ቢንት ዓውፍ በላይ የሚነግረን የለም። እንዲህ ስትል አውግታለች፡-

አንድ ቀን ከጦልሐ ዘንድ ስገባ በሐሳብ ተውጦ አገኘሁትና፡- ‹‹ምን አገኘህ?›› ስል ጠየቅኩት። ‹‹ገንዘቤ በጣም በዝቶ አሳሰበኝ።›› አለኝ። ‹‹ይህን ያህል የሚያስጨንቅህ ከሆነ ለሰዎች አካፍለው›› አልኩት። ተነሳና ሰዎችን ጠራ። አንዲት ዲርሃም (ቤሳቤስቲን) ሳያስቀርም ሁሉንም አደላቸው።

ጃቢር ቢን አብደላህ የጦልሐን ቸርነት ሲያወሳ እንዲህ ይላል፡-

‹‹ገንዘብ ሳይለምኑት በመስጠት እንደ ጦልሐ ቸር አላየሁም። ለቤተሰቦቹና ለዘመዳቹ በጣም ደግ ነበር። ብዙ ቢሆኑም ሁሉንም ይቀልባቸዋል። ይህን በተመለከተ ከበኒ ተሚም ጎሳ ውስጥ የማይረዳው አንድም ግለሰብ እንደሌለ ተነግሮለታል። እያንዳንዱን አባወራ ከነቤተሰቡ ይደጉመዋል። ያላገቡትን ያጋባል። ድሆችን ያገለግላል። የባለ እዳዎችን እዳ ይከፍላል።››

አንድ ሰው ከጦልሐ ቢን ዑበይዲላህ ዘንድ መጣና ገንዘብ ይደጉመው ዘንድ ጠየቀው። የዝምድና ትስስር እንዳላቸውም አጫወተው። ‹‹ይህ ከአሁን ቀደም አንድም ሰው ያልነገረኝ የዝምድና መስመር ነው። ዑስማን ቢን አፋን 3 ሺህ (ዲርሃም) ሊገዛኝ የጠየቀኝ መሬት አለ። ከፈለግክ ውሰደውና ተጠቀምበት። ከፈለግኩም ለዑስማን በ3 ሺህ ዲርሃም ልሸጠውና ገንዘቡን ልስጥህ።››አለ። ሰውየውም ‹‹ገንዘቡን ብትሰጠኝ ይሻለኛል።›› አለ። ገንዘቡን ሰጠው።

ሕልፈተ ሕይወት

ጦልሐና ዙበይር ከዓሊ ጋር ተወዛገቡ። ውዝግባቸውም ወደ አሳዛኝ እርምጃ ተሸጋገረ። ዓሊ ለሰላም ጉጉ በመሆናቸው እንዳች ነገር ለሁለቱም አስታወሷቸው። እነርሱም ሳይከራከሩ ተቀበሏቸው። ጦልሐ በዓሊ ንግግር ልቡ ተነካ። ዓሊ እንዲህ ነበር ያሉት፦

‹‹የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ማለታቸውን አልሰማህምን? አላህ ሆይ፣ ዓሊን የተወዳጀን ተወዳጀው። እርሱን ጠላት ያደረገን ጠላት አድርገው።

ከኔ ጋር ቃል ኪዳን (በይዓ) የፈጸምከው ቀድመህ ነበር። ግና ቃል ኪዳንህን አፈረስክ አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ فَمَن نَّكَثَ فَإِنَّمَا يَنكُثُ عَلَىٰ نَفْسِهِۖ ﴿١٠﴾ ﴾ الفتح: ١٠

‹‹ ቃልኪዳኑን ያፈረሰ የሚጎዳው ራሱን ነው።›› (አልፈትህ 10)

ጦልሐ ይህን የአሊ ቃል ሲሰደ ‹‹አላህን ምህረት እለምናለሁ›› አሰና ተመለሰ። መርዋን ቢን ሐከም አየው። በቀስት አስወነጭፎም ገደለው።

አኢሻ እንዲህ ብለዋል፦

ከቤት ውስጥ ነበርኩ። የአላህ መልእክተኛ ከሳሎን ተቀምጠዋል። ጦልሐ ቢን ኡበይዲላህ መጣ። በኔና በነርሱ መካከል ግርዶ አለ። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፦ ‹ሞቶ በምድር ላይ የሚራመድ ሰው ማየት የፈለገ ጦልሐን ይመልከት።››

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የጦልሐ ቢን ኡበይዱላህ ባህሪና የአላህ መልእክተኛ የሰጡትን የቅጽል ስሞች አስታውስ፡፡

2) የኡሁድ ዘመቻ እለት ጦልሐ የነበረውን አቋም ግለጽ፡፡ ከዚህ አቋሙ ምን ተማርክ?

3) የጦልሐን ፍጻሜ አውሳ፡፡ ከአቋማቸው ምን ተማርክ?

4) ከጦልሐ ታሪክ የቀሰምከውን ትምህርት ዘርዝር፡፡

5) ከጦልሐ ስብእና ውስጥ የትኞቹ ገጽታዎች ይበልጥ ተጽእኖ አሳደሩብህ፡፡ ይህ ተጽእኖ በተግባራዊ ሕይወትህ ውስጥ የተጫወተው ሚና ካለ አውሳ፡-

* * *

ዙበይር ቢን ዓዋም

(ከሂጅራ በፊት 28-36 ሂጅሪያ)

(596-656 ዓ.ል)

አጠቃላይ ዓላማዎች

1) ተማሪው የዙበይር ቢን አዋምን ልቅና እነዲገነዘብ

2) ከዙበይር ገድሎች ውስጥ አንኳሮቹን እንዲረዳ

3) የዙበይርን አገዳደል እንዲያስታውስ

4) ከዙበይር ታሪክ የቀሰማቸውን ትምህርቶች እንዲዘረዝር፡፡

ታሪኩ ባጭሩ

ዙበይር ቢን አዋም የሰለመው የስምንት አመት ልጅ እያለ ሲሆን፣ ወደ መዲና ሲሰደድ እድሜው 18 ዓመት ነበር፡፡ በሰለመ ጊዜ አጎቱ በጣም ተቆጣ፡፡ ጠራውም፡፡ ‹‹ወደ ክህደት ተመለስ፡፡›› እያለም እሳት አንድዶ በጭስ በማፈን ቀጣው፡፡ ዙበይርም፡- ‹‹በፍጹም አልከፍርም›› ሲል በእምነቱ ጸና፡፡[1]

ዙበይር የሰለመው በጣም ቀድሞ ነው፡፡ ያኔ ገና ልጅ ቢሆንም አላህ ለእስልምና ልቦናውን ከፈተለት፡፡ እስልምናን በቀዳሚነት ከተቀበሉ ሙስሊሞች መካከል አንዱ ነው፡፡ በእስልምና ታሪክ መጀመሪያ የተመዘዘው ሰይፍ የዙበይር ሰይፍ ነበር፡፡

ዙበይር ቢን አል ዓዋም የነቢዩ ሐዋርያ ነው፡፡ ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ጦልሐና ዙበይር ጀነት ውስጥ ጎረቤቶቼ ናቸው፡፡››

እነዚህ ሁለት ስብእናዎች ከነብዩ ጋር በወንድማማችነት መተሳሰራቸውን ይህ ዘገባ ያሳያል፡፡

---

[1] አቡ ኑዓይም፡፡

ዙበይር የአዋም ልጅ፣ የኹወይሊድ ልጅ፣ የአሰድ ልጅ፣ የአብዱል ኢዝ ልጅ፣ የቁሰይ ልጅ፣ የኪላብ ልጅ ነው። በቁሰይ በኩል ከነቢዩ ጋር በዝምድና ይገናኛሉ። እናቱ የነቢዩ አክስት ሶፍየህ ቢንት አብዱል ሙጦሊብ ናት። በጃሂልያም በእስልምናም ዘመን ስሙ ዙበይር ሲሆን፣ አቡ አብደላህ በሚል ቅጽል ስምም ይታወቃል።

እርሱና ጦልሐ በአንድ ዓመት ውስጥ ተወለዱ፣ በተመሳሳይ ዓመት ውስጥም ሸሂድ ሆነው ተገደሉ። ጦልሐ በተወሳ ቁጥር ምንጊዜም አብሮት ይወሳል። ዙበይር ሲወሳም ጦልሐ አብሮ ይወሳል።

ጦልሐና ዙበይር በበርካታ ባህሪዎች ይመሳሰላሉ። ሁለቱም ባለጸጋዎች ፣ የተከበሩ፣ በአላህ ላይ ጽኑ እምነት ያላቸውና በጣም ጀግኖች ነበሩ። ሁለቱም በጀነት ተበስረዋል።

የዙበይር አንኳር ገድሎች

ዙበይር አንድም ቀን ለጣኦት አልሰገደም። በጃሂልያ ዘመን ጸያፍ ድርጊት አልፈጸመም። ከአላህ መልእክተኛና ከሙሐጅሮች ጋር ተሰዷል። ወደ ሁለቱም ቂብላዎች የመስገድ እድል አግኝቷል። አንድ ቀን ሙስሊሞች ዳረል አርቀም ከተባለው ቦታ በድብቅ ተሰባስበው እያለ፦ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ተገደሉ።›› የሚል ወሬ ተናፈሰ። ዙበይር ወሬውን ሲሰማ እጅግ ተቆጣ። ቁጣውም እንደ ብርቱ የመሬት ነውጥ፣ ሐይለኛ እሳተ ጎመራ ወይም አስፈሪ መብረቅ ሆነ።

ሰይፉን ከአፎቱ መዞ ይህን አሳዛኝ ወሬ ለማጣራት ገሰገሰ። ከመካ ከፍታ ላይም የአላህ መልእክተኛ አገኙት። ምን ሆኖ እንደሁ ሲጠይቁት የሰማውን ወሬ ነገራቸው። ያሰበውንም አጫወታቸው። የአላህ መልእክተኛ ለርሱም ለሰይፉም ድል አድራጊ ይሆኑ ዘንድ ዱዓ አደረጉላቸው።

አዎ፣ ዙበይር የላቀ ክብር ሊቸረው የተገባ ሰው ነው። ለክብሩ ተከታዩ የአላህ መልእክተኛ ምስክርነት ይበቃዋል፦

‹‹ሁሉም ነብያት ሐዋርያት አሏቸው፡፡ የኔ ሐዋርያ ዙበይር ቢን አልዓዋም ነው፡፡››

ሰኢድ ቢን ሙሰየብን በመጥቀስ ፈዲኢሊ እንደዘገቡት ዙበይር መካ ውስጥ እያለ ነቢዩ ተገደሉ የሚል ወሬ ሰማ፡፡ ከድንጋጤው የተነሳ ሰይፉን ይዞ እርቃኑን ወጣ፡፡ መንገድ ላይ ነቢዩ አገኙትና ‹ምን ሆነህ ነው?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ እርስዎ ተገደሉ የሚል ወሬ ሰምቼ ነው፡፡›› አላቸው፡፡ ‹‹ታዲያ ምን ልታደርግ አሰብክ?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ ‹‹የመካውያንን ደም አንድም ሳላስቀር እንደ ጎርፍ ላፈሰው ወሰንኩ፡፡›› አላቸው፡፡ ሳቁና ኩታቸውን አውልቀው አለበሱት፡፡ ወዲያውም ጅብሪል ወረደና እንዲህ አላቸው፡- ‹‹አላህ ሰላምታ አቅርቦልሐል፡፡ ለዙበይርም ሰላምታዬን አድርስልኝ ብሎሐል፤ በአላህ መንገድ ሰይፉን የመዘዘ የመጀመሪያው ሰው በመሆኑ አንተ በነብይነት ከተላክ ጀምሮ እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ለአላህ ሲሉ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን ሁሉ የሚያህል ምንዳ የነርሱ ምንዳ ሳይጓደል- አላህ እንዳዘጋጀለትም ትነግረው ዘንድ አዞሐል፡፡››

ቢን ሰእድ ጦበቃት በተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ እንደዘገቡት ዙበይር እንዲህ ሲል አውግቷል፡-

‹‹የበድር እለት መላኢኮች ከቦቃ ፈረስ ላይ ሆነው እና ቢጫ ጥምጣም ለብሰው ወረዱ።››

ዙበይር ያኔ ቢጫ ጥምጣም ለብሶ ነበር፡፡ መልእክተኛውም፡- ‹‹መላኢኮች በዙበይር ሰማይ ላይ ወረዱ፡፡›› ሲሉ ተናገሩ፡፡

ኢብን ኢስሐቅን በመጥቀስ ዩኑስ እንዳወሱት የበድር እለት የቁረይሾች አርማ ተሸካሚ የነበረው አቡ ጦልሐተል ዓብደሪይን ለሁለትዮሽ ግጥሚያ ሙስሊሞችን ጋበዘ፡፡ ሰዎች ከርሱ ሲሸሹ ዙበይር ሊገጥመው ወጣ፡፡ ዘሎም ከግመሉ ላይ መጣበት፡፡ ይዞትም ወደ መሬት ወረደ፡፡ በሰይፉም አረደው፡፡ የአላህ መልእክተኛም አድራጎቱን አሞገሱ፡፡ እንዲህም አሉ፡-

‹‹ሁሉም ነብያት ሐዋሪያት አሏቸው። የኔ ሐዋርያ ዙበይር ነው። ሰዎች ከርሱ (ከቢን ጦልሐ) ሲሸሹ ሳይ ዙበይር ሊፋለመው ባይወጣ ኖሮ እኔ እፋለመው ነበር።››[1]

በኡሁድ ዘመቻ እለትም የቁረይሽ ሰራዊት የጦርነቱን መስክ ለቆ ወደ መካ ካቀና በኋላ ነቢዩ ዙበይርን እና አቡበክርን የቁረይሾች ሰራዊት ያሳድዱ ዘንድ አሰማሯቸው። ይህን ያደረጉት ቁረይሾች የሙስሊሞችን ብርታት እንዲያዩና ወደ መዲና ተመልሰው ውጊያ ለመጀመር እንዳያስቡ ለማድረግ ነው። አቡበክርና ዙበይር ሰባ ሙስሊሞችን አስከትለው ቁረይሾችን ያሳድዱ ጀመር። የሚያሳድዱት ጦር ጊዜያዊ ድል ያገኘ ሰራዊት ቢሆንም እነ አቡበክር የተከተሉት የጦርነት ስልት ቁረይሾችን ማስደንገጡ አልቀረም።

የሙስሊሞችን ኪሣራ በተመለከተ ስሌታቸው ስህተት እንደሆነ እንዲያስቡ አደረጉ። በተጨማሪም በአቡበክርና በዙበይር የተመራውና ሐይልና ጥበብን ያሳየው ይህ ጦር ከኋላው በነቢዩ የሚመራ ሌላ ጦር ያስከተለ እንዲመስላቸው አደረጉ። ስለሆነም ወደ መካ በፍጥነት ለማምለጥ ተገደዱ።

የየርሙክ ዘመቻ እለት በርካታ የሙስሊሞች ጦር ከሮሞች ግዙፍ ሰራዊት ፊት ሲያፈገፍግ ዙበይር በተመለከተ ጊዜ ትእይንቱን መታገስ አልቻለም። አላሁ አክበር! በማለት ወደ ሮሞች ጦር ገስግሶ ክፉኛ አጠቃቸው።

ዙበይር የእስልምና መሠረት

ዑርወት ቢን ዙበይር እንዲህ ሲል አውግቷል፡-
የነቢዩ ሶሐቦች የየርሙክ ቀን ለዙበይር፡- ‹‹ካህድያንን አጥቃልን እኛም አብረንህ እናጠቃቸዋለን።››አሉት። ‹‹እኔ ሳጠቃ ወደ ኋላ እንዳትቀሩ›› አላቸው። ‹አናደርገውም›› አሉት። ሮሞችን ብቻውን አጠቃ። ሰልፋቸውን ሰንጥቆም አለፈ። የተከተለው አልነበረም። ተመልሶ መጣ።

[1] አል ቢዳያህ ቅ 3 ገጽ 20

የፈረሱን ልጓም ያዙና ሁለት ጊዜ ከትከሻው ላይ መቱት። አንደኛው የበድር እለት የተመታበት ቦታ ነበር። እነዚህ ምቶች ከፈጠሩት የአካሉ መሰርጎድ ውስጥ በልጅነቱ ጣቴን እያስገባሁ እጫወት ነበር።
አብደላህ ቢን ዙበይር አብሮት ነበር። እድሜው 20 ዓመታት ነበር። ከፈረሱ ላይ አወጣው። አንድ ሰውም ወከለለት።› (ቡኻሪ)
ዑመር ቢን አልኸጧብ እንዲህ ብለዋል፡-
‹‹ዙበይር ከእስልምና መሠረቶች መካከል አንዱ ነው።››
ዙበይር ለዲኑ ታማኝ ሆኖ በአላህ መንገድ በተደረገ ትግል መስዋእት (ሸሂድ) እስከሆነበት እለት ድረስ ለአላህ መልእክተኛ በገባው ቃል ኪዳን እንደጸና ኖሯል። ሐሳን ቢን ሳቢት የተባለ ገጣሚ ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፡-

ለነቢዩ የገባውን
ተጠባብቆ ቃል ኪዳኑን
ዝንፍ ሳይል ከቅን ፍኖት
ሆኖ የርሳቸው ሐዋርያ ረዳት
ቃሉን ከተግባሩ አዋዶ
ፍትህን ከቃሉ አዋህዶ
የርሳቸውን ጎዳና ጠብቆ
የሐቅን ወዳጅ አጥብቆ
እውቅ ፈረሰኛ ጀግና
ታዋቂ ስመ ገናና
እስልምናን በመታደግ
ያካበተ ክብር ዝና
ታላቁን ነብይ መስጦፋን
ከጠላት ጥቃት ተከላክሏል።
ዝንብ እንኳ እንዳያርፍባቸው
ነፍሱን ሸጦ ግዳይ ጥሏል።
በገፍ ይመንዳው ጌታ
መቼም አያልቅበት ስጦታ።

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ በጀነት አብስረውታል፡-

‹‹ጦልሐና ዙበይር ጀነት ውስጥ ጎረቤቶቼ ናቸው፡፡››

ጀነት ውስጥ የአላህን መልእክተኛ ጉርብትና ታድሏል፡፡ ኢብን አባስ ስለ ጦልሐና ዙበይር ተጠይቀው እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ይዘንላቸው፡፡ በአላህ እምላለሁ፡፡ ሙስሊሞች፣ ሙእሚኖች፣ ደጋጎች፣ አላህን የሚፈሩ፣ በጎ ሰሪዎች፣ በላጮችና ንጹሐን ነበሩ፡፡››

ቡኻሪና ሌሎችም እንደዘገቡት ዙበይር የተገደለው በ36 ዓ.ሂ በወርሃ ረጀብ ሲሆን፣ ገዳዩ አምር ቢን ጀርሙዝ ይባላል፡፡ ለዙበይር አላህ ይዘንለት፡፡

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የዙበይር ቢን አዋምን ልቅና አብራራ፣
2) ገድሎቹን አብራራ፡፡ ከገድሎቹ መሐል ይበልጥ የመሰጠህን አውሳ፡፡
3) ዙበይር ቢን አል አዋም የተገደለበትን ክስተት አስታውስ፡፡
4) ከዙበይር የሕይወት ታሪክ የሚቀሰመውን ትምህርቶች ዘርዝር፡፡
5) ከዙበይር የሕይወት ታሪክ የቀሰምካቸውን ትምህርቶች በሕወትህ ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርጋቸው አስረዳ፡፡

ምእራፍ 6

ኣል ዒባዳ

አጠቃላይ ዓላማ

አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረበትን ዓላማ መረዳት

﴿ وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦ ﴾ الذاريات: ٥٦

‹‹ኢጋንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› (አል ዛሪያት 56)

ዝርዝር አላማዎች

1) የመፈጠርን ዓላማ ማብራራት (አል ዛሪያት 56)

2) የኢባዳን ትክክለኛ እና ሁለንተናዊ ትርጉም፣ እንዲሁም የተለያዩ ገጽታዎቹን ማብራራት

3) ኢባዳ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ አስፈላጊ መስፈርቶችን መዘርዘር

4) የኢባዳን አስፈላጊነትና ክብደት መረዳት

5) ሁለንተናዊ የሆነውን ኢባዳ እውን ለማድረግ ተገቢው ጥረት እንዲደረግ ማገዝ

የመፈጠርን ዓላማ ማብራራት

ንዑስ ዓላማዎች

ሀ) የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓላማ ማብራራት

ለ) በሰው ልጅና በዙሪያው ባለው ዩኒቨርስ መካከል ያለውን ግንኙነት መገንዘብ

ሀ) የሰው ልጅ የተፈጠረበት ዓላማ፡- አላህ የሰውን ልጅ ለምን ፈጠረው? የሰው ልጅ የሕይወት ተልእኮ ምንድን ነው? እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ሊጠይቀው፣ መልሱንም በእርጋታ ሊያስብበት የሚገባ ጥያቄ ነው፡ ፡ የትኛውም ስህተት መጥፎ ውጤቱ የቱን ያህል ቢሆንም ይቅር ሊባል

ይችላል። የሰው ልጅ የሕልውናውን ሚስጥር፣ የሕይወቱን ዓላማ፣ በምድር ላይ ያለውን ተልእኮ አለማወቁ ግን ፈጽሞ ይቅር የሚባል አይደለም።

አንድን ነገር የሚሰራ አካል፣ ያን ነገር የሰራበትን ዓላማና ሚስጥር ያውቃል። ስለዚህም የሰው ልጅ ፈጣሪና የጉዳዮቹ አስተናባሪ የሆነውን አምላክ ‹‹የሰውን ልጅ ለምን ፈጠርከው?›› በማለት እንጠይቀው።

አላህ መልሱን በተከበረው መጽሐፍ ሰጥቶናል። የሰው ልጅ የተፈጠረው በምድር ላይ የርሱ ምትክ (ኸሊፋ) እንዲሆን መሆኑን ነግሮናል። አደምን የፈጠረበትን ዓላማ ሲያብራራ ይህንኑ ገልጿል። መላእክትም የርሱን ቦታ መመኘታቸውን ተመልክቷል። አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ وَإِذۡ قَالَ رَبُّكَ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي جَاعِلٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ خَلِيفَةٗۖ قَالُوٓاْ أَتَجۡعَلُ فِيهَا مَن يُفۡسِدُ فِيهَا وَيَسۡفِكُ ٱلدِّمَآءَ وَنَحۡنُ نُسَبِّحُ بِحَمۡدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَۖ قَالَ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٣٠ ﴾ البقرة: ٣٠

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላእክት “እኔ በምድር ላይ ወኪል (ኸሊፋህ) ለመፍጠር አቅጃለሁ” ባላቸው ጊዜ (የሆነውን አሰታውስ፣ ለሕዝቦችህም ተርክላቸው።) “(አንተን በመወንጀል) ጥፋት የሚፈፅምን፥ ደሞችን (በግፍ) የሚያፈስን (ፍጡር) ከርሷ (ከምድር) ላይ ትፈጥራለህን? እኛ አንተን ከማመስገን ጋር ከጉድለት የምናጠራህ፥ የምናወድስህም ሆነን እያለ?” አሉት። “እናንተ የማታውቁትን ዐ ውቃለሁ” አላቸው።››› (አል በቀራህ 30)

የዚህ ኸሊፋነት የመጀመሪያው ሐላፊነት ሰውየው አምላኩን በሚገባ አውቆ፣ በአግባቡ ማምለኩ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ وَمِنَ ٱلۡأَرۡضِ مِثۡلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ ٱلۡأَمۡرُ بَيۡنَهُنَّ لِتَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدۡ أَحَاطَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عِلۡمَۢا ١٢ ﴾ الطلاق: ١٢

‹‹አላህ ያ ሰባት ሰማያትን የፈጠረ (አምላክ) ነው። ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሯል)። አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ መሆኑን ታውቁ ዘንድ (ይህንን ገልጸላችኋል)።›› (አል ጦላቅ 12)[1]

እንዲህም ብሏል፡-

﴿ وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦ ﴾ الذاريات: ٥٦

‹‹አጋንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› (አል ዛሪያት 56)

ይህ ቁርአናዊ መልእክት ከአራት ቃላት የተዋቀረ ቢሆንም የሕልውናችንን ታላቅ እውነታ፣ የመፈጠራችንን ጥበብ በውስጡ ይዟል። እርሱም አላህን በብቸኝነት ማምለክ ነው። ሙዓዝ ኢብን ጀበል የሚከተለውን አውግተዋል፡-

ከአላህ መልእክተኛ ጋር አብረን በመጓዝ ላይ እያለን፡- ‹‹ሙዓዝ ሆይ፣ አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን መብት ታውቃለህን?›› ሲሉ ጠየቁኝ። ‹‹አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ›› አልኳቸው። ‹‹አላህን በርሱ ላይ ምንንም ነገር ሳያጋሩ በብቸኝነት ሊያመልኩት ነው።››አሉኝ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

የሰው ልጆችና አጋንንት የተፈጠሩበት ዓላማ ዒባዳ በተሰኘው በዚህ ተግባር ይገለጻል።

ይህን ተግባር በትክክል የፈጸመ የሕይወቱን ግብ አሳክቷል። በአግባቡ ያልተወጣው ደግሞ የሕልውናውን ዓላማ ስቷል። ሕይወቱም ተግባርና ዓላማ አጥታለች። የመጀመሪያና መሠረታዊ እሴቷን ከምታገኝበት የሕልውና ትርጉሟ ነጥፋለች። በዚህ ተግባር የሰው ልጅ፣ አላህ እርሱን

[1] አል ኢባዳህ ፊል ኢስላም ዶክተር ዩሱፍ አልቀረዷዊ

የፈጠረበትን ዋነኛ ዓላማ ያከናውናል። እርሱም አላህን ማምለክ ሲሆን፣ በምድር ላይ ለአላህ ወኪልነት የሚያበቃውዋነኛ ተግባርም ይህ ነው።››[1]

አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ባሮቼ ሆይ፣ እናንተን የፈጠርኳችሁ የብቸኝነት ስሜቴን እንድትገፉልኝ፣ የቁጥር አናሳነቴን እንድታበዙልኝ፣ የተሳነኝ አንዳች ነገር ኖሮ እርሱን ለመፈጸም እንድታግዙኝ፣ አንዳች ጥቅም እንድታስገኙልኝ ወይም ጉዳትን እንድትከላከሉልኝ አይደለም። የፈጠርኳችሁ ለረኸርም ጊዜ እንድታመልኩኝ፣ ብዙ ጊዜ እንድታወሱኝና ጠዋት ማታ ክብሬን እንድትመሰክሩ ነው።››

የሁሉም ነብያት ጥሪ

አላህን ብቻ ማምለክ አላህ ከሰው ልጅ ጋር የተጋባው እና ከአፈጣጠራቸው ውስጥ በቀደር ብእር የመዘገበው ቃል ኪዳን ነው። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَلَمۡ أَعۡهَدۡ إِلَيۡكُمۡ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ أَن لَّا تَعۡبُدُواْ ٱلشَّيۡطَٰنَۖ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ٦٠ وَأَنِ ٱعۡبُدُونِيۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٦١ ﴾ يس: ٦٠ - ٦١

“የአደም ልጆች ሆይ! ሰይጣንን አትታዘዙ። እርሱ ለናንተ ግልጽ ጠላት ነውና፥” የሚል ትእዛዜን (በመልዕክተኞቼ አማካይነት) አላስተላለፍኩላችሁም ነበርን? “እኔን ብቻ አምልኩ፤ ቀጥተኛውም ጎዳና ይህ (ብቻ) ነው፥ (አላልኳችሁምን?)” (ያሲን 60-61)

ቁርአን በተከታዩ አንቀጽ የገለጸው ይህን በአላህና በባሮቹ መካከል የተደረገ ቃል ኪዳን ነው፡-

[1] ሰይድ ቁጥብ ፊዚላሊል ቁርአን

﴿ وَإِذۡ أَخَذَ رَبُّكَ مِنۢ بَنِيٓ ءَادَمَ مِن ظُهُورِهِمۡ ذُرِّيَّتَهُمۡ وَأَشۡهَدَهُمۡ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ أَلَسۡتُ بِرَبِّكُمۡۖ قَالُواْ بَلَىٰۛ شَهِدۡنَآۛ أَن تَقُولُواْ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ إِنَّا كُنَّا عَنۡ هَٰذَا غَٰفِلِينَ ١٧٢ أَوۡ تَقُولُوٓاْ إِنَّمَآ أَشۡرَكَ ءَابَآؤُنَا مِن قَبۡلُ وَكُنَّا ذُرِّيَّةٗ مِّنۢ بَعۡدِهِمۡۖ أَفَتُهۡلِكُنَا بِمَا فَعَلَ ٱلۡمُبۡطِلُونَ ١٧٣ ﴾ الأعراف: ١٧٢ - ١٧٣

‹‹ጌታህ ከአደም ልጆች ከጀርባዎቻቸው ዝርያዎቻቸውን ያወጣና "ጌታችሁ አይደለሁምን?" በማለት በራሳቸው ላይ ባስመሰከራቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። "አዎ፥ (ጌታችን መሆንህን) መስካሪዎች ነን።" አሉ። "በዕለተ ትንሳኤ፥ ይህንን (ቃልኪዳን) ፈጽሞ አናስታውስም፥" እንዳትሉ፥ "ወይም ደግሞ ያጋሩት በፊት የኖሩት አባቶቻችን ናቸው። እኛ የነርሱ ዝርያዎች በመሆናችን (ተከትለናቸዋል)። አጥፊዎች በሠሩት (ጥፋት) ታጠፋናለህ?" እንዳትሉ (ይህን ፈጽመናል)።" (አላቸው)። (አል አዕራፍ 172-173)

ከዚህ አጎያ ወደ ሰው ልጆች የተላኩ የአላህ መልእክተኞች ሁሉ ዋነኛ ጥሪ ይህን መልእክት የሚያስታውስ መሆኑ አያስገርምም። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَۖ ﴾ النحل: ٣٦

‹‹መልዕክተኞችን "አላህን ብቻ አምልኩ፤ ጣዖታትንም ተከልከሉ።"(የሚል መልዕክት አስይዘን) በሁሉም ሕዝቦች ውስጥ በእርግጥ አስነሳን።›› (አል ነህል 36)

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥ ﴾

‹‹ከአንተ በፊት መልዕክተኛን አላክንም፥ "እነሆ፥ ከኔ ሌላ አምላክ የለም። ስለሆነም (በብቸኝነት) አምልኩኝ።" የሚል መልዕክት የምናወርድለት ቢሆን እንጅ።›› (አል አንቢያእ 25)

የበርካታ ነብያትን ካወሳ በኋላ እንዲህ ብሏል፦

﴿ إِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَٰحِدَةً وَأَنَا۠ رَبُّكُمْ فَٱعْبُدُونِ ﴿٩٢﴾ ﴾ الأنبياء: ٩٢

ይህች በእርግጥም (ተመሳሳይ እምነ ትና ፍኖት ያላት) ሕዝባችሁ ናት። አንድ ሕዝብ። እኔም (እውነተኛ) ጌታችሁ ነኝ። ስለዚህ (በብቸኝነት) አምልኩኝ። *(አል አንቢያእ 92)*

ሁሉም በኢባዳ ታዘዋል። ነቢዩ ሙሐመድንም እንዲህ ሲል አሏቸዋል፦

﴿ وَٱعْبُدْ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأْتِيَكَ ٱلْيَقِينُ ﴿٩٩﴾ ﴾ الحجر: ٩٩

‹‹ጌታህንም ሞት እስኪመጣህ ድረስ አምልከው።›› (አል ሂጅር 99)

ኢሳ ሕዝባቸው በርሳቸው ላይ የለጠፈውን ቅጥፈት ካስተባበሉ በኋላ የተገኘቦትን አደብ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፦

﴿ مَا قُلْتُ لَهُمْ إِلَّا مَآ أَمَرْتَنِى بِهِۦٓ أَنِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ رَبِّى وَرَبَّكُمْ ۚ وَكُنتُ عَلَيْهِمْ شَهِيدًا مَّا دُمْتُ فِيهِمْ ۖ فَلَمَّا تَوَفَّيْتَنِى كُنتَ أَنتَ ٱلرَّقِيبَ عَلَيْهِمْ ۚ وَأَنتَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ شَهِيدٌ ﴿١١٧﴾ ﴾ المائدة: ١١٧

‹‹(ይላልም)፦ "የነገርኳቸው ያዘዝከኝን ብቻ ነው። የኔም የናንተም ጌታ የሆነውን አላህን ብቻ አምልኩ (ነው ያልኳቸው)። ከመካከላቸው በነበርኩበት ወቅት ስለነርሱ መስካሪ ነበርኩ። እንዳርግ ካደረግከኝ በኋላ ግን የነርሱ ጠባቂና ተቆጣጣሪ አንተው ነበርክ። አንተ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ ነህ።" (አል ማኢዳህ 117)

ትክክለኛው ሐይማኖት ከጥንት ይዞ እስከዛሬ አላህን በብቸኝነት ማምለክን አስተምሯል። ሁሉም ነብያት ወደዚህ ቁም ነገር ተጣርተዋል፡

ስለዚህም በሁሉም የአላህ መልእክተኞች እንደተሰበከው የሰው ልጅ አይነተኛ ዓላማ ኢባዳ ነው።[1]

[1] አል ኢባዳህ ፊል ኢስላም ዶክተር ዩሱፍ አልቀረዷዊ

ለ) በሰው ልጅና በዙሪያው ባለው ዓለም መካከለ ያለው ግንኙነት

አላህ ይህን ድንቅና ውብ ዓለም ለሰው ልጅ ፈጠረ። ነብያትን ሁሉ ወደ ቅኑ ጎዳና ይመሩት ዘንድ አስነሳ። በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹የአደም ልጅ ሆይ፣ ሁሉንም ነገሮች ላንተ ፈጥሬያቸዋለሁ። አንተን ግን የፈጠርኩህ ለኔ ነው። ላንተ በተፈጠረው ነገር መጠመድህ በተፈጠርክበትን ዓላማ እንዳያዘናጋህ ተጠንቀቅ።››

አላህ በቁርአኑ ለሰው ልጅ የዋለውን ውለታ ካወሳ በኋላ የሰው ልጅ በምላሹ ይህን ጸጋውን በመካድ ያሳየውን አስገራሚና በዳይ አቋም ይሐይሳል፡-

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزْقًا لَّكُمْ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلْفُلْكَ لِتَجْرِىَ فِى ٱلْبَحْرِ بِأَمْرِهِۦ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلْأَنْهَٰرَ ﴿٣٢﴾ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ دَآئِبَيْنِ ۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ ﴿٣٣﴾ وَءَاتَىٰكُم مِّن كُلِّ مَا سَأَلْتُمُوهُ ۚ وَإِن تَعُدُّوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحْصُوهَآ ۗ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَظَلُومٌ كَفَّارٌ ﴿٣٤﴾ ﴾ إبراهيم: ٣٢ - ٣٤

‹‹አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣ ከሰማይም ውሃን ያወረደና በርሷም ለናንተ ሲሳይ ይሆናችሁ ዘንድ (የተለያዩ) ፍራፍሬዎችን ያበቀለ (አምላክ) ነው። መርከብንም ባሕሩ ላይ መንዝ ትችል ዘንድ - በትእዛዝ- ገራላችሁ። ወንዞችንም ገራላችሁ። ፀሐይንና ጨረቃንም፥ ዘወትር ተንገሮች አድርጉ፥ ገራላችሁ። ሌትንና ቀንንም ገራላችሁ። (ለሕይወት) የሚያስፈልጋችሁንም ነገሮች ሁሉ ሰጥታችኋል። የአላህን ፀጋዎች ቆጥራችሁ አትዘልቋቸውም። የሰው ልጅ በእርግጥም በዳይ፣ ከሓዲ ነው።›› (ኢብራሂም 32-34)

የፈጠረ አላህ፣ ሲሳይ የሚሰጥ፣ ያስተማረ አላህ፣ ለሰው ልጅ ክብርን ያጎናጸፈ አላህ። የሰው ልጅ ለዚህ ሁሉ ጸጋ እውቅና አይሰጥምን? በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ተብሏል፡-

‹‹እኔ በአንድ በኩል፣ አጋንንትና ሰዎች በሌላ በኩል በአስገራሚ ሁኔታ ውስጥ ነን። እኔ ፈጥሪያቸው ሌላን ያመልካሉ። ሲሳይ የለገስኳቸው እኔ ሆኜ እያለሁ ሌላን ያመሰግናሉ።››

ሱዩጢ አቡ ደርዳእን ዋቢ አድርገው ዘግበውታል። አላህ እንዲህም ብሏል፡-

﴿ كَلَّآ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَيَطۡغَىٰٓ ٦ أَن رَّءَاهُ ٱسۡتَغۡنَىٰٓ ٧ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجۡعَىٰٓ ٨ ﴾ العلق: ٦ - ٨

‹‹በእውነቱ የሰው ልጅ ወሰንን ያልፋል፣ የዚህ ምክንያቱ ራሱን የተብቃቃ አድርጐ መገመቱ ነው። (የሁሉም ነገር) መመለሻ ወደ ጌታህ ብቻ ነው።›› (አል ዓለቅ 6-8)

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የሰው ልጅ የተፈጠረበትን አላማ ግለጽ።
2) በሰው ልጅና በዙሪያው ባለው ዓለም መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት አብራራ

* * *

የኢባዳ ትክክለኛና ሁለንተናዊ ትርጉም

የርእሱ ዓላማ

ሀ) ተማሪው የኢባዳን ሁለንተናዊ እና ትክክለኛ ትርጉም እንዲገነዘብ

ለ) የኢባዳን የተለያዩ ገጽታዎች መዘርዘር

የኢባዳ ትክክለኛና ሁለንተናዊ ትርጉም

አላህ ፍጹም ፍቅር በተቀላቀለው ፍጹም ታዛዥነት እንድናመልከው ፈጥሮናል። ይህ ታዛዥነት በምን መልኩ፣ በየትኛው አኳኋን ይገለጻል? ለዚህ ጥያቄያችሁ የምንሰጠው መልስ አድማሱ-ሰፊ የሆነውን የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ ይከስትልናል።

የሐይማኖት ክንውኖችን ማጠቃለሉ

ኢማም ቢን ተይሚያህ፡- ‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ጌታችሁን አምልኩ።››[1] የሚለውን የቁርአን አንቀጽ በተመለከተ፡- ‹‹ኢባዳ ምንድን ነው?፣ ዘርፎቹስ?›› ተብለው ተጠይቀው እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-

‹‹ኢባዳ አላህ የሚወዳቸውን ግልጽም ስውርም የሆኑ ተግባራት እና ንግግሮች ሁሉ ያጠቃለለ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ሶላት፣ ዘካ፣ ጾም፣ ሐጅ፣ እውነት መናገር፣ አደራን ማድረስ፣ የወላጆችን መብት መጠበቅ፣ ዝምድናን መቀጠል፣ ቃልኪዳንን መመላት፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ ካህድያንንና ሙናፊቆችን መፋለም፣ ለጎረቤት፣ ለየቲም፣ ለድሃ፣ ለባሪያ፣ እንዲሁም ከሰው አልፎ ለእንስሳ በጎ መዋል፣ ዱዓ፣ ዚክር፣ ቁርአን መቅራትና መሰል መንፈሳዊ ተግባራት፣ አላህንና መልእክተኛውን መውደድ፣ አላህን መፍራት፣ ወደርሱ መመለስ፣ ስራን በኢኽላስ መፈጸም፣ ውሳኔውን በትእግስት ማስተናገድ፣ ለጸጋዎቹ ምስጋና ማድረስ፣ ፍርዱን መውደድ፣ በርሱ መመካት፣ እዝነቱን ተስፋ

[1] አል በቀራህ 21

ማድረግ፣ ቅጣቱን መፍራትና መሰል ድርጊቶች ሁሉ ኢባዳዎች ናቸው።››

ኢብን ተይሚያህ እንዳብራሩት የኢባዳ መስክ እጅግ ሰፊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ኢባዳ በተለመዱ መንፈሳዊ ክንውኖች ብቻ የሚገደብ አይደለም፡፡ ከነርሱ በጣም ይሰፋል። ከፈርድ በተጨማሪ ሱንና ኢባዳዎች፣ ቁርአን መቅራት፣ ዱዓ፣ ኢስቲግፋር፣ ተስቢህ፣ ተህሊል፣ ተክቢር፣ ተህሚድ እና ሌሎችንም ዚክሮች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የፍጡራንን መብት ሁሉም ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ የወላጆችን መብት መጠበቅ፣ ዝምድናን መቀጠል፣ ለየቲም፣ ለድሃና መንገድ ላይ ስንቅ ላለቀበት በጎ መዋል፣ ለደካሞችና ለእንስሳት ማዘን፡፡ ሰብአዊ የሞራል ይዞታዎችን ሁሉም ያጠቃልላል፡፡ ‹‹አምላካዊ ስን ምግባሮች›› በመባል የሚታወቁትን ተግባራት፣ ለምሳሌ አላህንና መልእክተኛውን መውደድ፣ አላህን መፍራት፣ ወደርሱ መመለስ፣ ኢኽላስ፣ ውሳኔውን መታገስ፣ ማመሰገን፣ ፍርዱን መውደድ፣ በርሱ መመካት፣ እዝነቱን ተስፋ ማድረግና መሰል የቀልብ ክንውኖችን ሁሉም ያጠቃልላል፡፡ የዲን አስኳል የሆኑትን ክንውኖችም ያጠቃልላል፡፡ እነርሱም በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል፣ እንዲሁም ካህድያንና ሙናፊቆችን በአላህ መንገድ መፋለም ናቸው፡፡››[1]

በሰው ልጅ ቁሳዊ ሕይወት ውስጥ እጅግ ወሳኝ ስፍራ ያለውን አንድ ነገርም ያጠቃልላል፡፡ ሸይኹል ኢስላም ቢን ተይሚያህ ‹አል ዐብዲያህ›› ከተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ በሌላ ስፍራ አውስተውታል፡፡ እርሱም የምክንያትና ውጤት (Cause and Effect) ተፈጠሯዊ ሕግን በመረዳት ለመልካም ውጤት የሚያበቁ ምክንያቶችን መከተልና ከአላህ የተፈጥሮ ሕግ አኳያ ሕይወትን መምራት ነው፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ባሮቹን ያዘዘበትን ሰበብ ሁሉ ማድረስም ኢባዳ ነው፡፡››

ከዚህ በተጨማሪ ሸይኹል ኢስላም ቢን ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፡-

[1] አል ኢባዳ ፊል ኢስላም- ዶክተር ዩሱፍ አልቀረዷዊ

‹‹ሐይማኖት ባጠቃላይ በኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ይካተታል፡፡ ምክንያቱም ዲን የሚለው ቃል መተናነስንና መዋረድን በውስጡ ይዟል፡፡ በዓረብኛ ‹‹ዲንቱሁ›› ማለት አዋረድኩት ማለት ነው፡፡ ‹‹የዲኑ ሊላሂ›› ስንል ‹‹አላህን ያመልካልም፣ ይታዘዛል ለርሱ ይተናነሳል›› ማለታችን ነው፡፡

የአላህ ዲን እርሱ ማምለክ፣ መታዘዝና ለርሱ መተናነስ ነው፡፡ ኢባዳም መሠረታዊ ትርጉሙ መተናነስ በመሆኑ የኢባዳ እና የዲን ትርጉሞች ከቋንቋም ከሸሪዓም አኳያ ይመሳሰላሉ፡፡

ኢባዳ ሕይወትን ሁሉ ያጠቃልላል

ኢባዳ መላ ሕይወትን ያስተካክላል፡፡ ጉዳዮቿን ያደራጃል፡፡ ከአመጋገብና ከአጠጣጥ ስርዓት ጀምሮ እስከ መንግስት አስተዳደር፣ የፍትህ እና የገንዘብ ስርዓት፣ እስቪልና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግጋት፣ እስከ መንግስታት የሰላምና የጦርነት ግንኙነት ድረስ ሁሉንም የሕይወት ዘርፎች ያካተተ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ቁርአን ለሙእሚኖች የተለያዩ የሕይወት ገጽታዎችን በማውሳት ትእዛዝ ሲያስተላልፍ እናነባለን፡፡ ለምሳሌ በአልበቀራህ ምእራፍ ውስጥ ‹‹ኩቲበ አለይኩም›› (በናንተ ላይ ግድ ሆኗል) በሚል መወጠኛ ተከታዮቹ ትእዛዛት ሰፍረዋል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡقِصَاصُ فِي ٱلۡقَتۡلَىۖ ﴾ البقرة: ١٧٨

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የነፍስ ግድያ ወንጀል ሲፈፀም “ቂሷስ” በናንተ ላይ ተደንግጓል።›› (አል በቀራህ 178)

﴿ كُتِبَ عَلَيۡكُمۡ إِذَا حَضَرَ أَحَدَكُمُ ٱلۡمَوۡتُ إِن تَرَكَ خَيۡرًا ٱلۡوَصِيَّةُ لِلۡوَٰلِدَيۡنِ وَٱلۡأَقۡرَبِينَ بِٱلۡمَعۡرُوفِۖ حَقًّا عَلَى ٱلۡمُتَّقِينَ ١٨٠ ﴾ البقرة: ١٨٠

‹‹ከመካከላችሁ አንዱ ለሕልፈት በተቃረበበት ጊዜ ትቶት የሚሄደው ሃብት ካለው ለወላጆቹና ለቅርብ ዘመዶቹ ፍትሃዊ ኑዛዜ

እንዲያስተላልፍ በናንተ ላይ ተደንግጓል። (ይህ ድንጋጌ) በጥንቁቆች ላይ በግዴታነት ፀንቷል።›› (አል በቀራህ 180)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ ﴾ البقرة: ١٨٣

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም ለነዚያ ከናንተ በፊት ለነበሩት (ሕዝቦች በግዴታነት) እንደተደነገገ ሁሉ በናንተም ላይ ተደንግጓል። ጥንቁቆች ትሆኑ ዘንድ።›› (አል በቀራህ 183)

﴿ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡقِتَالُ وَهُوَ كُرۡهٞ لَّكُمۡۖ وَعَسَىٰٓ أَن تَكۡرَهُواْ شَيۡـٔٗا وَهُوَ خَيۡرٞ لَّكُمۡۖ وَعَسَىٰٓ أَن تُحِبُّواْ شَيۡـٔٗا وَهُوَ شَرّٞ لَّكُمۡۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ٢١٦ ﴾ البقرة: ٢١٦

‹‹(እናንተ ሰዎች ሆይ! ከከሓዲያን ጋር) መፋለም፥ እናንተ እየጠላችሁት ተደነገገባችሁ። አንድ ነገር ጠልታችሁት ያ ነገር ለናንተ መልካም የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። አንድን ነገር ደግሞ ወዳችሁት ያ ነገር ለናንተ መጥፎ የሚሆንበት አጋጣሚ ይከሰታል። አላህ (የነገሮችን ፍጻሜ፥ በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚበጃችሁንና የሚጠቅማችሁን) ጠንቅቆ ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም።›› (አል በቀራህ 216)

በነዚህ አናቅጽ የሰፈሩ የግድያ ወንጀል ቅጣትን፣ ኑዛዜን፣ ጾምንና ውጊያን የሚመለከቱ ትእዛዛት በአማኞች ላይ ግድ የተደረጉ ናቸው። እነዚህን ትእዛዛት በመፈጸም አላህን ሊያመልኩ ግድ ሆኖባቸዋል።

የኢባዳ መስክ ከዚህም በጣም ይሰፋል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢ لَا شَرِيكَ لَهُۥۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرۡتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ١٦٣ ﴾ الأنعام: ١٦٢ - ١٦٣

“ስግደቴም፥ የማቀርበው መስዋእትም፥ ሕይወቴም፥ ሞቴም የዓለማት ጌታዬ የሆነው የአላህ ነው።” በልም፤ “(ለእርሱ) ተጋሪ የለውም።ይህን

እንድፈጽም ታዝዣለሁ። እኔ ከሙስሊሞች (ለአላህ ትእዛዝ ካደሩ ወገኖች) የመጀመሪያው ነኝ።" (በላቸውም)። (አል በአንዓም 162-163)

እኛ በተለምዶ የምናከናውናቸውን የእለት ከእለት ተግባራት ሳይቀር ያካትታል። አቡ ኡማማን በመጥቀስ ኢማም አህመድ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ፡- ባሪያ እኔን ከሚያመልክባቸው ነገሮች መካከል በላጩ ለኔ ታማኝ መሆኑ ነው፣ ብሏል።›› አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ጥሩ ነው። ጥሩ ነገርን እንጅ አይቀበልም። አላህ መልእክተኞችን ባዘዘበት ነገር አማኞችንም አዟል። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُلُ كُلُواْ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًاۖ إِنِّي بِمَا تَعۡمَلُونَ عَلِيمٞ ٥١ ﴾

"እናንተ መልዕክተኞች ሆይ! መል ካም ነገሮችን (ሁሉ) ተመገቡ። በጐ ሥራንም ሥሩ። እኔ የምትሠሩትን (ሁሉ) ዐዋቂ ነኝ።›› (አል መኡሚኑን 51)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُلُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقۡنَٰكُمۡ وَٱشۡكُرُواْ لِلَّهِ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ ١٧٢ ﴾ البقرة: ١٧٢

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከሰጠናችሁ ሲሳይ መልካም ነገሮችን ብቻ ተመገቡ። ለአላህ -እርሱን ብቻ የምታመልኩ እንደሆናችሁ- ተገቢውን ምስጋና አድርሱ።›› (አል በቀራህ 172)

ከዚያም ረዥም መንገድ የተጓዙ፣ ጸጉ የተንጨባረረ፣ አቧራ የለበሰ፣ ወደ ጌታውም፡- አምላኬ ሆይ፣ እያለ እጁን የሚዘረጋ አንድ ሰው አወሱ። ‹‹ምግቡ ሐራም፣ መጠጡ ሐራም፣ አልባሳቱ ሐራምና አካሉ በሐራም የተገነባ ሆኖ እያለ ዱዓው እንዴት ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል?›› አለም። (ሙስሊም)

ይህ ሐዲስ በስራ፣ በንግግርም ሆነ በእምነት ሐላል ነገሮችን ብቻ እንድንመርጥ ያነሳሳናል። አላህ በይዩልኝና በኩራት የተበከለን ስራ አይቀበልም። ከገንዘብም ሐላልን እንጅ አይቀበልም። አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፦

የሰው ልጅ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍሉ ምጽዋት አለበት። ጸሐይ በምትወጣበት በእያንዳንዱ ቀን ሁለት ሰዎችን በፍትህ መዳኘት ሶደቃ ነው። አንድን ሰው ከመጓጓዣው ማድረስህ ወይም እቃውን ማቀበልህ ሶደቃ ነው። ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድህ ሶደቃ ነው።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

አቡ ዘር ባስተላለፉት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ ‹‹ከናንተ ውስጥ አንዳችሁ ጾታዊ ግንኙነት መፈጸሙ ሶደቃ ነው።›› አሉ። ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ስጋዊ ስሜታችንን ስላረካን ምንዳ ይጻፍልናልን? ሲሉ ጠየቋቸው። ‹‹እስኪ ንገሩኝ፣ በሐራም አድርጋችሁት ቢሆን ኖሮ ወንጀል ይሆንባችሁ አልነበረምን? በሐላል ስታደርጉት ደግሞ ምንዳ ይጻፍላችኋል።›› ሲሉ መለሱ። (ሙስሊም)

ሙስሊም መላ ሕይወቱንና ጊዜውን ኢባዳ ማድረግ ይችላል። ይህም የሚሆነው በእያንዳንዱ በጎ እንቅስቃሴው የአላህን ውዴታ ሲነያ ነው። ይህ ሲሆን አካሉ በስራ ሲደክም የዋለ ሰራተኛ አላህን አምላኪ ይሆናል። እንቅልፍ አጥቶ ትምህርቱን ሲያጠና ያነጋ ተማሪ አላህን እያመለከ ነው። ተመራማሪ ምርምር ሲየደርግ አላህን እያመለከ ነው። ለልጆቿ እና ለባሏ ደስታና ረፍት ደፋ ቀና የምትል እንስት አላህን እያመለከች ነው።

ይህ ሲሆን ኢባዳ ለአላህ የመታዘዝና የመተናነስ፣ ለፈቃዱ የማደር እና የፍጹም ፍቅር ዳርቻ ይሆናል። ፍቅር፣ አቅም በፈቀደ መጠን የአላህን ዲን ለመርዳት የመስራትንና የማይነጥፍን የበጎ ስራ ስሜት ያቀጣጥላል። ሰውየው እንቅስቃሴና ረፍቱን፣ ስሜቱን እና ጉጉቱን ሁሉ እውነትን፣ ፍትህንና ዲኑን ለመርዳት ተግባር እንዲያውለው ያደርገዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱرۡكَعُواْ وَٱسۡجُدُواْ وَٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمۡ وَٱفۡعَلُواْ ٱلۡخَيۡرَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ٧٧ وَجَٰهِدُواْ فِي ٱللَّهِ حَقَّ جِهَادِهِۦۚ هُوَ ٱجۡتَبَىٰكُمۡ وَمَا جَعَلَ عَلَيۡكُمۡ فِي ٱلدِّينِ مِنۡ حَرَجٖۚ مِّلَّةَ أَبِيكُمۡ إِبۡرَٰهِيمَۚ هُوَ سَمَّىٰكُمُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ مِن قَبۡلُ وَفِي هَٰذَا لِيَكُونَ ٱلرَّسُولُ شَهِيدًا عَلَيۡكُمۡ وَتَكُونُواْ شُهَدَآءَ عَلَى ٱلنَّاسِۚ فَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱعۡتَصِمُواْ بِٱللَّهِ هُوَ مَوۡلَىٰكُمۡۖ فَنِعۡمَ ٱلۡمَوۡلَىٰ وَنِعۡمَ ٱلنَّصِيرُ ٧٨ ﴾ الحج: ٧٧ - ٧٨

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሩኩዕም ሱጁድም አድርጉ። ጌታችሁንም (በብቸኝነት) አምልኩ። መልካም ሥራም ሥሩ። በአላህ (መንገድ) ተገቢውን ትግል አድርጉ። እርሱ (ለዚህ ክብር ከሌ ሎች ሕዝቦች) እናንተን መርጧል። ከሃይማኖት ውስጥ የሚያስቸግር ነገር አላደረገም። (ይህ) የአባታችሁ የኢብራሂም ጐዳና ነው። እርሱ (አላህ) ከዚህ ቀደም (በሌሎች መጽሐፍት) ሙስሊሞች ብሎ ጠርቷችኋል። በዚህ (ቁርአን) ውስጥም እንዲሁ። መልዕክተኛው በናንተ ላይ መስካሪ፣ እናንተ ደግሞ በሰው ዘሮች ላይ መስካሪዎች ትሆኑ ዘንድ። ስለሆነም ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ። ዘካንም ስጡ። በአላህም ተጠበቁ። እርሱ (ብቸኛው) ጠባቂያችሁ ነውና። ጠባቂነቱ እጅግ የላቀ ነው! ረዳትነቱም እጅግ ያማረ ነው!›› (አል ሐጅ 77-78)

አላህ በዚህ አንቀጽ በመጀመሪያ በስግደት፣ ቀጥሎም በኢባዳ አዘዘ። ኢባዳ ከሶላት የሰፋ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ኢባዳ የግዴታ (ፈርድ) ነገሮችን ሁሉ ያካትታል። መስኩ ሰፍቶም የሰውን ልጅ እንቅስቃሴና ውስጣዊ ስሜት ሁሉም ያጠቃልላል።

ቀልብ ወደ አላህ ከዞረ የሰው ልጅ የሕይወት እንቅስቃስ ሁሉ፣ ከሕይወት ጸጋዎች የሚያገኛቸው ጣፋጭ ነገሮች ሁሉ ሳይቀሩ፣ የበጎ ስራ መዝገቡን የሚያወፍሩ ኢባዳዎች ይሁኑለታል።››[1]

የቀንና የሌሊት አደቦች፣ ሰውየው ምንጊዜም ከአላህ ጋር እንዳለ እንዲሰማው ያደርጉታል። ጠዋት ነቅቶ ማታ ተመልሶ እስኪተኛ ድረስ።

[1] አል ኢባዱ- ጀውሃሩሃ ወአሩቁሐ፣ አል ሸይኽ ሙሐመድ አብደላህ አል ጃጢብ (በማሳጠር)

ለምሳሌ ከእንቅልፉ ሲነቃ አላህን ያወሳል። የአብሮነት ስሜት ይሰማዋል። እንዲህ ይላል፦

‹‹ከገደለን በኋላ ሕያው ያደረገን አምላክ ምስጋና የድረሰው። መመለሻም ወደርሱው ነው።››

ልብሱን ሲለብስ፣ መሰታውት ሲያይ፣ ከቤቱ ሲወጣ፣ ወደ ገበያ ቦታ ሲገባና ሲወጣ ወዘተ ማታ ተመልሶ እስኪተኛ ድረስ የአላህ አብሮነት ለአፍታ ሳይለየው ይውላል። ይህን በተመለከተ የኢማም ነወዊን ‹‹አደቡል የውሚ ወለይላ›› እና የሸህ አቡበክር ጀዛኢሪን ‹‹ሚንሐጀል መስለም›› እንዲያነቡ ተጋብዘዋል።

በላጩ ኢባዳ

ኢባዳ በኢስላም እይታ ከላይ እንደተብራራው ሁለንተናዊ ከሆነ ከኢባዳዎች መካከል የትኛው በላጩ፣ ከአላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ፣ ደረጃውም ይበልጥ ከፍ ያለው ኢባዳ የትኛው ነው? ኢማም ቢን አልቀይም ‹‹መዳሪጁ ሳሊኪን›› በተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ በላጩ ኢባዳ እንደየ ወቅቱ እንደሚለያይ ጽፈዋል። እንዲህ ይሉናል፦

በላጩ ኢባዳ በየትኛውም ጊዜ አላህ የሚወደውንና ወቅቱ የሚጠይቀውን በጎ ተግባር መፈጸም ነው። በጅሃድ ወቅት በላጩ ኢባዳ ጅሃድ ይሆናል። ሱንና ዚክሮችን፣ የሌሊት ሶላቶችንና ሱንና ጾሞችን ሌላው ቀርቶ ፈርድ ኢባዳን ማሟላትን የሚያስቀር ቢሆንም እንኳ። እንግዳ በሚመጣ ጊዜ እንግዳውን ማስተናገድ እና ሱንና ኢባዳዎችን ትቶ እርሱን መንከባከብ በላጭ ኢባዳ ይሆናል። የባለቤትንና የቤተሰብን መብት ማድረስ ተገቢ በሚሆንበት ሰአትም እንደዚሁ። በሱህር ወቅት በላጩ ኢባዳ በሶላት፣ በቁርአን፣ በዱዓ፣ በዚክርና በኢስቲግፋር መጠመድ ይሆናል። በትምህርት ወቅት በላጩ ኢባዳ ተማሪውን በሚገባ ማስተማር፣ አላዋቂን ማሳወቅ ይሆናል። በአዛን ወቅት በላጩ ኢባዳ ሌሎች ኢባዳዎችን ትቶ ለሙአዚኑ ምላሽ መስጠት ይሆናል። በአምስት ወቅት ሶላቶች ጊዜ በላጩ ኢባዳ ሶላቶችን አሟልቶና አጣርቶ በወቅታቸው

መፈጸም ይሆናል። በዚህ ወቅት ወደመስጊድ መሄድም ተገቢ ነው። መስጊዱ ራቅ ካለ ምንዳው የበለጠ ይበረክታል። የተቸገረን መርዳት ግድ የሚሆንበት አጋጣሚ ሲፈጠር በላጩ ኢባዳ ሌሎች ሰናይ ተግባራትን ትቶ እሱን መርዳት ይሆናል። በቁርአን ወቅት ቁርአን መቅራት መልእክቱን ለመገንዘብና ለማስተንተን፣ አላህ የሚያናግርህ ያህል ተሰምቶህ ቀልብህን መሰብሰብና ትእዛዙን ለመፈጸም መወሰን በላጭ ኢባዳ ነው።

አረፋ ላይ በቆሙ ጊዜ በላጩ ኢባዳ በዱዓና በዚክር መመሰጥ ነው። አካልን በማድከም ከዚህ ተመስጦ የሚያቅብን ጾም መከልከልም ተገቢ ነው። በአስሩ የዙል ሂጃ ቀናት በላጩ ኢባዳ አምልኮንና ዚክርን፣ በተለይም ተክቢር፣ ተህሊል እና ተህሚድ ማብዛት ነው። በረመዳን የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በላጩ ኢባዳ ከሰዎች ጋር መቀላቀልን አቁሞ መስጊድ ውስጥ በመገለል ኢእቲካፍ ማድረግ ነው። ሙስሊም ወንድምህ በታመመ ወይም በሞተ ጊዜ በላጩ ኢባዳ እርሱን መጠየቅ፣ ጀናዛውን መሸኘት ይሆናል።››

በጥቅሉ በየትኛውም ጊዜ በላጩ ኢባዳ በዚያ ወቅት የአላህን ትእዛዝ ከምንም ነገር ማስቀደም፣ ወቅቱ የሚጠይቀውን ተግባርና ሐላፊነት መወጣት ነው። ኢብኑል ቀይም እንዲህ አይነት ሰዎችን ‹‹ያልተገደበ አምልኮ (ኢባዳ መጥለቃ) ባለቤቶች›› ይሏቸዋል። እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹የዚህ አይነት ኢባዳ ባለቤት ዓላማው የአላህን ውዴታ የትም ቢሆን መከተል ነው። የኢባዳ ምህዋሩ እርሱ ነው። በመሆኑም በተለያዩ የኢባዳ እርከኖች ውስጥ ያለ ገደብ ይንቀሳቀሳል። አንዱ እርከን በተገለጸለት ጊዜ ሌላኛው እስኪከሰትለት ድረስ ወደርሱ ይሄዳል። በርሱ ይጠመዳል። የጉዞ ባህሪው እስከ ፍጻሜው ይህን ይመስላል። አሊሞችን ስታይ ከነርሱ ጋር ታየዋለህ። አቢዶችን ስታይ ከነርሱ ጋር ታየዋለህ። ሙጃሂዶችን ስታይ ከነርሱ ጋር ታየዋለህ። ዛኪሮችን ስታይ ከነርሱ ጋር ታየዋለህ። በጎ ሰዎችን ስታይ ከነርሱ ጋር ታየዋለህ። ገደብ አልባ ባሪያ ማለት ይህ

ነው። ለአምልኮው ወሰን የለውም። በጎ ስራውን አንዳች ርእስ አይገድበውም። ለነፍሱ ሳይሆን ለአላህ ፈቃድና ፍላጎት ያድራል። ነፍስያው የምትወደውን ነገር ትቶ አምላኩን የሚያስደስትን በጎ ነገር ይፈጽማል። ‹አንተን ብቻ እናመልካለን፣ አንተን ብቻም እገዛ እንጠይቃለን›› የሚለው ቁርአናዊ መልእክት በእርግጥ የተተገበረው በዚህ ሰው ነው።

የአላህ ትእዛዝ በዞረበት ሁሉ ይዞራል። ልጓሙን ለርሱ አስረክቦ እርሱን ብቻ ይከተላል። ከገባበት ይገባል፣ ከወጣበት ይወጣል። እርሱን ያጸደቀውን ያጸድቃል፣ የጠላውን ይኮንናል። የትም ቦታ ቢያርፍ ጠቃሚ እንደሆነ ዝናብ ወይም ደግሞ ቅጠሏ እንኳ በከንቱ እንደማይወድቅ፣ ሁለነገሯ እሰኟ ሳይቀር እንደሚጠቅም የዘንባባ ተክል ማለት ነው። የአላህ ትእዛዝ ሲጣስ፣ ክልክሉ ሲደፈር ይቆጣል።››[1]

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የኢባዳን ትክክለኛና ሁለንተናዊ ትርጉም አብራራ።

2) ኢብን ተይሚያህ ስለኢባዳ ትርጉም ተጠይቀው ኢባዳ ማለት- - - - ሲሉ መልሰዋል። ባዶ ቦታውን ሙላ።

3) ኢባዳ መላ ሕይወትን የሚያካትት ጽንሰ ሐሳብ ነው። አብራራ

4) የኢባዳን የተለያዩ ገጽታዎች አብራራ

5) በኢስላም እይታ የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ ከላይ የተብራራውን ዓይነት ሁለንተናዊነት ካለው ከኢባዳዎች ሁሉ መካከል በላጩ፣ ከአላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጁና ደረጃውም ከፍ ያለው የትኛው ነው?

* * *

[1] መዳሪጀ አሳሊኪን ቢን አልቀይም ቅ 1

የኢባዳ ተቀባይነት መሰፈርቶች

ዓላማ

⇒ ተማሪው የኢባዳ ተቀባይነት መስፈርቶችን ማብራራት እንዲችል መርዳት፡፡

⇒ ለኢባዳ ተቀባይነት ሁለት መስፈርቶች ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም

1) ስራው ለአላህ ብቻ ሲባል መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2) አፈጻጸሙም አላህ በሸሪዓው ባስተማረው መልኩ ሊፈጸም ይገባል፡፡

የመጀመሪያውን መስፈርት በተመለከተ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ስራ የተባለ ሁሉ በኒያ ነው፡፡ ሁሉም ሰው የኒያውን ያገኛል፡፡ ስደቱ ለአላህና ለመልእክተኛው የሆነ ስደቱ ለአላህና ለመልእክተኛው ይሆናል፡፡ ስደቱ ሊያገኛት ላሰባት ዱንያ ወይም ሊያገባት ላሰባት እንስት ከሆነም ስደቱ ወደተሰደደበት ነገር ነው፡፡››

ይህ ሐዲስ የስራ ውስጣዊ መስፈርት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ለአላህ ተብሎ ያልተሰራ ስራ ሁሉ ምንዳ አያስገኝም፡፡ ተቀባይነትም የለውም፡፡ ሰእድ ቢን አቡ ወቃስን በመጥቀስ ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት ነቢዩ (ሶ.ወ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የአላህን ውዴታ በመሻት በምትሰጠው ምጽዋት፣ ከሚስትህ አፍ ላይ በምታደርገው ጉርሻ ሳይቀር ምንዳ ታገኛለህ፡፡››

ሁለተኛውን መስፈርት በተመለከተ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በዚህ በጉዳያችን ውስጥ የርሱ አካል ያልሆነን አዲስ ነገር የጨመረ ጭማሬው ውድቅ ነው፡፡›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

ይህ ደግሞ የስራ ውጫዊ መስፈርት ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ወደ አላህ መቃረቢያ ባላደረጉት ስራ ወደ አላህ የተቃረበ ስራው ከንቱ ነው፡፡

ተቀባይነት የለውም። ለምሳሌ ዳንስን ወይም ሙዚቃን ማዳመጥን ወደ አላህ መቃረቢያ አድርጎ የያዘ።

ቀደምት ደጋግ ሙስሊሞች (ሰለፉነሷሊሂን) በዚህ ረገድ አርአያ ይሆኑናል። ዘይድ አልኻሚ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በሁሉም ነገር ላይ ኒያ እንዲኖረኝ እፈለጋለሁ። በምግብና በመጠጥ ላይ ሳይቀር።››

ዳውድ ጧዒ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መልካም ንያ የበጎ ነገሮች ሁሉ መቋጠሪያ ውል ሆኖ አገኘሁት።››

ፉዳይል ቢን ኢያድ፡-

‹‹አላህ ከስራዎች መሐል ይበልጥ ንጹህና ትክክለኛውን እንጅ አይቀበልም።›› በማለት ተናገሩ። ‹‹ይበልጥ ንጹህና ትክክለኛ ማለት ምን ማለት ነው።› ተብለው ተጠየቁ። ‹‹ይበልጥ ንጹህ ማለት ለአላህ ሲባል ብቻ የተፈጸመ ሲሆን፣ ይበልጥ ትክክለኛ ማለት የአላህ ሸሪዓ በደነገገው መልክ የተፈጸመ ማለት ነው።›› ሲሉ መለሱ።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

የኢባዳ ተቀባይነት መስፈርቶችን አብራራ

* * *

የኢባዳ ክብደትና ፋይዳ

ዓላማዎች

1) ኢባዳ ለግለሰብ ያለውን ጠቀሜታ ማሳየት፣

2) ኢባዳ ለቤተሰብ ያለውን ፋይዳ መዘርዘር፣

3) ኢባዳ ለሕዝቡ ያለውን ጠቀሜታ ማብራራት።

ኢባዳ የሰው ልጅ ሕልውና ተልእኮ መሆኑንና መላ ሕይወትንና ሁሉንም የሐይማኖት መስኮች እንደሚያጠቃልል አውቀናል። ግና ለምን አላህን እናመልካለን? እርሱ ከኛም ሆነ ከአምልኳችን የተብቃቃ ሆኖ እያለ ለምን ኢባዳ ግዴታ አደረገብን? እርሱን ማምለካችን፣ ለርሱ ታዛዦች በመሆናችን እና ለፈቃዱ በማደራችን የሚጠቀመው ነገር ይኖር ይሆን? ወይስ ተጠቃሚዎቹ እኛ ፍጡራን ነን? ይህ ከሆነስ ከኢባዳ የምናገኘው ጥቅም ምንድን ነው? መልሱም፣ አላህ የሰዎች ኢባዳ አይጠቅመውም፣ አመጻቸውም አይጎዳውም። የአመስጋኞች ምስጋና ከንግስናው አንዳች ነገር አይጨምርለትም። የካህድያን ክህደትም ስልጣኑን አያጎድልበትም። እርሱ ሐብታም እኛ ደግሞ ድሆች ነን።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلۡفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ١٥ ﴾ فاطر: ١٥

‹‹የሰው ልጆች ሆይ! እናንተ ከአላህ ከጀዮች ናችሁ። አላህ ግን (ከማንም እገዛ) የተብቃቃና ምስጉን ነው።›› (ፋጢር 15)

ያዘዘን ነገር ጠቀሜታ እርሱን በእያንዳንዱ የሕይወት እስትንፋሳችን ቅጽበት ለምንፈልገው ለኛ እንጅ ለርሱ አይደለም። ፈጣሪ ከፍጡሩ እንዴት አንዳች ነገር ይከጅላል? አላህ በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ባሮቼ ሆይ፣ ትጎዱኝ ዘንድ አቅም የላችሁም። ትጠቅሙኝ ዘንድም አቅም የላችሁም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያዎቻችሁም የመጨረሻዎቻችሁም፣ ሰዎቻችሁም አጋንንቶቻችሁም ከመካከላችሁ ይበልጥ አላህን የሚፈራውን ሰው ልቦናን ቢይዙ ከስልጣኔ ቅንጣት

ታክል አይጨምሩልኝም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያዎቻችሁም የመጨረሻዎቻችሁም ሰዎቻችሁም ጋኔኖቻችሁም ከመሐከላችሁ ይበልጥ ወንጀለኛ የሆነውን ሰው ልቦና ቢይዙ ከስልጣኔ ቅንጣት ታክል አይቀንሱብኝም።›› (ሙስሊም)[1]

ሀ) የኢባዳ ግለሰባዊ ፋይዳ

አላህን ማምለክ በዚህች ዓለም ክብርን፣ በመጭውም ዓለም መዳን ን መጎናጸፍ ነው። ጠቀሜታው በሚከተሉት ነጥቦች ሊጠቃለል ይችላል፡-

1) ኢባዳ - የሰው ልጅ ለዚህ ተግባር በአላህ የመመረጡን ክብር ያጸናል፡- ሰማያት፣ ምድርና ተራራዎች ይህን ሐላፊነት ለመቀበል እምቢ ብለዋል። ፈርተውታልም። የሰው ልጅ ግን ተቀበለው።

﴿ إِنَّا عَرَضۡنَا ٱلۡأَمَانَةَ عَلَى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلۡجِبَالِ فَأَبَيۡنَ أَن يَحۡمِلۡنَهَا وَأَشۡفَقۡنَ مِنۡهَا وَحَمَلَهَا ٱلۡإِنسَٰنُۖ ﴾ الأحزاب: ٧٢

‹‹እኛ አደራን ለሰማያትም፣ ለምድርም፣ ለጋራዎችም አቀረብን። ሊሸከሙት አልፈቀዱም። ፈሩት። የሰው ልጅ ግን ተሸከመው። (ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱም) በዳይና አላዋቂ ሆነ።›› (አል አህዛብ 72)

አላህ የሰውን ልጅ በእጁ የፈጠረው፣ ከመንፈሱም የነፋበት፣ መላእክትንም ያሰገደለት ለዚሁ አላማ ነው። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَإِذَا سَوَّيۡتُهُۥ وَنَفَخۡتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُواْ لَهُۥ سَٰجِدِينَ ٢٩ ﴾ الحجر: ٢٩

“(ውብ አድርጌ) በቀረጽኩትና ከመንፈሴም በነፋሁበት ጊዜ ለርሱ ስገዱ።”(አል ሂጅር 29)

[1] አል ኢባዳ ፊል ኢስላም- ዶክተር ዩሱፍ ልቀረዷዊ

﴿ وَإِذۡ قَالَ رَبُّكَ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي جَاعِلٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ خَلِيفَةٗۖ قَالُوٓاْ أَتَجۡعَلُ فِيهَا مَن يُفۡسِدُ فِيهَا وَيَسۡفِكُ ٱلدِّمَآءَ وَنَحۡنُ نُسَبِّحُ بِحَمۡدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَۖ قَالَ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٣٠ ﴾ البقرة: ٣٠

‹‹ጌታህ ለመላእክት “እኔ በምድር ላይ ወኪል (ኸሊፋህ) ለመፍጠር አቅጃለሁ” ባላቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ፤ ለሕዝቦችህም ተርክላቸው።) “(አንተን በመወንጀል) ጥፋት የሚፈፅምን፥ ደሞችን (በግፍ) የሚያፈስን (ፍጡር) ከርሷ (ከምድር) ላይ ትፈጥራለህን? እኛ አንተን ከማመስገን ጋር ከጉድለት የምናጠራህ፥ የምናወድስህም ሆነን እያለ?” አሉት። “እናንተ የማታውቁትን ዐውቃለሁ” አላቸው።›› (አል በቀራህ 30)

﴿ وَإِذۡ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ أَبَىٰ وَٱسۡتَكۡبَرَ وَكَانَ مِنَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ٣٤ ﴾ البقرة: ٣٤

(ሙሐመድ ሆይ!) ለመላእክት “ለአደም ሰገዱ” ባልናቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ፤ ለሕዝቦችህም ተርክላቸው)። ሁሉም ሰገዱ፤ ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር። (እርሱ ግን) እምቢ አለ፤ ኮሰራም። (በዚህ እምቢተኝነቱ ሰበብ) ከከሓዲያን ተፈረጀ። (አል በቀራህ 34)

2) ኢባዳ ለመንፈስ ምግብ፣ ለቀልብ እርካታ ነው፡- የሰው ልጅ ማለት አካላዊ እሱነቱ አይደለም፡፡ አስፈልጎቱ በምግብና በመጠጥ የተገደበ አይደለም፡፡ የሰው ልጅ እውነተኛ ማንነት፣ ሰው የመባልን ክብር ያስሰጠው፣ በምድር ላይ ካሉ ፍጡራን ሁሉ የላቀ ያደረገው፣ የአላህ እስትንፋስ የሆነ ውስጣዊ ማንነቱ ነው፡

አካል በሕይወት ለመቆየትና ለማደግ ምግብና መጠጥ እንደሚያስፈልገው ሁሉ መንፈስም ሕያው ትሆንና ትጸዳ ዘንድ ወደ አላህ የመቃረብና እርሱን የመማጸን (የኢባዳ) ምግብ ያስፈልጋታል፡፡ኢባዳ ለመንፈስ ምግብ፣ የማይነጥፍ የሐይል ምንጭ ይሆናታል፡፡

ቀልብ ምንጊዜም አላህን ይሻል። እርሱን የመከጀል ጥልቅ ስሜት አለው። ይህ ስሜቱ የመሠረታዊ ስሪቱ አካል ሲሆን፣ የሕልውና አምላክ ከሆነው ከአላህ ጋር መልካም ግንኙነት ከመፍጠሩ ውጭ ይህን ስሜት የሚያረካ፣ ረሃቡን የሚያስታግስ፣ ክፍተቱን ሊሞላ የሚችል ሌላ ነገር የለም። ኢባዳ በትክክል ሲፈጸም የሚጫወተው ሚና ይህ ነው። ኢብን ተይሚያህ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ቀልብ በሁለት መስመሮች አላህን ይከጅላል። በኢባዳ እና በርሱ በመታገዝ መስመር።››

﴿إِيَّاكَ نَعۡبُدُ وَإِيَّاكَ نَسۡتَعِينُ ۝٥﴾ الفاتحة: ٥

‹‹አንተን ብቻ እናመልካለን። አንተን ብቻም እገዛ እንጠይቃለን።›› (አል ፋቲሐ 5)

ቀልብ አምላኩን በብቸኝነት በማምለክ፣ እርሱን በመውደድ፣ ወደርሱ በመመለስ ብቻ እንጅ በሌላ ነገር አይስተካከልም፣ አይድንም፣ አይደሰትም፣ ለዛና ጣእም አያገኝም፣ አይሰክንም፣ አይረካም። ስጋዊ ደስታን ሊሰማ የሚችሉ ነገሮችን ሁሉ ቢያገኝ እንኳ እርካታና ስክነት አይኖረውም። ምክንያቱም አምላክ፣ ተፈቃሪ እና የሚከጅል የሆነን አላህን በተፈጥሮው ይፈልጋል። እርሱን ሲያገኝ ደስታን ያገኛል። ሲያመልከው ይረካል። ወደርሱ ሲመለስ ይረጋል። ይሰክናል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ አላህ በሚያደርግለት እገዛ ብቻ ነው። ይህን ጸጋ እንዲያገኝ የሚያስችለው አላህ ብቻ ነው። ስለዚህም ሁሌም፦ ‹‹አንተን በቻ እናመልካለን። የአንተን እገዛ ብቻም እንሻለን።›› የሚለውን እውነታ ይከጅላል።

አንድ ደካማ የአላህ ባሪያ የሚሰማህን ውስጣዊ እርካታ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፦

‹‹የጀነት ሰዎች አሁን ባለሁበት ሁኔታ ውስጥ ከሆኑ ኑሯቸው ጥሩ ነው የምልበት ጊዜ አልፎ አልፎ ይከሰታል።››

ወደ አላህ በተቃረቡ ጊዜ የሚሰማቸውን የእርካታ ስሜት መግለጻቸው ነው። ሌላ ደግ ሰው ደግሞ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ዝንጉዎች አሳዛኝ ናቸው። የዚህችን ዓለም እጅግ ጣፋጭ ጸጋ ሳይቀምሱ ዓለምን ተሰናበቱ።››

‹‹እርሱ ምንድን ነው›?› ተብለው ሲጠየቁም፡- ‹‹አላህን መውደድና በአብሮነቱ መደሰት›› ሲሉ መለሱ።

ሌላኛውም እንዲህ አሉ፡-

‹‹ንጉሳንና ልጆቻቸው እኛ የምንገኝበትን እርካታ ቢያውቁ ኖሮ በሰይፍ በነጠቁን ነበር።››

ይህ የሚነግሩን የእምነትን ለዛ ነው። ይህ ለዛ ከልቦና ላይ ሲገኝ ባለቤቱ ኢባዳን ትእዛዝን ከመፈጸም መቁጠሩን ያቆማል። ይልቁንም አላህን በማምለክ፣ በመታዘዝና የርሱን ውዴታ በመሻት ፍጹም እርካታን ይጎናጸፋል። በምድራዊ ሐብት የተንበሸበሹ ወገኖች የማይሰማቸው ውስጣዊ ደስታ ይሰማዋል።

3) ኢባዳ የነጻነት ጎዳና ነው፡- አላህን ብቻ ማምለክ ነጻነት ነው። የእውነተኛ ሰብአዊ ክብር መንገድም ነው። ቀልብን ከፍጡራን ባርነት፣ ከአላህ ውጭ ለሌላ አካል ከመንበርከክ ውርደት የሚታደገውም እርሱ ብቻ ነው። ቀልብ የሚያመልከው አካል ይፈልጋል። በዚያ አካል መንጠልጠልን፣ እርሱን ለማስደሰት መስራትን ይሻል። እናም አላህን በብቸኝነት ካላመለከ ሌሎች አካሎችን ማምለኩ አይቀሬ ነው። አላህን ብቻ በሚያመልክና ሌላን አካል አምላኩ ባደረገ ሰው መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት አለ፡-

﴿ ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا رَّجُلٗا فِيهِ شُرَكَآءُ مُتَشَٰكِسُونَ وَرَجُلٗا سَلَمٗا لِّرَجُلٍ هَلۡ يَسۡتَوِيَانِ مَثَلٗاۚ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٩ ﴾ الزمر: ٢٩

‹‹አላህ፥ እርስ በርስ ለማይግባቡ በርካታ ጌቶች ያደረን ባሪያና ለአንድ ጌታ ብቻ ያደረን ባሪያ በምሳሌነት አቀረበ። እነኝህ ሁለቱ እኩል

ናቸውን? ምስጋና ለአላህ ይሁን። ግና ብዙዎቹ (እውነትን) አያውቁም።›› *(አል ዙመር 29)*

መንገዱ ሁለት ብቻ ነው። ሦስተኛ አማራጭ የለም። አንድም አላህን ያለ ተጋሪ በብቸኝነት ማምለክ፤ አለያም የገንዘብ፣ የስልጣን ወይም የመቃብሮችና የዶሪሆች ባሪያ መሆን። ቀልብ ከፍጡራን ባርነት ነጻ ሊሆን የሚችለው አላህን ብቻ ሲያመልክ ከርሱ ውጭ ሌላን አካል ማምለክ ሲያቆም፣ በርሱ ብቻ ሲታገዙ፣ በርሱ ብቻ ሲመካ፣ አላህን በሚደስደስተው ነገር ብቻ ሲደሰት፣ እርሱን በሚያስከፋው ነገር ሲከፋ፣ የርሱን ወዳጆች ሲወዳጁ፣ ጠላቶቹን ሲጠላ፣ ለአላህ ብቻ ሲወድ፣ ለአላህ ብቻም ሲጠላ፣ መስጠቱም መንፈጉም ለአላህ ብቻ ሲሆን ነው።

4) ኢባዳ ለመጭው ዓለም ደስታና ስኬት መሠረት ነው፡- የዚህች ዓለም ሕይወት አጠረም ረዘመ ግብ አይደለም። የሰው ልጅ ሕይወትና ፍጻሜ በርሱ አይጠናቀቅም። ዱንያ ወደ ዘልዓለማዊው አገር መሸጋገሪያ እርከን ናት። የሰው ልጅ የተፈጠረው ለዱንያ ሳይሆን ለአኼራ ነው። በዚህች ዓለም የማኖረው ለመጭው ዓለም ለመዘጋጀት ነው።

በዚህች ዓለም ሕይወት ውስጥ አንድ ሰው የላቀ ቦታ ከከጀለ ብርቱ ጥረት ማድረግ፣ ፈተናዎችን ማለፍ ይጠበቅበታል። ለአጭሩ ሕይወታችን ይህን ያህል መልፋትና መፈተን ካለብን ለዘልዓለማዊ ሕይወትስ?

የሰው ልጅ የመጭውን ዓለም ጸጋና ድሎት፣ የአላህን ፍቅርና እርሱን የማየትን እድል እንዲሁ ያለ ልፋትና ያለ ፈተና፣ ያለ ጥረትና ያለ ስራ ለማግኘት ይከጅላልን? ታታሪዎች እና ሰነፎች፣ በጎዎችና ክፉዎች እኩል ይሆናሉን? በፍጹም! በአላህ ፍትህ እኩል አይደሉም። ስኬታማ ማለት ከእሳት ድኖ ጀነት የገባ ነው፡-

﴿ كُلُّ نَفۡسٖ ذَآئِقَةُ ٱلۡمَوۡتِۗ وَإِنَّمَا تُوَفَّوۡنَ أُجُورَكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۖ فَمَن زُحۡزِحَ عَنِ ٱلنَّارِ وَأُدۡخِلَ ٱلۡجَنَّةَ فَقَدۡ فَازَۗ وَمَا ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَآ إِلَّا مَتَٰعُ ٱلۡغُرُورِ ١٨٥ ﴾

‹‹እያንዳንዷ ነፍስ ሞትን ቀማሽ ናት። የሥራ ዋጋችሁን የምትሰጡት የትንሳኤ ዕለት ነው። ከእሳት እንዲርቅና ገነት እንዲገባ የተደረገ በእርግጥም ስኬታማ ሆኗል። የዚህች ዓለም ሕይወት መታለያ እንጂ ሌላ አይደለችም።›› (ዓሊ ዒምራን 185)

5) ነፍስን መግራት እና ስነ ምግባርን ማስተካከል፦ ነፍስን ማስተካከልና መግራት የኢባዳ ፍሬ እንጅ አላማ አይደለም። የኢባዳ ዓላማ የአለማት ጌታ የሆነውን አላህን ማምለክ፣ ለርሱ ታዛዥነትን መግለጽ ነው። ሶላት፣ ጾም፣ ዘካ ሐጅ፣ ቁርአን መቅራት፣ ዚክር፣ ዱዓ፣ ኢስቲግፋር፣ ሸሪዓውን መከተል፣ የሐራምና የሐላል ወሰኑን መጠበቅ እና መሰል ኢባዳዎች በራሳቸው ግቦች ሲሆኑ፣ በትክክል ከተፈጸሙ እግረ መንገዳቸውን ነፍስን ያስተካክላሉ። ባህሪን ይገራሉ። ሶላት እየሰገዱ፣ ተገቢ ያልሆኑ ተግባራትን ስለሚፈጽሙ ሰዎች የአላህ መልእክተኛ ተጠይቀው የሰጡት መልስ ይህንኑ ያሳያል፦

‹ሶላታቻው ታቅባቸዋለች።›

ስለዚህም የኢባዳ ዋነኛ ዓላማ ለአላህ ከፍጹም ፍቅር ጋር መተናነስ ነው። እንዲህ ያለው ሰው አላህ ይዘንለት፦

‹የኢባዳ ዓይነተኛ ባህሪ ከትርጉሙ ላይ ሳያተኩሩ ማምለክ ብቻ ነው።›

ቁርአን ውስጥ የአማኞች ባህሪ ኢባዳንና መልካም ስነ ምግባርን አዋህዶ የያዘ ሆኖ እናገኛዋለን። ተከታዩን መልእክት እናንብብ፦

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ٢ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنِ ٱللَّغۡوِ مُعۡرِضُونَ ٣ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِلزَّكَوٰةِ فَٰعِلُونَ ٤ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِفُرُوجِهِمۡ حَٰفِظُونَ ٥ إِلَّا عَلَىٰٓ أَزۡوَٰجِهِمۡ أَوۡ مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُهُمۡ فَإِنَّهُمۡ غَيۡرُ مَلُومِينَ ٦ فَمَنِ ٱبۡتَغَىٰ وَرَآءَ ذَٰلِكَ

فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْعَادُونَ ﴿٧﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ لِأَمَٰنَٰتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَٰعُونَ ﴿٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَوَٰتِهِمْ يُحَافِظُونَ ﴿٩﴾ ﴾ المؤمنون: ١ – ٩

አማኞች በእርግጥ ስኬታማ ሆኑ።እነዚያ ሶላታቸውን በፍፁም ተመስጦ የሚፈጽሙት፤እነዚያ ከውድቅ ንግግር የራቁት፤እነዚያ ዘካን (ሳያንዷሉ) የሚሰጡትእነዚያ ብልቶቻቸውን የሚጠብቁት፥ከሚስቶቻቸው ወይም በሥሮቻቸው ካሉ (የሴት አገልጋዮቻቸው) ጋር ካልሆነ በቀር። (ከነርሱ ጋር ሕጋዊ የሆነ ወሲብ በመፈፀማቸውስ) ተወቃሾች አይሆኑም።ግና (ለወሲብ ስሜታቸው) ከዚህ ውጭ ሌላን መንገድ የከጀሉ እነርሱ ወሰን አላፊዎች ናቸው።እነዚያ አደራዎቻቸውንም ቃልኪዳ ኖቻቸውንም ጠባቂዎች የሆኑት፤እነዚያ ሶላቶቻቸውን ወቅታቸውን ጠብቀው የሚሰግዱት፤

አላህ በመጀመሪያ የጠቀሰው ባህሪያቸው በሶላት ውስጥ ተመስጦ (ኹሹእ) ሲሆን፣ መጨረሻ የተጠቀሰው ባህሪያቸው ደግሞ ሶላትን ደንቡን ጠብቀው መስገዳቸው ነው። በነዚህ መካከል ሌሎች ኢባዳዎች እና በጎ ስነ ምግባሮች ተጠቅሰዋል።

በአልመዓሪጅ ምእራፍ ውስጥም የሚከተለው ተጠቅሷል፡-

﴿ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ خُلِقَ هَلُوعًا ﴿١٩﴾ إِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ جَزُوعًا ﴿٢٠﴾ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلْخَيْرُ مَنُوعًا ﴿٢١﴾ إِلَّا ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٢٢﴾ ٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ دَآئِمُونَ ﴿٢٣﴾ وَٱلَّذِينَ فِىٓ أَمْوَٰلِهِمْ حَقٌّ مَّعْلُومٌ ﴿٢٤﴾ لِّلسَّآئِلِ وَٱلْمَحْرُومِ ﴿٢٥﴾ وَٱلَّذِينَ يُصَدِّقُونَ بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٢٦﴾ وَٱلَّذِينَ هُم مِّنْ عَذَابِ رَبِّهِم مُّشْفِقُونَ ﴿٢٧﴾ إِنَّ عَذَابَ رَبِّهِمْ غَيْرُ مَأْمُونٍ ﴿٢٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ لِفُرُوجِهِمْ حَٰفِظُونَ ﴿٢٩﴾ إِلَّا عَلَىٰٓ أَزْوَٰجِهِمْ أَوْ مَا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُهُمْ فَإِنَّهُمْ غَيْرُ مَلُومِينَ ﴿٣٠﴾ فَمَنِ ٱبْتَغَىٰ وَرَآءَ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْعَادُونَ ﴿٣١﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ لِأَمَٰنَٰتِهِمْ وَعَهْدِهِمْ رَٰعُونَ ﴿٣٢﴾ وَٱلَّذِينَ هُم بِشَهَٰدَٰتِهِمْ قَآئِمُونَ ﴿٣٣﴾ وَٱلَّذِينَ هُمْ عَلَىٰ صَلَاتِهِمْ يُحَافِظُونَ ﴿٣٤﴾ ﴾ المعارج: ١٩ - ٣٤

‹‹የሰው ልጅ ትዕግስት አልባ ሆኖ ተፈጠረ፤ ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜ የሚበሳጭ፥ መልካም ነገር ባገኘው፥ (የሲሳይ በር በተከፈተለት) ጊዜ (የባለመብቶችን ድርሻ) ከልካይ (ሆኖኖ ተፈጠረ)። ሰጋጆች ሲቀሩ፤ እነዚያ በሶላታቸው ላይ ዘውታሪዎች የሆኑት፤ እነዚያ በገንዘቦቻቸው ላይ የታወቀ ድርሻ ያለባቸው የሆኑት - ለሚለምኑና ከመለመን ለታቀቡ (ችግረኞች የሚሰጥ)። እነዚያ በፍርዱ ቀን የሚያምኑ

የሆኑት። እነዚያ እነርሱ የጌታቸውን ቅጣት በእጅጉ የሚፈሩት። የጌታቸው ቅጣት የማይታመን ነውና። እነዚያ እነርሱ ብልቶቻቸውን የሚጠብቁት፤ ከሚስቶቻቸውና በቁጥጥራቸው ሥር ካሉ (ባሮች) ጋር ሲቀር፤ እነርሱ (ከነኝህ ጋር በሚፈጽሙት ግንኙነት) የሚወቀሱ አይደሉም። ከዚህ (ከሚስቶቻቸውና ከባሮቻቸው) ሌላ የሚሹት፥ እነርሱ ድንበር አላፊዎች ናቸው። እነዚያ እነርሱ አደራቸውንና ቃል ኪዳናቸውን የሚጠብቁት፤ እነዚያ እነርሱ በምስክርነቶቻቸው ላይ የፀኑ (በሐቅ የሚመሰክሩ) የሆኑት። እነዚያ እነርሱ ሶላታቸውን የሚጠብቁ የሆኑት (ሰጋጆች ሲቀሩ)።›› (አል መዓሪጅ 19-34)

እዚህም ላይ በሶላት ጀምሮ በሶላት አጠናቀቀ። በመሐል ላይ በመጭው ዓለም ማመንን፣ የአላህን ቅጣት መፍራትንና ሌሎች የመልካም ስነ ምግባር መገለጫዎችን ዘከረ። ቁርአን አንዳንድ ጊዜ የኢባዳን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የስነ ምግባርን ገጽታዎች ያነሳል። አልዛሪያት ምእራፍ ውስጥ አላህ እንዲህ ይላል፦

﴿ كَانُواْ قَلِيلٗا مِّنَ ٱلَّيۡلِ مَا يَهۡجَعُونَ ١٧ وَبِٱلۡأَسۡحَارِ هُمۡ يَسۡتَغۡفِرُونَ ١٨ وَفِيٓ أَمۡوَٰلِهِمۡ حَقّٞ لِّلسَّآئِلِ وَٱلۡمَحۡرُومِ ١٩ ﴾ الذاريات: ١٧ - ١٩

‹‹ከሌሊቱ የሚተኙት ጥቂትን ብቻ ነበር። ከሌሊቱ የመጨረሻ ወቅቶች ላይ (አላህን) ምሕረት ይማፀናሉ። ለማኞችና (ከልመና) የተቆጠቡ ደሆች ከገንዘቦቻቸው ድርሻ አላቸው።›› (አል ዛሪያት 17-19)

አል ረእድ ምእራፍ ውስጥ ደግሞ እንዲህ ይላል፦

﴿ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩ ٱلَّذِينَ يُوفُونَ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ وَلَا يَنقُضُونَ ٱلۡمِيثَٰقَ ٢٠ وَٱلَّذِينَ يَصِلُونَ مَآ أَمَرَ ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ وَيَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ وَيَخَافُونَ سُوٓءَ ٱلۡحِسَابِ ٢١ وَٱلَّذِينَ صَبَرُواْ ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِمۡ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنفَقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ سِرّٗا وَعَلَانِيَةٗ وَيَدۡرَءُونَ بِٱلۡحَسَنَةِ ٱلسَّيِّئَةَ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ٢٢ ﴾ الرعد: ١٩ - ٢٢

‹‹ከጌታህ የተወረደልህ (መልዕክት) እውነት መሆኑን የሚያውቅ፥ እንደዚያ እውር እንደሆነ ነውን? የሚገሰፁት አስተዋዮች ብቻ ናቸው፥

እነዚያ ለአላህ የገቡትን ቃልኪዳን የሚሞሉ፥ ቃላቸውንም የማያፈርሱ የሆኑት፤ እነዚያ አላህ እንዲቀጠል ያዘዘውን የሚቀጥሉት፥ (የ)ጌታቸውንም (ትእዛዝ) የሚያከብሩት፥ (የመጭውን ዓለም) የከፋ ምርመራም የሚፈሩት፤ የአላህን ፍቅርና ውዴታ በመሻት የሚታገሱት፥ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱት፥ ከሰጠናቸውም ሲሳይ በምስጢርም በይፋም የሚመፀውቱት፥ ክፉን በበጐ የሚመልሱት፥ እነዚህ በመጭው ዓለም (መልካም) ፍጻሜ አላቸው።›› *(አል ረዕድ 19-22)*

በእርግጥ ከላይ የተወሱት አብዛኛዎቹ ባህሪያት ዓለማዊ ሳይሆን መለኮታዊ ማለትም የኢባዳ እና አላህን የመፍራት ቃና ያላቸው ናቸው። መአሚኖች የአላህን ቃል ይሞላሉ። አላህ እንዲቀጠል ያዘዘውን ይቀጥላሉ። የአላህን ውዴታ በመሻትም ይታገሳሉ።

የመአሚን ኢባዳ የስነ ምግባሩ አካል፣ ስነ ምግባሩም የኢባዳው አካል ናቸው። ኢባዳው ስነ ምግባር ነው። ምክንያቱም ለአላህ ስለበጎ ውለታው ጥሩ መመለስ፣ ስለውለታው ማመስገን፣ ለበጎ አድራጎቱ እውቅና መስጠት፣ መከበር ያለበትን አካል ማክበር ነው። እነዚህ ደግሞ የመልካም ስነ ምግባር መገለጫዎች ናቸው። ይህም በመሆኑ አላህ መአሚኖችን በበጎ ባህሪያት ይገልጻቸዋል። ለምሳሌ፦

﴿ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ صَدَقُواْۖ ﴾ البقرة: ١٧٧

‹‹ (በእምነታቸው) እውነተኞች፣ ጥንቁቆችም እነዚህ (ከላይ የተወሱ ድንቅ ባሕሪያት ባለቤቶች ብቻ) ናቸው።›› (አል በቀራህ 177)

﴿ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ ١٥ ﴾ الحجرات: ١٥

‹‹ እውነተኞቹ እነርሱ ብቻ ናቸው።›› (አል ሁጁራት 15)

የመአሚን ስነ ምግባር ኢባዳ ነው። ምክንያቱም መነሻቸው በአላህ ማመን፣ የሕልውናቸው መሠረት የመጭውን ዓለም መኖር መቀበል፣

ዓላማቸው የአላህን ውዴታ እና ምንዳ መሻት የሆኑ አምላካዊ ስነ ምግባሮች ናቸውና።

መእሚን እውነት ይናገራል። አደራውን ያደርሳል። ቃል ኪዳኑን ይሞላል፡ በመከራ ጊዜ ይታገሳል። የተቸገረን ይረዳል። ደካማን ይደግፋል፣ ለትንሽ ያዝናል። ትልቅን ያከብራል። ውሎው መልካም እንዲሆን ይጥራል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው የአላህን

ውዴታና ምንዳ በመከጀል ነው፡-

﴿ وَيُطۡعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسۡكِينٗا وَيَتِيمٗا وَأَسِيرًا ٨ إِنَّمَا نُطۡعِمُكُمۡ لِوَجۡهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمۡ جَزَآءٗ وَلَا شُكُورًا ٩ إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوۡمًا عَبُوسٗا قَمۡطَرِيرٗا ١٠ ﴾ الإنسان: ٨ - ١٠

‹‹ምግብን፥ ለነርሱ እያስፈለጋቸው፥ ለችግረኛ፣ ለሙት ልጅና ለምርኮኛ ይመግባሉ፤ "የምናበላችሁ የአላህን ውዴታ በመሻት ነው። ከናንተ (ለውለታችን) ምላሽም ሆነ ምስጋና አንሻም። "ከጌታችን ዘንድ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን እንፈራለን" (በማለት)።›› (አል ኢንሳን 8-10)

የመእሚን ስነ ምግባር ኢባዳ የሆነበት ሌላው ምክንያት የጥሩና የመጥፎ፣ የበጎና የክፉ መለኪያው፣ የድርጊቶቹ መነሻ የአላህ ትእዛዝና ፍኖት ነው። አላህ ያዘዘው ነገር ሁሉ መልካም ሲሆን፣ የከለከለው ሁሉ ደግሞ መጥፎ እና ውርደት ነው። ሕሊና ብቻውን ከስህተት የራቀ፣ አእምሮ ብቻውን ከግድፈት የተጠበቀ አይደለም። ባሕልና ልምድም ተለዋዋጭ ነገር ናቸው። ስለዚህ መእሚን የማይስት፣ የማይለወጥ፣ የማይበድል የሆነውን የአላህን ውሳኔ የስነ ምግባር መስፈርቱ አደረገ።

﴿ وَمَنۡ أَحۡسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكۡمٗا لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ٥٠ ﴾ المائدة: ٥٠

‹‹ጽኑ እምነት ላላቸው ሰዎች በፍርድ ከአላህ የተሻለ ማን ነው?›› (አል ማኢዳህ 50)

ለ) የኢባዳ ቤተሰባዊ ጠቀሜታ፡-

አላህን ማምለክ ለዚህችም ሆነ ለመጭው ዓለም፣ ለግለሰባዊ ሐሴትና ስኬት ጠቃሚ መሆኑን አብራርተናል። ቤተሰብ የሕብረተሰብ መነሻና የግለሰብ እነጻ ማእከል መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አኳያ የዓለማት ጌታ የሆነውን አላህን በብቸኝነት ማምለክ ፋይዳው ጎልቶ የሚታይበት ቦታ ቤተሰብ ነው። ምክንያቱም ኢባዳ ለቤተሰቡ አባላት አንድ ዓላማ ያጎናጽፋል። እርሱም የአላህን ግዴታና ምንዳ መሻት ሲሆን ተከታዩ የአላህ ቃል ሁሉንም ይገዛል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ وَأَهۡلِيكُمۡ نَارٗا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُ عَلَيۡهَا مَلَٰٓئِكَةٌ غِلَاظٞ شِدَادٞ لَّا يَعۡصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمۡ وَيَفۡعَلُونَ مَا يُؤۡمَرُونَ ٦ ﴾ التحريم: ٦

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንም ቤተሰቦቻችሁንም መቀጣጠያዋ ሰዎች እና ድንጋይዎች ከሆነች እሳት ጠብቁ። በርሷ ላይ ጨካኞችና ኃይለኞች የሆኑ መላእክት ተመድበውባታል። አላህን፥ ያዘዛቸውን ባለመፈፀም አይወነጅሉም። የታዘዙትን (በትክክል) ይፈጽማሉ።›› (አል ተህሪም 6)

በቤት ውስጥ ተመሳሳይ ዓላማ ሲኖር ሁሉም አባላቱ አንድ ሐሳብ ይኖራቸዋል። ለዚህ ዓላማ ሁሉም ይሰራሉ። መፈክራቸውም ይህ ይሆናል፣

﴿ وَعَجِلۡتُ إِلَيۡكَ رَبِّ لِتَرۡضَىٰ ٨٤ ﴾ طه: ٨٤

‹‹ ጌታዬ ሆይ! ትደሰት ዘንድ ወዳንተ ቸኮልኩ።” አለ።(ጧሃ 84)

ዓላማ ሲገናኝ፣ የሐሳብና የጥረት አቅጣጫ አንድ ዓይነት ሲሆን ቤተሰቡ ልዩ ድባብ ይላበሳል። ሚስት ባሏን መንከባከቧ፣ በሐላል ነገርም መታዘዟ፣ ወደ ሐራም እንዳያይ ለመጠበቅ ለርሱ መዋቧ፣ ልጆቹን በአግባቡ ለማሳደግ መልፋቷ ኢባዳ ይሆናል። ባልም እንደዚሁ ቤተሰቡን ሲንከባከብ፣ ልጆቹን በአግቡቡ ሲያሳድግ አላህ ሐላፊነት ያሸከመውና

ወደፊትም የሚተሳሰበውን ሥራ ሁሉ ሲያከናውን ኢባዳ እያደረገ ነው። ልጆችም ወላጆቻቸውን ሲታዘዙ፣ ሲንከባከቡ፣ እነርሱን ለማገልገል ሲደክሙ፣ ዝምድናን ለመቀጠል ሲተጉ፣ ሽሪዓው ያዘዛቸውን ሌሎች ተግባራት ሲያከናውኑ ኢባዳ እያደረጉ ነው።

የቤተሰቡ አባላት ንያቸውን ሳስተካከሉ በነዚህ ሁሉ በጎ ተግባራት ፈላህን ያመልካሉ። ምንዳም ያገኛሉ። ሁሉም አባላቱ አላህን ሰመታዘዝ፣ ወደርሱ ለመቃረብ የሚተጉበትን በዓይነ ሕሊናችን እንመልከት። ከአኼራ በፊት በዱንያ ለዚህ ቤት አላህ የሚያደርግለትን ጥበቃ፣ የሚውለውን ስኬት፣ የሚያሰፍንበትን የኢባዳ በረካ እናስብ።

አዛን ሲደመጥ አባትና ልጆች ወደ መስጊድ ይሮጣሉ። እናት እና ሴት ልጆቿ በቤት ውስጥ ለመስገድ ይጣደፋሉ። ባልና ሚስት ይመካከራሉ። ሚስት የባሏን ምክር በሰፊ ልቦና ትቀበላለች። ባልም የሚስቱን ምክር በትህትና ያስተናግዳል። ተመሳሳይ ግብና ለዚህ ግብ ብቻ መስራት ስሜትን አንድ ያደርጋል። ደስታና ሐዘንን ይጋራሉ። ለነገሮች ያላቸው እይታ ይመሳሰላል። ከሌሎች ቤተሰቦችና ግለሰቦች ጋር ያላቸው ቅርበት ወይም ርቀት ሌሎቹ ለአላህ ካላቸው ቅርበት እና ርቀት አኳያ ይወሰናል። ወጭ የሚያወጡት ወይም የሚነፍጉት የአላህን ውዴታ ወይም መጥላት ታሳቢ አድርገው ነው። ባል ቤቱን ሐላፊነት እና አደራ አድርጎ ያየዋል። በቂያማ ቀን ከአላህ ፊት ስለቤቱ፣ ስለ ሚስቱ፣ ስለ ልጆቹ እንደሚጠየቅ ያውቃል። ሚስትና ልጆችም የአላህን ውዴታ ለማግኘት ከአባወራው ጋር ይተባበራሉ። እናም ቤተሰቡ እርጋታና እዝነት፣ ፍቅርና ስክነት የሰፈነበት ይሆናል።

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا لِّتَسْكُنُوٓا۟ إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٢١﴾ ﴾ الروم: ٢١

‹‹ከራሳችሁም የሆነችን ተጣማሪ (ትረኩባት ዘንድ) መፍጠሩ፥ በመካከላችሁም ፍቅርንና መተዛዘንን ማድረጉ ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ (ለሚያስተነትኑ ሰዎች) ተአምራት አለ።›› (ሱል ሩም 21)

﴿ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَمۡ يَلۡبِسُوٓاْ إِيمَٰنَهُم بِظُلۡمٍ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلۡأَمۡنُ وَهُم مُّهۡتَدُونَ ٨٢﴾

“እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል ያልበከሉት ሰላም የነርሱ ብቻ ነው።” ቅኑን ጉዳና የተመሩትም እነርሱ ብቻ ናቸው።” (አላቸውም)።››› (አል አንዓም 82)

የኢባዳ ማሕበረሰባዊ ፋይዳ

አባላቱ በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃ አላህን በአግባቡ ለማምለክ የሚተጉበት ማሕበረሰብ አላህን የሚያመልክ፣ ተልእኮው ራሱን የአላህ ተገዥ ማድረግ መሆኑን የተረዳ፣ የአላህን መለኮታዊ መልእክት በጎ ፍሬዎች የሚያጣጥም ማሕበረሰብ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ከዚህ መለኮታዊ መልእክት ፍሬዎች መካከል ነጻነት፣ እኩልነት፣ ወንድማማችነትና ሰላም በዋነኛነት ተጠቃሾች ናቸው።

ነጻነት

ከመስጊድ ውስጥ ከሚሰግድ ሰው የበለጠ ነጻ የለም። ከአላህ ውጭ ለሌላ አካል ባሪያ ከመሆን ነጻ ሆኗል። አላህን በብቸኝነት ያለ ተጋሪ ያመልካል። ለርሱ ብቻ ያንበረክካል። ለርሱ ብቻ ሱጁድ ያደርጋል። ለእርሱ ሲል ብቻ ይሰራል። እርሱን ብቻ ይፈራል። ሰዎች ግን የቱን ያህል ምድራዊ ደረጃና ክብር ቢኖራቸውም እንደሱው ባሪናያዎች ናቸው። በርሱ ላይ ምንም ዓይነት ስልጣን የላቸውም።

﴿وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا ١٨﴾ الجن: ١٨

‹‹መስጊዶቹ የአላህ ብቻ ናቸው። በመሆኑም ከአላህ ጋር ማንንም አታምልኩ።›› (አል ጅን 18)

ይህ የሰው ልጅ የሕሊና ነጻነት ሲሆን፣ ከየትኛውም የነጻነት ዓይነት የበለጠና ጥልቅ ነው።

ሐሳብ የመግለጽ እና ገንቢ ሂስ የመሰንዘር ነጻነትን በተመለከተ ሶላት ውስጥ ኢማሙ ሲሳሳት ተከታዮቹ ከስህተት እንዲመልሱት መደንገጉ ጥሩ መገለጫ ነው። በዚህ ረገድ የአድሜ ወይም የጾታ ልዩነት የለም። ኢማሙ ወደ ሚንበር ሲወጣ ያሻውን የመናገር መብት የለውም። ታዳሚዎችም ሚናቸው በጸጥታ ማድመጥ ብቻ አይደለም። የአላህን ትእዛዝት የጣሱ ሰዎች ሊያስተካክሉት ግድ ይሆንባቸዋል። ዑመር ቢን አልኸጣብ የሴትን ልጅ ጥሎሽ ጣሪያ ሊገድቡ ባሰቡ ጊዜ የሆነውን አስተውል። ይህን ሐሳባቸውን በመስጊድ ውስጥ ተናገሩ። አንዲት እንስትም ተቃረነቻቸው። ‹‹ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አላህ እንዲህ አላለም። በማለት ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ ጠቀሰች፡-

﴿ وَإِنۡ أَرَدتُّمُ ٱسۡتِبۡدَالَ زَوۡجٖ مَّكَانَ زَوۡجٖ وَءَاتَيۡتُمۡ إِحۡدَىٰهُنَّ قِنطَارٗا فَلَا تَأۡخُذُواْ مِنۡهُ شَيۡـًٔاۚ أَتَأۡخُذُونَهُۥ بُهۡتَٰنٗا وَإِثۡمٗا مُّبِينٗا ٢٠ ﴾ النساء: ٢٠

‹‹አንዷን ሚስታችሁን በሌላ ለመተካት ከወሰናችሁ፥ ለመጀመሪያዋ የሰጣችኋት (የጥሎሽ) ገንዘብ በርካታ ቢሆንም እንኳ ከርሱ ቅንጣት እንዳትወስዱ። በግፍና ግልጽ በሆነ ኃጢአት ትወስዱታላችሁን?›› (አል ኒሣእ 20)

ዑመር ስህተታቸውን ከመቀበል ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም። በግልጽ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ይህች ሴት ትክክል ናት። ዑመር ተሳስቷል።››

እኩልነት

ቀልቦቻቸው ወደ አንድ አምላክ የዞሩ፣ ከርሱ ጋር ሌላ አካል ያላጋሩ፣ በርሱና በነርሱ መካከል አገናኝ ደላላ (ዋሲጣ) ያላበጁ ሰዎች ሕይወት መሠረቱ እኩልነት መሆኑ እሙን ነው። መስጊድ ውስጥ ጌታ ከተገኘ፣ ሐብታም ከድሐ፣ አለቃ ከሰራተኛው ጋር በአንድ ረድፍ ትከሻ ለትከሻ ተጠጋግተው ይሰግዳሉ። ምሁሩ ከቀኙ ወዛደር፣ ለግራው ገበሬ አድርጎ ይቆማል። መስጊድ ውስጥ የመጀመሪያውን ረድፍ (ሶፍ) ለተለዩ ሰዎች የሚመድብ ውስጠ ደንብ የለም። ሰዎች እንደ አመጣጣቸው ቅደም

ተከተል ብቻ ይሰለፋሉ። ይህ እውነታ ፈረንሳዊውን ፈላስፋ ‹ሪናን› እንዲህ እንዲል አስገድዶታል፡-

‹‹ወደ ሙስሊሞች መስጊድ በገባሁ ቁጥር ውስጤ በተመስጦ ይቆዝማል። ሙስሊም ባለመሆኔ እቆጫለሁ።›››

ጸምም እንደዚሁ ነው። የችግረኞችን መከራ በተጨባጭ ያስተውሳል። የረሃብ ድምጻቸውን በአንደበት ወይም በቃላት ሳይሆን በተግባር ያሰማል። ከሆድ፣ ከጨንራና ከአንጀት በሚፈልቅ ጥሪ ያስደምጣል። የተሟላ እኩልነት ግሩም ማሳያ ነው። የብዙ ሐብት ባለቤቶች የእለት ጉርስ ከማያገኘው ሰው ጋር የአላህን ውዴታ በመሻት እኩል ይራባሉ። ዩሱፍ የአገራቱ ካዝና ሐላፊ ሆነው እያለ ለምን አብዝተው እንደሚጸሙ ተጠይቀው፡- ‹‹ጠግቤ የድሆችን ረሃብ እንዳልረሳ እሰጋለሁ።›› ሲሉ መልሰዋል።

የዘካ ስርዓት ሐብታም እየኖረ፣ ድሃም በድህነቱ እየተቸገረ እንዲኖር ኢስላም አለመሻቱን ያሳያል። ዘካን ከባለ ሐብቶች ሰብስቦ ለድሆች እንዲያከፋፍል መንግስትን ያስገድደዋል። ሁሉም ዜጎች ናቸው። መንግስት ከሐብታሙ ስለሐብቱ ግብር ይቀበለዋል። ለድሃው መሠረታዊ ፍላጎቱን እንዲያሟላ ይሰጠዋል። ሐብታሙ የአላህን ውዴታ በመሻት እና ለድሃው በማዘን ይመጸውታል። ድሃው ደግሞ አላህን አመስግኖ ይቀበላል። ሐብታም ወንድሙን ይወዳል።

ሐጅም የእኩልነትን ጽንሰ ሐሳብ በአስገራሚ ሁኔታ ይዟል። ሁሉም እንደየአገሩና ማሕበራዊ መደቡ፣ እንደየ ባህሉና ዝንባሌው ይጎናጸፏቸው የነበሩ አልባሳትን ሁሉ ትተው መገነጥ የሚመስል ብጣሽ ጨርቅ ያለ ልዩነት ከአካላቸው ላይ ጣል ያደርጋሉ። ንጉስና ባለስልጣኑ ልክ እንደ ድሃና ተራ ሰዎች ይለብሳል። ሁሉም ተመሳሳይ የሐጅ ተግባራትና በተመሳሳይ ቦታና ጊዜ ያከናውናሉ። ከመካከላቸው ልዩነት ሳይኖር በእለተ ቂያማ ለፍርድ በሚቆሙበት አኳኋን ዓረፋ ላይ ይቆማሉ።

አለማቀፋዊ ወንድማማችነትና አንድነት

የፍቅርንና የወንድማማችነትን መንፈስ በተመለከተ የእያንዳንዱ ቀዬ ነዋሪዎች በቀን 5 ጊዜ ለሶላት በመስጊድ ውስጥ እንደሚሰባሰቡ ማወቅ ብቻ በቂ ነው። አካል ለአካል ይነካካሉ። ፊቶች ይተዋወቃሉ። እጆች ይጨባበጣሉ። ሁሉም ለአንድ ዓላማ ይገናኛሉ። በአንድ ኢማም ጀርባ ይሰግዳሉ። አንድን አምላክ ይማጸናሉ። አንድን መጽሐፍ (ቁርአንን) ያነባሉ። ወደ አንድ ቂብላ ይዞራሉ። ተመሳሳይ እንቅስቃሴም ያደርጋሉ። ይህ ሲሆን ተከታዩ የአላህ ቃል በገቢር ይገለጻል፡-

﴿ إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ إِخۡوَةٞ فَأَصۡلِحُواْ بَيۡنَ أَخَوَيۡكُمۡۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ١٠ ﴾

‹‹አማኞች ወንድማማቾች ናቸው። በመሆኑም በወንድሞቻችሁ መካከል እርቅንና ሰላምን አስፍኑ። ይታዘንላችሁ ዘንድም አላህን ፍሩ።›› (አል ሁጁራት 10)

ተከታዩ የነቢዩ ሐዲስም እንደዚሁ፡-

‹‹ሙእሚኖች የመዋደዳቸውና የመተዛዘናቸው ነገር ልክ እንደ አንድ አካል ናቸው። አንዱ የሰውነት ክፍል ሲታመም ሌሎች ሕመሙንና እንቅልፍ ማጣቱን ይጋራሉ።›› (ቡኻሪና ሙስሊም)

በጾም ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ ከምግብና ከመጠጥ ይታቀባሉ። በተመሳሳይ ጊዜም ያፈጥራሉ። አንደኛው ሌላኛው ወንድሙ የሚሰማው የረሃብና የጥማት ስሜት ይሰማዋል። በጾም ወቅት ቸርነትና መተሳሰብ የሚበዛውም ለዚሁ ነው።

ይህ ለአላህ ተገዥነት፣ ይህ የስሜት ትስስር የሙስሊሞችን ወንድማማችነትና ፍቅር ከጠባብ የአካባቢ መስክ ወደ ሰፊ ዓለም ያወጣዋል። ከአካባብ ወይም ከሐገር አልፎ ዓለማቀፋዊ አንድነት በሐጅ ይገለጻል። ሐጅ በአንድ አገር ንጉስ ወይም ኘሬዝዳንት ሳይሆን በዓለማት ጌታ የተጠራ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ነው። በሐጅ ወቅት ሙስሊም ከተለያየ የዓለም ክፍል የመጡ፣ ሐገራቸውን፣ የቆዳ ቀለማቸው ቋንቋቸውና

ዘራቸው ቢለያይም በእስልምናና በኢማን የተሳሰሩ፣‹‹ለበይክአላ ሁመ ለበይክ›› በማለት አንድ ዓይነት ዜማ የሚያዜሙ ወንድሞችን ያገኛል።

በዚህ አኳኋን በሐጅ ወቅት የስሜት ውህደት፣ የአምልኮ አንድነት፣ የዓላማ አንድነት፣ የተግባርና የቃል አንድነት ታያለህ። የቆዳ ቀለም፣ የዘር ወይም የመደብ ጠባብነት ይወገዳል። በአያመተሸሪቅ መሐል የተላለፈውን ተከታዩን የአላህ መልእክተኛ አዋጅ ሰምተዋልና፡-

‹‹ሰዎች ሆይ፣ ጌታችሁ አንድ ነው። አባታችሁም አንድ ነው። አዋጅ ዓረብ ከሌላው፣ ሌሎችም ከአረብ፣ ቀዩ ከጥቁር፣ ጥቁር ከቀዩ በተቅዋ ካልሆነ በቀር ብልጫ የለውም።››

ሰላም

ሐጅ ለሙስሊም ድንቅ የሰላም ስልጠና ይሰጣል። የሰላም መንፈስ ያሰርጽበታል። ሐጅ በሰላም ጊዜ፣ ወደ ሰላም ቦታ የሚደረግ የሰላም ጉዞ ነው። የሐጅ ቦታ አላህ ለሰዎች ማእከል ያደረገው ሐረም ነው።

﴿ وَمَن دَخَلَهُۥ كَانَ ءَامِنًا ۗ وَلِلَّهِ ﴾ آل عمران: ٩٧

‹‹ክርሱ ውስጥ የገባ ሰላምን ይጐናፀፋል።›› (አል ዒምራን 97)

የእንስሳትንና የእጽዋትን ሰላም ይጨምራል። እንስሳት አይታደኑም። እጽዋት አይቆረጡም። ሳሩ አይታጨድም።

ሐጅ በሚፈጸምበት የዙልሂጃ ወርም የሰላም ወራት እንዲሆኑ አላህ ከደነገጋቸው ወራት መካከል አንዱ ነው። በዚህ ወር ሰይፎች ወደሰገባቸው ይከተታሉ። ደሞች ይጠበቃሉ። ውጊያዎች ይቆማሉ።

ሙስሊም በሐጅ ወቅት በዙሪያው ካሉ ሰዎችና ፍጡራን ጋር ፍጹም ሰላማዊ ይሆናል። እጽዋት እንኳ አይቆርጥም። እንስሳትን አያድንም። ሌሎች ያደኑትን እንኳ አይመገብም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَحُرِّمَ عَلَيۡكُمۡ صَيۡدُ ٱلۡبَرِّ مَا دُمۡتُمۡ حُرُمًا ۗ ﴾ المائدة: ٩٦

‹‹ ግና በሐጅ ሥራ ውስጥ ሆናችሁ የየብስ እንስሳትን ማደን ተከልክላችኋል።›› (አል ማኢዳህ 96)

የራሱን ጸጉር እንኳ አይላጭም፡፡ ወይም አያሳጥርም፡፡ ፍጥሩን አይቆርጥም፡፡ ሐጁን እስኪያጠናቅቅ ድረስ በእንዲህ ዓይነት የሰላም ድባብ ውስጥ ይቆያ፡፡ በምድር ላይ እንዲህ ዓይነት ተግባራዊ የሰላም ስልጠና የሚሰጥበት ሌላ ማእከል አለን?

እዚህ ላይ እጅግ ጠቃሚው ነገር ይህ ባህሪ ለጊዜያዊ ጥቅም ብቻ ተብሎ የሚደረግ ሳይሆን የሙስሊም ግለሰብም ሆነ የማሕበረሰቡ መሠረታዊ ባህሪ ነው፡፡፡ የአላህን ውዴታ በመሻት፣ እዝነቱን በመከጀልና ቅጣቱን በመፍራት ይፈጽሙታል፡፡ ግና የአላህ ወሰኖች ሲጣሱ፣ የአላህ ጠላቶች ወሰን ሲያልፉ፣ ግፍ ሲሰሩ፣ ሐገር ሲበክሉና ሲያወድሙ ሙስሊም በአላህ መንገድ ለሚደረግ ትግል ነፍሱን ይሰጣል፦" ተከታዩን የአላህ ቃል ይተገብራል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ ٱشۡتَرَىٰ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ أَنفُسَهُمۡ وَأَمۡوَٰلَهُم بِأَنَّ لَهُمُ ٱلۡجَنَّةَۚ ﴾

‹‹አላህ ከአማኞች ነፍሶቻቸውንም ገንዘቦቻቸውንም ገዛ። በለውጡም ገነትን አዘጋጅቶላቸዋል።›› (አል ተውባህ 111)

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የኢባዳን ግለሰባዊ ጠቀሜታ አብራራ
2) የኢባዳን ቤተሰባዊ ጠቀሜታ አብራራ
3) የኢባዳን ማሕበረሰባዊ ጠቀሜታ አብራራ

ሁለንተናዊ የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብን እውን ማድረግ

ዓላማ

1) ተማሪው ሁለንተናዊ ኢባዳን እንዴት እውን ማድረግ እንዳለበት እንዲያብራራ

2) የኢባዳን ጽንሰ ሐሳብ ምን ያህል በገቢር እንዳዋለ እንዲያስረዳ

ሀ) ሁለንተናዊ ኢባዳን እውን ማድረግ

የሰው ልጅ ምድራዊ ተልእኮ የፈጠረውንና ያስተካከለውን፣ ግልጽም ስውርም ጸጋውን የለገሰውን አምላኩን ማምለክ እንደሆነ አውቀናል። የኢባዳን ትርጉም እና እያንዳንዱን የሰው ልጅ እንቅስቃሴ የሚያካትት ጽንሰ ሐሳብ መሆኑንም ተገንዝበናል። የሰው ልጅ ኢባዳን በመላ ሕይወቱ እንዴት እውን ማድረግ ይችላል?

የአላህ የተሟላ ተገዥነት ሁሉንም ጉዳዮች በሚወደውና በሚፈቅደው መስመር ማስኬድ ነው። እምነትን፣ ንግግርንና ተግባርን በፈቃዱ ማስገዛት ነው። ሕይወትን፣ ባህሪንና ጸባይን በአላህ ሸሪዓ ስር ማድረግ ነው። ትእዛዙን ወይም እቀባውን እንዲህ በሚል መንፈስ መቀበል ነው፡-

﴿ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٢٨٥ ﴾ البقرة: ٢٨٥

‹‹ ጥሪህን ተቀብለናል፥ ለትዕዛዝህ አድረናል። ምሕረትህን እንሻለን። ጌታችን ሆይ! መመለሻም ወደ አንተ ነው።›› (አልበቀራህ 285)

ከላይ እንዳብራራነው ኢስላም የኢባዳን መስክ በማስፋት የሰው ልጅ ኢባዳ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ክንውኖች ሁሉ አካትቷል። ለምሳሌ፡-

ጠቃሚ ማሕበራዊ ተግባራት ዒባዳዎች ናቸው

የምታከናውነውን ጠቃሚ ማሕበራዊ ተግባራት ሁሉ ኢስላም ከበላጭ ኢባዳዎች ፈርጆታል። ዓላማህ ርካሽ ዝናና ክብር ለማግኘት ሳይሆን ለአላህ እስከሆነ ድረስ የምትሰራት እያንዳንዷ በጎ ስራ ኢባዳ ትሆናለች። የተቸገረን መርዳት፣ የአዛኝን እንባ ማበስ፣ የተራበን ማጉረስ፣ የተበደለን ማገዝ፣ እዳ የተጫነውን እዳውን ማቃለል፣ ቤተሰብ የበዛበትን ልመና ለማይደፍር ድሃ ችግሩን ማቃለል፣ መንገድ የማያውቅን ማመላከት፣ እንግዳ ማስተናገድ፣ ሰውን ከመጓጓዣው ላይ ለማውጣት መርዳት፣

ተማሪውን ማስጠናት፣ አይነ ስውርን መምራት፣ በሽተኛ መጠየቅ፣ ጠበኞችን ማስታረቅ፣ ዝምድና መቀጠል፣ ወንድምን መጎብኘት፣ መንገድ ላይ እንቅፋት ማስወገድ፣ ከክፉት መታቀብ፣ ይህ ሁሉ በተስተካከለ ኒያ ከተፈጸመ ኢስላም የኢባዳ አካል፣ የእምነት ዘርፍ አድርጎታል።

እንጀራ መፈለግም ኢባዳ ነው

የእለት ጉርስህን ለማግኘትና የቤተሰቦችህን ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟላት የምታደርገው ጥረትም የሚከተሉትን መስፈርቶች ካሟላ ኢባዳ ይሆናል፡-

1) ስራው በእስልምና እይታ የተፈቀደ (ሐላል) መሆን አለበት። በዲን ሐራም የተደረጉ ስራዎች ግን ለምሳሌ፡- በአራጣ ተቋም፣ በቡና ቤት፣ በዳንስ ሙያ ወዘተ መሰማራት ኢባዳ ሊሆን ፈጽሞ አይችልም። አላህ ጥሩ ነው፡ ጥሩን እንጅ አይቀበልም።

2) መልካም ንያ ሊጎዳኘው ይገባል። ይህውም የርሱንና የቤተሰቡን ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟላት እና አላህ ያዘዘውን ምድርን የማነጽ ተግባር ለመፈጸም መነየት ተገቢ ነው።

3) ስራውን በጥራት ማከናወን አለበት። በሐዲስ እንዲህ ተብሏል፡- ‹‹ከናንት አንዳችሁ አንዳች ስራ ሲሰራ በብቃት እንዲሰራው አላህ ይወዳል።››

4) በስራህ የአላህን ወሰኖች መጠበቅ ግድ ነው። ማንንም መበደል፣ መክዳት፣ ማጭበርበር ወይም ሐቁን መዳፈር የለብህም።።።

5) ዱንያዊ ስራህ ከዲን ሐላፊነትና ግዴት ሊያዘናጋህ አይገባም።።። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُلۡهِكُمۡ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡ عَن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ وَمَن يَفۡعَلۡ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٩ ﴾ المنافقون: ٩

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁም ልጆቻችሁም አላህን ከማስታወስ አያዘናንችሁ። ይህንን የሚፈጽሙ (በገንዘቦቻቸውና በልጆቻቸው ሳቢያ አላህን ከማስታወስ የሚዘናጉ ሰዎች) እነዚያ እነርሱ ከሣሪዎች ናቸው።›› (አል መናፊቁን 9)

﴿ رِجَالٌ لَّا تُلْهِيهِمْ تِجَٰرَةٌ وَلَا بَيْعٌ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَإِقَامِ ٱلصَّلَوٰةِ وَإِيتَآءِ ٱلزَّكَوٰةِ ﴾ النور: ٣٧

‹‹ንግድም ሆነ ሽያጭ አላህን ከማውሳት፣ ሶላትን በአግባቡ ከመስገድና ዘካም ከመስጠት የማታዘናጋቸው።›› (አል ኑር 37)

እነዚህን መስፈርቶች ካሟላህ ስራህ ኢባዳ ይሆንልሐል። መስጊድ ውስጥ ባትሆን እንኳ አላህን እየተገዛህ ነው። ሙስሊም የሌሎች ሸክም መሆን የለበትም። በሁሉም የሕይወት መስኮች ስራውን በብቃት የሚሰራ እንዲሆን ይፈለጋል። ይህን ሁሉ ሲያደርግም በሶላት እና በጅሃድ ላይ እንደሆነ እየተሰማው ነው።

ጸታዊ ግንኙነት ኢባዳ ነው

ኢስላም ስጋዊ ፍላጎትን ለማሟላት የሚፈጸሙ ተግባራትን፣ ማለትም መብላት መጠጣት፣ ከዚህም አልፎ ጸታዊ ግንኙነትንም ከሰፊው የኢባዳ መስክ ውስጥ አካቶታል። እንዲህ ዓይነት የተለመዱ ክንውኖች ኢባዳ ይሆኑ ዘንድ የሚያስፈልገው ኒያ ብቻ ነው። እርሱ ሲጨመር የየእለት ተግባራት ከአምልኮ ተቆጥረው ምንዳ ያስገኛሉ። ለዚህ አባባል አብዩ ምስክር ተከታዩ የአላህ መልእክተኛ ንግግር ነው፡-

‹‹ከናንተ አንዳችሁ ጸታዊ ግንኙነት መፈጸሙ ምጽዋት ነው።››ሲሉ ተናገሩ። ‹‹ስጋዊ ስሜቱን ስላረካ ምንዳ ያገኛልን?›› በማለት ጠየቁቸው። ‹‹እስኪ ንገሩኝ። በሐራም አድርጎት ቢሆን ኖሮ ወንጀል ይሆንበት አልነበረምን?›› በማለት መልእክተኛው ጠየቁ። ‹‹አዎ›› አሏቸው። ‹በሐላል ሲያደርገው ደግሞ ምንዳ ያስገኝለታል›› አሉ። (ሙስሊምና ቲርሚዚ)

ዓሊሞች እንደሚሉት ይህ ከአላህ የሆነ ችሮታ ነው። ባሮቹ ጸታዊ ስሜታቸውን ስላረኩ ይህን ያደረጉት የባልነት ግዴታቸውን ለመወጣትና ብልታቸውን ከሐራም ለመጠበቅ በመሆኑ ምንዳ ያገኛሉ። አላህ የተመሰገነ ይሁን።

ሕይወትህ ኢባዳ ይሆንልህ ዘንድ አቅጣጫህን አስተካክል

ራስህን የአላህ ምድራዊ ወኪል (ኸሊፋ) አድርገህ ማየትህ፣ ዓላማህ ትእዛዙን መፈጸም፣ ወሰኑን ማክበርና ማስከበር፣ ቃሉን የበላይ ማድረግ፣ እርሱን ብቻ ማምለክ መሆኑን መገንዘብህ ብቻ እያንዳንዱ እንቅስቃሴህን በመለኮታዊ መንክር ለማስዋብ በቂ ነው። ቃልህ፣ ተግባርህ፣ እንቅስቃሴህ፣ ረፍትህ ዒባዳ ይሆን ዘንድ መስፈርቱ ይህ ብቻ ነው። ሸህ ሙሐመድ አልገዛሊ ‹‹ሐዛዲኑና›› በተሰኘ መጽሐፋቸው ይህን እውነታ እንዲህ አስውበው ገልጸውታል፡-

‹‹ኢስላም ማለት በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ተግባራትን ሳይጨምሩና ሳይቀንሱ እንደወረዱ ማከናወን ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በምድር ላይ የተወሰነለትን ተልእኮ በመወጣቱ ሂደት የተስተካከለ የሕይወት መስመር መከተሉ ነው። ኢስላም ከሰው ልጅ ከምንም በፊት ስነ ልቦናዊ አወቃቀሩን ይሻል። ውስጣዊ ማንነቱ እንዲስተካከል ይሻል። ውስጡ በሚፈለገው መልኩ እና ከምር ከተስተካከለ፣ መልካም አቅጣጫ ከያዘ በሕይወት ውስጥ የሚያከናውነው ነገር ሁሉ በራሱ ወደ ኢባዳነት ይለወጣል። ልክ እንደ ማሽን ማለት ነው። ጥሬ ማእድን ይገባለታል። ውድ ዋጋ ያለው ሌላ ነገር አድርጎ ያወጣዋል። ሙስሊምም እንደዚሁ ነው። የትኛውንም ዱንያዊ ስራ በሚሰራ ጊዜ የእምነቱን በረከት፣ የዓላማውን ውበትና ድምቀት ሲጨምርበት ያ ስራው ውድ ዋጋ ወዳለው ኢባዳ ይቀየርለታል። በሕይወት መስክ ውስጥ በጎ ስራዎች ከሙስሊም ዘንድ ስፍር ቁጥር የላቸውም። ዓይነታቸውም ውስን አይደለም። ኢባዳ

ከርሱ ዘንድ ራስን ለአምላክ ፈቃድ በማስገዛትና ስራን በማስተካከል ወደሚፈለገው ምሉእነት ማዝገም ነው።››[1]

ለ) ሁለንተናዊውን የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ በገቢር ማዋል

የኢባዳን ሁለንተናዊ ትርጉም አውቀናል። ኢባዳ ሁሉንም ሐይማኖታዊ ተግባራት፣ እንዲሁም መላ ሕይወትን እንደሚያጠቃልል፣ ጠቃሚ ማሕበራዊ ክንውኖች ኢባዳ መሆናቸውን፣ የእለት ጉርስ ለማግኘት የሚደረግ ሩጫ መስፈርቶችን ካሟላ ወደ ኢባዳነት እንደሚቀየር፣ ከዚህም አልፎ ስጋዊ ስሜትን ማርካት እንኳ መልካም ኒያ ከተጎዳኘው ኢባዳ እንደሚሆን አብራርተናል። እናም ይህን ሁለንተናዊ የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ በተግባር ምን ያህል እያዋልነው እንደሆነ ራሳችንን መገምገምና መፈተሽ ይጠበቅብናል። በተከታዩ ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡ መጠይቆች በዚህ ረገድ ያለንን ደረጃ ለመመዘን ይረዱናል። ሰዎች የኢባዳ አካል መሆናቸውን የሚዘነጓቸውን ክንውኖች በዚህ ሰንጠረዥ ለማካተት ተሞክሯል። ሌሎች ክንውኖችንም እንደዚሁ በተመሳሳይ መጠይቅ መዳሰስ ተገቢ ነው።

በማሕበራዊ ክንውኖች ራስህን ገምግም

ተ.ቁ	ባህሪ	ኢምንት	አልፎ አልፎ	ሁል ጊዜ
1	በስራዎቼ የአላህን ውዴታ እነያለሁ			
2	የሰዎችን ርካሽ ሙገሳና ዝና አልሻም			

[1] አል ኢባዳ ፊል ኢስላም -ዶክተር ዩሱፍ አልቀረዷዊ

3	የማውቃቸውን ሰዎች ሁሉ ከችግሮቻቸው ለማቃለል እጥራለሁ፡ ፡			
4	በሐዘን የተጎዳን ሰው እንባ ለማበስ እጥራለሁ፡፡			
5	የተራበን ለማጉረስ እተጋለሁ			
6	እገዛዬን የሚሻን ሁሉ እረዳለሁ			
7	ዓይነ ስውር ሳገኝ መንገድ እመራዋለሁ			
8	በሽተኛን ለመጠየቅ ትጉ ነኝ፡፡			
9	ጠበኞችንለማስታረቅ እጥራለሁ።			
10	የወላጆቼን መብት ለመጠበቅ እጥራለሁ፡ ፡			
11	ዝምድናን ለመቀጠል እጥራለሁ።			
12	የተበደለን እደግፋለሁ፡፡			

13	በዳይን ከበደሉ ለማቀብ እተጋለሁ			
14	እዳ የተጫነውን ሰው እዳውን ለማቃለል እሞክራለሁ፡፡			
15	ቤተሰብ የበዛበትን እና ከልመና የተቆጠበን ድሃ ለመርዳት እጥራለሁ፡፡			
16	መንገድ ለጠፋው መንገድ አመለክታለሁ፡፡			
17	ከኔ ዘንድ ያረፈን እንግዳ አልቃለሁ፡፡			
18	የአላህ ወንድሜን ለመዘየር እተጋለሁ፡፡			
19	ከመንገድ ላይ እንቅፋትን አስወግዳለሁ			
20	በሰዎች ላይ ክፉ ከመስራት እታቀባለሁ፡፡			

ከፍተኛ ነጥብ 60

- ሕይወትህን በሙሉ ለአላህ ኢባዳ ታደርግ ዘንድ ከፍተኛውን ነጥብ ለማግኘት ትጋ፡፡

እንጀራ ፍለጋ በምታደርገው እንቅስቃሴ ራስህን ገምግም

ተ.ቁ	ባህሪ	ኢምንት	አልፎ አልፎ	ሁልጊዜ
1	ምግቤ ሐላል እንዲሆን እጥራለሁ።			
2	በስራዬ ራሴን ከሌሎች ድጋፍና ችሮታ ለማላቀቅ አልማለሁ።			
3	በስራዬ የቤተሰቤን አስፈልጎት ለማሟላት አልማለሁ።			
4	በስራዬ ማሕበረሰቡን ለመጥቀም አልማለሁ።			
5	በስራዬ መሬትን አላህ እንዳዘዘው ለማልማት አልማለሁ።			
6	ስራዬን በአግባቡና በብቃት ለመስራት እጥራለሁ።			
7	በስራዬ የአላህን ወሰኖች አከብራለሁ።			
8	አልበድልም፣ አልከዳም፣ አላታልልም።			
9	የሌሎችን መብት (ሐቅ) አልዳፈርም።			

(ከፍተኛ ነጥብ 27)

- ✓ እንጀራ ፍለጋ የምታደርገው ጥረት አላህን ማምለክ (ኢባዳ) ይሆንልህ ዘንድ ከፍተኛውን ነጥብ ለማግኘት ትጋ።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) ሁለንተናዊውን የኢባዳ ጽንሰ ሐሳብ እንዴት እውን ማድረግ እንደምትችል አብራራ
2) እያንዳንዷን ቀንህን እንዴት ኢባዳ ማድረግ እንደምትችል አብራራ
3) እስካሁን ያላከናወንካቸውን የኢባዳ አይነቶች ዘርዝር
4) እስካሁን ያላከናወንካቸውን የኢባዳ ዓይነቶች ማከናወን ትችል ዘንድ ለራስህ እቅድ አዘጋጅ።

* * *

ምእራፍ ሰባት

የኢማንና የመልካም ስነ ምግባር ትስስር

ዓላማ

1) የመልካም ስነ ምግባርን ጽንሰ ሐሳብ ማብራራት

2) በኢማንና በመልካም ስነ ምግባር መካከል ያለውን ትስስር ማብራራት

3) የአንዳንድ መልካም ስነ ምግባር ገጽታዎችን፣ መገለጫዎቻቸውንና በነርሱ ለመታነጽ የሚረዱ ስልቶችን ማብራራት

የመልካም ስነ ምግባር ጽንሰ ሐሳብ

ዝርዝር ዓላማዎች

1) የስነ ምግባርን ቋንቋዊ ትርጉም መረዳት

2) በእስልምና የስነ ምግባርን መልእክትና ይዘት ማብራራት

3) የስነ ምግባር መሠረቶችን ማብራራት

1)የስነ ምግባር ቋንቋዊ ትርጉም

የስነ ምግባር ቋንቋዊ ትርጉሙ ባህሪ ማለት ነው፡፡ እነዲህ ልንገልጸው እንችላለን፡-

‹‹ሰውየው አንድን ድርጊት ለመፈጸም ወይም ለመታቀብ ይወስን ዘንድ ድርጊቱ ጥሩ ወይም መጥፎ መሆኑን የሚመዝንባቸው ከሕሊና ውስጥ የጸኑ መስፈርቶች ስብስብ ስነ ምግባር ይባላል፡፡››[1]

2) በእስልምና የስነ ምግባር ትርጉም

ኢማም አቡ ሐሚድ አልገዛሊ ስለ ስነ ምግባር ባሰፈሩት ድንቅ ጽሑፍ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ስነ ምግባር ማለት በሕሊና ላይ የጸናና ስራዎች ማሰብ ሳያስፈልጋቸው በቀላሉ የሚመነጩበት ነገር ነው፡፡››

[1] ኡስሉ ዳእዋ- አብዱልከሪም ዘይዳን

በአእምሮ ሚዛንም በሸሪዓውም እይታ መልካም የሚሰኙ ተግባራት ከመነጨበት መልካም ስነ ምግባር ይባላል። መጥፎ ተግባራትን ከመነጨ ደግሞ መጥፎ ስነ ምግባር ይባላል።

‹‹በሕሊና ላይ የጸና›› ያልንበት ምክንያት ለስለት ወይም አንዳች ጉዳይ ገጥሞት ገንዘብ የሰጠ ሰው ይህ ድርጊቱ የስብእናው ጥልቅ አካል እና ልምዱ እስካልሆነ ድረስ ቸርነት ባህሪው ነው ሊባል አይችልም።

ስራዎች ማሰብና መገደድ ሳያስፈልጋቸው በቀላሉ የሚመነጨበት›› ያልነውም ለምሳሌ በቀላሉ ሳይሆን ከራሱ ጋር ብዙ ታግሎ ገንዘብ የመጸወተ ቸር ሊሰኝ አይችልም።

በጎ ተግባራትን ማወቅ ብቻም መልካም ስነ ምግባር አይሰኝም። አንዳንድ ጊዜ እውቀቱ ይኖርና የመፈጸም ጉልበት ሊያንስ ይችላል። በጎ ስራ መስራት ብቻም ስነ ምግባር አይደለም። ቸርነት ባህሪው ሆኖ ገንዘብ ስለሌለው የማይሰጥ፣ ንፉግ ሆኖም ለይዩልኝ ሲል ወይም ተገዶ የሚሰጥ በርካታ ሰው አለ።

ስነ ምግባር ማለት መልካም ስራ ለመስራት ውስጣዊ ዝግጁነት፣ የነፍስ ውስጣዊ ውበትና ባህሪ ነው። አንድ ሙስሊም ዓሊም፡-‹‹የአርስቶትልን የሞራል ፍልስፍና አንብበውታልን?›› ተብለው ተጠየቁ። ‹‹ከርሱ ተጨማሪ የነቢዩ ሙሐመድ ቢን አብደላህን የሞራል ትምህርት አንብቢያለሁ። የአርስቶትልን እና የመሰሎቹን ፈላስፎች የሞራል ፍልስፍና አነበብን። የነቢዩ ሙሐመድንም አነበብን።። ፈላሰፎች ከብዙ ጥረትና ልፋት በኋላ ከፊል ገጽታው የተሟላ፣ ከፊል ገጽታው ደግሞ ጎደሎ የሆነ ተምሳሌታዊ ስብእና በምናባቸው ሳሉ። ይህ ስብእና እጅግ በተሟላና በደመቀ መልኩ ስጋ ለብሶና ነፍስ ዘርቶ በተጨባጩ ዓለም ውስጥ የግሰለቦች ሕይወት፣ የሕብረተሰብ የኑሮ ስርዓት፣ የግዙፍ ሐይማኖት አስኳል ሆኖ አገኘነው። ይህም የሙሐመድ ቢን አብደላህ የሞራል ትምህርት ነው።››

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለሚያስተምሩት የሞራል ትምህርት ለባልንጀሮቻቸው መካከል ዋነኛ አርአያ ሆነው ኖረዋል። ይህን የመጠቀ ስነ ምግባር በሶሐቦች ስብእና ውስጥ ከቃል በፊት በተግባር አስርጸዋል።

3) የመልካም ስነ ምግባር መሠረቶች

1) የእውቀት ሐይል፡- በርሱ አማካይነት ትክክለኛውን ከተሳሳተው ይለያል። ጥበብ የሚባለውም ይህ ነው። ለክፉ አላማ በመዋል ሲባክን ‹‹ኸብስ›› ይባላል። ሲያንስ ደግሞ ቂልነት ነው። መካከለኛው ጥበብ ይሰኛል። እውቀት ክፉውን ከደጉ፣ መልካሙን ከመጥፎ ለመለየት ያስችላል።

2) ጀግንነት፡- በአእምሮ ልጓም የተያዘ የቁጣ ሐይል ጀግንነት ይባላል። የቁጣ ጉልበት ከልክ ሲያልፍ ወደ አደጋ መማገድ (ተሐውር)፣ ከልክ ሲያንስ ደግሞ ፍርሃት ይሆናል። ጀግንነት የክብር ሽማ ያላብሳል። ከተግባር መልካሙን ለመምረጥ፣ ቁጣን ለመቆጣጠርና ለታጋሽነት ይረዳል።

3) ቁጥብነት፡- የስጋዊ ስሜትን (ሻህዋን) ጉልበት በአእምሮና በሸሪዓ ልጓም መቆጣጠር ቁጥብነት (ዒፍፋህ) ይባላል። የሻህዋ ጉልበት ከልክ ሲያልፍ ስግብግብነት፣ ከልክ ሲያንስ ደግሞ ስንፈት ይሆናል። ቁጥብነት እኩይ ቃልና ተግባር ከመፈጸም ያቅባል። የበጎ ነገሮች ሁሉ ዓይነታ የሆነውን የይሉኝታ (ሐያእ) ባህሪ ያላብሳል። ሐያእ ከብልግና፣ ከውሸት፣ ከሐሜትና ነገር ከማሳበቅ የሚታደግ ስነ ምግባር ነው።

4) ፍትህ፡- የቁጣንና የሻህዋን ጉልበት ተቋቁሞ ነፍስን በጥበብ ጎዳና የሚያስኬድ ባህሪ ፍትህ ይባላል። ፍትህ ከልክ ሲያልፍ ወይም ሲያንስ የሚችል ባህሪ አይደለም። በራሱ ሚዛናዊ ነው። የርሱ ተቃራኒ ባህሪ በደል ይባላል። ፍትህ ባህሪን ሚዛናዊ፣ ስነ ምግባርን ልከኛ ያደርጋል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የስነ ምግባርን ቋንቋዊ ትርጉም አውሳ

2) የእስልምናን የስነ ምግባር ትርጉም ግለጽ

3) የስነ ምግባር መሠረቶችን ዘርዝር

የኢማንና የስነ ምግባር ትስስር

የትምህርቱ ዓላማ

1) ተማሪው የመልካም ስነ ምግባርን ጠቀሜታ የሚገልጹ የነቢዩ ሐዲሶችን እንዲያስታውስ

2) መልካም ስነምግባር የኢማን ፍሬ መሆኑን እንዲረዳ

3) መጥፎ ስነ ምግባር የኢማን ድክመት ምልክት መሆኑን እንዲገነዘብ

4) የተላቀ ስነ ምግባር ባለቤት የሆኑትን የመልእክተኛውን ከፊል ባህሪያት ማስታወስ

1) የመልካም ስነ ምግባር ክብደትና ፋይዳ

ስነ ምግባር በእስልምና ከፍተኛ ስፍራ ተሰጥቶታል። የአላህ መልእክተኛ የተላኩበትን ዓይነተኛ ዓላማ፣ የዳዕዋቸውን ጉልህ ሚና እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል፡-

‹‹እኔ የተላክኩት መልካም ስነ ምግባራትን ለመመላት ነው።››

አላህ እርሳቸውን ሲያሞግስ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ﴿٤﴾ ﴾ القلم: ٤

‹‹አንተ የላቀ ሥነ-ምግባር ባለቤት ነህ።›› (አል ቀለም 4)

ሙስሊሞች ከዓለም መሪነት ሚናቸው የተወገዱት ኢስላም ካመጣው መልካም ስነ ምግባር ርቀው በልዋጩ አንዴ የምእራቡን፣ ሌላ ጊዜ የምስራቁን እሴቶች በማማተራቸው ነው።

ከአላህ መልእክተኛ ትምህርት በጥቂቱ

ኡሳማ ቢን ሸሪክ እንዲህ ሲል አስተላልፏል፡-

ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ፣ ከራሳችን ላይ በራሪ ያረፈ ያህል አንገታችንን ደፍተን በጽናት ተቀምጠን እያለ ሰዎች መጡና፡-

‹‹ከአላህ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ የሆኑ የአላህ ባሮች እነማን ናቸው?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ ‹‹ስነ ምግባራቸው የበለጠ መልካም የሆነው›› በማለት መለሱ፡፡ (ጦበራኒ)

በሌላ ዘገባ፡- ‹‹የሰው ልጅ ከሚታደላቸው ስጦታዎች ሁሉ በላጩ የትኛው ነው?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ ነቢዩም፡- ‹‹መልካም ስነ ምግባር›› በማለት መለሱ፡፡ (ቲሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ብልግና መናገርና መፈጸም የእስልምና አካል አይደለም፡፡ ከሰዎች መካከል እስልምናው ይበልጥ ያማረው በስነ ምግባር በላጩ ነው፡፡›› (ቲርሚዚ)

አብደላህ ቢን ዓምር እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ፡-

‹‹ከኔ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅና በእለተ ቂያማም ለኔ ይበልጥ የቀረበ ማረፊያ የሚኖረው ሰው ማን እንደሆነ ልንገራችሁን?›› በማለት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ደጋግመው ጠየቁ፡፡ ‹‹አዎ›› አሏቸው፡፡ ‹‹ስነ ምግባሩ ይበልጥ ያማረው ሰው ነው፡፡›› ሲሉ መለሱ፡፡ (አህመድ)

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በእለተ ቂያማ ከሙእሚን ሚዛን ላይ ከመልካም ስነ ምግባር የሚከብድ ነገር የለም፡፡ አላህ ባለጌን አይወድም፡፡ የልካም ስነ ምግባር ባለቤት ጿሚዎችና ሰጋጆች ከሚደርሱበት ደረጃ ይደርሳል፡፡›› (አህመድ)

መልካም ስነ ምግባር የኢማን ፍሬ ነው

ኢስላም ለስነ ምግባር ከፍተኛ ትኩረት ከመስጠቱ የተነሳ የኢማን ፍሬ አድርጎ ቆጥሮታል። ከዚህም በላይ የኢማን ሕልውና ተግባራዊ መገለጫ አድርጎታል። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በአላህና በመጭው ዓለም የሚያምን እንግዳውን ያክብር። በአላህና በመጭው ዓለም የሚያምን ዝምድናውን ይቀጥል። በአላህና በመጭው ዓለም የሚያምን መልካም ይናገር ወይም ዝም ይበል።›› (ቡኻሪ)

ኢማን የሚረጋገጠው በስነ ምግባርና በጥሩ ባህሪያት እሴቶች ነው። ሌላው ቀርቶ ኢስላም የደነገጋቸው የአምልኮ ተግባራት እንኳ ከሚያስገኟቸው በጎ ፍሬዎች መካከል አንዱ ስነ ምግባር ነው።

ሶላትን አላህ ግዴታ ሲያደርግ እርሷን በአግባቡ የመስገድን ጥበብ እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

﴿وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَۖ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِۗ﴾ العنكبوت: ٤٥

‹‹ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከወሲብና እኩይ አድራጎቶች ትጠብቃለችና።›› *(አል አንከቡት 45)*

ከመጥፎ ንግግሮች እና ድርጊቶች መራቅ የሶላት አብይ ውጤት ነው። በሐዲሰል ቁድስ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

‹‹ሶላቱን የምቀበለው በርሷ አማካይነት ለልዕልናዬ ሲል ለተናነስ፣ በርሷ ሰበብ ከፍጡራኔ ላይ ላይኮፈስ፣ እኔን በመሐጥየት ላይ ላልዘወተረ፣ ቀኑን እኔን በማሰታወስ፣ ለድሆች፣ መንገድ ላይ ስንቅላቋረጣቸው፣ ባሎቻቸውን በሞት ላጡ እንስቶችና አንዳች መከራ ለደረሰባቸው ሰዎች በማዘን ላሳለፈ ነው።›› (በዛር)

ዘካ ከሰዎች እጅ በሐይል የሚወሰድ ግብር ሳይሆን የማዘንን ስሜት ለማስረጽ፣ በተለያዩ መደቦች መካከል የመተዋወቅ፣ የመረዳዳትና

የመግባባት ስሜት ይጠናከር ዘንድ ታልሞ የተደነገገ ኢባዳ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ خُذۡ مِنۡ أَمۡوَٰلِهِمۡ صَدَقَةٗ تُطَهِّرُهُمۡ وَتُزَكِّيهِم بِهَا ﴾ التوبة: ١٠٣

‹‹ ከኃጢአት) የምታጠራቸውን፥ (የመ ልካም ሥራቸውን ምንዳም) የምታሳሳላቸውን ምጽዋት (ዘካ) ተቀበላቸው።›› *(አል ተውባህ 111)*

እንዲሁም የጾም ዓላማ ከምግብና ከመጠጥ ለተወሰነ ጊዜ ሰዎችን አቅቦ ማዋል አይደለም። ነፍስ ከሐራም የምትጠበቅበትን ስልጠና መስጠት እንጅ። የአላህ መልእክተኛ ይህን እውነታ እንዲህ ሲሉ አጽንተዋል፦

‹‹የሐሰት ንግግርንና በርሱ መስራትን ያልተዎ፣ ምግብና መጠጥ መተው ብቻ ለአላህ ግድ አይሰጠውም።›› (ሙስሊም)

ቁርአን የጾምን በጎ ውጤት እንዲህ ሲል ዘክሯል፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ ﴾ البقرة: ١٨٣

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም ለነዚያ ከናንተ በፊት ለነበሩት (ሕዝቦች በግዴታነት) እንደተደነገገ ሁሉ በናንተም ላይ ተደንግጓል። ጥንቁቆች ትሆኑ ዘንድ።›› (አል በቀራህ 183)

ወደተቀደሰው የመካ ምድር በመሄድ ኢስላም አቅም ላላቸለው ተከታዮች ግዴት ያደረገውን የሐጅ ስርዓት ማከናወንን ምንም ዓይነት መልእክት እና ጥበብ የሌለው ተራ ጉዞ አድርገው ሰዎች ሊያስቡት ይችላሉ። ምክንያቱም ሐይማኖቶች ትርጉም አልባ መንፈሳዊ ክንውኖችን መያዛቸው የተለመደ ነውና። በእርግጥ ይህ ከእስልምና ጋር በተያያዘ ስህተት ነው። አላህ ስለሐጅ ሲናገር እንዲህ ይላል፦

﴿ ٱلۡحَجُّ أَشۡهُرٞ مَّعۡلُومَٰتٞۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلۡحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِي ٱلۡحَجِّۗ وَمَا تَفۡعَلُواْ مِنۡ خَيۡرٖ يَعۡلَمۡهُ ٱللَّهُۗ وَتَزَوَّدُواْ فَإِنَّ خَيۡرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقۡوَىٰۚ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩٧ ﴾ البقرة: ١٩٧

‹‹የሐጅ (ጊዜ) የታወቁ ወራት ናቸው። በነኝህ (ወራት) ውስጥ ሐጅን በራሱ ላይ ግዳጅ ያደረገ ሐጅ ውስጥ ከሴት ጋር መገናኘት፥ (በአላህ ላይ) ማመጽም፥ (ክባልደረቦቹ) ጋር መከራከርም የለበትም። ከበጉ ምግባር የምትፈጽሙትን አላህ ያውቃል። ተሰነቁ። ከስንቅ ሁሉ በላጩ አላህን መፍራት ነው። እናንተ አስተዋዮች ሆይ! ፍሩኝ።›› (አል በቀራህ 197)

ከላይ የሰጠው ጥቅል ማብራሪያ ሐይማኖት ከስነ ምግባር ጋር ያለውን ጠንካራ ግንኙነት ለማሳየት በቂ ይመስለናል። በይዘትና በቅርጽ የሚለያዩ ዒባዳዎች የአላህ መልእክተኛ እንዲህ በማለት ካስቀመጡት ዓላማ ላይ ይገናኛሉ።

‹እኔ የተላክኩት መልካም ስነ ምግባራትን ለማሟላት ነው።›››

እንዲህም ብለዋል፡-

‹‹ኢማን ከስልሳ ወይም ከሰባ በላይ ዘርፎች አሉት። ከፍተኛው ላኢላሐ ኢለላህ የሚለው ቃል ሲሆን፣ ዝቅተኛው ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ ነው። ይሉኝታ (ሐያእ) የኢማን ዘርፍ ነው።›› (ሙስሊም)

በዚህ አኳኋን መልካም ስነ ምግባሮች፣ ኢምንት ብለን የምናስባቸው ድርጊቶች ሳይቀሩ የትክክለኛው ኢማን አካሎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ከዚህም በላይ ምሉእ ኢማንን መጎናጸፍ ከስነ ምግባር መስተካከል ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ከሙእሚኖች መካከል እምነቱ ይበልጥ ምሉእ የሆነው የትኛው ነው?›› የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው፡- ‹‹ስነ ምግባሩ የበለጠ ያማረው።›› በማለት መልሰዋል።

አንድ ሰው በእምነቱ አማካይነት ቀልቡ ካልጸዳና ከአላህና ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ካልተስተካከለ ከስሯል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِنَّهُۥ مَن يَأۡتِ رَبَّهُۥ مُجۡرِمٗا فَإِنَّ لَهُۥ جَهَنَّمَ لَا يَمُوتُ فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ٧٤ وَمَن يَأۡتِهِۦ مُؤۡمِنٗا قَدۡ عَمِلَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَأُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلدَّرَجَٰتُ ٱلۡعُلَىٰ ٧٥ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ وَذَٰلِكَ جَزَٰٓؤُاْ مَن تَزَكَّىٰ ٧٦ ﴾ طه: ٧٤ - ٧٦

‹‹እነሆ አመፀኛ ሆኖ ወደ ጌታው የሚመጣ ሰው ገሃነም ተዘጋጅቶለታል። ከርሷ ውስጥ አይሞትም፤ አይሆንም። አማኞችና መልካም ሥራ የሠሩ ሆነው የመጡት ግን የላቁ ደረጃዎች ተዘጋጅተውላቸዋል። ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመኖሪያ ገነቶችም (ይጠብቋቸዋል)። ከውስጣቸው ዘንተ ዓለም ይኖራሉ። ይህ (ከጋጢአት) የፀዱ ሰዎች ምንዳ ነው።›› (ጧሃ 74-76)

ቁርአን በመልካም ስነ ምግባር ከማዘዙ በፊት ‹‹ሙእሚኖች ሆይ፣›› በማለት ኢማንን እንደ ቀዳሚ መስፈርት ማቅረቡ የተለመደ ነው። ከዚያ በኋላ ትእዛዙን ያስከትላል። ለምሳሌ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَكُونُواْ مَعَ ٱلصَّٰدِقِينَ ١١٩ ﴾ التوبة: ١١٩

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ። ከእውነተኞችም ሁኑ።›› (አል ተውባህ 119)

የአላህ መልእክተኛ ተከታዮቻቸውን ከአልባሌ ንግግር አንደበታቸውን ያቅቡ ዘንድ ሲመክሩም ኢማንን እንደ መስፈርት አስቀድመው እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በአላህና በመጭው ዓለም ያመነ መልካም ይናገር ወይም ዝም ይበል።›› (ቡኻሪ)

በዚህ አኳኋን ቁርአንና ሱንና የእምነትን እውነተኝነትና ምሉእነት መሠረት አድርገው ፍሬያቸው በሕይወት መድረክ ላይ የሚታዩ መልካም ስነ ምግባሮችን በሰው ልጅ ልቦና ውስጥ ማስረጻቸውን

ይቀጥላሉ። ቁርአን ውስጥ በአልማሉን ምእራፍ በፍርዱ ቀን የማያምኑ ሰዎች ባህሪያት እንዲህ ተገልጸ ብታገኘው አይግረምህ፤

﴿ فَذَٰلِكَ ٱلَّذِى يَدُعُّ ٱلۡيَتِيمَ ۝٢ وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ۝٣ ﴾

‹‹ይህም ያ የቲምን በኃይል የሚገፈትር (ነው)። ችግረኞችን እንዲመግቡም ሌሎችን አያነሳሳም።›› (አል ማኡን 2-3)

ገጽታው የጨለመ፣ ባህሪው የተወላገደ፣ ለማንም ደንታ ሳይኖረው እኩይ ድርጊት የሚፈጽምን ሰው አስመልክተው የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ሐያእና ኢማን የማይነጣጠሉ ባልንጀሮች ናቸው። አንደኛው ሲወገድ ሌላኛውም አብሮ ይወገዳል።›› (ሐኪምና ጦበራኒ)

ጎረቤቶቹን በሚያውክን ግለሰብ እስልምና ጨካኝ ፍርድ ያስተላልፍበታል። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ ‹‹በአላህ እምላለሁ አላመነም።›› በማለት ሦስት ጊዜ ደጋግመው ተናገሩ። ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ማነው ያላመነው?›› ተብለው ተጠየቁ። ‹‹ጎረቤቱ ተንኮሉን የሚሰጋው ሰው።›› ሲሉ መለሱ። (ቡኻሪ)

መጥፎ ስነ ምግባር የኢማንን መድከም አመልካች ነው

አንዳንድ ወገኖች የግዴታ ኢባዳዎችን በማከናወኑ ሂደት ቸልተኞች ሆነው ስነ ምግባራቸው ግን መልካም ሆኖ ታያቸዋለህ። ሌሎች ደግሞ ኢባዳ ላይ በርትተው በስነምግባር ረገድ ግን ዲኑ የማይቀበላቸውን መጥፎ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ትመለከታለህ። ሁለት ዓይነት ሰዎችን ከኛ ዘንድ ማየት ተለምዷል። በእርግጥ ሁለቱም ተቀባይነት የላቸውም። አንደኛው በኢባዳ ላይ ብርቱ ሆኖ ስነ-ምግባሩ መጥፎ ሲሆን ሌላኛው ስነምግባሩ መልካም ሆኖ ‹‹ሐይማኖት በልብ ነው›› በሚል እሳቤ ስለ ኢባዳ ደንታ ቢስ የሆነ ነው። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከነዚህ ወገኖች በጥብቅ አስጠንቅቀዋል። በአንድ ወቅት፦ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እገሊት የተባለች ሴት ሶላት፣ጾምና ሶደቃ በማብዛት ትታወቃለች።

ግና ጎረቤቶቿን በምላሷ ታውካለች›› ተባሉ፡፡ ‹‹የእሳት ሰው ናት፡፡›› ሲሉ መለሱ፡፡ ‹‹እገሊት ደግሞ ሶላቷና ጾሟ አናሳ ነው፡፡ ቁራጭ አይብ ብቻ ትመጸውታለች፡፡ ጎረቤቶቿን ግን አታውክም፡፡›› አሏቸው፡፡ ‹‹የጀነት ናት››ሲሉ መለሱ፡፡ (አህመድ)

መልካም ስነ ምግባር ከኢማንና ከኢባዳ ጋር ያለውን ትስስር የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) የሚያብራሩት፣ የዲንና የመጭው ዓለም ስኬት መሠረት መሆኑን የሚገልጹት ጥያቄ ሲቀርብላቸው ብቻ አልነበረም፡፡ ስነ ምግባር በአእምሮና በልቦና ውስጥ በጽናት ይሰርጽ ዘንድ ተከታታይ ትምህርትና ምክር ይሻል፡፡ ኢማን፣ በጎነት እና ስነምግባር ሊነጣጠሉ የማይችሉ ተጣማሪዎች ናቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ አንድ ቀን ባልንጀሮቻቸውን፡- ‹‹ድሃ ማለት ማን እንደሆነ ታውቃላችሁን?›› ሲሉ ጠየቁ፡፡ ‹‹ድሃ ማለት ከኛ ዘንድ ገንዘብ የሌለው ነው፡፡›› አሏቸው፡፡ እንዲህ አሉ፡- ‹‹ከተከታዮቼ መካከል ድሃ ማለት በእለተ ቂያማ ሶላት፣ ዘካና ጾም ይዞ ግና ይህን ሲሳደብና የሌላኛውን ስም ሲያጠፋ፣ የዚያን ገንዘብ በልቶ፣ የዚህኛውን ደም አፍስሶ፣ ያኛውን መትቶ የሚመጣ ነው፡ ፡ ለበደላቸው ሰዎች ከምንዳው እየተቀነሰ ይሰጣቸዋል፡፡ ምንዳው ካለቀበት ከወንጀላቸው ተቀንሶ እርሱ እንዲሸከም ይደረግና ወደ እሳት ይጣላል፡፡›› (ሙስሊም)

እውነተኛ ድሃ ይህ ነው፡፡ ከሱቁ ውስጥ የመቶ ሺህ ብር ሸቀጥ ይዞ የ200 ሺህ ብር ባለ እዳ እንደሆነ ነጋዴ ማለት ነው፡፡ ይህ ሚስኪን በምን ስሌት ሐብታም ሊሰኝ ይችላል?

ጥቂት ኢባዳዎችን ካከናወነ በኋላ የክፋት ቋት፣ ገጽታው የጨለመ፣ ሰው የሚተናኮል ሆኖ የሚውል ሰው በምን ስሌት ሐይማኖተኛ ሊሰኝ ይችላል? የአላህ መልእክተኛ ለዚህ ዓይነቱ ሰው ቅርብ ምሳሌ መስጠታቸው ተዘግቧል፡፡ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ውሃ በረዶን እንደሚያቀልጠው መልካም ስነ ምግባር ወንጀልን ያቀልጣል፡፡ ኸል ማርን እንደሚያበላሸው ክፉ ስነ ምግባርም በጎ ስራን ያበላሻል፡፡›› (በይሐቂ)

እኩይ ድርጊቶች ሲፋፉ፣ ጉዳታቸው ሲገለጽ፣ አደጋቸው ሲበረታ ሰውየው ልብሱን እንደሚያወልቀው ኢማኑንም አውልቆ ይጥላል። ከዚያ በኋላ አማኝ ነኝ ማለቱ አይበጀውም። ሐይማኖት ያለ ስነ ምግባር ምን ፋይዳ አለው? ለአላህ አድሪያለሁ እያሉ በካይ መሆን እምነትን ትርጉም ያሳጣል።

ቁርአንን ስታነብ በኢማን፣ በስነ ምግባርና በኢባዳ መካከል መነጣጠልን አታይም። የሙእሚኖች ባህሪያት የጥሩ ስነ ምግባርና የተስተካከለ ኢባዳ የማይነጣጠል ጥምረት ሆኖ ታገኘዋለህ። ተከታዩን አንቀጽ አንብብ፡-

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ٢ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنِ ٱللَّغۡوِ مُعۡرِضُونَ ٣ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِلزَّكَوٰةِ فَٰعِلُونَ ٤ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِفُرُوجِهِمۡ حَٰفِظُونَ ٥ إِلَّا عَلَىٰٓ أَزۡوَٰجِهِمۡ أَوۡ مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُهُمۡ فَإِنَّهُمۡ غَيۡرُ مَلُومِينَ ٦ فَمَنِ ٱبۡتَغَىٰ وَرَآءَ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡعَادُونَ ٧ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِأَمَٰنَٰتِهِمۡ وَعَهۡدِهِمۡ رَٰعُونَ ٨ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَلَىٰ صَلَوَٰتِهِمۡ يُحَافِظُونَ ٩ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡوَٰرِثُونَ ١٠ ٱلَّذِينَ يَرِثُونَ ٱلۡفِرۡدَوۡسَ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ١١ ﴾ المؤمنون: ١ - ١١

አማኞች በእርግጥ ስኬታማ ሆኑ።እነዚያ ሶላታቸውን በፍፁም ተመስጦ የሚፈጽሙት፤እነዚያ ከውድቅ ንግግር የራቁት፤እነዚያ ዘካን (ሳያንዱሉ) የሚሰጡት፤እነዚያ ብልቶቻቸውን የሚጠብቁት፥ከሚስቶቻቸው ወይም በሥሮቻቸው ካሉ (የሴት አገልጋዮቻቸው) ጋር ካልሆነ በቀር። (ከነርሱ ጋር ሕጋዊ የሆነ ወሲብ በመፈፀማቸውስ) ተወቃሾች አይሆኑም።ግና (ለወሲብ ስሜታቸው) ከዚህ ውጭ ሌላን መንገድ የከጀሉ እነርሱ ወሰን አላፊዎች ናቸው።እነዚያ አደራዎቻቸውንም ቃልኪዳኖቻቸውንም ጠባቂዎች የሆኑት፤እነዚያ ሶላቶቻቸውን ወቅታቸውን ጠብቀው የሚሰግዱት፤ወራሾች እነርሱ ናቸው።እነዚያ ገነትን የሚወርሱት። ከውስጧም ዝንተ ዓለም ይኖራሉ።የሰውን ልጅ ከነጠረ ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው። (ሱል መእሚኑን 1-11)

ይህንንም ቅራ፡-

﴿ وَعِبَادُ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلَّذِينَ يَمۡشُونَ عَلَى ٱلۡأَرۡضِ هَوۡنٗا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ ٱلۡجَٰهِلُونَ قَالُواْ سَلَٰمٗا ٦٣ ﴾ الفرقان: ٦٢ - ٦٣

‹‹ የአር-ረሕማን ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በእርጋታ የሚንዙና መሃይማን ባናገሯቸውም ጊዜ፦ "ሰላም" የሚሉ ናቸው።›› (አል ፉርቃን 62-63)

በተከበረው ቁርአን ውስጥ እንዲህ አይነት በርካታ ገለጻዎችን ታገኛለህ። ኢማን ከበጎ ስነ ምግባር ጋር ያለውን ትስስር የሚያጸድቀውን ይህን ግልጽ መርህ ለማጽናት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ሦስት ባህሪያት ያሉበት ሰው ቢጾም ቢሰግድ፣ ሐጅና ዑምራ ቢያደርግ ወይም እኔ ሙስሊም ነኝ ቢል እንኳ ሙናፊቅ ነው። ሲያወጋ የሚዋሽ፣ ቀጠሮ (ቃሉን) የሚያፈርስ፣ ሲታመን የሚከዳ።›› (ሙስሊም)

በሌላ ዘገባም እንዲህ ብለዋል፦

‹‹የሙናፊቅ ምልክቶች ሦስት ናቸው። ሲያወጋ ይዋሻል። ቀጠሮ ያፈርሳል። ቃል የገባውን ይጥሳል። ቢሰግድ፣ ቢጾም፣ እና ሙስሊም እንደሆነ ቢያስብም የነዚህ ባህሪያት ባለቤት ሙናፊቅ ነው።›› (ቡኻሪ)

የአላህ መልእክተኛ በርካታ ኢባዳዎችን አስተምረዋል። ከብዙ ጠላቶቻቸው ጋር ፈታኝ እና ረዥም ትግል ካደረጉ በኋላ መንግስት አቋቁመዋል። ሐይማኖታቸው ሰፊ፣ የበጎ ምግባር ዘርፎቹም ብዙ ሆነው እያለ በእለተ ቂያማ ከሚዛን ላይ የሚከብደው መልካም ስነ ምግባር መሆኑን ገልጸዋል። ይህ የሚያሳየው መልካም ስነ ምግባር በእስልምና ያለውን ጉልህ ስፍራ ነው። እንዲህ ብለዋል፦

‹‹በእለተ ቂያማ ከሙእሚን የስራ ሚዛን ከመልካም ስነ ምግባር ይበልጥ የሚከብድ ነገር የለም። አላህ ባለጌን አይወድም። የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት የጾመኞችንና የሰጋጆችን ደረጃ ያገኛል።›› (አህመድ)

የተላቀ ስነ-ምግባር ባለቤት

የአላህ መልእክተኛ ይህን መርህ ተከታዮቻቸው በአግባቡ እንዲገነዘቡት ለማድረግ በቃልም በተግባርም አርአያ ለመሆን ብርቱ ጥረት አድርገዋል፡

1) አብደላህ ቢን ዑመር እነዲህ ብለዋል፡-

የአላህ መልእክተኛ በብልግና ንግግርም ሆነ ድርጊት አልተሳተፉም፡፡ ‹‹ከናንተ መካከል በላጩ ስነ ምግባሩ ይበልጥ ያማረው ነው፡፡›› ይሉ ነበር፡፡ (ቡኻሪ)

2) አነስ እንዲህ ብሏል፡-

ነቢዩን ለአስር አመታት አገልግያለሁ፡፡ በአላህ እምላለሁ፣ አንድም ጊዜ ገላምጠውኝ ወይም ‹‹ይህን ለምን ሰራህ? ይህን ለምን አልሰራህም›› ብለውኝ አያውቁም፡፡

3) አነስ እንዲህ ብለዋል፡-

የሴት ባሪያ የአላህን መልእክተኛ እጅ ይዛ ወደፈለገችው ቦታ ትወስዳቸው ነበር፡፡ አንድ ሰው ከጨበጣቸው ከርሱ በፊት እጃቸውን አይመልሱም፡፡ ፊታቸውንም እርሱ እስካልዞረ ድረስ አያዞሩም፡፡ ጉልበቶቻቸውን አብሯቸው ከተቀመጠው ሰው አያስቀድሙም (ከርሱ ጋር እኩል ይሆናሉ፡፡ አይኮሩም፡፡) (ጦልሐ ቲርሚዚ)

4) አኢሻ እንዲህ ብለዋል፡-

የአላህ መልእክተኛ ሁለት አማራጮች ከቀረቡላቸው ሐጢአት እስካልሆነ ድረስ ገሩን ይመርጣሉ፡፡ ሐጢአት ከሆነ ግን ከማንም በላይ ይርቁታል፡፡ ለራሳቸው ጉዳይ ሲሉ ተቆጥተው አያውቁም፡፡ የአላህ ወሰን ሲደፈር ግን ይቆጣሉ፡፡ በአላህ መንገድ በሚደረግ ትግል ውስጥ ካልሆነ በቀር አገልጋያቸውን ወይም ሌላው ሰው መትተው አያውቁም፡፡ (ሙስሊም)

5) አነስ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡-

ከአላህ መልእክተኛ ጋር በመሄድ ላይ ነበርኩ። ወፍራም ኩታ ለብሰዋል፡ ፡ አንድ በደዊ አገኛቸው። በጣም ጎተታቸው። በጣም ስለጎተታቸው ከአንገታቸው ላይ የመፈግፈግ ምልክት ታየ። ከዚያም፡- ‹‹መሐመድ ሆይ፣ ካንተ ዘንድ ካለው የአላህ ገንዘብ እዘዝልኝ።›› አላቸው። የአላህ መልእክተኛም ወደርሱ ዞሩና ሳቁ። ገንዘብ እንዲሰጠውም አዘዙ። (ቡኻሪ)

6) ቃዲ አያድ እንዲህ ብለዋል፡-

ነቢዩ ከሰው ሁሉ ይበልጥ መልካም፣ ይበልጥም ጀግና ነበሩ። አንድ ሌሊት ላይ መዲና ውስጥ የሚያስደነግጥ ድምጽ ተሰማ። ሰዎች ድምጹን ወደሰሙበት አቅጣጫ ተመመ። የአላህን መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሲመለሱ አገኟቸው። የአቡ ጦልሐን ፈረስ ጋልበውና ሰይፍ አንግበው የሆነውን ለማጣራት ሄደው ኖሯል። ‹‹አይዟችሁ አትደንግጡ። ችግር የለም›› ሲሉም ሰዎችን አረጋጉ።

7) የአላህ መልእክተኛ ሁሌም ገጽታቸው ብሩህ፣ ባህሪያቸው ገራገርና ለስላሳ ነበሩ። ሸካራ ወይም ጨፍጋጋ አይደሉም። አይጮሁም። ብልግና አይናገሩም። ሂስም ሆነ ሙገሳ አያበዙም። የግድ የማያስፈልጋቸውን ነገር አይሹም። አንዳች ነገር ከርሳቸው ፈልጎ የሄደ አያጣም።

8) አኢሻ እንዲህ ብለዋል፡

ከአላህ መልእክተኛ ይበልጥ ጸባዩ መልካም የለም። ከባልደረቦቻቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው መካከል አንዱ ሲጠራቸው ምን ጊዜም፡- ‹‹ለበይክ›› ነበር የሚሉት።

9) አነስ እንዲህ ብለዋል፡-

የአላህ መልእክተኛ አንድ ሰው ከተገናኛቸው እርሱ እስኪዞር ድረስ እርሳቸው አይዞሩም።

10) የአላህ መልእክተኛ ዝምታ ያበዙ ነበር። አስፈላጊ ካልሆነ አይናገሩም። አግባብ ያልሆነ ቃል ከተናገረ ሰው ይገስላሉ። ሳቃቸው ፈገግታ ነበር። ንግግራቸው ያልረዘመና ያላጠረ ልከኛና ግልጽ ነበር።

መስሊሞች የርሳቸውን መልካም ስብእና በአርአያነት ይከተሉ ዘንድ አላህ እንዲህ ሲል አዟል፡-

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

‹‹የአላህ መልዕክተኛ፥ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፥ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ፥ መልካም አርአያ ነው።›› (አል አህዛብ 21)

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የመልካም ስነ ምግባርን ክብደትና አስፈላጊነት የሚያብራሩ ሐዲሶችን አስታውስ፡፡

2) ‹‹መልካም ስነ ምግባር የኢማን ፍሬ ነው፡፡›› ይህን ሐሳብ አብራራ፣

3) ‹‹መጥፎ ስነ ምግባር የኢማን ድክመት ምልክት ነው፡፡›› አብራራ፣

4) የታላቅ ስነ ምግባር ባለቤት ከሆኑት ነብይ ድንቅ ባህሪያት መካከል ጥቂቶችን ዘርዝር፡፡

* * *

የመልካም ስነ ምግባር ከፊል ገጽታዎች፣ መገለጫዎቻቸውና እነርሱን ለመጎናጸፍ የሚያስችሉ ስልቶች

አንደኛ፡- ሐያእ

የትምህርቱ ዓላማ

1) የሐያእን ትርጉም እና ባህሪ ማብራራት

2) የሐያእን ባህሪ ለመላበስ የሚረዱ ተግባራዊ እምጃዎችን መረዳት

3) የሐያእን ዓይነቶችና መገለጫዎች ማብራራት

4) የሐያእ አይነቶች በተናጠል እውን የሚሆኑባቸውን ስልቶች መረዳት

5) የሐያእን ባህሪ እንዴት መላበስ እንዳለበት ማብራራት

1) የሐያእ ትርጉም

ሐያእ በቋንቋ ደረጃ ሰውየው የሚያከናውነውን ተግባር ከመፈጸም መጠንቀቁና መቆጠቡ ሐያእ ይባላል። በሸሪዓ ደረጃም፡- እኩይን ከመስራትና ግዴታን ካለመወጣት የሚያቅብ ውስጣዊ ባህሪ ነው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ኢማን ከስልሳ በላይ ዘርፎች አሉት። ሐያእ ከኢማን ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው።›› (ቡኻሪ)

ሐያእ ያለው ሰው በሐያኡ ከወንጀል ይታቀባል። ስለዚህም ልክ እንደ ኢማን በርሱና በሐጢአት መካከል ግርዶ ይሆንለታል። ሐያእ የኢማን አካል ነው የተባለው የኢማን አላማ የአላህን ትእዛዝ ለመፈጸም እና የከለከለውን ለመታቀብ ስለሚያደርስ ነው። ይህ ባህሪ በሐያእ አማካይነት ስለሚገኝ ሐያእ የኢማን አካል ተሰኝቷል።

ሐያእ የላቀ ስነ ምግባር፣ ሙስሊም ሊላበሳቸው ከሚገቡ መልካም ባህሪያት መካከል ታላቁ፣ የምጡቅ ጸባያት ፈርጥ ነው። የአላህ

መልእክተኛ ሐያእን የሙስሊም መለያ ባህሪ እስከማድረግ ክብር ችረውታል። እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እያንዳንዱ ሐይማኖት መለያ ስነ ምግባር አለው። የኢስላም መለያ ስነ ምግባር ሐያእ ነው።›› (ቢን ማጃህ)

የአላህ መልእክተኛ የሐያእን ክብር ከሁሉም በላይ ከፍ በማድረግ የመልካም ነገሮች ሁሉ ጓል፣ የስኬት መሠረት፣ የመዳን ዓይነተኛ መስፈርት አድርገውታል። እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሐያእ ሁለ ነገሩ መልካም ነው።›› (ሙስሊም)

‹‹ሐያእ ውጤቱ መልካም እንጅ ሌላ አይሆንም።›› (ቡኻሪ)

ሙእሚን ከምንም በፊት ትኩረት የሚችረው ለሸሪዓው እይታ ነው።

ሐያእ ማለት በሸሪዓው ሚዛን ነውር ከሆነ ነገር መታቀብ ነው። ያን ነገር ሰዎች ነውር አድርገው ባያዩትም። ለምሳሌ ገደብ አልባ የጾታዎች መቀላቀልን አንዳንድ ሰዎች ነውር አድርገው አያዩትም። ግና ሸሪዓው ከልክሎታል።

በሌላ በኩል ሰውየው ባልንጀሮቹን ወይም በሕብረተሰቡ ዘንድ ክብር ያላቸውን ወገኖች መጥፎ ድርጊት ሲፈጽሙ ለመገሰጥ ሳይደፍር ሲቀር፣ ለክብራቸው ወይም ወዳጅነታቸውን ላለማጣት ሲል በመልካም የማዘዝና ከመጥፎ የመከልከል ሐላፊነቱን ችላ በማለት በሸሪዓው ኪሣራ ከነርሱ ጋር ሲግባባ፣ ሰዎች ሐያእ ያለው አድርገው ይቆጥሩታል። ግና ይህ ድርጊቱ በሸሪዓው ሐያእ አይሰኝም። ፈጻሚውም ይሉኝተኛ ሊባል አይችልም። ይልቁንም ደካማና ፈሪ ነው።

የሐያእ ባህሪ

ሐያእ ተፈጥሯዊና በጥረት የሚገኙ ገጽታዎች አሉት።

ሀ) ተፈጥሯዊ፡- አላህ በሁሉም ሰዎች ልቦናዎች ውስጥ ያስቀመጠው ባህሪ ነው። ተፈጥሮው ያልተበከለና ያልተዛባ ሁሉ ይህ የሐያእ ገጽታ ይኖረዋል። ለምሳሌ ሐፍረተ ገላን ለመግለጥ ማፈር።

ለ) በጥረት የሚገኝ፡- በአላህ በማመን፣ ሐይማኖቱን በመከተል፣ የተለያዩ ስነ ስርዓቶችንና ስነ ምግባሮችን በመማር የሚወረስ ባህሪ ነው፡፡ ሙእሚን አላህን በመፍራት ከወንጀል እንዲታቀብ የሚያደርገውም ይህ ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ዝንባሌና ዝግጁነት ለተሟላ ሐያእ መሠረት መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ዓይናፋርነት ባህሪያቸው የሆኑ ግለሰቦችን እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል በባህሪያቸው ሲበዛ አይናፋር የሆኑም እናገኛለን፡፡ በእርግጥ አይናፋርነት የሐያእ አይነተኛ ንጥረ ነገር መሆኑ ቢታወቅም ከበጎም ከክፉም ድርጊት ላይ ሊጥል ይችላል፡፡ ግና ሐያእ የሚሰኘው የሸሪዓውን ወሰን የጠበቀው ብቻ ነው፡፡[1]

ሐያእ በአራት ቃላት

አብደላህ ቢን ሙሐመድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ፡- ‹‹ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ ይኑርህ፡፡›› በማለት ተናገሩ፡፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ እኛ ሐያእ እናደርጋለን፡፡ አላህ የተመሰገነ ይሁን›› አልናቸው፡፡ ‹‹ይህን ማለቴ አይደለም፡፡ አላህ ትክክለኛ ሐያእ ማድረግ ማለት ራስንና እርሱ የያዘውን፣ ሆድንና የቋጠረውን መጠበቅና መጠንቀቅ፣ እንዲሁም ሞቶ መበስበስን ማስታወስ፣ ነው፡፡ አኼራን የፈለገ የዱንያን ጌጥ ይተው፡፡ እነዚህን የፈጸመ ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ አለው፡፡›› ሲሉ አስረዱን፡፡ (ቲርሚዚ)

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በዚህ ሐዲሳቸው ውጫዊና ውስጣዊ የስብእናን ክፍል ያሳተፈን የሐያእ ትክክለኛና ሁለንተናዊ ገጽታ ያብራሩልናል፡፡ ሙስሊምን የምሉእ ሐያእ ባለቤት ሊያደርገው የሚችልን የኢማናዊ ሕሊና ንቃት ይገልጹልናል፡፡

ሙስሊሞች ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ እንዲኖራቸው ነቢዩ አዘዙ፡፡ የሶሐቦች ምላሽ ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ የሚገልጽ ነበር፡፡ ‹‹እኛ ሐያእ አለን፡፡›› አሉ፡፡ በእርግጥ እውነት ብለዋል፡፡ ከነርሱ በላይ ሐቀኛ ላሳር ነው፡፡ ቀጥሎ ለዚህ ሐያእና ቅን መመሪያ ያበቃቸውን አላህን አመሰገኑ፡፡ ነቢዩ

[1] ሙሐመድ አልገዛሊ- ኹሉቁል ሙስሊም

ግን የሐያእን ሌላ ገጽታ ሊያወጓቸው ፈለጉ። ‹‹ይህን ማለቱ አይደለም›› በማለት ጀመሩና ከላይ የሰፈረውን ማብራሪያ ሰጡ። ትክክለኛና የተሟላ ሐያእ በነፍስ ውስጥ ይጸና ዘንድ አራት ነገሮች አስፈላጊ መሆናቸውን ነቢዩ አብራርተዋል። እነርሱም፡-

ሀ) ራስንና የያዘውን መጠበቅ፣

ለ) ሆድንና የቋጠረውን መጠንቀቅ፣

ሐ) ሞቶ መበስበስን ማስታወስ፣

መ) የዱንያን ጌጥ መተው፣

1) ራስንና እርሱ የያዘውን መጠበቅ

ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ የመጀመሪያው መገለጫ ራስን (አእምሮን) ለወንጀል አለመጠቀም፣ ከአላህ ውጭ ለሌላ አለመስገድና አለማጎብደድ፣ ራስን በኩራት ከፍ አለማድረግ ነው። እንደዚሁም እርሱ የያዛቸውን፣ ማለትም ዓይንን፣ ምላስን፣ ጆሮን ለሐራም አለመገልገል፣ አእምሮ የቋጠረውንና ወደ ውጭ የሚያወጣውን መረጃ በአግባቡ መጠቀምን ሁሉ ያጠቃልላል።

ተግባራዊ እርምጃዎች

ራስንና የያዛቸውን አካላት እንዴት እንጠብቃለን?

1) ከአላህ ውጭ ለሌላ አካል አለማጎብደድ፣ በሶላት ውስጥ አለመዟዟር

2) እይታን ከሐራም መጠበቅና ሰውን አለመሰለል። (የሰውን ነውር አለማነፍነፍ)

3) ዩኒቨርሱንና የአላህን ድንቅ ችሎታ ማስተዋልና ማስተንተን

4) ሐሜት፣ ነገር ማሳበቅ፣ ብልግናና መሰል ሐራሞችን አለማድመጥ

5) ቅንድቦችን መላጨት፣ ጥርስን ማስፈንጨትና መሰል ሐራም ጌጦችን አለማጌጥ።

6) ከአልባሌ ነገሮች መራቅና ቁርአንን አዘውትሮ ማዳመጥ

7) አስካሪ መጠጥ፣ አደንዛዥ እጽና ሌሎችንም አእምሮን የሚያደንዙ ነገሮችን መራቅ

2) ሆድና የቋጠረው

ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ ሁለተኛው መገለጫ ሆድን አላህ በከለከለው ነገር ከመሙላት መታቀብ ነው። ሆድ (በጥን) የሚለው ቃል ውስጣዊ ማንነትን ሊያመለክት ይችላል። የላያዊ ማንነት ተቃራኒ ነው። ወይም የሆድ እቃዎችን የያዘውን የአካል ክፍል ሊያመለክት ይችላል። ቀልብንና ብልትንም ዓረቦች ‹‹በጥን›› ይሏቸዋል። ስለዚህም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ከሐራም መጠበቅ የሐያእ አብይ አካል ነው።

ተግባራዊ እርምጃ

ሆድንና የቋጠረውን እንዴት እንጠብቃለን?

1) አላህን ስለጸጋዎቹ ማመስገን፣

2) ቀልብን ከክህደት፣ ከሽርክ፣ ከኒፋቅ መጠበቅ። እንደዚሁም ኩራት፣ ይዩልኝ፣ በራስ መደነቅ፣ ምቀኝነት፣ ጥላቻ፣ የመታወቅ ጉጉትና መሰል የቀልብ በሽታዎችን መጠንቀቅ፣

3) ሐላል ለመመገብ መትጋት፣

4) የአመጋገብን ሱንና መከተል፣ ይህውም ከሆዳችን ሲሶውን ለምግብ፣ ሲሶውን ለመጠጥ እና ቀሪውን ሲሶ ለአየር መጠቀም።

5) ብልትን ከሐራም መጠበቅ፣

6) ሳቅን ማብዛት ቀልብን ይገድላልና ከርሱ መጠንቀቅ፣

3) ሞቶ መበስበስን ማስታወስ

ለአላህ ትክክለኛ ሐያእ ሦስተኛው መገለጫ ሞቶ መበስበስ መኖሩን ማስታወስ ነው። ይህም ትውስታ አላህን ለመፍራት ይረዳል። ሰውየው

የሕልውናውን ዓይነተኛ ምክንያት እንዲያስታውስም ይረዳዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَٰكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ ﴿١١٥﴾ ﴾ المؤمنون: ١١٥

"የፈጠራችሁ ለቀልድ እንደሆነና እናንተም ወደኛ እንደማትመለሱ ገመታችሁን? (አል ሙእሚኑን 116)

﴿ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ ﴾ الذاريات: ٥٦

‹‹አጋንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።›› (አል ዛሪያት 56)

የሰው ልጅ ሞትን ማስታወሱ በልቦናው ውስጥ ሐያእ እንዲፋፋ እና ወደ መላ ሰውነቱም እንዲሰራጭ ይረዳዋል። አስተዋይ ለሆነ ሰው ስብእናውን ለመግራትና ከአንጉል ድርጊቶች በላይ ለመሆን ሞትን ማስታወስ ብቻ በቂው ነው። ወንጀል ከመፈጸም ተስፋ ለመቁረጥ እና ለበጎ ስራ ለመቻኮል በሞት ከማመን የተሻለ አነሳሽ የለም።

ተግባራዊ እርምጃዎች

ሞቶ መበስበስን እንዴት እናስታውሳለን?

1) ጣእረ ሞትን፣ ቀብርንና የቂማን ትእይንቶች ዘወትር ማስታወስ

2) በሽተኞችን መጎብኘት እና ካሉበት ሁኔታ ትምህርት መቅሰም

4) የዱንያን ጌጦች መተው

ይህ ማለት አላህ ለባሮቹ መጠቀሚያነት ይፋ ያደረጋቸውን ጌጦች (ጸጋዎች) ኢስላም ይከለክላል ማለት አይደለም። እዚህ ላይ ማለት የተፈለገው በሐራም ከማግኘትና ለሐራም ከመገልገል መጠንቀቅ ነው።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قُلۡ مَنۡ حَرَّمَ زِينَةَ ٱللَّهِ ٱلَّتِيٓ أَخۡرَجَ لِعِبَادِهِۦ وَٱلطَّيِّبَٰتِ مِنَ ٱلرِّزۡقِۚ قُلۡ هِيَ لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا خَالِصَةٗ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٣٢ قُلۡ إِنَّمَا حَرَّمَ رَبِّيَ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَ وَٱلۡإِثۡمَ وَٱلۡبَغۡيَ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ وَأَن تُشۡرِكُواْ بِٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ سُلۡطَٰنٗا وَأَن تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٣٣ ﴾ الأعراف: ٣٢ - ٣٣

‹‹በላቸው፡- “ያችን ለባሮቹ የፈጠራትን የአላህ ጌጥ፥ ከሲሳይም መልካሞቹን እርም ያደረገ ማን ነው?” በላቸውም፡-“እርሷ በዚህች ዓለም ለአማኞች የተዘጋጀች ናት። በመጭውም ዓለም የነርሱ ብቻ ናት።” አንቀጾችን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ለዐዋቂዎች እናብራራለን። “ጌታዬ እርም ያደረገው በግልጽም ይሁን በስውር የሚፈፀሙ ፀያፍ ተግባራትን፣ ኃጢአትን፣ ያለ አግባብ የሚፈፀምን በደል፣ ቅንጣት (የተጋሪ ነት) መብት የሌለውን አካል በአላህ ማጋራታችሁንና በአላህ ላይ የማታውቁትን ማለታችሁን ነው።” በላቸው።››› (አል አዕራፍ 32-33)

﴿ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِي ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٗ وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِ حَسَنَةٗ وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ٢٠١ ﴾

“ጌታችን ሆይ! በቅርቢቱ ዓለም መልካም ነገርን በመጨረሻይቱም ዓለም መልካም ነገርን ለግሠን። ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።” (አል በቀራህ 201)

ተግባራዊ እርምጃ

የዱንያን ጌጦች እንዴት እንተዋለን?

1) ከሐራም ሙሉ በሙሉ መራቅና የተፈቀዱ ነገሮችን አብዝቶ አለመጠቀም

2) አላህን ስለ ወሰነልህ ሲሳይ ማመስገን

3) የባለሐብቶችን ጸጋ አለመመልከት እና እንደነርሱ መሆንን አለመመኘት

4) የመጭውን ዓለም ጸጋ ከአላህ መለመን

ሐያእ ሁለ ነገሩ መልካም ነው

አንዳንድ ሰዎች ሐያእን ከሌላ ነገር ጋር ሲያሳክሩ ይስተዋላሉ። ወይም ከሌላ ባህሪ ጋር እንደሚጋጭ ያስባሉ። አንዳንዶቹ ሐያእን የስነ ልቦና ድክመትና ፍርሃት ወይም የይዩልኝ ባህሪ መገለጫ አድርገው ይወስዱታል። ግና ሐያእ ከነዚህ ሁሉ የተለየ የእስልምና ትልቅ ዘርፍ ነው። የአላህ መልእክተኛ የኢማንን ዘርፎች ሲያወሱ ሐያእን አውስተውታል። እንዲህ ብለዋል።

‹‹ኢማን ከሰባ ወይም ከስልሳ በላይ ዘርፎች አሉት። ከፍተኛው ላኢላሐ ኢለላህ የሚለው ቃል ሲሆን ዝቅተኛው ከመንገድ ላይ እንቅፋትን ማስወገድ ነው። ሐያእ የኢማን ዘርፍ ነው።›› (ሙስሊም)

እንዲህም ብለዋል፦

‹‹ሐያእ ሁለ ነገሩ መልካም ነው።›› (ሙስሊም)

‹‹ሐያእ ውጤቱ መልካም እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም።›› (ቡኻሪ)

ስለዚህ ሐያእ ከላይ የተወሱ አሉታዊ ባህሪያትን ፈጽሞ ሊይዝ አይችልም።
የሐያእ ባለቤት ከማንም በላይ ለመብቱ ቀናኢና ለሐቅ ተሟጋች፤ በዚህ ሂደትም የተችዎችን ትችት የማይፈራ ጽኑ ሰብእና ነው።

የሐያእ አይነቶችና መገለጫዎች

አላህን ሐያእ ማድረግ

የአላህ መልእክተኛ ለአንዱ ባልደረባቸው እንዲህ ብለውታል፦

‹‹ከወገኖችህ መካከል በጎ የሆነን ሰው ሐያእ እንደምታደርገው አላህንም ሐያእ እንድታደርግ እመክርሐለሁ።›› (ጦበራኒና በይሐቂ)

አንድ ሰለፍ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ ባንተ ላይ ባለው አቅም መጠን ፍራው፡፡ ካንተ ባለው ቅርበት መጠንም ሐያእ አድርገው፡፡››

አንድ በጎ ሰው አላህን ሐያእ ስለማድረግ ትርጉም ተጠይቀው እንዲህ አሉ፡- ‹‹አላህን ሐያእ ማድረግ በሦስት ባህሪያት ይገለጻል፡-

- አንተ አጥፊና ወንጀለኛ ሆነህ እያለህ አላህ ዘወትር በጎ እንደሚውልልህ ማስተዋል
- እያንዳንዱ እንቅስቃሴህ በአላህ እይታ ስር መሆኑን ማወቅ
- ከአላህ ፊት ቆመህ ለተግባሮችህ ሁሉ -ከትንሽ እስከ ትልቅ- እንደምትጠየቅ ማስታወስ፡፡

አላህን ሐያእ ማድረግ ከሁለት ይከፈላል፡፡

ሀ) የጥፋት ሐያእ፡- ከሐጢአተኝነት ስሜት የሚመነጭ፣ ወንጀል ከፈጸሙ በኋላ የሚከሰት ሐያእ ስሜት ነው፡፡ አደም እንዳይመገቡ የታዘዙትን ዛፍ ከበሉ በኋላ ከጀነት ወጥተው ሲሄዱ ይህ ስሜት ተሰምቷቸዋል፡፡ ይህውም በፍጥነት አፈተለኩ፡፡ አላህም፡- ‹‹ከኔ እየሸሸህ ነውን?›› ሲል ጠየቃቸው፡፡ እርሳቸውም፡- ‹‹አይደለም፡፡ ጌታዬ ሆይ፣ (የሸሸሁት) አንተን ሐያእ ስላደረግኩ ነው፡፡›› በማለት መለሱ፡፡

ለ) ሐላፊነትን ያለመወጣት ሐያእ፡- የአላህን መብት አላደረስኩም፣ ሐቁን አልተወጣሁም፣ እንደሚገባው አላመለኩትም ከሚል ስሜት የሚመነጭ ሐያእ ነው፡፡ አላህ እንዲህ በማለት የገለጻቸው መላእክት ይህ ስሜት ተሰምቷቸዋል፡፡

﴿ يُسَبِّحُونَ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ لَا يَفۡتُرُونَ ٢٠ ﴾ الأنبياء: ٢٠

‹‹ሌት ከቀን ያመሰግኑታል። ረፍት የላቸውም።›› (አል አንቢያእ 20)

﴿لَّا يَعۡصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمۡ وَيَفۡعَلُونَ مَا يُؤۡمَرُونَ ٦﴾ التحريم: ٦

‹‹ አላህን፥ ያዘዛቸውን ባለመፈፀም አይወነጅሉም። የታዘዙትን (በትክክል) ይፈጽማሉ። (አል ተህሪም 6)

ይህም ሆኖ ግን ለአላህ እንዲህ ብለውታል፡-

‹‹በትክክል አላመለክንህም፡፡››

አቡ ሐኒፋ የሌሊቱን ግማሽ በሶላት ያሳልፉ ነበር፡፡ አንድ ቀን በመንገድ ሲያልፉ ሰዎች ወደርሳቸው እየጠቆሙ፡- ‹‹ይህ ሰው ሌሊቱን ሙሉ በሶላት ያሳልፋል›› በማለት ሲያንሾካሹኩ ሰሙ፡፡ ‹‹ሰዎች በሌለኝ በጎ ባህሪ ያሞግሱኛል፡፡›› አሉና ከዚያ ቀን ጀምሮ ሌሊቱን ሙሉ በሶላት ማሳለፍ ጀመሩ፡፡ እንዲህም አሉ፡-

‹‹አላህን ሐያእ ስለማድረግ እርሱን በማምለክ ረገድ የሌለኝን ባህሪ ሰዎች ሊያወሱብኝ አልሻም፡፡››

ሐ) የማላቅ ሐያእ፡- የአላህን ልእልናና ልቅና በጥልቀት ከመረዳት የሚመነጭ ሐያእ ነው፡፡ ሰውየው አላህን የበለጠ ባወቀው ቁጥር ሐያኡ የዚያኑ ያህል ይበረታል፡፡ ሱራፊል የተባለው መላእክ አላህን ሐያእ አድርጎ በክንፎቹ መጠቅለሉ ይነገራል፡፡

አቡበክር ሲዲቅ ወደ መጸዳጃ ቤት ሲገቡ አላህን ሐያእ በማድረግ አንገታቸውን ይደፉ ነበር፡፡

አስወድ ቢን የዚድ ነኽኤይ ጣእረ ሞት ላይ እያሉ አለቀሱ፡፡ ‹‹ለምን እንደዚህ ተከፉ?›› የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ ‹‹እንዴት አልከፋ? ከኔ ይበልጥስ ለመከፋት ተገቢ ማን አለ? አላህ እንደሚምረኝ ቢነገረኝ እንኳ ለሰራሁት ወንጀል አፍረዋለሁ፡፡ በሰው ላይ ጥፋት የፈጸመ እንኳ ተበዳዩ ይቅር ብሎት እያለ እርሱ ግን በሐፍረት ይሸማቀቃል፡፡›› አሉ፡፡

መ) የልመና ሐያእ፡- አንድ ሰው አላህን አንዳች ጉዳይ በሚጠይቅ ጊዜ ራሱን እሳንሶ ከማየቱ የሚመነጭ ሐያእ ነው። ሙሳ እንዲህ በማለት ይህን የሐያእ ስሜታቸውን ገልጸዋል፡-

‹‹አምላኬ ሆይ፣ አንድ ዓለማዊ ጉዳይ ይገጥመኝና አንተን ለመለመን አፍራለሁ።›››

አላህም እንዲህ አላቸው፡-

‹‹ሙሳ ሆይ፣ መሰሰቴ ሳያሰጋህ ትልቅ ነገር ጠይቀኝ። ትንሽ ነገር ለመጠየቅም አትፈር። ያሻህን ጠይቀኝ። ለፍየሎችህ ግጦሽ ሳይቀር ለምነኝ።›› (ሐኪምና ቲርሚዚ)

ሰዎችን ሐያእ ማድረግ

እነርሱን ከማወክና ወንጀልን በአደባባይ ከመፈጸም በመታቀብ ይገለጻል። አነስ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሰዎችን ሐያእ ያላደረገ አላህን ሐያእ አያደርግም።››

ሰዎችን ሐያእ ማድረግ የሚከተሉት ክፍሎች አሉት፡-

ሀ) የደግነት ሐያእ፡- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ሶሐቦቻቸውን ለዘይነብ ሰርግ ግብዣ ጠሩ። ሶሐቦችም ከነቢዩ ቤት ለረኻቦም ጊዜ ቆዩ። እርሳቸውም ‹‹ሂዱ›› ለማለት ይሉኝታ (ሐያእ) ያዛቸው። ይህን በተመለከተም አላህ ለሶሐቦች መመሪያ አወረደ። ይህ (ይሉኝታ) ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ደግነት የመነጨ ነው።

ለ) የአይናፋርነት ሐያእ፡- ዓሊይ ቢን አቢ ጧሊብ ስለ መዝይ[1] ጉዳይ ነቢዩን መጠየቅ ፈለጉ። ግና የሚስታቸውን አባት ነቢዩን በቀጥታ መጠየቅ አልደፈሩም። ሐፍረት (ለሐያእ) ያዛቸው። እናም ሚቅዳድን

[1] መዝይ የወሲብ ሰሜት በሚነቃቃ ጊዜ ከብልት የሚወጣ ቀለም አልባ ፈሳሽ ነው።

ላኩት፡፡ ወንድ ልጅ የባለቤቱን ዘመድ ከወሲብ አጀንዳ ጋር የተያያዘ ነገር ማውጋት አይፈልግም፡፡ አሊ ይህን ክስተት ሲያወጉ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መዝይ ይበዛብኝ ነበር፡፡ ነቢዩን የሚስቱ አባት ስለሆኑ ልጠይቃቸው አፈርኩ፡፡ ሚቅዳድንም ላክኩት፡፡ ጠየቃቸው፡፡ ‹‹ብልቱን ይጠብና ውዱእ ያድርግ›› ሲሉ መለሱለት፡፡›› (ሙስሊም)

ሐ) የልቅና ሐያእ፡- ለራሱ ክብርና ልቅና የሚሰማው ሰው ከደረጃው ያነሰ ችሮታ እና ጥረት ሲያሳይ ሐፍረት ይሰማዋል፡፡ ይሉኝታ ይይዘዋል፡፡ ሰጭው እርሱ ሆኖ እያለ ልክ እንደተቀባይ በሐያእ ይሸማቀቃል፡፡

ሰዎችን እንዴት ሐያእ እናደርጋለን?

ተግባራዊ እርምጃዎች

- ✓ ከነርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት አላህ በሸሪዓው ባስቀመጠው መልክ ማድረግ፣
- ✓ አለማዊ ጉዳይ አለመጠየቅ፣
- ✓ ከነርሱ ጋር ባለን ግንኙነት ሸሪዓዊ ጉዳዮችን መከተል፡፡

ራስን ሐያእ ማድረግ

ክብርና ልቅና ያላቸው ሰዎች ነፍሳቸውን ለማስደሰት ወደታች በመውረዳቸው፣ እርሷን ለማግባባት ዝቅ በማለታቸዉ የሚሰማቸው የሐያእ ስሜት ነው፡፡ ይህ ሲሆን ሰውየው ራሱን ያፍራል፡፡ ከነፍሱ ይሉኝታ ይይዘዋል፡፡ አንደኛዋ ሌላኛዋን የምታፍር ሁለት ነፍሶች ያሉት ይመስል፡፡ ይህ በእርግጥ ምሉእ የሐያእ ደረጃ ነው፡፡ አንድ ሰው ራሱን ካፈረ ሌሎችን የማፈር ባህሪው ይበልጥ የጎለበተ ይሆናል፡፡

ራስን ሐያእ የማድረግ መገለጫ ቁጥብነትና ከሰው ተገልሎም ቢሆን አልባሌ ነገር ከመስራት መታቀብ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሰዎች ቢያዩብህ የምትጠላውን ድርጊት ብቻህን ስትሆን ጊዜም አትፈጽመው፡፡›› (ቢን ሂባን)

አንድ ዓሊም እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በይፋ ቢሰራው የሚያፍርበትን ድርጊት ለነፍሱ ክብር ሳይሰጥ ለብቻው የፈጸመ ነፍሱን ከማንም በላይ ንቋታል፡፡››

ለራሳችን እንዴት ሐያእ ይኖረናል?

- ነፍሳችን አላህን እንድትወነጅል እና ወደ እሳት እንድታዘግም አለመፍቀድ
- ከሰው ተከልለን ብቻችን የምንሆንባቸውን ጊዜያት አላህን ከሚያስቆጡ ድርጊቶች መጠበቅ፡፡
- ከእኩይ ድርጊቶች እና መጥፎ ስነ ምግባሮች ራሳችንን መጠበቅ

አንድ ሰው ከላይ ተዘረዘሩትን ሦስቱንም የሐያእ ዓይነቶች፣ ማለትም ከአላህ፣ ከሰዎችና ከራሱ ጋር ሐያእ ሲያጎለብት የኸይር ነገሮችን ሁሉ ሰበብ አሟልቷል፡፡ የክፋት ሰበቦችም ከርሱ ዘንድ ተወግደዋል፡፡ በልቅናው የሚታወቅ፣ በጥሩ አድራጎቱ የሚወሳ ይሆናል፡፡ ሸህ መሐመድ አልገዛሊ ‹ኹሉቁል መስሊም›› በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሐያእ የሰው ልጅ ባህሪ አስኳል ነው፡፡ የእምነቱን ዋጋ እና የአደቡን ደረጃ ያመለክታል፡፡ አንድ ሰው ለርሱ ተገቢ ያልሆነን ነገር ከመስራት ሲቆጠብ ወይም ደግሞ አግባብ ያልሆነ ድርጊት በመፈጸሙ ፊቱ በሐፍረት ሲቀላ ካየህው ሕሊናው ንቁ፣ ውስጡ ሰላም፣ ልቦናው ጽዱ መሆኑን እወቅ፡፡ በሌላ በኩል ስሜቱ የደነዘ፣ ለድርጊቶቹ ደንታ የሌለው ሰው ካየህ እርሱ በእርግጥ በጎ ነገር የለበትም፡፡ ወንጀል ከመስራት፣ ቆሻሻ ድርጊት ከመፈጸም የሚታደገው ሐያእ እንደሌለውም ተረዳ፡፡››[1]

[1] ኹሉቁል መስሊም- ሸህ መሐመድ አልገዛሊ

በመጨረሻም ስነ ምግባር በተልእኮ ትምህርት ወይም በትእዛዝ ከልቦና ውስጥ ሊጸና እንደማይችል ማስታወስ እንወዳለን። ፍሬያማ ስነ ምግባር ረዥም ትምህርትና ስልጠና ይሻል። ዘወትራዊ ልምምድ ይፈልጋል። በተጨማሪም ባዶ ምኞትን ሳይሆን ከልብ የሆነ ውሳኔን፣ ጽናትንና ተግቶ መስራትን ይጠይቃል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡۗ﴾ الرعد: ١١

‹‹አላህ ሰዎች የሚኖሩበትን ሁኔታ፥ እነርሱ ውስጣቸውን እስካልቀየሩ ድረስ፥ አይቀይርም።›› (አል ረዕድ 11)

እንደዚሁም ስነ ምግባር በልቦና ላይ በድንገት አይሰፍርም። ጠንካራና የጎለበተ ሆኖም አይወለድም። ስርጸቱ ጊዜ ይሻል። አድጎ የሚጎለብተው በሂደት ነው። እኩይ ባህሪያት ዘወትር እንደሚፈታተኑ፣ ውሎን ውል ለማስሳት በየጊዜው እንደሚያስቸግሩ ይታወቃል። ስለዚህም በአንድ ጊዜ ሕክምና ክፋታቸው አይገታም። ሽንኩፋቸው አይነቀልም። የነርሱን ጥንካሬ የሚመጥን የረዥም ጊዜ ሕክምና ይፈልጋሉ። ይህ ሲሆን መድሐኒቱ ውጤት ያመጣል።

ሰውየው ነፍሱን ለማጽዳት፣ ለማስተካከልና የአላህን ውዴታ የሚያጎናጽፉ በጎ ባህሪያትን ለመላበስ ከሚያደርገው ጥረት የበለጠ ግሩምና ከአላህ ዘንድ የሚያስመሰግነው ድርጊት አልፈጸመም።

የሐያእን ባህሪ ለመላበስ

ወደ ሐያእ የሚያደርስ መርሃ ግብር

በዚህ መርሐ ግብር ውስጠ የሐያእ ባህር አበይት መገለጫዎችን በዝርዝር አስቀምጠናል። እነዚህን መገለጫዎች በገቢር ካዋልክ- በአላህ ፈቃድ- በልቦናህ ውስጥ የሐያእን ባህሪ ለማስረጽ በምታደርገው ጥረት ጥሩ እርምጃ ተራምደሐል።። መርሐ ግብሩ በስምንት ሳምንታት ተከፋፍሎ እንደዲተገበር ተደርጎ የተሰናዳ ነው። ይህውም፡-

1) በእያንዳንዱ ሳምንት የሚተገበሩ የሐያእ መገለጫዎች ተዘርዝረዋል።

2) እነዚህ መገለጫዎች በገቢር መዋላቸውን ለመፈተሽ በየቀኑ ምርመራ ይደረጋል።

3) የአንደኛውን ሳምንት መገለጫዎች በተገቢው መንገድ ሳይተገብሩ ወደ ቀጣዩ ሳምንት ክንውኖች መሸጋገር አይቻልም።

ሳምንት	ተግባር	ቀን							
		1	2	3	4	5	6	7	
1ኛ ሳምንት	1) አላህ ሐያእ ይለግስህ ዘንድ ዱዓ በብዛት ማድረግ፣ 2) በሁሉም ሁኔታዎች እውነትን ብቻ መናገር፣ 3) ስትናገር ድምጽህን ዝቅ ማድረግ፣ 4) የጎረቤትን ሚስጥር ከመስማት ጆሮን ማቀብ።								

2ኛ ሳምንት	1) አላህ እንደሚያየኝና አብሮነቱን ዘወትር ማስታወስ 2) ሐያእን የማያሳድፉ ስእሎች ያሉባቸውን ምርቶች አለመጠቀም 3) በትራንስፓርትና በገበያ ቦታዎች ላይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር አለመጋፋት												
3ኛ ሳምንት	1) በቀንና በሌሊት ሞትን ማስታወስ 2) ከሐሜትና ነገር ከማሳበቅ መጠበቅ 3) እይታን አላህ ከከለከለው ነገር ማቀብ 4) በር ሲከፈት ከፊት ለፊት አለመቆም።												

| | | |

7ኛ ሳምንት	1) በቂያማ ቀን ስለ ወንጀል የመጠየቅን ክብደትና አስከፊነት ማስታወስ 2) ወንጀልን መደበቅ 3) እንግዳ የቱን ያህል ቢበዛም እንደሸክም አለማየትና አለማማረር 4) በትራንስፖርትና በሌሎችም አገልግሎቶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተጠጋግቶ አለመቀመጥ፡፡											
8ኛ ሳምንት	1) ምላስን ከስድብ ማቀብ 2) ሐያእን በሚያጎድፍ ወግ ውስጥ አለመሳተፍ 3) ሴቶችና ወንዶች በአንድ ላይ የሚቀመጡበት አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር በመካከላቸው ግርዶ ማድረግ 4) ሐያእን የሚያጎድፍን ሰው ማውገዝ											

ማስታወሻ፡- በጥሩ ሁኔታ አከናውኘዋለሁ በምትለው ተግባር ፊት ለፊት ምልክት አድርግ፡፡ አላከናወንኩትም ወይም ክንውኔ ድክመት

አለበት ከምትለው ድርጊት ፊት ለፊት ደግሞ የ× ምልክት አድርግ። የዚህን መርሐ ግብር ውጤት ጣሪያውን ከፍ በማድረግ እና በሂደት ከሚፈለገው ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ደጋግሞ መሞከር ይቻላል።

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የሐያእን ትርጉምና ባህሪ አብራራ

2) ሐያእን በገቢር ለማዋል የሚያስችሉ ስልቶችን አብራራ

3) የሐያእን የተለያዩ ገጽታዎች በተግባር የማዋልህን ውጤት ፈትሽ። ደካማ ጎኖችህን ነቅሰህ አውጣ። ድክመትህን ለማረም ልትወስዳቸው ያሰብካቸውን እርምጃዎች አብራራ

4) የሐያእን አይነቶችና መገለጫዎች አብራራ

4) እያንዳንዷ የሐያእ አይነት በምን መልኩ በተግባር እውን ሊሆን እንደሚችል አብራራ

5) የሐያእን ባህሪ እንዴት መላበስ እንደሚቻል አብራራ

6) የሐያእ ዓይነቶችን በገቢር የማዋልህን መጠን መዝን። ደካማ ጎኖችህን ነቅሰህ አውጣ። ድክመትህን ለማሻሻል ልትወስዳቸው ያሰብካቸውን እርምጃዎች ዘርዝር።

ቁጥብነት (ተዓፉፍ)

የትምህርቱ ዓላማ

- የቁጥብነትን ትርጉም ማወቅ
- የቁጥብነት (ዒፍፉ) ዓይነቶችን መረዳት
- ቁጥብነትን ከሚመለከቱ ሐዲሶች መካከል የተወሰኑትን ማስታወስ
- ከነቢዩ፣ ከሶሐቦችና ከደጋግ ሰዎች ታሪክ ውስጥ የቁጥብነት ናሙናዎችን መዘርዘር

የቁጥብነት ትርጉም

ሀ) ቋንቋዊ ትርጉም፡- ቁጥብነት በቋንቋ ደረጃ ‹‹ከመጥፎ ነገር መታቀብ›› ማለት ነው፡፡ ቢን ሙንዚር እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ቁጥብነት ሐላል ካልሆኑ ነገሮች መቆጠብ፣ ከወንጀል ጉድፍ መንጻት ነው፡፡››

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَلْيَسْتَعْفِفِ ٱلَّذِينَ لَا يَجِدُونَ نِكَاحًا حَتَّىٰ يُغْنِيَهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضْلِهِۦ ﴾ النور: ٣٣

‹‹እነዚያ ለጋብቻ አቅም የሌላቸው አላህ በችሮታው ብቁ እስኪያደርጋቸው ድረስ (ከዝሙት) ይጠበቁ፡፡›› (አል ኑር 33)

ማለትም በጾምና መሰል ክንውኖች ስጋዊ ስሜቱን ይቆጣጠር ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ጾም ስሜትን ይሰብራል፡፡ በሐዲሱም ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ቁጥብነትን የፈለገ አላህ ይለግሰዋል፡፡››

ቁጥብነት አንድን ነገር መታገስ እና ከርሱ መንጻት ነው፡፡ ተከታዩ ሐዲስ ይህን ያሳያል፡-

‹‹አላህ ሆይ፣ ቁጥብነትንና ሐብትን እለምንሐለሁ፡፡››

ለ) ሸሪዓዊ ትርጉም፡- አልራጊቢ ቁጥብነትን እንዲህ ሲሉ ተርጉመውታል፡-

‹‹ቁጥብነት የሻህዋን ጉልበት መግታት የሚያስችል ውስጣዊ ባህሪ ነው፡፡››

እንዲህም ተተርጉሟል፡-

‹‹ቁጥብነት ከእንስሳዊ ባህሪና ድርጊት ራስን ማቀብ ነው፡፡››

አልሲበዊ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ቁጥብነት ሐላል ካልሆነ ነገር መታቀብ ነው።››

አልጃዚዝ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ነፍስን ከሻህዋ ማቀብ ነው።››

ዓይነቶቹ

ሀ) **ከሐራም መቆጠብ**[1]**-** ይህ ክፍል በርካታ ዓይነቶችን በውስጡ ይዟል፡-

1) **ብልትን መቆጣጠር**፡- ብልትን አላህ ከከለከለው ድርጊት መቆጣጠር የቁጥብነት አንዱ መገለጫ ነው። ምክንያቱም የብልትን ሐራምነት ሸሪዓው ያስጠነቀቀውና አእምሮም የሚያወግዘው መሆኑ እየታወቀ መዳፈር ግልጽ የሆነ እርቃንነት ነው።

2) **ምላስን መቆጠብ፡-** ማለትም አለመዋሸት፣ አለማማት፣ በሰዎች አለማፌዝ፣ መጥፎ ቃላትን መጠንቀቅ፣ በጥቅሉ ወደ ጥፋት የሚያደርሱ የምላስ በሽታዎችን መጠንቀቅ ነው። ምክንያቱም ምላስን አለመቆጣጠር የቂሎች ባህሪ፣ የጅላጆሎች የበቀል ስልት ነው።

3) **እይታን መቆጣጠር፡-** አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَلۡيَسۡتَعۡفِفِ ٱلَّذِينَ لَا يَجِدُونَ نِكَاحًا حَتَّىٰ يُغۡنِيَهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ ﴾ النور: ٣٣

‹‹እነዚያ ለጋብቻ አቅም የሌላቸው አላህ በችሮታው ብቁ እስኪያደርጋቸው ድረስ (ከዝሙት) ይጠበቁ። ›› (አል ኑር 33)

የጋብቻ እድል ያልተመቻቸላቸው አማኞች ቁጥብ እንዲሆኑ፣ ራሳቸውን ከብልግና እንዲጠብቁ፣ አላህ ከችሮታው እስኪለግሳቸው ድረስም በዚሁ ባህሪ እንደጸኑ እንዲቆዩ በዚህ አንቀጽ ታዘዋል። እይታን የመቆጣጠርን ግዴታነት በተመለከተም ግልጽ መልእክት በቁርአን ተላልፏል፡-

[1] የማውርዲን አከፋፈል መሠረት ያደረገ

﴿ قُل لِّلۡمُؤۡمِنِينَ يَغُضُّواْ مِنۡ أَبۡصَٰرِهِمۡ وَيَحۡفَظُواْ فُرُوجَهُمۡۚ ذَٰلِكَ أَزۡكَىٰ لَهُمۡۗ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا يَصۡنَعُونَ ٣٠ ﴾ النور: ٣٠

‹‹ለአማኝ ወንዶች እይታቸውን እንዲቆጣጠሩና ብልቶቻቸውን እንዲጠብቁ ንገራቸው። ይህ ለነርሱ ተመራጭ ነው። አላህ የሚሠሩትን (ሁሉ) ጠንቅቆ ያውቃል።›› (አል ኑር 30)

ቁርአን የቁጥብነትን ድንቅ ተምሳሌት በነቢ ዩሱፍ ታሪክ ውስጥ አስፍሮልናል። እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَرَٰوَدَتۡهُ ٱلَّتِي هُوَ فِي بَيۡتِهَا عَن نَّفۡسِهِۦ وَغَلَّقَتِ ٱلۡأَبۡوَٰبَ وَقَالَتۡ هَيۡتَ لَكَۚ قَالَ مَعَاذَ ٱللَّهِۖ إِنَّهُۥ رَبِّيٓ أَحۡسَنَ مَثۡوَايَۖ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٢٣ ﴾ يوسف: ٢٣

‹‹የሚኖርበት ቤት ባለቤትም ይገናኛት ዘንድ ፈለገች። እናም በራፎችን ሁሉ ዘጋች። "አሁን ና" አለችውም። "በአላህ እጠበቃለሁ። በእውነቱ (ባለ ቤትሽ) አሳዳሪዬ ነው። መኖሪያየንም መልካም አድርጐልኛል፤ (ሚስቱን ደፍሬ ልበድለው አልሻም)። እነሆ፥ በዳዮች አይድኑምና።" አለ።›› (ዩሱፍ 23)

4) **የሆድን ሻህዋ መቆጣጠር፡-** ከጨጓራ የመፍጨት አቅም በላይ የሆነ የምግብ መጓት ሆድን ማሸከም ለበርካታ በሽታዎች መንስኤ መሆኑ ይታወቃል። ይህም በመሆኑ በሐዲስ እንዲህ ተብሏል፡-

‹‹የአደም ልጅ ከሆዱ ይበልጥ ክፉ እቃ አልሞላም።።።››

የሆድ ባሪያ መሆን ተገቢ አይደለም። ይህም ማለት በዚህች ዓለም የመኖርን ዋነኛ ዓላማ ሆድ ማድረግ፣ የዘወትር ጥረት፣ የቀን ሐሳብ፣ የሌሊት ሕልም ማእድን በምግብ ዓይነቶች መመላት መሆን የለበትም።

ሐሳብና ጥረታቸው ሆዳቸውን መመላት የሆነ፣ ለዚህም የተለያዩ አዳዲስ የምግብ አበሳሰል ስልቶችን በመፍጠር የሚጠበቡ ወገኖች ለቁም ነገር አይበጁም። ጎታች ሐሳባቸው ለትግል እና ለመስዋእትነት እንዲንቀሳቀሱ አያደርጋቸውም።

ሰውየው ምክንያት አልባ በሆነ እቀባ ብቻ የምግብ ፍጆታውን መቀነስ አይችልም። ይህን ለማድረግ ትክክለኛው መንገድ ራስን ከትልልቅ ዓላማዎች ጋር ማስተሳሰርና እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት መጣር ነው።

ይህ ሲሆን ትኩረቱ ከርካሽ መዝናኛዎችና ጣፋጭ ነገሮች ይዞርለታል። ይህ ማለት ግን ሰውየው ከሕይወት እነዲርቅ ኢስላም ይሻል ማለት አይደለም። ሐላልን ሐራም ማድረግ፣ ሐራምን ሐላል›› ማድረግ የማይተናነስ ጥፋት መሆኑ እሙን ነው፡-

﴿ لَيۡسَ عَلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ جُنَاحٞ فِيمَا طَعِمُوٓاْ إِذَا مَا ٱتَّقَواْ وَّءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ ثُمَّ ٱتَّقَواْ وَّءَامَنُواْ ثُمَّ ٱتَّقَواْ وَّأَحۡسَنُواْۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٩٣ ﴾ المائدة: ٩٣

በነዚያ በአመኑትና መልካም ሥራዎ ችን በሠሩት ላይ (ባለፉት ዘመናት) በተመገቡት (እርም) ምግብ ኃጢ አት የለባቸውም፥ (እርም የተደረጉ ነገሮች እርምነታቸው ከተነገራቸው በኋላ) እስከተጠነቀቁና እስካመኑ፥ መልካም ሥራዎችንም እስከሠሩ፥ አሁንም እስከተጠነቀቁና እስካመ ኑም፥ እንዲሁም እስከተጠነቀቁና መልካምን እስከሠሩም ድረስ። አላህ መልካም ሠሪዎችንም ይወዳልና፡ (አል ማኢዳህ 93)

5) **የአለባበስ ልከኝነት፡-** በአለባበስ ሚዛናዊ መሆንንም ኢስላም ያዛል። ወንዶች በአለባበስ እንዲፎካከሩና እንዲወዳደሩ ወይም መኩሪያና መኮፈሻ እንዲያደርጉት ኢስላም አይሻም። ላያዊ ገጽታን ማሳመርንም የታላቅነት መለኪያ አድርጎ አያየውም። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ጸጉሩ የተንጨባረረ፣ አቧራ የለበሰና ልብሶቹ የነተቡ፣ ግና በአላህ ላይ ቢምል አላህ መሐላውን የሚሞላለት ብዙ ሰው አለ።›› (ቲርሚዚ)

ወጣቱ ልብሶቹንና ገጽታውን የግርምት እይታዎች ከየአቅጣጫው የሚያርፉበት የፋሽን ማእከል ማድረጉ ቂልነት ነው። በቤታቸው ውስጥ ረዥም ጊዜ ራሳቸውን በማስዋብ የተጠመዱ ቂላቂል ኮረዶችም በብዛት ይስተዋላሉ። ይህን ጊዜያቸውን በእውቀት ፍለጋ ላይ እንዲያውሉ

ቢጠየቁ ግን ፈቃደኛ አይሆኑም። ኢስላም እንዲህ ዓይነቱን ቂልነት አስጠንቅቋል። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦

‹‹በዱንያ ውስጥ ባለ ዝና ልብስ የለበሰ በቂያማ ቀን አላህ የውርደት ልብስ ያለብሰዋል። እሳትም ያነድበታል።›› (ቢን ማጃህ)

ይህ ማለት ግን ኢስላም ጥሩ ያልሆኑ፣ ለእይታ የሚያስጠሉ፣ ወይም በየቦታው የተለጣጠፉ የነተቡ አልባሳትን እንዲለብሱ ተከታዩቹን ያበረታታል ማለት አይደለም። አንድ ሰው የነተበ ልብስ ለብሶ ከመልእክተኛው ዘንድ መጣ፦ ‹‹ገንዘብ አለህን?›› ሲሉ ጠየቁት። ‹‹አዎ›› አላቸው። ‹‹ምን ዓይነት ገንዘብ?›› ሲሉም ጠየቁት። ‹‹የተለያዩ አይነት ንብረቶችን አላህ ሰጥቶኛል።›› አላቸው። ‹‹አላህ ገንዘብ ከሰጠህ የጸጋውንና የችሮታውን ፋና ካንተ ላይ ማየት ይፈልጋል።›› አሉት። (ነሣኢ)

ኢስላም ተከታዮቹ እንዲዋቡ፣ መልካም ገጽታ እንዲኖራቸው ይሻል። ግና ላዩን አስውቦ ውስጡን ችላ የሚል፣ ውድ ጊዜውን እና ገንዘቡን ለሚለብሰው ብጣሽ ጨርቅ በመጨነቅና በመጠበብ በሚያሳልፍ እና ዋነኛ ዓላማው ውስጣዊ ማንነቱን ማስተካከል፣ ስብእናውን ማሟላት ሆኖ ግዴታዎቹን በአግባቡ እየተወጣ በመሐሉ ጥሩ ልብስ መልበሱን በማይዘነጋ ሰው መካከል እጅግ ሰፊ ልዩነት አለ።

6) ከገንዘብ ነክ ሐራሞች መጠበቅ

ሙእሚን፦

✓ ሐላል ስራዎችን ይመርጣል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ كُلُواْ مِمَّا فِي ٱلۡأَرۡضِ حَلَٰلٗا طَيِّبٗا وَلَا تَتَّبِعُواْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٌ ١٦٨ ﴾ البقرة: ١٦٨

‹‹እናንተ ሰዎች ሆይ! ከምድር ላይ ካሉ ነገሮች የተፈቀዱና መልካም የሆኑትን ተመገቡ። የሰይጣንን ፈለግ አትከተሉ። ግልጽ ጠላታችሁ ነውና።›› (አል በቀራህ 168)

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹በሐራም የበቀለ ስጋ ለእሳት የተገባ ነው፡፡››

የዚህ ኡምማ ቀደምት አባላት በዚህ ረገድ ድንቅ አርአያ ሆነውናል፡፡ አቡበክር፣ አገልጋያቸው ምንጩን የማያውቁትን ምግብ አመጣላቸው፡፡ ያለወትሯቸው ከየት አንደዳመጣው ሳይጠይቁት ጥቂት ተመገቡለት፡፡ ሌላ ጊዜ ግን ይጠይቁት ነበር፡፡ አገልጋያቸውም፡- ‹‹ሁሌም ጠዋት ከመመገብህ በፊት ትጠይቅ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ሳትጠይቅ ተመገብክ›› አላቸው፡፡ ‹እርቦኝ ስለነበር ነው፡፡››አሉ፡፡ በእርግጥ ጾመኛ ነበሩ፡፡ ‹‹ይህን ምግብ የት እንዳመጣሁት ታውቃለህን?›› ሲል ጠየቃቸው፡፡ ‹‹አላውቅም›› አሉት፡፡ ‹‹በመሐይምነት ዘመን ለሰዎች የጥንቆላ ተግባር ፈጸምኩላቸው፡፡ ያኔ ምንም ነገር አልሰጡኝም፡፡ ዛሬ ግን በነርሱ በኩል ሳልፍ ሰጡኝ።›› አላቸው፡፡ አቡበክር ይህን ሲሰሙ ገበቱ እንዲቀርብላቸው አዘዙ፡፡ ውሃም አስመጡ፡፡ ውሃ እየጠጡ ጣታቸውን ወደ ጉሮሯቸው በመክተት የበሉት በሙሉ እንዲያስመልሳቸው አደረጉ፡፡ በዙሪያቸው የነበሩ ሰዎች፡- ‹‹ለዚህች ቁራጭ ስጋ ይህን ያህል ይሰቃያሉን?›› ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ‹‹በአላህ እምላለሁ፣ እርሷን ለማውጣት ነፍሴን አብሬ ማውጣት የግድ ቢሆንብኝ እንኳ አወጣታለሁ፡፡ ምክንያቱም የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡- በሐራም የበቀለ አካል ለእሳት ተገቢው ነው፣ ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡››አሉ፡፡

የሶሐባ ሴቶች በዚህ ረገድ ጥንቁቆች ነበሩ፡፡ እናም ባለቤታቸው ጠዋት ከቤት ሲወጣ፡- ‹‹ረሃብን መታገስ እንችላለን፡፡ እሳትን ግን አንታገስም›› በማለት ይመክሩ ነበር፡፡

እዳን በአግባቡ መክፈልንም እስልምና አበረታትቷል፡፡ በዚህ ረገድ ተከታዮቹ ነጥቦች ትኩረትን ይሻሉ፡-

⇒ እዳን በወቅቱ መክፈል፡- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

> ‹‹የብድር ውለታ ምላሹ ብድርን መመለስ እና ማመስገን ነው፡፡›› (አህመድ)

⇒ አበዳሪን ማመስገንም ተገቢ ነው። ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹ሰዎችን ያላመሰገነ አላህን አያመሰግንም።››

ኢስላም ለገንዘብ ነክ ግንኙነቶች ያለው እይታ

ንግድ ነክና ሌሎች ግንኙነቶች ባጠቃላይ የእስልምና ሸሪዓ ማሠረታዊ አካሎች ናቸው። ምክንያቱም የሰው ልጅ ማሕበራዊ ሕይወት አብይ ክፍሎች ናቸውና። ‹‹ሐይማኖት ማለት የተስተካከለ ግንኙነት ነው።›› ይባላል። የዲን አካሎች የሆኑት ኢማን፣ ኢባዳ እና ስነ ምግባር ከሰዎች ጋር በሚኖር መልካም ግንኙነት ይገለጻሉ ማለት ነው። ገንዘብ ነክ ግንኙነቶች ከፍተኛ ትኩረት የሚሹ በመሆናቸው ከአላህ መልክተኞች መካከል አንዱ ለወገኖቹ ያቀረበላቸው ጥሪ የአላህን አሐዳዊነት ከማስተማር ቀጥሎ፣ የገንዘብ ግንኙነቶቻቸውን ያስተካክሉ ዘንድ መገሰጽ ሆኗል።

﴿ وَإِلَىٰ مَدۡيَنَ أَخَاهُمۡ شُعَيۡبٗاۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥۖ وَلَا تَنقُصُواْ ٱلۡمِكۡيَالَ وَٱلۡمِيزَانَۚ إِنِّيٓ أَرَىٰكُم بِخَيۡرٖ وَإِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٖ مُّحِيطٖ ٨٤ وَيَٰقَوۡمِ أَوۡفُواْ ٱلۡمِكۡيَالَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَلَا تَبۡخَسُواْ ٱلنَّاسَ أَشۡيَآءَهُمۡ وَلَا تَعۡثَوۡاْ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُفۡسِدِينَ ٨٥ ﴾ هود: ٨٤ - ٨٥

‹‹ወደ መድየንም ወንድማቸውን ሹዐይብን (መልዕክተኛችን አድርገን ላክን)። “ወገኖቼ ሆይ! አላህን ብቻ አምልኩ። ከርሱ ሌላ አምላክ የላችሁም። ስፍርንና ሚዛንንም አታንድሉ። እንደማያችሁ በሃብት ውስጥ ናችሁ። ግና እኔ በናንተ ላይ የከባቢውን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ።” አላቸው። “ወገኖቼ ሆይ! ስፍርንና ሚዛንን በትክክል ሙሉ። የሰዎችንም ንብረቶቻቸውን አታጉድሉባቸው። ምድር ላይም ንቅዘትን አታስፋፉ።” (ሁድ 84-85)

አላህ ገንዘብ ነብ ጉዳዮችን የሚመለከት ሕግ የመደንገግ መብት እንዳለው እነኝህ ሰዎች ዘንግተዋል። ሰርተው ያገኙትን ገንዘብ ባሻቸው መንገድ የመበተን መብት እንዳላቸውም ገምተዋል። ወይም ደግሞ አላህ

በዚህ ረገድ መልእክት ካስተላለፈም ተግሳጽና ምክር እንጅ አስገዳጅ መሆን እንደሌለበት አስበዋል። ስለዚህም እንዲህ አሉ፡-

﴿ قَالُواْ يَٰشُعَيۡبُ أَصَلَوٰتُكَ تَأۡمُرُكَ أَن نَّتۡرُكَ مَا يَعۡبُدُ ءَابَآؤُنَآ أَوۡ أَن نَّفۡعَلَ فِيٓ أَمۡوَٰلِنَا مَا نَشَٰٓؤُاْۖ إِنَّكَ لَأَنتَ ٱلۡحَلِيمُ ٱلرَّشِيدُ ٨٧ ﴾ هود: ٨٧

‹‹(እነርሱም)፡- "ሹዐይብ ሆይ! አባቶቻችን ያመልኩት የነበረውን እንተው ዘንድ ወይም በገንዘቦቻችን የፈለግነውን እንዳናደርግ ሶላትህ ታዝሃለችን? አንተ (እውነትም) ካታጋሽና ቅን አሳቢዛ ነህ።" አሉት። (ሁድ 87)

በኢስላም የገንዘብ ነክ ድንጋጌዎች የሚከተሉትን ልዩ ባህሪያት የተላበሱ ናቸው፡-

⇒ የገንዘብ ነክ ግንኙነቶች እንደሌላው የሐይማኖት ክፍሎች ከአላህና ከመልእክተኛው መመሪያ አካያ ብቻ መከናወን ይኖርባቸዋል።

⇒ በዚህ ረገድ ከአላህ እና ከመልእክተኛው የሚተላለፉ መመሪያዎች ሁሉ የአስገዳጅነታቸው መጠን እንደየ ድንጋጌዎቹ ባህሪ ይለያያል። ይህም በሊቃውንት ምርምር (ኢጅቲሐድ) ይብራራል።

⇒ የሰው ልጅ ስለገንዘብና ቀለብ ምንጩ በቂያማ ቀን ከአላህ ፊት ቀርቦ ይጠየቃል። በሐራም ምግብ የበቀለ ስጋ ለእሳት ተገቢ ነው። ምግቡን መልካም ያደረገ ዱዓው ተቀባይነት ያገኛል። አላህ መልካም ነው። መልካምንም ይወዳል። በዚህ አካኋን የእስልምና ኢማናዊና ስነ ምግባራዊ ትምህርት ከገንዘብ ነክ ድንጋጌዎች ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳላቸው እንረዳለን።

⇒ የእስልምና መመሪያዎች የሰውን ልጅ መንታ ገጽታ፣ ማለትም ስጋውንም መንፈሱንም፣ እንዲሁም ግለሰባዊና ማሕበራዊ ማንነቱን ያጤኑ ናቸው። ፈርድ (ግዴታ) እና በፈቃድ የሚፈጸም (ነፍል) የሚሰኙ ደረጃዎችም አሏቸው። የኢስላም የገንዘብ ነክ ጉዳዮች

ሕግጋት በእነዚህ ሁሉ ዘርፎች ሚዛናዊነትን በጠበቀ መልኩ የተቀረጹ ናቸው።››

⇒ በኢስላም የገንዘብ ነክ መመሪያዎች ውስጥ መጠናቸው ተወስኖ ግዴታ የሆኑ እናገኛለን። ለምሳሌ ዘካ። መጠናቸው ያልተገደበና ከሰውየው አቅምና ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ግድ የሚሆኑ እናገኛለን። ለምሳሌ የቤተሰብ ቀለብ።

⇒ ኢስላም ግለሰብን ወይም ማሕበረሰብን የሚጎዳን ገንዘብ ነክ ጉዳይ ሁሉ ከልክሏል። ከዚህም ውስጥ አራጣ፣ ማታለል፣ ስርቆት፣ ጉቦ፣ ሸቀጥን በሞኖፖሊ መያዝ እና መሰል ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮች ሁሉ ይጠቀሳሉ። በአንጻሩ ብድርን፣ የተቸገረን መደጎምን፣ መረዳዳትን፣ ዘካን፣ ሶደቃንና የበጎ አድራጎት ተግባራትን ፈቅዷል። ይህ ሁሉ በሰው ልጅ ዓለማዊም ሆነ የመጭው ዓለም ሕይወት ላይ ተጽእኖ እንዳለውም አብራርቷል።

⇒ በእስልምና አተያይ መሠረት የገንዘብ እውነተኛ ባለቤት አላና ብቻ ሲሆን፣ የሰዎች ባለቤትና ገዥም እርሱ ነው። ስለዚህም የገንዘብ አጠቃቀማችን አላህ በደነገገልን መልኩ መሆን እንዳለበት እናምናለን። ይህን በመፈጸምም የርሱን ውዴታ ተስፋ እናደርጋለን። ጊዜያዊ የገንዘብ ባለቤትነት ከአላህ ሊያርቀን ወይም ውዴታውን ከማግኘት ሊያቅበን አይገባም።

በመሆኑም ገንዘብ ምንጩና አጠቃቀሙ ንጹህ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ በሌሎች ላይ ለመኩራት ሳይሆን እነርሱን ለማስደሰት ተግባር መዋል ይኖርበታል።

ለ) ክብርን መጠበቅና አለመለመን

ቁጥብ ሙእሚን ሰዎችን ኢምንት ነገር ለመጠየቅ አይፈቅድም። አላህ እንዲህ በማለት የገለጻቸውን ሰዎች ባህሪ ይላበሳል፡-

﴿ لِلۡفُقَرَآءِ ٱلَّذِينَ أُحۡصِرُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ لَا يَسۡتَطِيعُونَ ضَرۡبٗا فِي ٱلۡأَرۡضِ يَحۡسَبُهُمُ ٱلۡجَاهِلُ أَغۡنِيَآءَ مِنَ ٱلتَّعَفُّفِ تَعۡرِفُهُم بِسِيمَٰهُمۡ لَا يَسۡـَٔلُونَ ٱلنَّاسَ إِلۡحَافٗاۗ وَمَا تُنفِقُواْ مِنۡ خَيۡرٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ٢٧٣ ﴾
البقرة: ٢٧٣

‹‹(ምጽዋታችሁን) ራሳቸውን በአላህ መንገድ በሚደረግ ትግል ለሰጡ ድሆች አድርጉ። (እነኝህ ወገኖች በአላህ መንገድ የሚደረግ ትግል በመጠመዳቸው) ምድር ላይ መንቀሳቀስ (እና የእለት ጉርሳቸውን ማግኘት) አይችሉም። ቁጥቦች ከመሆናቸው የተነሳ የማያውቅ ሰው ሃብታሞች እንደሆኑ ያስባል። በአኳኋናቸው ታውቃቸዋለህ። ሰዎችን ፈጽሞ አይጠይቁም። ከጽድቅ ተግባር የምትፈጽሙትን አላህ ጠንቅቆ ያውቀዋል።›› (አል በቀራህ 273)

ስልጣኑን ተጠቅሞ የግል ጉዳዩን አየፈጽምም። የሚበላው ባጣበት ሁኔታ እንኳ ሰዎች ሐብታም አድርገው ያስቡታል። ኢብን አባስ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ከሰዎች ተብቃቁ። ከልመና ኢምንትም ቢሆን ተቆጠቡ። ይህ ለናንተ መልካም ነው።››

‹‹በርስዎም ቢሆን?››ሲሉም ጠየቋቸው። ‹‹አዎ፣ ከኔም ቢሆን›› ሲሉ መለሱ። (ጦበራኒ)

አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሚስኪን ማለት አንድ ወይም ሁለት ተምር ወይም አንድ ወይም ሁለት ጉራሽ የሚመልሱት ሳይሆን ከልመና የተቆጠበው ነው። ከፈለጋችሁ፡- ‹‹ሰዎችንም በችክታ አይለምኑም።›› የሚለውን የቁርአን መልእክት አንብቡ። (ቡኻሪ)

ሐ) ከአሻሚ ነገሮች መቆጠብ

የተገኘነት ባህሪ ከቀልብ ላይ ሲጸና ባለቤቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ያመጥቀዋል። ይህ ሲሆን ከሐራም ለመጠበቅ ሲል ሐራም ያልሆነውን ነገር ይተዋል። አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አንድ ሰው ከሌላው መሬት ገዛ። ከውስጡም በእንስራ የተሞላ ወርቅ አገኘበት። ለሻጩም፡- ‹‹ወርቅህን ያዝ። እኔ የገዛሁህ መሬቱን እንጅ ወርቁን አይደለም።›› አለው። ሻጭም፡-‹‹እኔም የሸጥኩልህ መሬቱን ከነይዞታው ነው።›› ሲል ሞገተው። ከዳኛ ዘንድ ሄዱ። ‹‹ልጆች አሏችሁን?›› ሲል ዳኛው ጠየቀ። አንደኛው፡- ‹‹ወንድ ልጅ አለኝ›› አለ። ሌላኛው፡- ‹‹ሴት ልጅ አለችኝ።››አለ። ዳኛውም፡- ‹‹እነርሱን አጋቡና ገንዘቡን ለነርሱ ስጧቸው››ሲል ፈረደላቸው።

3) ቁጥብነትን የሚመለከቱ ሐዲሶች

1) ኢብን ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ልጆቻችሁ የናንተን መብት እንዲያከብሩ እናንተ የወላጆቻችሁን መብት አክብሩ። ሴቶቻችሁ እንዲጠበቁ እናንተ ቁጥቦች ሁኑ።›› (ሙንዚር)

2) አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሦስት ሰዎችን አላህ ሊረዳቸው ተገቢ ሆኗል። እነርሱም በአላህ መንገድ የሚታገል፣ ራሱን ከባርነት ነጻ ለማድረግ የሚሰራና ከሐራም ለመጥጠበቅ ሲል ጋብቻ የከጀለ።›› (ቲርሚዚ)

3) ኢብን ዑመርና አኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ባለሐቅ ሐቁን ሰጡትም አልሰጡትም በአግባቡ ይጠይቅ።›› (ቢን ማጃህ)

4) አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ጀነት ቀድመው የሚገቡ ሦስት ሰዎች ቀረቡልኝ፡፡ እነርሱም ሸሂድ፣ ቁጥብ፣ እንዲሁም አላህን በአግባቡ ያመለከና ለባለቤቶቹ ታማኝ የሆነ ባሪያ ናቸው፡፡›› (ቲርሚዚ)

4) የቁጥብነት ናሙናዎች

1) ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተግባራዊ ምሳሌ

⇒ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ወደ ቤቴ ስሄድ ከመኝታዬ ላይ ተምር ወድቆ አገኝና ልበላው ካነሳሁት በኋላ ድንገት የሶደቃ እንዳይሆን በመስጋት እተወዋለሁ፡፡›› (ቡኻሪ)

⇒ አነስ ቢን ማሊክ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መንገድ ላይ ተምር አዩ፡፡ ‹‹ሶደቃ እንዳይሆን ባልሰጋ ኖሮ መመገብ ከጅዬ ነበር፡፡››አሉ፡፡ (ቡኻሪ)

2) ሙስሊሞች ቃድሲያን በድል በተቆጣጠሩ ጊዜ ምርኮዎችን እየያዙ በመምጣት ለዑመር አስረከቡ፡፡ ዑመርም እንዲህ አሉ፡-

ይህን ሁሉ ሐብት ያመጡ ሰዎች በእርግጥም ታማኞች ናቸው፡፡›› ሰዎችም፡- ‹‹እርስዎ ቁጥብ ስለሆኑ ተከታዮችዎም ቁጥቦች ሆነዋል፡፡ እርስዎ ለግብግብ ቢሆኑ ኖሮ እነርሱም ስግብግቦች ይሆኑ ነበር፡፡›› አሏቸው፡፡

3) ዑመር ቢን አልኸጣብ ከሚንበር ላይ ቆመው እንዲህ አሉ፡-

‹‹ሙያ የሌላትን እንስት ባሪያ ሰርታ ገንዘብ እንድመጣ አታስገድዷት፡፡ ምክንያቱም የምትሰራው በብልታ ይሆናልና፡፡ ሕጻንን ልጅ እንዲሰራ አታስገድዱት፡፡ ምክንያቱም ሰርቶ ገንዘብ ማግኘት ካልቻለ ይሰርቃልና፡፡›› (ሙወጠእ)

4) ልጃቸው አንድ ሺህ ዲርሃም የሚያወጣ ቀለበት መግዛቱ ለዑመር ቢን አብድል አዚዝ ተነገራቸው። እንዲህ የሚል መልእክት ላኩለት፡-

‹‹አንድ ሺህ ዲርሃም የሚያወጣ ቀለበት መግዛትህን ሰምቻለሁ። ይህ መልእክቴ እንደደረሰህ ቀለበቱን ሸጥና አንድ ሺህ ድሆችን መግብበት። ቀጥሎም የብረት ቀለበት ግዛና፡- ‹‹ደረጃውን ያወቀ ሰው አላህ ይዘንለት›› የሚል መልእክት ጻፍበት።››

የመመዘኛ ጥያቄዎች

- ✓ የቁጥብነትን ትርጉም አብራራ፣
- ✓ የቁጥብነት አይነቶችን ዘርዝር፣
- ✓ ስለቁጥብነት የተነገሩ ሐዲሶችን በከፊል አስታውስ፣
- ✓ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እና ከሶሐቦች፣ እንዲሁም ከደጋግ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ቁጥብነት የሚያሳዩ ናሙናዊ ታሪኮችን አውሳ።
- ✓ በሕይዎትህ ውስጥ ከቁጥብነት ገጽታዎች አንዱን ያንጸባረቅክበትን አጋጣሚ ጥቀስ። ከዚህ አጋጣሚ ምን ትምህርት ቀሰምክ?
- ✓ በየትኛው የቁጥብነት ገጽታ ድክመት ይስተዋልብሐል?

መቻልና ቁጣን መቆጣጠር

የትምህርቱ ዓላማዎች

- የመቻልን (የመታገስን) ትርጉም መረዳት፣
- ጠቀሜታውን ማብራራት
- ይህን ባህሪ ለመላበስ የሚረዱ ተግባራዊ ናሙናዎችን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ውስጥ መዘክር
- የታጋሽነትን እና ቁጣን የመቆጣጠርን መገለጫዎች መዘርዘር፣
- ቁጣን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን መዘርዘር

የታጋሽነት ትርጉም

ቋንቋዊ ትርጉም፡- በቁጣ ወይም አንዳች መጥፎ ነገር በሚደርስ ጊዜ፡-

1) መበቀል እየቻሉ ረጋና ሰከን ማለት፡፡

2) እርጋታና ነፍስን መቆጣጠር፡፡

3) ‹‹ሐሊም›› የሚለው የዓረብኛ ቃል ‹‹አእምሮ›› የሚል ትርጉም አለው፡፡ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ ይመልከቱ፡፡

﴿ أَمْ تَأْمُرُهُمْ أَحْلَٰمُهُم بِهَٰذَآ أَمْ هُمْ قَوْمٌ طَاغُونَ ﴿٣٢﴾ ﴾ الطور: ٣٢

አዕምሮዎቻቸው ናቸው በዚህ (እብለት) ያዘዟቸው? ወይስ ወሰን አላፊዎች ሕዝቦች በመሆናቸው ነው (በአስተባባይነት አቋም የፀኑት)?

(አል ጡር 32)

‹ሐሊም› (ታጋሽ) ከአላህ መልካም ስሞች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሸጧቢ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ በእርግጥም ይቅር ባይ፣ የማይቸኩል፣ ቁጣ የማያሸንፈው፣ የባለጌና የወንጀለኛ ድርጊት ወሰን የማያሳልፈው፣ ለቅጣት የማይቸኩል፣ ሁሉንም ነገር በወቅቱና በታቀደለት መጠን የሚፈጽም አምላክ ነው፡፡››

ገዛሊ እንዲህ ሲሉ አክለዋል፡-

‹‹ቁጣ አሸንፎት ለብቀላ እንዲቸኩል የማያደርገው፡፡››

﴿ وَلَوْ يُؤَاخِذُ ٱللَّهُ ٱلنَّاسَ بِمَا كَسَبُواْ مَا تَرَكَ عَلَىٰ ظَهْرِهَا مِن دَآبَّةٍ وَلَٰكِن يُؤَخِّرُهُمْ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۖ فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمْ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِعِبَادِهِۦ بَصِيرًا ﴿٤٥﴾ ﴾ فاطر: ٤٥

‹‹አላህ የሰው ልጆችን በፈፀሟቸው ኃጢአቶች ሁሉ የሚቀጣ ቢሆን ኖሮ ምድር ላይ አንድም የሚንቀሳቀስ ፍጡር ባልተወ ነበር። ግና (ኃጢአተኞችን) እስከተወሰነው ዕለት ድረስ ያቆያቸዋል። ያ ዕለታቸው

በደረሰም ጊዜ (ይቀጣቸዋል)። አላህ ባሮቹን ተመልካች ነውና።›› *(ፋጢር 45)*

ታጋሽነት የአእምሮን ምሉእነት እና ብርታት፣ እንዲሁም የቁጣ ጉልበት መሰበሩንና ለአእምሮ ፈቃድ ማደረን ያመለክታል።

የታጋሽነት ጠቀሜታና ክብደት

1) ሰውየው መበቀል እየቻለ በመታገሱ እና ቁጣውን በመቆጣጠሩ መጠን ከአላህ ዘንድ ያለው ደረጃና ከፍ ይላል። የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መበቀል እየቻለ ቁጣውን የተቆጣጠረ አላህ በእለተ ቂያማ ከሰዎች መካከል ይጠራውና የፈለጋትን ሁረል አይን እንዲመርጥ ያደርገዋል።›› (ቲርሚዚና አቡ ዳውድ)

አባደት ቢን ሷሚት እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፡-

‹‹አላህ ግንብን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር ልንገራችሁን?" ‹‹አዎ፣ ይንገሩን›› አሏቸው። ክፉ የሰራብህን መታገስህ፣ የበደለህን ይቅር ማለትህ፣ ለነፈገህ መስጠትህ፣ ዝምድናህን የቆረጠውን መቀጠልህ ነው›› አሉ።

ቁርአን እነዚህን ባህሪያት በመዘርዘር ለጀነት የሚያበቁ መሆናቸውን መስክራል።

﴿ وَسَارِعُوٓاْ إِلَىٰ مَغۡفِرَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ أُعِدَّتۡ لِلۡمُتَّقِينَ ١٣٣ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي ٱلسَّرَّآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَٱلۡكَٰظِمِينَ ٱلۡغَيۡظَ وَٱلۡعَافِينَ عَنِ ٱلنَّاسِۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٣٤ ﴾ آل عمران: ١٣٣ - ١٣٤

‹‹የጌታችሁን ምሕረት ለመጐናፀፍና ስፋቷ የሰማያትንና የምድርን ስፋት የሚመጥነውን ገነት ለመውረስ ተቻኮሉ። አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ተዘጋጅታለች። ለነዚያ ለደግም ሆነ ለክፉም ቀን (ገንዘባቸውን በአላህ መንገድ) ለሚለግሱ ቁጣቸውን ለሚቆጣጠሩትና ሰዎችን ይቅር

ባዮች ለሆኑ። አላህ መልካም ሥሪዎችን ይወዳል።›› *(አሊ ዒምራን 133-134)*

2) ታጋሽነትና ሆደሰፊነት የጠላትህን ጥላቻው በማሟሸሽ ወዳጅህ ያደርገዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ وَلَا تَسۡتَوِي ٱلۡحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُۚ ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِي بَيۡنَكَ وَبَيۡنَهُۥ عَدَٰوَةٞ كَأَنَّهُۥ وَلِيٌّ حَمِيمٞ ٣٤ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلَّذِينَ صَبَرُواْ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٖ ٣٥ ﴾ فصلت: ٣٤ - ٣٥

መልካም ሥራና ክፉ ሥራ ፈጽሞ እኩል አይደሉም። (ሰዎች ባንተ ላይ የሚያደርሱትን በደል) በዚያች መልካም በሆነችው (ምግባርህ) መልስ። ያን ጊዜ በአንተና በርሱ መካከል ጥል የነበረበት ሰው ልክ እንደቅርብ ወዳጅህ ይሆናል። (ይህችን መልካም ባሕሪ) እነዚያ የታገሱት እንጅ ሌላ ማንም አያገኟትም። የታላቅ ዕድል ባለቤቶች እንጅ ሌላ ማንም አይጐናፀፉትም።›› *(ፉሲለት 34-35)*

ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል፦

‹‹አላህ ሙእሚኖችን ሲቆጡ እንዲታገሱ፣ ክፉ ሲሰራባቸው ሄደ ሰፊ እንዲሆኑ፣ የበደላቸውን ይቅር እንዲሉ አዟቸዋል። እነዚህን ካደረጉ አላህ ከሰይጣን ይጠብቃቸዋል። ጠላቶቻቸውንም ወዳጅ ያደርግላቸዋል።››[1]

3) ሆደ ሰፊነት የሰውየውን ውስጣዊ ጥንካሬና ክህሎት ያመለክታል። ኢብን መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦

‹‹ከናንተ ዘንድ ብርቱ የምትሉት እንዴት ዓይነቱን ሰው ነው? ሲሉ ጠየቁ። ‹‹ሰዎች ታግለው የማያሸንፉት›› የሚል ምላሽ ተሰጣቸው። ‹‹ግና ብርቱ ማለት በቁጣ ጊዜ ራሱን የሚቆጣጠር ነው።›› አሉ። (ሙስሊም)

[1] ሙኽተሰር ሚንሐጀል ቃሲዳን

አንድ ሰው ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ)፡- ‹‹ይምከሩኝ፡፡ ግና እንዳልረሳው ምክር አያብዙብኝ›› አላቸው፡፡ እርሳቸውም ‹‹አትቆጣ› አሉት፡፡ (ማሊክ)

4) ሰውየው ራሱን እንዳይስትም ያቅበዋል፡፡ አንድ ሰው ነፋስ ኩታውን ከላዩ ላይ ገፈፈችበት፡፡ በዚህ ተቆጥቶ ሲረግማት የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሰሙ፡፡ ‹‹አትርገማት፡፡ ምክንያቱም በአላህ የታዘዘች ናት፡፡ እነሆ፣ ለእርግማን ተገቢ ያልሆነን አካል የረገመ እርግማኑ ወደርሱ ይመለሳል›› አሉት፡፡ (ቲርሚዚ)

5) የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) አንድ ቀን ምሽት ላይ ለሰዎች ንግግር አደረጉ፡፡ ከተናገሩት መሐል የሚከተለው ይገኝበታል፡-

‹‹ሰዎች ባህሪያቸው የሚበርድለት ሰው አለ፡፡ ቶሎ ተቆጥቶ ቶሎ የሚበርድም አለ፡፡ ሲቆጣም ሲበርድም በእርጋታ የሆነ አለ፡፡ የመጀመሪያው ሁለተኛውን ያካክስለታል፡፡ አዋጅ፣ ቶሎ ተቆጥቶ ቀስ ብሎ የሚበርድም አለ፡፡ ከሁሉም በላጩ ቀስ ብሎ የሚቆጣውና ቶሎ የሚበርደው ነው፡፡ መጥፎው ደግሞ ቶሎ የሚቆጣውና ቀስ ብሎ የሚበርደው ነው፡፡ መጥፎው ደግሞ ቶሎ የሚቆጣውና ቀስ ብሎ የማበርደው ነው፡፡ አዋጅ፣ ከሰዎች ውስጥ ሲያበድርም ሲበደርም መልካም የሆነ አለ፡፡ ሲያበድር መጥፎ ሲበደር መልካም የሆነ አለ፡፡ ሲበደር መጥፎ ሲያበድር መልካም የሆነ አለ፡፡ የመጀመሪያው የሁለተኛውን ያካክሰዋል፡፡ ሲያበድርም ሲበደርም መጥፎ አለ፡፡ አዋጅ፣ ከነዚህ ውስጥ በላጩ ሲያበድርም ሲበደርም መልካም የሆነው ነው፡፡ መጥፎው ደግሞ ሲያበድርም ሲበደርም መጥፎ የሆነው ነው፡፡ አዋጅ፣ ቁጣ ከሰው ልጅ ልቦና ውስጥ ያለ ፍም እሳት ነው፡፡ ሰው ሲቆጣ ዓይኖቹ እንዴት እንደሚቀሉና የደም ስሩ እንዴት እንደሚግተረተር አላያችሁምን? እንዲህ ዓይነት ስሜት የተሰማው ሰው ወደ መሬት ይጠጋ፡፡ ባለበት ይቀመጥ፡፡›› (ቲርሚዚ)

የቁጣ ስሜቱን ተከትሎ የሚጋልብ ዓቅሉን በሳተበት እና ስሜቱ ባየለበት ሁኔታ ብዙ ነገሮችን ያበላሻል። የማስተካከል እድልም አይኖረውም።[1]

6) ታጋሽነት የኢማንን ጥልቀት ያመለክታል። አንዳንዱ ሰው በቁጣ ጊዜ ዓቅሉን ይስታል። ያለማቋረጥ ይናገራል፣ ይበሳጫል፣ ፊቱ በጣም ይጨፈገጋል። ሲብስበት ወባ እንደያዘው ሰው ይንዘፈዘፋል። ይሳደባል፣ ይራገማል፣ ኢስላም እንዲህ አይነቱን ባህሪ ይኮንናል።

የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹ሙእሚን ሰዎችን በምላሱ አይወጋም። ተራጋሚ፣ ተሳዳቢና ብልግና ተናጋሪም አይደለም።›› (ቲርሚዚ)

ተግባራዊ ናሙናዎች

1) የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለራሳቸው ጉዳይ ተቆጥተው እንደማያውቁ ተነግሯል። የአላህ ወሰን ካልተደፈረ በቀር። ‹‹ጣኦታውያንን ይርገሟቸው›› ተብለው ተጠየቁ። ‹‹አዛኝ እንጅ ተራጋሚ ተደርጌ አልተላክኩም።›› ሲሉ መለሱ። (ሙስሊም)

አቻ ከማይገኝላቸው የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የይቅርታ ታሪኮች መካከል ለሙናፊቆች መሪ ለአብደላህ ቢን ኡበይ ያደረጉት ይቅርታ ይጠቀሳል። አብደላህ የሙስሊሞች ቀንደኛ ጠላት ነበር። ሁሌም ይተናኮላቸዋል። አጋጣሚ እየፈለገ ያጠቃቸዋል። እነርሱን ለመጉዳት ከሰይጣናት ጋር ተባብሮ ይሰራል። እነርሱን ወይም ነቢዩን የሚያጠቃበት እድል ካገኘ እንዲሁ አያሳልፈውም። በአሊሻ ላይ አግባብ ያልሆነ ወሬ ያስወራው እርሱ ነው። እኩያንም የርሱን ሐሰት ተቀብለው በማሰራጨት የሕብረተሰቡን መሰረት እስከማናጋት ደረሱ። ግና አላህ እውነትን ይፋ አደረገ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አብደላህ ቢን ኡበይ በሞተ ጊዜ ልጁ መጥቶ ይቅር እንዲሉት ሲጠይቃቸው አላንገራገሩም። በቀሚሳቸው ይገነዝ ዘንድም ጠየቃቸው። ቀሚሳቸውን ሰጡት፣ እንዲሰግዱበትና

[1] ሹዑቡል ሙስሊም (ገዛሊ)

ምህረት ከአላህ እንዲለምኑለትም ጠየቃቸው። ይቅር ባዩ ነብይ ይህን ጥያቄውም እምቢ አላሉትም። ትላንት ክብራቸውን ካጎደፈው ሰው ጀናዛ ፊት ቆመው ምህረት ሊለምኑለት ሲሰናዱ አላህ እንዲህ የሚል ትእዛዝ አወረደላቸው፡-

﴿ ٱسۡتَغۡفِرۡ لَهُمۡ أَوۡ لَا تَسۡتَغۡفِرۡ لَهُمۡ إِن تَسۡتَغۡفِرۡ لَهُمۡ سَبۡعِينَ مَرَّةٗ فَلَن يَغۡفِرَ ٱللَّهُ لَهُمۡۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ كَفَرُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٨٠ ﴾ التوبة: ٨٠

‹‹ምሕረትን ብትጠይቅላቸውም ባትጠይቅላቸውም ለውጥ የለውም። ሰባ ጊዜ ምሕረትን ብትለምንላቸውም አላህ ፈጽሞ አይምራቸውም። ምክንያቱም እነርሱ በአላህና በመልዕክተኛው ክደዋልና። አላህ አመፀኞችን አይመራም።›› (አልተውባህ 80)[1]

2) አቡበክር አገልጋያቸውን ሲራገሙ የሰሙት ነብይ (ሶ.ዐ.ወ) ድርጊቱን ነቀፉ። እንዲህም አሉ፡-

‹‹እውነት ባዩ ሲዲቅ ተራጋሚ ሊሆን አይገባም።›› (ሙስሊም)

በሌላ ዘገባ እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል፡-

‹‹ተራጋሚም ሲዲቅም ልትሆኑ አትችሉም።››

አቡበክር ለዚህ ስህተታቸው ማካካሻ ይሆን ዘንድ አገልጋያቸውን ነጻ ለቀቁት። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣትም፡- ‹‹ይህን ጥፋት ዳግም አልፈጽምም›› ሲሉ ቃል ገቡ።[2]

በአኢሻ ላይ በተሰነዘረው የሐሰት ወሬ ስርጭት የተሳተፈውን ሙጦህ የተባለ ወዳጃቸውን እንደወትሮው ቀለብ ላይሰፍሩለት በማሉ ጊዜ አላህ የሚከተለውን መልእክት አወረደ፡-

[1] ኹሉቁል መስሊም

[2] ያለፈው ምንጭ

﴿ وَلَا يَأۡتَلِ أُوْلُواْ ٱلۡفَضۡلِ مِنكُمۡ وَٱلسَّعَةِ أَن يُؤۡتُوٓاْ أُوْلِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينَ وَٱلۡمُهَٰجِرِينَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۖ وَلۡيَعۡفُواْ وَلۡيَصۡفَحُوٓاْۗ أَلَا تُحِبُّونَ أَن يَغۡفِرَ ٱللَّهُ لَكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٢٢ ﴾

‹‹ከናንተ ውስጥ የችሮታና የክብረት ባለቤቶች ለቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ለድሆችና በአላህ መንገድ ለተሰደዱ (ነዳያን) (ምጽዋት) ላለመስጠት አይማሉ። (እጥፊዎችን) ይቅር ይበሉ፣ ይለፏቸውም። አላህ ምሕረትን እንዲለግሳችሁ አትሹምን? አላህ መሓሪም አዛኝም ነውና።›› *(ሱል ኑር 22)*

አቡበክርም፡-‹‹አዎ፣ በአላህ እምላለሁ፣ አላህ እንዲምረኝ እፈልጋለሁ››አሉና ቀለብ መስፈራቸውን ቀጠሉ። ‹‹መቼም ቢሆን አላቆምበትም›› ሲሉም ቃል ገቡ።

2) ኢብን አባስ እንዳስተላለፉት ኡየይናህ ቢን ሐስን በመጣ ጊዜ ከወንድሙ ልጅ ከጀድ ቢን ቀይስ ዘንድ አረፈ። ዑመር ከሚያቀርቧቸው ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። ጀድ የቁርአን አዋቂና የዑመር ምክክር (ሹራ) ጉባኤ አባል ነው። ዑየይናህም፡- ‹‹ወደ ዑመር እገባ ዘንድ አስፈቅድልኝ›› አለው። አስፈቀደለትና ሲገባ ‹‹ዑመር ሆይ፣ እንደሚገባው አትሰጠንም። በፍትህም አትፈርድልንም››አላቸው። ዑመርም በጣም ተቆጡ። ሊቀጡትም አሰቡ። እሱም፡- ‹‹የአማኞች መሪ ሆይ፣ አላህ ለነቢዩ እንዲህ ብሏቸዋል፡-

﴿ خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ١٩٩ ﴾ الأعراف: ١٩٩

‹‹ይቅር ባይ ሁን። በመልካምም እዘዝ። ከማሃይማንም ራስህን አግልል።›› (ሱል አእራፍ 199)

ይህ ሰው ከመሐይማን መካከል አንዱ ነው።›› አላቸው። ዑመር ይህን አንቀጽ ሊተላለፉ አልፈቀዱም። የአላህን ኪታብ መልእክት በወጉ የሚተገብሩ ሰው ነበሩ።

ዑመር የተቆጡት ይህ በደዊን ወሰን በማለፉ ነው። ሊቀጡት አሰቡም። ምክንያቱም የገባው ሊመክራቸው ወይም መብቱን ፈልጎ ሳይሆን በሐላፊነት ላይ ያለን ባለስልጣን ያለ ምክንያት ለመስደብ ነው። ሰውየው ከመሐይማን መሆኑ ሲነገራቸው ትተውት ዘወር አሉ።

4) የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለአሸጅ አብዱልቀይስ እንዲህ ብለውታል፡-

‹‹አላህ የሚወዳቸው ሁለት ባህሪያት አሉህ። እነርሱም ታጋሽነትና እርጋታ ናቸው።›› (ሙስሊም)

ኢማም ነወዊ ይህን ሐዲስ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መታገስ ማስተዋል ነው። እርጋታ ደግሞ ማረጋገጥና አለመቸኮል ነው። ነቢዩ ይህን ያሉበት አጋጣሚ አንድልዑክ መዲና እንደደረሰ ወደ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተጣድፎ ሄደ። አሸጅ ደግሞ ከማረፊያ ቦታቸውቆየ። ጓዙን አስተካከለ። ግመሉን አሰረ። ጥሩ ልብስም ለበሰ። ከዚያ በኋላ ወደ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አመራ። ነቢዩ አቀረቡት። ከጎናቸውም አስቀመጡት።

‹‹ራሳችሁንና ወገኖቻችሁን ወክላችሁ ቃል ኪዳን (በይዓ) ትገባላችሁን?›› ሲሉም ጠየቋቸው። ሰዎችም፡- ‹‹አዎ›› አሉ። አሸጅ ግን እንዲህ አለ፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሆይ፣- - - ራሳችንን ወክለን ከርስዎ ጋር ቃል እንጋባለን። ለወገኖቻችንም ጥሪ የሚያደርግላቸው እንልካለን። የተከተሉን የኛው አካል ይሆናሉ። እንቢ ያሉንን ግን እንዋጋለን። ነቢዩም፡- ‹‹እውነት ብለሐል። አላህ የሚወዳቸው ሁለት ባህሪያት አሉህ።- -- ›› በማለት ተናገሩ።

ቃዲ ኢያድ እንዳሉት እርጋታ የአንዳች እርምጃ ፋይዳ እስኪረጋገጥ ድረስ አለመቸኮል ነው። ታጋሽነት ደግሞ የአእምሮን ጤንነት፣ ብስለትና ፍጻሜን የማስተዋል ክሕሎቱን የሚያረጋግጥ ነው።

የታጋሽነትና ቁጣን የመቆጣጠር መገለጫዎች

1) የባለጌዎችን ሁከት ሳይበቀሉ መታገስ

2) የተቃራኒ ወገንን እይታ ማክበር

3) ከተቃራኒ ወገን እይታ አወንታዊ ገጽታውን ማየትና በርሱ ለመጠቀም መሞከር

4) ክርክርንና ንትርክን መቀነስ

5) ፍቅንና አክብሮትን ለማግኘት መትጋት

6) ስህተትን መቀበል

ስትቆጣ ምን ማድረግ አለብህ?

1) ከተረገመው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ

2) ቆመህ ከሆነ ተቀመጥ፣ ተቀምጠህ ከሆነ ተጋደም

3) ቁጣህ ካልበረደ ቦታውን ለቀህ ሂድ

4) ውዱእ አድርግ

5) ሁለት ረከዓ ስገድ። ሱጁድ አስረዝም።

6) ከነቢዩ የተገኘውን ተከታዩን ዱዓ አብዛ፡- ‹‹የነቢዩ መሐመድ ጌታ ሆይ፣ ወንጀሌን ማርልኝ። የቀልቤን ቁጣ አስወግድልኝ። መንገድ ከሚያስቱ ፈተናዎችም ጠብቀኝ።››

የመመዘኛ ጥያቄዎች

1) የታጋሽነትን ትርጉም ግለጽ

2) ክብደቱንና ጠቀሜታውን አብራራ

3) ከነቢዩ ታሪክ ውስጥ የታጋሽነት ተምሳሌት የሆኑ አጋጣሚዎችን አውሳ

4) የታጋሽነትንና ቁጣን የመቆጣጠርን ድንቅ ባህሪ ያስተዋልክበትን አጋጣሚ አስታውስ። ባንተ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖም አስረዳ።

5) የታጋሽነትንና ቁጣን የመቆጣጠርን መገለጫዎች ዘርዝር

6) የታጋሽነትንና ቁጣን የመቆጣጠርን ባህሪ በተግባር ምን ያህል ማረጋገጥ እንደቻልክ አስረዳ።

7) ቁጣን ለመቆጣጠር የሚረዱ ስልቶችን ዘርዝር

የሐያእ፣ የቁጥብነት፣ የታጋሽነት እና ቁጣን የመቆጣጠር ባህሪያትን ማጎልበትን ለመፈተሽ የሚረዱ መጠይቆች

1) የሐያእ ባህሪ

ባህሪ	ሁሌ	በአብዛኛው	አንዳንዴ	አልፎ አልፎ
ከፍተኛው ደረጃ = 4 X የባህሪያቱ ቁጥር	4	3	2	1
ከፍተኛ ደረጃ 124 **ራስንና እርሱ የያዘውን ለመጠበቅ** ✓ ከአላህ ውጭ ለሌላ አላጎበድድም ✓ እይታዬን ከሐራም አቅባለሁ ✓ የሰዎችን ነውር አላነፈንፍም ✓ ዩኒቨርሱን አስተውላለሁ። የአላህን ችሎታ አስተነትናለሁ። ✓ ሐሜት፣ ነገር ማሳበቅ፣ ብልግናና ሌሎች ሐራም ነገሮችን ከመስራት እርቃለሁ። ✓ ከአልባሌ ነገሮች እጠበቃለሁ። ቁርአንን አዘውትሬ እሰማለሁ።				

✓ ከአስካሪ መጠጥ፣ ከአደንዛዥ እጽና አእምሮን ከሚያደንዙ ሌሎች ነገሮች እታቀባለሁ። **ሆድንና በውስጡ የቋጠረውን ለመጠበቅ** ✓ አላህን ለሰጠኝ ጸጋ አመሰግነዋለሁ። ✓ ሐላል ነገሮችን ለመመገብ እና ለመጠጣት እተጋለሁ። ✓ በአመጋገቤ የነቢዩን ሱንና እከተላለሁ። ✓ ብልቴን ከሐራም እጠብቃለሁ። ✓ ሳቅ ማብዛት ቀልብን ስለሚገድል ከርሱ እቆጠባለሁ። **ሞቶ መበስበስን ለማስታወስ** ✓ የጣእረ ሞትን፣ የቀብርንና የቂያማን ትእይንቶች ዘወትር አስታውሳለሁ። ✓ በሽተኞችን ለመጎብኘት ከነርሱ ለመማር እተጋለሁ። **የዱንያን ጌጦች ለመተው** ✓ ከሐራም ሙሉ በሙሉ እታቀባለሁ። ሐላል ነገሮችንም አላበዛም።				

✓ አላህን ስለወሰነልኝ ሲሳይ አመሰግነዋለሁ፡፡ ✓ የመጭውን ዓለም ጸጋ አላህን አዘውትሬ እጠይቃለሁ፡፡ **ከአላህ ሐያእ ለማድረግ** ✓ እኔ ጥፋተኛ ከመሆኔ ጋር አላህ ዘወትር በጎ እንደሚውልልኝ አስታውሳለሁ፡፡ ✓ አላህ እያንዳንዱን እንቅስቃሴዬን እንደሚያውቅ አውቃለሁ፡፡ ✓ ከአላህ ፊት ቆሜ ለትንሹም ለትልቁም ጥፋቴ እንደምጠየቅ አስታውሳለሁ፡፡ ✓ አላህን የሚገባውን ያህል እንዳላመለክኩት ይሰማኛል፡፡ ✓ የአላህ ልቅናና ልዕልና ይታወሰኛል። ✓ አላህን ስለዓለማዊ ጉዳይ ስጠይቀው ራሴን እንቃለሁ፡፡ ሐፍረትም ይሰማኛል፡፡ **ከሰዎች ሐያእ ስለማድረግ** ✓ ከነርሱ ፊት ወንጀል አልሰራም፡ ፡ አላህ ይፋ እንዳይሆን የከለከለውን ነገር ይፋ				

አላደርግም፡፡ ✓ ከነርሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት አላህ በደነገገው መልኩ አደርጋለሁ፡፡ ✓ ዱንያዊ ጉዳይ አልለምናቸውም፡ ፡ ✓ ከነርሱ ጋር ባለኝ ግንኙነት የሸሪዓውን አደቦች እጠብቃለሁ፡ ፡ **ነፍሴን ሐያእ ስለማድረግ** ✓ ነፍሴ ወንጀል እንዳትሰራና ወደ እሳት እንድታዘግም አልፈቅድላትም። ✓ ከሰው በምገለልባቸው ጊዜያት አላህን ከመወንጀል እጠበቃለሁ፡ ፡ ✓ ስብእናዬን ዝቅ ከሚያደርጉ እኩይ ባህሪያት ነፍሴን እጠብቃታለሁ፡፡				

2) ቁጥብነት

ባህሪ	ሁሌ	በአብዛኛው	አንዳንዴ	አልፎ አልፎ
(ከፍተኛው ደረጃ 60)	4	3	2	1

✓ ከሐራም እታቀባለሁ፡፡ ✓ ‹‹አላህ ሆይ፣ ቁጥብነትንና ሐብትን ስጠኝ›› የሚለውን ዱዓ አበዛለሁ፡፡ ✓ ነፍሴን ከስጋዊ ስሜት ለማቀብ እተጋለሁ፡፡ ✓ ምላሴን አላህ ከከለከለው ነገር ሁሉ አቅባለሁ፡፡ ✓ በአለባበሴ ልከኛ እሆናለሁ፡፡ አልኮፊስም፡ አልኮራም፡፡ ✓ ላያዊ ገጽታዬን ለማሳማር እጥራለሁ፡፡ ይበልጡኑ ግን ስብእናዬን ለማፋፋትና ለማጎልበት እሰራለሁ፡፡ ✓ ሐላልን ከስብ እመርጣለሁ፡፡ ✓ ቃሌን አከብራለሁ፡፡ ✓ አበዳሪዬን አመሰግናለሁ፡፡ ምክንያቱም፡- ‹‹ሰዎችን ያላመሰገነ አላህንም አያመሰግንምና፡፡››				
✓ የገንዘብ ግንኙነቶቹ የሸሪዓውን ወሰኖች የጠበቁ እንዲሆኑ እጥራለሁ። ✓ አራጣን፣ ማታለልን፣ ጉቦን፣ የሸቀጥ ሞኖፖልን እና መሰል ሐራሞችን እታቀባለሁ። ✓ ሰዎችን ምንም ነገር አልለምንም፡፡				

✓ ስልጣኔን በመጠቀም የግል ጉዳዮቼን አልፈጽምም። ✓ ከሐራም ለመታቀብ ስል ሐላሉን እጠነቀቃለሁ።				

3) መታገስና ቁጣን መቆጣጠር

ባህሪ	ሁሌ	በአብዛኛው	አንዳንዴ	አልፎ አልፎ
(ከፍተኛው ደረጃ 24)	4	3	2	1
✓ ባለጌዎችን መበቀል እየቻልኩ እታገሳለሁ። ✓ ያወከኝን በሆደ ሰፊነት አልፈዋለሁ። ✓ ሰዎችን ማጥቃት እየቻልኩ እተዋቸዋለሁ። ✓ የተቃራኒ ወገንን እይት አከብራለሁ። ✓ ስህተቴን እቀበላለሁ። በራሴ ላይ እንኳ ቢሆን ሐቅ እናገራለሁ። ✓ በቁጣ ጊዜ ራሴን እቆጣጠራለሁ።				

በእያንዳንዱ ስነ ምግባሬ ላይ ያገኘህውን ደረጃ አስላ። ከከፍተኛው ደረጃ ጋርም አነጻጽረው። ውጤትህ መልካም ከሆነ አላህን አመስግን። በዚህ ባህሪህም ቀጥልበት። ውጤትህ ጥሩ ካልሆነ ግን አላህን ምህረት ለምነው። ጊዜው ከማለፉ በፊት ባህሪህን ታስተካክል ዘንድም በርትተህ ስራ። ለውጤት ትበቃ ዘንድ የተጠቆመውን ተግባራዊ እርምጃዎችን በአላህ በመታገዝ ፈጽም።

=ተፈጸመ= [1]

[1] የዚህ መጽሐፍ ትርጉም መስከረም 24 /2003 ከቀኑ 6፡22 ላይ በተርጓሚው መኖሪያ ቤት ውስጥ በአላህ ፈቃድ ተጠናቀቀ።